# ነገረ ክርስቶስ





አዘጋጅ፡- መምህር በትረ ማርያም አበባው
(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና
የመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ መምህር)
2016 ዓ.ም፣ ኢትዮጵያ

BSC CIVIL ENGINEERING

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩

### ኢየሱስ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሚጠራባቸው ስሞች አንዱ ኢየሱስ ነው። ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት ነው። ዓለም በአዳም በደል ምክንያት ታሞ ይኖር ነበር። ዓለምን መፈወስ የቻለ ሰው ደግሞ እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ አልተገኘም ነበር። ስለዚህ ዓለምን ለማዳን ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ተዋሐደ። ዓለምን የማዳን ሥራውም ከማኅፀን በተዋሕዶ ጀመረ። በዓለም ላይ ብዙ መድኃኒቶች ቢኖሩም መድኃኒትነታቸው የጸጋ ማዳን ነው። በባሕርይው አዳኝ የሆነ እግዚአብሔር ነው። እርሱ እግዚአብሔር ሥጋን ተዋሕዶ አድኖናልና ኢየሱስ ተብሏል። ሰውን ያዳነው፣ ወደቀደመ ቦታውም የመለሰው ኢየሱስ ነው። ሌሎች ፍጡራን ቢያድኑ ግን ማዳንን ከክርስቶስ በጸጋ ተቀብለው ነው። ኢየሱስ የሚለው ስም በአማርኛ መድኃኒት፣ መድኃኒ ዓለመ፣ መድኃኔ ዓለም ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። የኢየሱስ ስሙ፣ አካሉ፣ ሁለንተናው አዳኝ ነው። ስለሆነም በየጊዜው በየሰዓቱ ከሰይጣን ተንኮል ያድነን ዘንድ ስሙን እንጠራለን። ስለሆነም እንደ ደራሲው ኢየሱስ ኢየሱስ ኢየሱስ ሠረፀ እምቤተ ሌዊ፣ ኮሬባዊ መለኮታዊ፣ ቃል ሰማያዊ እምድንግል ተወልደ እንለዋለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪

### ክርስቶስ

ክርስቶስ በዕብራይስጥ ማስያስ፣ በዐረብ መሢሕ፣ በግሪክ ክርስቶስ፣ በግእዝ ቅቡዕ ማለት ነው። ቅቡዕ ማለትም የተቀባ ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ፣ አምላክ የሆነ ሰው ነው። ወልደ እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋ ሲዋሐድ በአምላክነት አከበረው። ሥጋም ቃልን ስለተዋሐደ ከብረ። ስለዚህም ቅቡዕ ተባለ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መባሉ በሰውነቱ እንደሆነ ሁሉ ቅቡዕ መባሉም በሰውነቱ ነው። በአምላክነቱ ክብርን (ቅብዕን) የሚሻ አይደለምና። ክርስቶስ ለተዋሐደው ሥጋ ክብር የሆነውም ራሱ ቃል ነው። እንጂ የቅባት እምነት አራማጆች እንደሚሉት መንፈስቅዱስ ቅብዕ (ክብር) አልሆነውም። በሥላሴ ዘንድ ቅብዕ፣ ተቀባዒ፣ ቅቡዕ የሚል አካላዊ ግብር የለምና። በማክበር፣ በክብር አንድ ስለሆኑ አብ አከበረው፣ ወልድ አከበረው፣ መንፈስ ቅዱስ አከበረው ቢል አንድ ነው። ለሥጋ ክብር የሆነው በተለየ አካሉ ቃል ነው። ምክንያቱም ሥጋ ቃልን ሆነ እንጂ ልብን ወይም እስትንፋስን አልሆነምና ነው። ሥጋ ከበረ መባሉ እንኳ ቃልን ሆነ ማለት ነውና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫

### አማኑኤል

አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ (እግዚአብሔር ምስሌነ) ማለት ነው። እግዚአብሔር በአካል ከፍጥረቱ ተለይቶ አያውቅም። እርሱ በአካል የሌለበት ቦታ የለምና። በረድኤትም በብሉይ ኪዳን ከቅዱሳን አበው፣ ከቅዱሳን ነቢያትና፣ ከቅዱሳን ነገሥታት ጋር

ነበር። ይህኛው "ምስሌነ" ግን አነጋገሩ ከረድኤት የተለየ "ምስሌነ" ነው። በረድኤት ከእኛ ጋር መኖርን ብቻ የሚገልጽ አይደለም። የእኛን ሥጋ ተዋሕዶ ከእኛ ጋር መኖሩንም የሚገልጽ አነጋገር ነው። አማኑኤል የሚለው ስም ስመ ሥጋዌውን የሚገልጽ ስም ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን እንደእኛ ሰው ሆኖ ክሦ፣ ቤዛ ሆኖ አድኖናል። እንግዲህ ምንንም፣ ማንንም አንፈራም። የሚያስፈራን ፍጡር የለም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው። በእምቢታችን ጸንተን፣ በራሳችን ፈቃድ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር አንፈልግም ብለን ከሰይጣን ጋር ካልተባበርን በስተቀር እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለሆነ በእርሱ ሁሉን አሸንፈን እንኖራለን። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆኖ ነጻነትን መለሰልን፣ ፍጹም መንፈሳዊ ደስታን ሰጠን። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ሁሉ አለን። ኵሉ ብነ እንዘ አልብነ ኵሉ እንዳለ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፬

## ቃለ እግዚአብሔር

ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ ዋነኛ ትምህርታችን ነው። ቅዱስ አትናቴዎስ በሃይማኖተ አበው እንደተናገረው ሥጋ መክበሩ ቃል ስለተዋሐደው ነው እንጂ መንፈስ ቅዱስ ክብር ሆኖት አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ ቃለ እግዚአብሔር ነው። ይህም ማለት ቃለ አብ፣ ቃለ መንፈስ ቅዱስ ነው ማለታችን ነው። በአንድ ህልውና በአንድ ባሕርይ ለሚኖሩ ሦስቱ አካላት ቃላቸው እርሱ ነው። ይህ ቃል ከሰው፣ ከእንስሳት፣ ከመላእክት ቃል (ድምፅ) የተለየ ነው። እነዚህ ቃላት (ድምፆች) ዝርዋን ናቸው እንጂ አካላውያን አይደሉም። ቃለ እግዚአብሔር አአትሪኮን፣ አተርጋዎን፣ ቦርፎሪኮን ከሚባሉት ቃላት የተለየ ቃል ነው። ቅዱሳን ነቢያት ከእግዚአብሔር የሰሙት ድምፅ እንኳ ዝርው ነው። አካላዊ ቃል የሚባለው ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ነው። ከንባብ (ንግግር) የተለየ አካላዊ ቃል ነው። ይህ ቃል ሥጋ ሆነ። ይህም ማለት ረቂቁ አካለ ቃል ግዙፉን አካለ ሥጋ በተዋሕዶ ገንዘቡ አደረገው ማለታችን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር እየተመላለሰ ሲያስተምር ለሕዝቡ ጆሮ ይሰማ የነበረው ድምፅ ዝርው ስለሆነ አካላዊ አይደለም። ራሱ ክርስቶስ ግን አካላዊ ቃል ነው። እርሱ የተናገረው ንግግር ግን ከእርሱ ከአካላዊ ቃል የተገኘ ንግግር (ንባብ) ነው እንጂ ራሱ ንግግሩ አካላዊ አልነበረም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፭

## ኢየሱስ ክርስቶስ የት ተወለደ?

የሕይወት እንጀራ ክርስቶስ በእንጀራ ቤት ተወለደ (ሉቃ. ፪፥፩-፲፮)። ቤተልሔም ማለት የእንጀራ ቤት ማለት ነው። የክርስቶስ መወለድ ድንገት እንደ እንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውሃ ፈሳሽ አይደለም። በቅዱሳን ነቢያት የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ እንደሚወለድ ትንቢት ሲነገር ነበርና (ኢሳ. ፯፥፲፬)። ከጽድቅ ለተራበው ዓለም መንፈሳዊ ምግብ ይሆን ዘንድ የሕይወት እንጀራ ክርስቶስ በእንጀራ ቤት ተወለደ። ቤተልሔም በእስራኤል ሀገር ያለች የዳዊት ከተማ የነበረች ቦታ ናት። ነቢያቱ፣ ነገሥታቱ ተወልደውባታል። የነቢያት ሀገር ናት። ከነቢያቱ፣ ከነገሥታቱ ግን የሕይወት እንጀራ ሆኖ የተራበውን ዓለም ማጥገብ የቻለ አልነበረም። ወልደ እግዚአብሔር ግን ከድንግል ማርያም ተወልዶ ዘለዓለማዊ ሕይወትን የሚሰጥ የሕይወት እንጀራ ሆነ። ምእመናን

ንሥሐ ገብተው፣ ሥጋውን በልተው፣ ደሙን ጠጥተው በእርሱ ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ:: እርሱም በእነርሱ ይኖራል::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፮

ኢየሱስ ክርስቶስ በአደገባት ከተማ ምክንያት ናዝራዊ እየተባለ ይጠራል:: ማቴ. ፪፥፳፫ "በነቢያት ናዝራዊ ይባላል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ናዝሬት ወደ ምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ" እንዲል:: ክርስቶስ በቤተልሔም እንደተወለደ ዕለቱን በአንድ ጊዜ ልደግ አላለም:: ሰው እንደመሆኑ እንደሰው በየጥቂቱ አደገ:: በበሕቅ ልሕቀ እንዲል:: ሥጋ መቼም ቃልን ተዋሕጃለሁ ብሎ በአንድ ጊዜ የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ ልሁን አላለም:: ክርስቶስ በሥጋ በቤተልሔም ተወልዶ በናዝሬት አደገ:: መድኃኒትነቱ ግን ለዓለም ሁሉ ስለሆነ መድኃኔዓለም እየተባለ ይጠራል:: ካህናትም በእርሱ የተሾሙ እርሱን የሚያገለግሉ ስለሆኑ ለሰው ልጅ ሁሉ እኩል ያስባሉ:: ለሁሉም ጸሎትን ያቀርባሉ:: በብሉይ ኪዳን ናዝራውያን የሚባሉት ለእግዚአብሔር ራሳቸውን የተለየ የሚያደርጉ ሰዎች ነበሩ (ዘኍ. ፮፥፪):: በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ክርስቶድ ናዝራዊ እንደተባለ ሁሉ በጥምቀት ተወልደን ከዓለም ተለይተን ውሉደ እግዚአብሔር የሆንን እኛ ክርስቲያኖች ናዝራውያን እንባላለን::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፯

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እንደጻፈው በመሢሕ መሢሓውያን እንባላለን:: ክርስቶስ ማለት መሢሕ ማለት ነውና:: ይህንን ቅድስት ቤተክርስቲያን ስታስተምረው የኖረችውና ወደፊትም እስከ ዕለተ ምጽአት የምታስተምረው ትምህርት ነው:: ሥጋ የአምላክነትን ክብር ሲያገኝ ክብር የሆነው ማን ነው የሚለውን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል:: የቅባት እምነት አራማጆች ለሥጋ ቅብዕ (ክብር) የሆነው መንፈስ ቅዱስ ነው ይላሉ:: ነገር ግን ቅዱስ አትናቴዎስ የሚነግረን ለሥጋ ክብር የሆነው ራሱ ቃል መሆኑን ነው:: ይህንንም "ሥጋ ረከበ ዕበየ ወብዝኀ ፍድፍድና በተሳትፎቱ ወበተዋሕዶቱ ምስለ ቃል" ብሎ በማያሻማ ቃል ነግሮናል (ሃይ. አበ. ፴፫፥፳፱):: ሥጋ የአምላክነትን ክብር ያገኘው ከቃል ጋር በመዋሐዱ ነው እንጂ መንፈስ ቅዱስ ክብር ሆኖት አይደለም:: መቀባት (ማክበር) ግን የሦስቱም የአንድነት ሥራ ስለሆነ አብ ቀባው፣ መንፈስ ቅዱስ ቀባው ቢል አንድ ነው:: በመንፈስ ቅዱስ ቀባው ሲል ቢገኝ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ ነው የሚል ትርጉምን አይሰጥም:: ቅዱሳት መጻሕፍት ረቂቅ ሥራዎችን ሁሉ ለመንፈስ ቅዱስ አድለው መናገር ልማዳቸው ነው:: ይሁን እንጂ በዚህ ጊዜ ለመንፈስቅዱስ የተጠቀሰው ከአካላዊ ግብር በስተቀር ለአብም ለወልድም ይሆናል:: ለምሳሌ "ከውሃና ከመንፈስቅዱስ ያልተወለደ መንግሥተ ሰማያት አይገባም" ይላል:: የተጠቀሰው መንፈስቅዱስ ስለሆነ የምንወለደው ከመንፈስቅዱስ ብቻ ነው አንልም:: ከወልድም ከአብም ያልተወለደ ማለት እንደሆነ ልብ ማድረግ ያስፈልጋል:: በዚህ አግባብ የተነገሩትን ቃላት ለመንፈስቅዱስ አካላዊ ግብር አድርጎ መውሰድ የጠማማ ኅሊና ሥራ ነው:: ግብረ ባሕርይን ከግብረ አካል ጋር ማቀላቀል ትልቅ በደል ነው:: ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ ስንል ምንጫችን ታላቁ ሊቅ ቅዱስ አትናቴዎስ ነው:: ቅዱስ አትናቴዎስ ሥጋ ከቃል ጋር በመዋሐዱ ክብርን አገኘ በማለቱ ምንታዌ ነው አንልም:: ምክንያቱም ሲከፈልም፣ ሲዋሐድም፣ ሲቀባም አንድ ጊዜ ነውና:: ስለዚህ በምንም

ተአምር ምንታዌ አያሰኝም። ቃል አክባሪ ሥጋ ከባሪ ካላችሁ የካቶሊክ ትምህርት ነው የሚሉ ሰዎች አሉ። ይህ አስቂኝ ነው። የካቶሊክ ትምህርት አንድ አካል ሁለት ባሕርይ የሚል ነው። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ ግን አንድ አካል አንድ ባሕርይ የሚል ነው። ከተዋሕዶ በፊት ቃል በቃልነቱ በክብሩ ጸንቶ ይኖር ነበር። ሥጋ ቃልን በተዋሐደበት ቅጽበት ደግሞ መምህረ ዓለም ቅዱስ ቄርሎስ "እንቲኣሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ዘእንበለ ኃጢአት ወእንቲኣሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል" ብሎ እንደተናገረው የቃል ገንዘብ ሁሉ ለሥጋ ሆነ የሥጋ ገንዘብ ሁሉ ደግሞ ለቃል ሆነ። ከቃል ገንዘቦች አንዱ ክቡርነት ነው። የቃል ክቡርነት ለሥጋ ሆነ። ስለዚህም በጊዜ ተዋሕዶ ቅዱስ አትናቴዎስ እንደተናገረው ሥጋ በቃል ከበረ እንላለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፰

በሥላሴ ዘንድ ያለው አካላዊ ግብር የሚከተለው ነው። የአብ መውለድ ማሥረጽ፣ የወልድ መወለድ፣ የመንፈስ ቅዱስ ደግሞ መሥረጽ ነው። ከዚህ ውጭ መቅባት፣ መቀባት፣ ቅብዕ መሆን የሚል አካላዊ ግብር የለም። ለግብረ ባሕርይ የተነገረውን ለግብረ አካል፣ ለግብረ አካል የተነገረውን ለግብረ ባሕርይ አድርገው ከተናገሩት ትልቅ ተፋልሶን ያመጣል። በግብረ አካል ሕይወትነት በተለየ የመንፈስቅዱስ ነው። በግብረ ባሕርይ ሲነገር ግን ሦስቱ አንድ የሚሆኑበት አፍኣዊ ግብር ነው። ይህ በሦስቱ ኵነታት ተገናዝቦ የሚገኝ ሕይወትነት ነው እንጂ ከሦስቱ ኵነታት አንዱ አይደለም። ለምሳሌ በሃይማኖተ አበው "አብ ሕይወት፣ ወልድ ሕይወት፣ መንፈስቅዱስ ሕይወት" ሲል ይገኛል። ይህ ሕይወትነት ሦስቱ አካላት አንድ የሚሆኑበት ሕይወትነት ነው እንጂ በግብረ አካል የተጠቀሰው እስትንፋስነት (ሕይወትነት) አይደለም። ምክንያቱም ሦስቱም አካላት በየአካላቸው ጸንተው የሚኖሩ ስለሆነ አብ መንፈስቅዱስን፣ መንፈስ ቅዱስም አብን አይሆኑምና ነው። በግብረ ባሕርይ አብን አባታችን እንደምንለው ሁሉ ወልድንም አባታችን ሆይ እንለዋለን። እኛን በመንፈሳዊ ልደት መውለድ የአብም፣ የወልድም፣ የመንፈስ ቅዱስም (ሦስቱም አንድ የሚሆኑበት) ሥራ ነው። በዚህኛው ግብረ ባሕርይ አብንም ወልድንም መንፈስቅዱስንም ወላዲ ወላዲ ወላዲ ልንላቸው እንችላለን። በግብረ አካል ወላዲ የሚባል ግን አብ ብቻ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ለግብረ ባሕርይ የተነገረውን ለግብረ አካል፣ ለግብረ አካል የተነገረውን ለግብረ ባሕርይ መናገር አይገባም ያልነው ይህ ነው። አፍቀርከ ጽድቀ ወዐመፃ ጸላእከ ወበእንተዝ ቀብዐከ እግዚአብሔር ቅብዐ ትፍሥሕት እምእለ ከማከ ብሎ ቅዱስ ዳዊት የተናገረው በመቅባት ሦስቱም አካላት አንድ ስለሆኑ ስለሦስቱም የተነገረ ቃል ነው። እለ ከማከ ተብለው ("እለ" የሚለው አገባብ በቁ ሆኖ ማለት ነው) ከተገለጹት ነቢያት የሚበልጥ ቅብዐ ትፍሥሕትን ቀባህ ተብሏል። ቅብዐ ትፍሥሕት ክብር ነው። የነቢያት ክብር የጸጋ ክብር ነው። አምላክ የተባሉ ነቢያት እንኳ ቢኖሩ አምላክነታቸው፣ ክብራቸው የጸጋ ነው። ረሰይኩከ አምላኮ ለፈርዖን እንዲል። ሥጋ አምላክነትን (ክብርን) ገንዘብ ያደረገው ግን በጸጋ ሳይሆን በባሕርይ በተዋሕዶ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፱

ወልደ እግዚአብሔር በከዊን ስሙ ቃል ይባላል። ሥላሴ በባሕርይ አንድ ናቸው። ባሕርይ የሚባለው የሦስቱ ኵነታት ማለትም የቃል፣ የልብ፣ የእስትንፋስ መገናዘብ ነው። ባሕርይ

አካላዊ ይባላል እንጂ አካል አይባልም። ባሕርየ ሥላሴ በቃል ከዊነ ሰው ሆነ ይባላል እንጂ በልብ ከዊን ወይም በእስትንፋስ ከዊን ሰው ሆነ አይባልም። ቃል ሰው ሲሆን ከልብነት ከእስትንፋስነት ተገናዝቦ ሳይለይ ነው። ሥጋ የቃልን ገንዘብ ሲወርስ አብ ልቡ፣ መንፈስቅዱስ እስትንፋሱ ሆነዋል። ሥጋም በቃል ርስት የአብ ቃል፣ የመንፈስ ቅዱስ ቃል ተባለ። ሥላሴ ስንል አብን፣ ወልድን፣ መንፈስ ቅዱስን ለማመልከት ነው። አብ የራሱ የሆኑ ፍጹም አካል አለው። ወልድም የራሱ ፍጹም አካል አለው። መንፈስቅዱስም የራሱ ፍጹም አካል አለው። እነዚህ አካላት አንዱ አካል በአንዱ አካል ህልው ሆነው ይኖራሉ። ህልው መሆን ብቻ ሳይሆን አንዱ ከአንዱ ተገነዛዝበው ይኖራሉ። ለምሳሌ ከምድር በላይ የፀሐይ ብርሃን በአየር ላይ ህልው ሆኖ ይኖራል። መገነዛዘብ ግን የለውም። አብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ፣ ወልድ በአብና በመንፈስ ቅዱስ፣ መንፈስ ቅዱስ በአብና በወልድ አለ (ህልው ሆኖ ይኖራል) ስንል ግን መገነዛዘብ ያለበት ህልውና ነው። ሦስቱ አካላት የሚገነዛዘቡት ደግሞ በከዊን ነው። አብ በልብ ከዊኑ የወልድም የመንፈስቅዱስም ልብ ነው። ወልድ በቃል ከዊኑ የአብም የመንፈስቅዱስም ቃል ነው። መንፈስቅዱስ በእስትንፋስነት ከዊኑ የአብም የወልድም ሕይወት ነው። ስለዚህ አብን ልብ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ነባቢ፣ አንባቢ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ እንለዋለን። ወልድን ቃል፣ ነባቢ፣ አንባቢ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ እንለዋለን። መንፈስቅዱስን ደግሞ እስትንፋስ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ነባቢ፣ አንባቢ እንለዋለን። የእነዚህ የሦስቱ ኵነታት ተገናዝቦ ባሕርይ ይባላል። ወልድ ሰው ሲሆን አካለ ቃል ከአካለ ትስብእት ጋር ተዋሕዷል። ባሕርየ ወልድ (ቃልነት) ከባሕርየ ትስብእት ተዋሕዷል ማለታችን ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፬

## የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ

አንዳንዶች ሰውነቱን ብቻ አይተው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ይመስላቸዋል። አንዳንዶች ደግሞ አምላክነቱን ብቻ አይተው ሰውነቱን ይዘነጉታል። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ፣ አምላክ የሆነ ሰው ነው። አምላክም ሰውም የሆነ አንድ ልጅ (ወልድ ዋሕድ) ነው። ሰው እንደመሆኑ በየጥቂቱ አደገ፣ ተራበ፣ ተጠማ፣ ስለእኛ መከራን ተቀበለ። አምላክ እንደመሆኑም የተራቡትን አጠገበ። ከኃጢአት በቀር የሰውነትን ሥራ ሁሉ ሠራ። በዚህም ሰውን አዳነ። ወንጌላዊው ሉቃስ የኢየሱስ ክርስቶስን የትውልድ ሐረግ ሲገልጽ "የእግዚአብሔር ልጅ የአዳም ልጅ" ብሎ ይናገራል (ሉቃ. ፫፣፴፰)። ሙስሊሞች አምላክ አይወልድም አይወለድም ብለው ይናገራሉ። ነገር ግን ይህ እግዚአብሔር የሆነውን ሳይሆን እንዲሆን የሚፈልጉትን ሐሳብ የሚያንጸባርቁበት ንግግር ነው። ቁርኣን ከመጻፉ በፊት የነበሩ የነቢያትና የሐዋርያት መጻሕፍት የሚናገሩት እግዚአብሔር ወልድ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ መሆኑን ነውና። "ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኩህ" እንዲል (መዝ. ፻፱፣፫)። እንግዲህ አላህ በቁርኣን ወንጌልንም ኦሪትንም ለዒሣ ገለጥኩ ብሎ ከተናገረ ወንጌልም ኦሪትም የአብ አንድ ልጅ ወልድ እንዳለው ይናገራሉ። ስለዚህ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ማመን ይገባቸው ነበር። የሃይማኖት ትምህርት በነጻነት የሚማሩት ነው። ስለዚህ ኅሊናን ነጻ አድርጎ፣ እውነታውን እየመረመሩ መረዳት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ፕሮቴስታንቶችም፣ ሙስሊሞችም፣ ቅባቶችም፣ ካቶሊኮችም፣ ሃይማኖት አልባዎችም ካላችሁ በነጻነት መነጋገር እንችላለን። ኑ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፩

የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ (ማቴ. ፩፥፩)። ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ቦታ ላይ የዳዊት ልጅ እየተባለ ተገልጿል። "የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ" እንዲል (ሉቃ. ፲፰፥፴፱)። ተለይቶ የዳዊት ልጅ የተባለው አስቀድሞ ለዳዊት "ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ" ብሎ ቃልኪዳን ገብቶለት ስለነበር ቃልኪዳኑን መፈጸሙን ለማሳወቅ የዳዊት ልጅ እየተባለ ይጠራል (መዝ. ፻፴፩፥፲፩)። በተጨማሪም ኢየሱስ ክርስቶስ ልደቱ ከዳዊት ዘር መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ቅዱስ ዳዊት እንደልቤ ተብሎ ተጠርቷል። የደግ ልጅ ደግ መሆኑን ለመግለጽ ነው። የዳዊት ፈጣሪ እርሱ በሥጋ ከዳዊት ዘር ተወልዶ የዳዊት ልጅ ተባለ። የአብርሃም ልጅ መባሉ ደግሞ "የምድር አህዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ" ተብሎ የተነገረው ትንቢት መፈጸሙን ለማሳወቅ ነው (ዘፍ. ፳፪፥፲፰)። የምድር አሕዛብ ሁሉ የሚባረኩበት ጌታ ከእርሱ መወለዱንና ትንቢቱ መፈጸሙን ለመንገር ጌታ የአብርሃም ልጅ እየተባለ ይጠራል። አብርሃም በደግነቱ አርከ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ወዳጅ) እየተባለ ተጠርቷል። ከእግዚአብሔር ወዳጅ ከአብርሃም የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ተወለደ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፪

ያዕቆብም ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደች የማርያምን እጮኛ ዮሴፍን ወለደ (ማቴ. ፩፥፲፮-፲፰)። ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ፲፪ ዓመት ከቆየች በኋላ አይሁድ እርሷን ከቤተመቅደስ አስወጥተው ዮሴፍ ይጠብቃትና ይንከባከባት ዘንድ በአደራ መልኩ ሰጥተውታል (ነገረ ማርያም ብራና)። እጮኛ ማለት ጠባቂ ማለት ነው። ፩ኛ መቃ. ፲፪፥፯ "እኔ ለቅድስና አጭቼሽ ነበር። አንቺ ግን ለዲያብሎስ ሆንሽ" እንዲል። እጮኝነት ሁለት ዓይነት ትርጉም አለው። አንደኛው አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ ሚስት ትሆን ዘንድ ማጨት ነው። ይህም ምሥጢሩ መጠባበቅን ያመለክታል። እስኪጋቡ ድረስ እርሷ ለእርሱ እርሱ ለእርሷ መሆኑን ተማምነው መቆየትን ያመለክታል (ዘዳ. ፳፥፯)። ሁለተኛው ትርጉም እጮኝነት የባልና የሚስት መተጫጨትን ሳይሆን መጠበቅን፣ መንከባከብን የሚያመለክት ነው። ድንግል ማርያም የዮሴፍ እጮኛ መባሏ በዚህኛው አግባብ ነው። "እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና" እንዲል (፪ኛ ቆሮ. ፲፩፥፪)። አረጋዊው ዮሴፍ ድንግል ማርያምን ይጠብቃትና ይንከባከባት ነበር። ወደ ግብፅ ስትሰደድ አብሯት ተሰዷል። "እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች" (ማቴ. ፩፥፲፰)። ያለወንድ ዘር፣ ያለሩካቤ በድንግልና መፅነስ በተፈጥሮ ሕግ አይቻልም። ይህ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ ነው። ከተፈጥሮ ሕግ በላይ የሆነ ነገር ሲደረግ ብዙ ጊዜ "ግብረ መንፈስ ቅዱስ (የመንፈስ ቅዱስ ሥራ)" እየተባለ ይገለጻል። ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች የሚለው አገላለጽ በዚህ አግባብ የተነገረ ነው። "መንፈስ ቅዱስ" ተብሎ ቢነገርም ይህ የባሕርይ ሥራ ስለሆነ ከአብ፣ ከወልድ ቢል ትርጉሙ አንድ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፫

የበኩር ልጇንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም (ማቴ. ፩፥፳፩-፳፭)። የበኩር ልጅ ማለት የመጀመሪያ ልጅ ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለድንግል ማርያም የመጀመሪያ ልጇ ነው።

መጀመሪያነቱም ሁለተኛነት የማይከተለው መጀመሪያ ነው፡፡ ድንግል ማርያም ልጇን በድንግልና ወለደችው፡፡ ድንግል ማርያም የበኵር ልጇን እስክትወልድ ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም ተብሏል፡፡ ከወለደች በኋላ ወንድ ሴትን በሚያውቅበት ግብር አወቃት ማለት አይደለም፡፡ "እስከ" ሁለት ዓይነት ትርጉም አለው፡፡ ይኸውም ፍጻሜ ያለው እስከ እና ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው፡፡ ፍጻሜ ያለው እስከ መድረሻ ያለው ነው፡፡ ለምሳሌ ከአዳም እስከ ሙሴ ሞት ነገሠ (ነግሠ ሞት እምነ አዳም እስከ ሙሴ) ሲል ከዚያ በኋላ አልነገሠም ማለት ነው፡፡ ፍጻሜ የሌለው እስከ የሚባለው ደግሞ "ኢወለደት ሜልኮል እስከ አመ ሞተት (ሜልኮል እስከሞተችበት ጊዜ ድረስ አልወለደችም)" ይላል፡፡ ከሞተች በኋላ ወለደች ማለት አይደለም፡፡ እስክትሞት ድረስም አልወለደችም ከሞተች በኋላም አልወለደችም ማለት ነው፡፡ ዮሴፍ ድንግል ማርያም የበኵር ልጇን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ተብሏል፡፡ ይህ እስከ ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው፡፡ ከወለደች በኋላም አላወቃትም ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ደግሞ ድንግል ማርያም ጌታን በጸነሰች ጊዜ ኅብረ መልኳ ይለዋወጥ ስለነበር በአንድ ወጥ ኅብር አያውቃትም ነበር፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደተናገረው ቦ አመ ታቀያይሕ፣ ወቦ አመ ታሕመለምል እንዲል፡፡ ከወለደች በኋላ ግን በአንድ ኅብረ መልክዕ አወቃት ማለት ነው፡፡ በዚህኛው ጊዜ የእስከ ትርጓሜ ፍጻሜ ያለው እስከ ይሆናል፡፡ ድንግል ማርያም ጌታን ከወለደች በኋላም በድንግልና ጸንታ ኖራለች፡፡ ቅድመ ጸኒስ፣ ጊዜ ጸኒስ፣ ድኅረ ጸኒስ፣ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ በድንግልና ጸንታ ኖራለች፡፡ ክርስቶስ ሕዝቡን ከኃጢአት የሚያድን ስለሆነ ኢየሱስ ተባለ፡፡ ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት ነውና (ማቴ. ፩፣፳፩-፳፭)፡፡ ስም ግብርን የሚገልጽ ሆኖ ይወጣል፡፡ ይህ የጌታ ስምም ግብሩን የሚገልጽ ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፬

"እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኗል" (ማቴ. ፩፣፳፫)፡፡

## የነቢያት ትንቢት

የክርስቶስ መወለድ ድንገት እንደ እንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውሃ ፈሳሽ አይደለም፡፡ ጎርፍ ድንገት ይመጣል፡፡ እንግዳም ድንገት ይመጣል፡፡ የክርስቶስ መወለድ ግን ድንገት የሆነ አይደለም፡፡ ነቢያት እንደሚወለድ አስቀድመው ትንቢት ተናግረዋል፡፡ በነቢያት ትንቢት አስነግሯል፡፡ ለዚያ ነው ወንጌላዊው ሲገልጽ "የተባለው ይፈጸም ዘንድ" ብሎ የገለጸው፡፡ ከነቢያት ነቢዩ ኢሳይያስ ስለክርስቶስ መወለድ ተናግሯል (ኢሳ. ፱፣፮፡ ኢሳ. ፯፣፲፬)፡፡ በቤተልሔም እንደሚወለድም ነቢዩ ሚክያስ ተናግሯል (ሚኪ. ፭፣፪)፡፡ የክርስቶስ መወለድ በነቢያት በብዙ አምሳል ተገልጿል፡፡ ነቢዩ ሕዝቅኤል "ወደ ምሥራቅም ወደ ሚመለከተው በስተውጭ ወዳለው ወደመቅደሱ በር አመጣኝ፡፡ ተዘግቶም ነበረ፡፡ እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል (ሕዝ. 44፣1-2) ብሎ ተናግሯል፡፡ ሕዝቅኤል ያየት መቅደስ የድንግል ማርያም ምሳሌ ናት፡፡ በዚህች መቅደስም እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ኖሮበታል፡፡ ወልድ ወደዚህች መቅደስ ሲገባ የድንግል ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም ነበር፡፡ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን

ቆይቶ ሲወጣም ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም። ጌታን ከወለደች በኋላም በድንግልናዋ ጸንታ ኖራለች። የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል መባሉ ለዚህ ነው። ክርስቶስ በምድር ያለአባት ከእናት ብቻ ተወለደ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፩

ማቴ. ፪፥፬ "ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው"።

## ሑረተ ሰብአ ሰገል

ሰብአ ሰገል ማለት የጥበብ ሰዎች ማለት ነው። በአባቶቻቸው መጽሐፍ ልዩ ኮከብ በወጣ ጊዜ ኮከቡን ተከትለው እንዲሄዱ ተነግሯቸው ነበር (ተአምረ ኢየሱስ)። በዚህም መሠረት ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ያ በመጽሐፍ የተገለጸላቸው ኮከብ ታየ። ኮከቡም በቆመ ብእሲ (በሰው ቁመት ልክ) ሆኖ እየመራቸው ወደ ቤተልሔም አቀኑ። ፲፪ ነገሥታት ከነሠራዊታቸው መንገድ ጀምረው ነበር። በኋላ ዘጠኙ ተመልሰው ሦስቱ ነገሥታት ከነሠራዊታቸው ወደ ኢየሩሳሌም አቀኑ። ሄደውም የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው ብለዋል። ክርስቶስ ንጉሠ ነገሥት ነው። ንጉሥነቱም የአይሁድ ብቻ አይደለም። በዚህ ጊዜ ሄሮድስ ሥልጣኔን ይወስድብኛል ብሎ ደነገጠ። ይህ ክርስቶስ ወዴት እንደሚወለድም በዘመኑ ለእግዚአብሔር ቃል የቀረቡ የካህናት አለቆችን ጠየቃቸው። በቤተልሔም እንደሚወለድም ነገሩት። እርሱም ሰብአ ሰገልን ባገኛችሁት ጊዜ እኔም እንድሰግድለት ንገሩኝ አላቸው። የሽንገላ ንግግር ነው። በልቡ ሊገድለው እየፈለገ በአፉ ግን እሰግድለት ዘንድ ብሏል። ኮከቡ ሰብአ ሰገልን ድንግል ማርያም ከእነ ልጇ ካለችበት ቦታ ላይ አደረሳቸው። ወደቤትም ገብተው ክርስቶስን ከእናቱ ከማርያም ጋር አገኙት። ሳጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅ፣ ከርቤ፣ ዕጣን አቀረቡለት። ሰብአ ሰገል ለጌታ ሰግደው እጅ መንሻ ያቀረቡለት በተወለደ በሁለት ዓመቱ ነበር። ዕለቱን አልደረሱም። ከሀገራቸው በኮከቡ እየተመሩ የደረሱት በሁለት ዓመታቸው ነው። ሰብአ ሰገል ለጌታ የሰጡት እጅ መንሻ ራሱ ጌታ ከሰጣቸው ነው። ቅዱስ ያሬድ ይህንን በሰብአ ሰገል ተገብቶ "አምኃ አባእነ ለከ ዕጣነ አቅረብነ ለከ እምዚኣከ ለክቡር ስምከ" ብሎ ገልጾታል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፯

"የጌታ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ ሄሮድስ ሕፃኑን ለመግደል ይፈልገዋልና ተነሣ። ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ። እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው" (ማቴ. ፪፥፲፫-፲፬)።

## ስደተ እግዚእ ምስለ እሙ

ልጄን ከግብፅ ጠራሁት የተባለው እንዲፈጸም ወደ ግብፅ ሄደ (ሆሴ. ፲፩፥፩)። ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ ነው። ስለዚህም እግዚአብሔር አብ "ልጄ" ይለዋል። ልጄ ያለው "ሥጋን" ብቻ ወይም "ቃልን" ብቻ አይደለም። ሥጋ ከቃል፣ ቃል ከሥጋ ጋር ተዋሕዷልና በአንድነት በተዋሕዶ ልጄ ይለዋል። ልደተ ክርስቶስን ቅባቶች ሦስት ያደርጉታል። ይኸውም ቅድመ ዓለም ከአብ አንድ፣ በማኅፀን ቃል በሥጋ ከአብ ሁለት፣ ከዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በኋላ

ከእመቤታችን ሦስት ይሆናል ይላሉ (ምንጭ:- ወልደ አብ የተባለው የቅባት መጽሐፍ)፡፡ ይህን ካሉ በኋላ ግን ግብሩን ሰጥተው ስም ይነሱና የማኅፀኑና የቅድመ ዓለሙ ከአንድ ይቆጠራልና ብለው ሁለት ለማድረግ ይጥራሉ፡፡ አስቂኝ ነው፡፡ መምህረ ዓለም ቅዱስ ቄርሎስ "እንቲኣሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ፣ ወእንቲኣሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል" ብሎ ተናግሯል፡፡ በማኅፀን የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ሆኗል፡፡ ቃለ አብ ወልድ የአብ ልጅ ነው፡፡ ሥጋ ቃልን በሆነ ጊዜ በቃል ርስት ወልደ አብ ተብሏል፡፡ በተጨማሪ ቃል ፈጣሪ ነው፡፡ ሥጋ ቃልን በሆነ ጊዜ በቃል ርስት ፈጣሪ ሆኗል፡፡ ሥጋ በቃል ርስት ፈጣሪ ሆነ እንለዋለን እንጂ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ አንልም፡፡ ፈጠረ ዓለም ከተዋሕዶ በፊት የተከናወነ ድርጊት ነው፡፡ ርስት ደግሞ የሚነገረው ከተዋሕዶ በኋላ ነው፡፡ ታዲያ ፈጣሪነትን ገንዘብ እንዳደረገ በምን እናውቃለን ከተባለ በደረቅ ግንባር ዓይንን በመፍጠሩ ይታወቃል፡፡ መከፈልን፣ መወለድን መፈጠር የሚል አማርኛ በቅዱሳት መጻሕፍት ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ሔዋን አዳም በተፈጠረ በሳምንቱ ዓርብ ተፈጠረች ሲል ተወለደች ማለት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ መከፈልን መፈጠር ሲለውም "ወኢተሳተፎ መኑሂ በፈጢረ ሥጋሁ" ሲል ይገኛል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፮

## ሞተ ሕፃናተ ሳሌም ወሞተ ሄሮድስ

"ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ" (ማቴ. ፪፣፲፭)፡፡ ሄሮድስ ሊገድለው በፈለገ ጊዜ ጌታ ክርስቶስ ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ወደ ግብፅ ተሰደደ፡፡ ይህ እጅግ በጣም ይደንቃል፡፡ ፈጣሪ ከፍጡር ለምን ሸሸ?! ሄሮድስን ማጥፋት ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን ራሱ ክርስቶስ እንደተናገረው የመጣው ሰውን ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አይደለም፡፡ "የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም" እንዲል (ሉቃ. ፱፣፶፮)፡፡ ስለዚህ ሊያድነው የመጣውን ሰው ላለማጥፋት ወደ ግብፅ ተሰደደ፡፡ ሁለተኛው ለእኛ አብነት ለመሆን ተሰደደ፡፡ ይኸውም እናንተም መከራ በጸናባችሁ ጊዜ ከሀገር ሀገር ሽሹ ብሎ ለስደተኞች ተስፋ ለመሆን ነው፡፡ "ኢየሱስ ስዱድ ተስፋሆሙ ለስዱዳን" እንዲል፡፡ ሦስተኛው "ልጄን ከግብፅ ጠራሁት" ያለው ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ነው፡፡ አራተኛ ከዚያው ከእስራኤል ሆኖ ሌሎች ሲገደሉ እርሱ ሳይሞት ቢቀር ምትሐት ነው ይሉት ነበርና ምትሐት አለመሆኑን ለማሳወቅ ወደ ግብፅ ተሰዷል፡፡ እንዳይሞት ደግሞ ጊዜው አልደረሰም ነበርና ነው፡፡ አምስተኛ "በግብፅ የነበሩ ጣዖታትን ያፈራርስ ዘንድ ነው" ፡፡ ክርስቶስ ወደ ግብፅ ሲገባ በግብፅ የነበሩ ጣዖታት ፈራርሰዋል፡፡ ሳይፈጥሩ የሚመለኩ የእጅ ሥራዎች የነበሩ ጣዖታት ፈጥሮ የሚመለክ እውነተኛው አምላክ መምጣቱን አይተው ወዳድቀዋል (ነገረ ማርያም ብራና)፡፡ ሄሮድስ መድኃኒቱን አሳደደ፡፡ ድንግል ማርያምም የዓለምን መድኃኒት ይዛ ወደ ግብፅ ተሰደደች፡፡ ሄሮድስ ጌታን እገድላለሁ ብሎ በሽንገላ ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ 144 ሺ ሕፃናትን አስገደለ፡፡ ስለክርስቶስ ብለው የሚቀበሉት መከራ ደስታን ያጎናጽፋል፡፡ ሄሮድስም ብዙ ጥፋትን ካጠፋ በኋላ ተዋርዶ ሞተ፡፡ ሕፃናተ ሳሌምም በክብር ሞቱ፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፰

### ሚጠተ እስራኤል ወደ እስራኤል መመለስ

ጌታ ከእናቱ ጋር መዋዕለ ስደቱን በግብፅ ሀገር ከፈጸመ በኋላ ያሳደደው ንጉሥ ሄሮድስ ስለሞተ ወደ እስራኤል ሀገር ተመልሷል። ጌታ ወጣንያን ሞትን ቢፈሩ መሸሽ እንዲገባቸው ለማስተማር ወደ ግብፅ ተሰዷል። ፍጹማን ሰማዕትነትን እንዲቀበሉ ደግሞ በመስቀል ተሰቅሎ በመሞት አሳይቷል። የሁሉም መምህር እርሱ ነው። ወደ እስራኤል ሀገር ከተመለሰ በኋላ ወደ ገሊላ አውራጃ ሄዶ ናዝሬት በምትባል ከተማ ኖረ።

### መጥምቁ ዮሐንስ

በቀድሞ ባህል ንጉሥ ከመምጣቱ በፊቱ ንጉሡ የሚመጣበትን መንገድ የሚጠርጉ ሰዎች ነበሩ። ንጉሠ ነገሥት (የነገሥታት ንጉሥ) ክርስቶስም ከማስተማሩ በፊት አስቀድሞ ሰውን የንሥሓ ጥምቀት ለማጥመቅ የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ ተልኳል (ኢሳ. ፵፫፣፲፬)። ዮሐንስ ጸያሔ ፍኖተ እግዚኡ ነው። ይህ ዮሐንስ ስለክርስቶስ ሲናገር ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ብሎ ተናግሯል። ሴቶች ከወለዷቸው ሁሉ ከዮሐንስ መጥምቅ የሚበልጥ የለም የተባለለት ዮሐንስ ደግሞ የጌታን ጫማውን እንኳ መሸከም አይገባኝም ብሏል። ክርስቶስ አምላክም ሰውም ስለሆነ ከዮሐንስ ይበልጣል። ፈጣሪ ከፍጡር መብለጡ ግን አይደንቅም። ራሱ ዮሐንስ እንደመሰከረው የዮሐንስ ጥምቀት የንሥሓ ጥምቀት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፱

እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል (ማቴ. ፫፣፲፩)። እሳት ወርቅን እንደሚያጠራ ሁሉ ምእመናንም ተጠምቀው በምግባር የጠሩ ይሆናሉ። ጌታ የሚያጠምቀን በመንፈስ ቅዱስ ነው ማለት በረቂቅ ሥራው ከእርሱ መወለድን ያድለናል፣ ልጅነትን ይሰጠናል ማለት ነው። ጌታ ክርስቶስ ከጎኑ ከሚፈሰው ማየ ገቦ ይወልደናል። የዮሐንስ ጥምቀት ልጅነትን አያሰጥም። ጥምቀቱ የንስሓ ጥምቀት ነበር። የጌታ ጥምቀት ግን ልጅነትን ያሰጣል። ልጅነትን የሚያስገኙ አራት ዓይነት አማናውያን ጥምቀቶች አሉ። እነዚህም:-

፩) በአርባ ቀን በሰማንያ ቀን ተጠምቀን የምናገኘው ጥምቀት አንዱ ነው። ወንዱ በተወለደ በ፵ ቀን፣ ሴቷ በተወለደች በ፹ ቀን የሚጠመቁት ጥምቀት ነው። ይህም አዳም በተፈጠረ በአርባኛው ቀን ወደ ገነት እንደገባ፣ ሔዋንም በተፈጠረች በ፹ ቀኗ ወደገነት እንደገባች ያለ ነው። ገነት የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት። ወይም ደግሞ ቤተክርስቲያን የገነት ምሳሌ ናት።

፪) ደመ ሰማዕታት:- አንድ ሰው አምኖ ሳለ ለመጠመቅ በዝግጅት ላይ እያለ በክፉ ሰዎች አማካኝነት በሰይፍ ተመትቶ ሰማዕትነትን ቢቀበል ደሙ ጥምቀት ይሆነዋል።

፫) ባሕረ እሳት:- አንድ ሰው አምኖ ሳለ ለመጠመቅ በዝግጅት ላይ እያለ በክፉ ሰዎች አማካኝነት ወደ እሳት ተጥሎ ቢሞት እሳቱ ጥምቀት ይሆነዋል። በእሳት ያጠምቃችኋል መባሉ አንዱ ምሥጢሩ ከዚህ ይገባል።

፬) አንብዐ ንሥሓ:- ንዑሳነ ክርስቲያን እግዚአብሔርን አምነው መሠረታዊውን የሃይማኖት ትምህርት እየተማሩ ለጥምቀት እየተዘጋጁ ሳለ መካከል ላይ ለሚጠመቁባት ጊዜ ሳይደርሱ ቢሞቱ እንባቸው ጥምቀት ሆኖ ይቆጠርላቸዋል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳

## የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት

ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጠመቅ ከነበረበት ገሊላ አውራጃ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። ዮሐንስም ጌታን በማጥመቁ መጥምቁ ዮሐንስ እየተባለ ይጠራል። ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃው ወጣ። ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ በራሱ ላይ በርግብ አምሳል ተቀመጠ። አብም የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ ድምፅ አሰማ (ማቴ. ፫፥፲፫-፲፯)። ምሥጢረ ሥላሴ በግልጽ ታወቀ። በመለኮት አንድ የሆነው እግዚአብሔር በአካል ሦስት መሆኑ ታወቀ። ወልድ ሥጋ ለብሶ በዮርዳኖስ ታየ። መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ታየ። አብ ከሰማያት ድምፁ ተሰማ። የድምፅ መገኛ አካል ነው። ስለዚህ የአብን አካላዊነት፣ የወልድንም አካላዊነት፣ የመንፈስ ቅዱስንም አካላዊነት አወቅን። ኢየሱስ መጠመቁ ለእኛ አርዓያ ለመሆን ነው። ተጠምቆ ተጠመቁ ለማለት እንጂ በመጠመቁ የሚጨመርለት ነገር ኖሮ አይደለም። ከመጠመቁ በፊትም ሁሉ የእርሱ የሆነ የባሕርይ አምላክ ነውና። ትንቢቱን ለመፈጸም በዮርዳኖስ ተጠመቀ (መዝ. ፻፲፫፥፫-፭)። ጥምቀት ምሥጢረ ሥላሴ የተገለጠበት ስለሆነ ዋዜማውን "ገሐድ (መገለጥ)" ብለን እንጸመዋለን። ምሥጢረ ሥላሴ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው። በአካል ሦስት ናቸው። ስመ አካላት የሚባሉት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። በአካል ግብር ሦስት ናቸው። እነዚህም መውለድ ማሥረጽ፣ መወለድ፣ መሥረጽ ናቸው። የአካል ግብር ስማቸውም ይህን መሠረት አድርጎ ወላዲ አሥራጺ፣ ተወላዲ፣ ሠራጺ ነው። በባሕርይ አንድ ናቸው። በባሕርይ ስምም አንድ ናቸው። ይኽንንም ሊቃውንት ዕበይ፣ መለኮት እያሉ ይገልጹታል። በኩነታት ሦስት ናቸው። የከዊን ስማቸውም የአብ ልብ፣ የወልድ ቃል፣ የመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ነው። ስለዚህም አብን ልብ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ፣ ነባቢ፣ አንባቢ እንለዋለን። ወልድን ቃል፣ ነባቢ፣ አንባቢ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ፣ ለባዊ፣ አለባዊ እንለዋለን። መንፈስ ቅዱስን ሕይወት (እስትንፋስ)፣ ሕያው፣ ማሕየዊ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ነባቢ፣ አንባቢ እንለዋለን።በግብረ ባሕርይ አንድ ናቸው። በባሕርይ ግብር ስምም አንድ ናቸው። ይኽውም አምላክ፣ እግዚአብሔር፣ ፈጣሪ፣ ኤልሻዳይ፣ አዶናይ፣ ሁሉን ቻይ እና በመሳሰሉ ስሞች ሦስቱም ይጠሩባቸዋል ማለታችን ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፩

"ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው" (ማቴ. ፬፥፩)። መንፈስ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ይተረጎማል። ነፋስ፣ ነፍስ፣ መልአክ፣ ሰይጣን፣ ፈቃድ፣ መለኮት፣ መንፈስ ቅዱስ እነዚህ ሁሉ መንፈስ ተብለው ይጠራሉ። ታዲያ ጌታ ኢየሱስን መንፈስ ወሰደው ሲል "መንፈስ" በየትኛው ይተረጎማል? ስንል "ፈቃድ እና መንፈስ ቅዱስ" በሚለው ያስተረጉማል። የራሱ ፈቃድ አነሳስቶት ወደ ምድረ በዳ ሄዷል። "መንፈሱሰ ሥምረቱ ይእቲ" እንዲል። ለምን ሄደ ስንል ለመናንያን ገዳምን ይባርክላቸው ዘንድ ነው። ፈቃዱ

አነሳስቶት ስንል ግን ፈቃዱ ከእርሱ የተለየ ነው ማለት አይደለም። ከአካል የተለየ ፈቃድ የለምና። መንፈስን መንፈስ ቅዱስ ብለን ከተረጎምነው ደግሞ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በፈቃድ አንድ ስለሆኑ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ገዳም መሄድ የአብም የመንፈስቅዱስም ፈቃድ ነውና። በህልውና አብ ወልድ መንፈስቅዱስ አንድ ናቸውና። ጌታ ወደ ገዳም የሄደው እፈተናለሁ ብሎ አይደለም። ለመናንያን ገዳምን ይባርክ ዘንድ ከሄደ ዘንድ ግን ሰይጣን ጾሩን ይዞ ፈትኖታል። ጌታም የሰይጣንን ጾሮች ሰባብሮበታል። በዚህም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሸንፎ ማሸነፍን አስተማረን። አሸንፎ አሸንፉ አለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፪

"መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር" (ማቴ. ፬፥፲፩)። ኢየሱስ ክርስቶስ የመላእክት ፈጣሪ ነው። ስለሆነም መላእክት ያገለግሉታል። መላእክት እርሱን አገልግለው የሚጠቀሙት እነርሱ ራሳቸው ናቸው። ለፈጣሪ የሚጨመርለት ምንም ነገር የለም። የመላእክት ዋና ሥራ ፈጣሪን በምስጋና ማገልገል ነው። ሥራቸው የሰውን ልመና ወደፈጣሪ ማቅረብ፣ የፈጣሪን ምሕረት ደግሞ ለሰው ማድረስ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ መላእክት የሚያገለግሉት አምላክ ነው እንጂ ሙስሊሞች እንደሚሉት ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) የሆነ የአምላክ አገልጋይ አይደለም። መጥምቁ ዮሐንስ ከሞተ በኋላ ጌታ ከናዝሬት ተነሥቶ በባሕር አጠገብ ወዳለችው ወደ ቅፍርናሆም ሄዶ ኖሯል። ፈጣሪውን ባለማወቅ ጨለማ ውስጥ የሚኖር ሕዝብ ጌታ ተወልዶ በመካከሉ እየተመላለሰ ስላስተማረው ታላቅ ብርሃንን አየ (ማቴ. ፬፥፲፮)። ዮሐንስ መጥምቅ ከሞተ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንሥሓ ግቡ" እያለ ማስተማር ጀመረ። የዮሐንስ መጥምቅ ትምህርት የእርሱ የጌታ ትምህርት መሆኑን ለማሳወቅ ዮሐንስ ያስተማረውን አስተማረ። ጌታ ኢየሱስ እስከ ሠላሳ ዓመቱ ድረስም የተለያዩ ተአምራትን እያደረገ ተግባራዊ ትምህርትን እያስተማረ ኖሯል። ትምህርቱን ዓይተው 12ቱ ሐዋርያት ተማሪዎቹ ሆነው ተከትለውታል። ክርስቶስ ራሱ ብርሃን ይባላል። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ብሏልና። ትምህርቱም ሰውን ከድንቁርና ጨለማ የሚያድን በመሆኑ ብርሃን ይባላል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፫

ኢየሱስ ክርስቶስ ፈዋሽም ፈውስም ነው። አዳኝም መድኃኒትም ነው። "በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር" እንዲል (ማቴ. ፬፥፳፫)። የእርሱ አዳኝነት የባሕርይ አዳኝነት ነው። ፍጡራን ቢያድኑ የማዳንን ጸጋ ከእግዚአብሔር አግኝተው ነው። ስለሆነው ፈዋሽነታቸው የጸጋ ነው። ሲፈውሱም ሁሉን አይፈውሱም። ለፈውሳቸው ወሰን አለበት። ለፈውሱ ምንም ገደብ የሌለበት ፈዋሽና አዳኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አንዳንድ መድኃኒቶች ጥቂት በሽታዎችን ብቻ ይፈውሳሉ። ሁሉንም በሽታዎች የማዳን ኃይል የላቸውም። ኢየሱስ ክርስቶስን መድኃኒት ስንለው ግን በሽታዎችን ሁሉ መፈወስ የሚችል መድኃኒት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። "በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ" ተብሎ የተገለጸው ለዚህ ነው። በባሕርይው አዳኝ የሆነ ከእግዚአብሔር ውጭ ማንም የለም። "ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም" እንዲል (ኢሳ. ፵፫፥፲፩)። ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ በባሕርይው የሚያድን ነው። በተሰጣቸው ጸጋ ግን ቅዱሳን ሐዋርያትም ያድናሉ። እንዲያድኑ ራሱ

ክርስቶስም ልኳቸው ነበር (ማቴ. ፲፣፩-፰)፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደመሆኑ የመፈወስን ሥልጣን ለሐዋርያት ሰጥቷቸዋል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፬

ሐዋርያትን ጌታ በማቴ. ፭፣፲፬ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" ብሏቸዋል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃናችን ነው እያልን እንናገራለን፡፡ ብርሃን ነው ስንል የእርሱ ብርሃንነት የባሕርይው (ከሌላ ያልተቀበለው የራሱ ገንዘብ) ነው ማለታችን ነው፡፡ ቅዱሳንን ብርሃን ስንላቸው ግን ብርሃንነታቸው የጸጋ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን እጅግ አድርገን የምንወደው ብርሃናችን፣ አምላካችን፣ አባታችን፣ ቤዛችን፣ መድኃኒታችን....... በመሆኑ ነው፡፡ ቅዱሳንን የምናከብራቸው እና የምንወዳቸው ደግሞ ከፈጣሪ በተሰጣቸው ጸጋ ስለሚያድኑን፣ ብርሃን ስለሆኑልን፣ የእግዚአብሔርን መንገድ በተግባርም፣ በትምህርትም ስለሚያሳዩን ነው፡፡ ጌታ ክርስቶስ ሐዋርያቱን የዓለም ብርሃን ያላቸው በዚህ አግባብ ነው፡፡ ስለቅዱሳን ስንናገር ክርስቶስን ይሸፍነዋል የሚሉ ሰዎች ያልገባቸው ነገር ይህ ነው፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያትን ክርስቶስ ራሱ "የዓለም ብርሃን፣ የምድር ጨው" እያለ ተናግሮላቸዋል፡፡ እኛም የእርሱን ቃል ቃል አድርገን የዓለም ብርሃን፣ የምድር ጨው፣ ቅዱሳን እያልን እንናገራለን፡፡ እነርሱን ቅዱስ፣ ብርሃን፣ ጨው ስንል ግን የጸጋ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ክርስቶስን ብርሃናችን፣ ሕይወታችን ስንል ግን በባሕርይው ብርሃን፣ ቅዱስ ስለሆነ ነው፡፡ ነቢያትን ያስተምሩ ዘንድ የላከ ራሱ ጌታ ስለሆነ ነቢያትንና የነቢያትን ትንቢት ሊሽር አልመጣም (ማቴ. ፭፣፲፯-፵፰)፡፡ ጌታ ከነቢያት ትንቢት፣ ከኦሪት ሕግ የሻረው የለም፡፡ ያሻሻለውና አዲስ የሠራው ሕግ ግን አለ፡፡ እነዚህም ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ናቸው፡፡ ዐሥሩ ትእዛዛት የጸኑ ናቸው፡፡ የኦሪት መሥዋዕት አቀራረብ ደግሞ በራሱ ሥጋና ደም እንዲለወጥ አድርጎታል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፭

አቡነ ዘበሰማያት ስንል አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ የምንለው ማንን ነው? አብን ነው? ወልድን ነው? ወይስ መንፈስ ቅዱስን? "በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ" እንዲል (ማቴ. ፮፣፱-፲)፡፡ ስለ አብ ስለ ወልድ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስንናገር ሁልጊዜም መዘንጋት የሌለብን ነገር አለ፡፡ ይኸውም ግብረ ባሕርያቸውንና ግብረ አካላቸውን መለየት ነው፡፡ ግብረ አካል አይቀላቀልም፡፡ የአብ ግብር መውለድ ማሥረጽ ነው፡፡ የወልድ ግብር መወለድ ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ግብር መሥረጽ ነው፡፡ በዚህ ግብር ሦስቱ አካላት ይለያያሉ፡፡ ለአንዱ የተነገረው ለሌላው አይሆንም፡፡ አብን ወላዲ እንዳልነው ሁሉ ወልድንም ወላዲ አንለውም፡፡ ወልድን ተወላዲ እንዳልነው አብንም ተወላዲ አንለውም፡፡ መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ እንዳልነው አብንም ሠራጺ አንለውም፡፡ በግብረ ባሕርይ ግን ሦስቱም አካላት አንድ ናቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ለአንዱ የተነገረው ለሁለቱም ይሆናል፡፡ ባሕርይ የሚባለው የኩነታት ተገናዝቦ ነው፡፡ ኩነታት ማለት መሆኖች ማለት ነው፡፡ ይኸውም የአብ ልብ መሆን፣ የወልድ ቃል መሆን፣ የመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ (ሕይወት) መሆን ናቸው፡፡ እነዚህ መሆኖች በአንድ ህልውና ተገናዝበው ባሕርይ ይባላሉ፡፡ ወይም ባሕርይ ማለት የኩነታት ተገናዝቦ ማለት ነው፡፡ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ልብ አይደሉም፡፡ ነገር ግን በአብ ልብነት ስለሚያስቡ ለባውያን፣ አለባውያን ይባላሉ፡፡

አለባውያን ስንላቸው ለፍጡራን ነው። ፍጡራንን ማለበም የሦስቱም የአንድነት ሥራ ነውና። አብና መንፈስ ቅዱስ ቃል አይደሉም። ነገር ግን በወልድ ቃልነት ስለሚናገሩ ነባብያን፣ አንባብያን ይባላሉ። አንባብያን ስንላቸው ለፍጡራን ነው። ፍጡራን እንዲናገሩ ማስቻል የሦስቱም የአንድነት ሥራ ነው። አብና ወልድ እስትንፋስ አይደሉም። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት (ሕይወትነት) ስለሚኖሩ ሕያዋን፣ ማሕየውያን ይባላሉ። ማሕየውያን ስንላቸው ለፍጡራን ነው። ፍጡራን ሕያዋን ሆነው እንዲኖሩ ማስቻል የሦስቱም ሥራ ነው። ከዚህ የምንገነዘበው ለፍጡራን ባላቸው ሥራ የሦስቱም አንድ ሥራ እንዳላቸው ነው። ስለዚህ እኛ አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ ስንል እኛ ፍጡራን እንደመሆናችን አባትነቱ የሦስቱም አንድ ሥራ ነው ማለት ነው። ስለዚህ አባታችን ሆይ ስንል አብንም፣ ወልድንም፣ መንፈስቅዱስንም ማለታችን ነው። እኛን በጸጋ በመውለድ ሦስቱም ወላዲ፣ ወላዲ፣ ወላዲ ይባላሉ። እርስ በእርሳቸው ባለው አካላዊ ግብር ግን ወላዲ የሚባል አብ ብቻ መሆኑን ልብ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህ ግብረ አካልንና ግብረ ባሕርይን ለይተን እንወቅ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፮

ኢየሱስ፣ ኢየሱስ ማለት ብቻውን አያጸድቅም። የምናምነው ኢየሱስ ማን እንደሆነ፣ ከእኛ ምን እንደሚፈልግ ማወቅ ይጠበቅብናል። እርሱ ራሱ ሲያስተምረን "ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም" ብሎናል (ማቴ. ፯፣፳፩-፳፱)። በስሙ አጋንንትን ማውጣት፣ በስሙ ትንቢትን መናገር፣ በስሙ ተአምራትን ማድረግ ብቻውን ወደ መንግሥተ ሰማያት አያስገባም። ይህ እምነት ብቻ የሚሉ ሰዎችን ትምህርት ከንቱ የሚያደርግ ትምህርት ነው። ትእዛዛቱንም መፈጸም እንጂ አምንሃለሁ ኢየሱስ ማለት ብቻ ወደ ገነት አያስገባም። የምናምነው ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክም ሰውም (ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው) መሆኑን ማመን፣ ማመን ብቻ ሳይሆን አድርጉ ያለንን ትእዛዙን በፍጹም ፍቅር መጠበቅና ሌላውም እንዲጠብቅ ማስተማር ይገባናል። በክርስቶስ ስም ትንቢት መናገር፣ ተአምራትን መሥራት፣ አጋንንትን ማውጣት ብቻቸውን የጽድቅ መንገዶች አይደሉም። እኒህን ነገሮች እያደረጉ የእርሱን ፈቃድ (ትእዛዝ) የማይፈጽሙ ሰዎችን ጌታ ራሱ "አላውቃችሁም" ብሏቸዋል (ማቴ. ፯፣፳፫)። ኢየሱስ ክርስቶስን የሚወድ ሰው ከፍሬው ይታወቃል። ይህም ማለት በመልካም አስተሳሰቡ፣ በመልካም ንግግሩ፣ በመልካም ሥራው በጠቅላላው በተቀደሰ ሕይወቱ ይታወቃል። ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይም በምድርም የአምላክነት ሥልጣን ያለው አምላክ በመሆኑ ሲያስተምር እንደ ባለሥልጣን ያስተምር ነበር ተብሏል (ማቴ. ፯፣፳፫)።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፯

ኢየሱስ ክርስቶስ የሁላችንንም መዳን የሚሻ ቸር አምላክ ነው። መጻጉዕ ጌታን ልታድነኝ ትወዳለህን ቢለው "እወዳለሁ ንጻ" (ማቴ. ፰፣፫) ብሎታል። እግዚአብሔር በሕመማችን የሚተወን ትሕትናን እንድንማር፣ ጸጋን እንድናገኝበት፣ ከኃጢአታችን እንድንመለስ ነው። እርሱ መጥቶ "የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ" ተብሎ እንደተገለጸው በሽታዎችን ሁሉ መፈወስ የሚችል አምላክ ነው (ማቴ. ፰፣፲፯)። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን ያሳወቀን ተአምራትን በማሳየት፣ በተፈጥሮ ላይ ያለውን ኃይል አይተን፣ በተአምረ ኢየሱስ እንደተገለጸው ከልጅነቱ

ጀምሮ ከጭቃ ወፍን ሲፈጥር እና የመሳሰሉ ድርጊቶችን በማድረግ ነው። መጻጉዕን እወዳለሁ ንጻ ብሎ አዳነው። አምላክ ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ነገሮች አሳይቶ አምላክነቱን አሳወቀን። የክርስትና ሃይማኖት የተመሠረተው በእርሱ (በክርስቶስ) በመገለጥ ነው። መገለጡም በተአምራትና በብዙ አምላካዊ ትምህርቶች የታጀበ ነው። ይህ ከእስልምና ሃይማኖት ይለየናል። እስልምና እምነት ነቢዩ መሐመድን መሠረት አድርጎ የተመሠረተ እምነት ነው። ነገር ግን ነቢዩ መሐመድ ራሱ ከአላህ ይላክ አይላክ በምን እናውቃለን? ብለን ብንጠይቅ ምላሽ አናገኝም። ያልተገለጠለትን ተገለጠልኝ ብሎ በልብ ወለድ ድርሰት ሰውን እያታለለ ይሁን አይሁን በምን እናውቃለን? ብንል መልስ የለም። ምክንያቱም ከአምላክ ለመላኩ ማረጋገጫ የሚሆን አንድም ተአምርን አልሠራም። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አምላክ ወልደ አምላክ ለመሆኑ በሥራው ታይቷል። እምነታችን የተገለጠ መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፰

"አንተ ልጅ አይዞህ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው" (ማቴ. ፱፥፪)። ለሰውም እንዲህ ያለ ሥልጣን የሰጠ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ብዙ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) አድርገው ያስቡት ነበር። አምላክነቱን ይዘነጉት ነበር። በኃጢአት ምክንያት ደዌ ይዞት የነበረውን ሰው ከደዌው ፈውሶታል። ኃጢአትህ ተሰረየችልህም ብሎታል። ኃጢአትን ይቅር ማለት የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ብዙዎች የኢየሱስን አምላክነት ስላልተረዱ "ኃጢአትህ ተሰረየችልህ" ሲለው ደንግጠዋል። ኃጢአትህ ተሰረየችልህ የማለት ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር ነውና። በኋላ ግን ለሰው እንዲህ ያለ ሥልጣን የሰጠ እግዚአብሔርን አመስግነዋል። በእርግጥ አለማወቃቸው እንጂ ሰው የአምላክነትን ሥልጣን ያገኘው ገና በማኅፀን ቃል ሥጋን ሲዋሐድ ነው። እየተናገርን ያለነው ስለክርስቶስ ሰውነት መሆኑን ልብ ማድረግ ያስፈልጋል። ክርስቶስ በሽተኛውን አድኖ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ያለው አይሁድ የሰው ልጅ የተባለ እርሱ አምላክም እንደሆነ እንዲረዱ ነበር። ወልደ እግዚአብሔር ሰው የሆነው የጽድቅን መንገድ በመካከላችን እየተመላለሰ ሊያሳየን ነው። ከኃጢአተኞች ጋር ቁጭ ብሎ ይበላ የነበረው በፍቅሩ ስቦ ወደ ጽድቅ ይመልሰን ዘንድ ነበር (ማቴ. ፱፥፲፩)። የወደደን እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመስገን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፱

ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር "ኃጢአተኛዎችን ወደ ንሥሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም" ብሏል (ማቴ. ፱፥፲፫)። አምላክ ሰው የሆነው በኃጢአት የጠፋውን ሰው ሊያድነው ነው። ሰው የመሆኑ ዋና ምክንያት ይህ ነው። ለዚህም ነው ኃጢአተኞችን ወደ ንሥሓ ልጠራ ነው እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም ያለው። ሰው ሁሉ በአዳም በደል ምክንያት ገነትን አጥቶ ይኖር ነበር። ስለዚህ ወደገነት ይመልሰው ዘንድ ሰው ሆነ። ጌታ ጻድቃን የተባሉ መላእክትን ሊጠራ አልመጣም። ምክንያቱም ቅዱሳን መላእክት የመጀመሪያ ጥሪውን ተቀብለው በዚያው የጸኑ ናቸውና። ሰው ግን የመጀመሪያ ጥሪውን ሳይቀበል በራሱ በደል ጠፍቶ ነበርና ጠፍቶ እንዳይቀር ሰው ሆኖ ወደ ድኅነት ጠርቶታል። ሰው ሁሉ በአዳም በደል ምክንያት ገነትን አጥቶ ስለኖረ (ኃጥእ) እየተባለ ይኖር ነበር። ኃጥእ ማለት ገነትን ያጣ፣

ዘለዓለማዊ ሕይወትን ያጣ፣ እግዚአብሔርን ያጣ ማለት ነውና፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ የጽድቅን መንገድ አሳየን፡፡ "ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም" ከሚለው ቃል ውስጥ "አልመጣሁም" የሚለው ቃል መተርጎም አለበት፡፡ መምጣት እንደጊዜ ግብሩ ይተረጎማል፡፡ በብሉይ ብዙ ጊዜ ረድኤት መስጠት ተብሎ ይተረጎማል፡፡ በሐዲስ ደግሞ ሰው መሆን (መዋሐድ) ተብሎ ይተረጎማል፡፡ ለምጽአት ስንተረጉመው ደግሞ መፍረድ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ስለዚህ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም የሚለው ትርጓሜው ሰው የሆንኩ ጻድቃንን ልጠራ አይደለም ኃጥኣንን ነው እንጂ ማለት ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴

"ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁን አላቸው፡፡ አዎን ጌታ ሆይ አሉት፡፡ ማንም እንዳያውቅ ተጠንቀቁ ብሎ በብርቱ አዘዛቸው" (ማቴ. ፱፥፳፰)፡፡ ጌትነት የባሕርይ ጌትነትና የጸጋ ጌትነት ተብሎ ይከፈላል፡፡ ጌትነት ማለት ምሥጢሩ መግዛት ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ፈጥሮ የሚገዛ ስለሆነ "ጌታ ሆይ" እየተባለ ተጠርቷል፡፡ በጸጋ ገዢዎች የሆኑ ሰዎችም "ጌታ" ተብለዋል፡፡ ሣራ አብርሃምን ጌታዬ ትለው እንደነበር ተጽፏል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ሆይ እየተባለ ይጠራ የነበረው በባሕርይው ገዢ በመሆኑ ነው፡፡ ፈጥሮ የሚገዛን አምላክ እርሱ ስለሆነ ጌታ ሆይ እንለዋለን፡፡ ሕሙማን የጌታን ሁሉን ቻይነት አምነዋል፡፡ ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁን ሲላቸው አዎን ብለውታል፡፡ እርሱም አምላክ እንደመሆኑ ፈወሳቸው፡፡ ከፈወሳቸው በኋላ ይህንን ለማንም እንዳይናገሩ በብርቱ አዘዛቸው ተብሏል፡፡ ይህም ለቅዱሳን አብነት ለመሆን ነው፡፡ ደጋግ ሰዎች እግዚአብሔር በእነርሱ አድሮ ተአምራትን ሲሠራ ከንቱ ውዳሴ እንዳያጋጥማቸው መልካም ሥራቸውን ከሰው ይሠውራሉ፡፡ ተአምርን እናደርጋለን ብለው እዩን እዩን አይሉም፡፡ ይህም ከጌታቸው የተማሩት ትሕትናን ስለሆነ ነው፡፡ ፈጥሮ የሚገዛ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመስገን፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴፩

በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር፡፡ ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው (ማቴ. ፱ ፴፭-፴፮)፡፡ የሰው ልጅ በአዳምና ሔዋን ስሕተት ምክንያት ሞትን በመፍራት እየተጨነቀ፣ በእግረ አጋንንት እየተጠቀጠቀ ይኖር ነበር፡፡ ሰውን ወዳጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እኛን ከወደቅንበት ለማንሣት፣ ከዲያብሎስ እሥራት ነጻ ሊያወጣን ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም መጣ፡፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ ገንዘቦች አንዱ ርኅራኄ ነው፡፡ እርሱ ሩኅሩኅ ስለሆነ ሰዎች ተጨንቀው ሲያይ ያዝንላቸው ነበር፡፡ ለዚያ ነው ወንጌላዊው ማቴዎስ ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው ብሎ የጻፈው፡፡ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀን ስንኖር በነፍስም በሥጋም የሚጠብቀን እረኛችን ክርስቶስ መጣልን፡፡ "አነ ውእቱ ኖላዊ ኄር" ቸር እረኛ እኔ ነኝ፡፡ ቸር እረኛ ለበጎቹ ሲል ራሱን አሳልፎ ይሰጣል ብሎም አስተማረን፡፡ ምንም በደል የሌለበት እርሱ ሰውን ለማዳን ስለሰው ተሰቀለ፡፡ አንድ ባለቅኔ:-

በይነ ጣዕዋ ሐንካስ ትትበላዕ ላሕም አምስጦ ዘይትከሃላ፡፡

ለይእቲ ላሕም መድኃኔዓለም ተመሰላ፡፡

ብለዋል። አንካሳ ጥጃዋን ለማዳን ከአራዊት ማምለጥ የምትችል ላም ስለጥጃዋ ብላ ትበላለች ይልና ክርስቶስም በደል የሌለበት ንጹሐ ባሕርይ ቢሆንም እኛን ለማዳን ግን ሞት የማይገባው እርሱ እንደሞተ በቅኔው ለማመልከት ሞክሯል። ቸር ጠባቂያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይመስገን

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴፪

በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ። (ማቴ. ፲፥፴፪)። ወልድ ስለ አብ ይመሰክራል። አብም ስለወልድ ይመሰክራል። አብ የሌለበት ቦታ የለም። ወልድም የሌለበት ቦታ የለም። ነገር ግን ከላይ ባለው ጥቅስ እንደምንረዳው አብን #በሰማያት #ያለ ብሎ ገልጾታል። ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለመግለጽ በሰማይ ያለ እያሉ ይገልጹታል። በደመና የሚመስሉበት ጊዜም አለ። "ወበእንተ ዕበይከ ትትሜሰል በደመና" እንዲል። ስለዚህ በሰማያት ያለ ሲል ህልውናውን በሰማይ ብቻ ወስኖ መናገሩ ሳይሆን ስለታላቅነቱ በሰማይ ያለ እንደተባለ መረዳት ይገባል። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በዓለም ሁሉ ህልዋን ናቸው። ከዓለም በአፍኣም ህልዋን ናቸው። እነርሱ የሌሉበት ቦታ የለም። ወልድ ስለአብ የሚመሰክር ብቻ አይደለም። አብም ስለወልድ ይመሰክራል። "የላከኝ አብም ስለእኔ ይመሰክራል" እንዲል (ዮሐ. ፰፥፲፰)። "የላከኝ" የሚለው ቃል ትርጉም "ሰው እንድሆን ያደረገኝ" ተብሎ ይተረጎማል። ወልድ የሰውን ሥጋ እንዲዋሐድ ያደረገው አብ ነው። አብ ብቻ ግን አይደለም። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በግብረ ባሕርይ አንድ ስለሆኑ አብ ቢጠቀስም ለሁለቱም የተነገረ እንደሆነ ልብ ማድረግ ያስፈልጋል። ወልድ ሰው የሆነው በአብ ፈቃድ፣ በራሱ ፈቃድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ነውና። "እስመ በፈቃዱ ወበሥምረተ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ መጽአ ወአድኀነነ" እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም (ውዳሴ ማርያም ዘሠሉስ)።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴፫

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት "ደዌንና ሕማምን ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው" ተብሏል (ማቴ. ፲፥፩)። ሐዋርያትንም በከንቱ ተቀብላችሁ በከንቱ ስጡ ብሏቸዋል። እግዚአብሔር ለእኛ ለሰው ልጆች የሰጠን ስጦታ ብዙ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደመሆኑ ለሐዋርያት በሽተኞችን ይፈውሱ ዘንድ ሥልጣንን ሰጥቷቸዋል። በሽተኞችን እንዲፈውሱ ሥልጣንን መስጠት የአምላክ ሥራ ነውና። ሐዋርያትም በተቀበሉት ጸጋ የሰውን ልጅ በነጻ እንዲያገለግሉ ታዝዘዋል። ሀብተ መንፈስ ቅዱስ በዘር፣ በገንዘብ፣ በሥልጣን የሚታደል አይደለም። ለሚገባው ሰው በነፃ የሚሰጥ ነው። የሀብቱ ባለቤት ኢየሱስ በከንቱ ተቀብላችሁ በከንቱ ሥጡ ብሏልና። አሁን አሁን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ያፈነገጡ ጳጳሳትን፣ ካህናትን፣ ምእመናንን እያየን ነው። ሀብተ መንፈስ ቅዱስ የሆነውን ክህነት በብሔር የሚያድሉ፣ በባለሥልጣን ጫና ጵጵስና የተሾሙ ሰዎችን ማየት የተለመደ ሆኗል። ምእመናንን በዘረኝነት ንግግር የሚያሳዝኑና የሚያበሳጩ ክፉ እረኞችን ማየት አዲስ ነገር አይደለም። ነገር ግን ምእመናን በዚህ ብዙ ሊያዝኑ አይገባም። ሁልጊዜም ዋናውን ጠባቂያችንን (እረኛችንን) ኢየሱስ ክርስቶስን ማየት አለብን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴፩

"በሁሉም ስለስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ" (ማቴ. ፲፥፳፪)። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ብሎናል። እርሱ ክርስቶስ እንደተባለ እኛም ልጆቹ በእርሱ ስም ክርስቲያን እንባላለን። እርሱ ርቱዕ እንደሆነ እኛም በእርሱ ርቱዓነ ሃይማኖት ስለሆንን በግሪክ ቋንቋ ኦርቶዶክስ እንባላለን። እርሱ ክርስቶስ በተዋሕዶ ከሁለት አካል አንድ አካል፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የሆነ እንደሆነ ሁሉ እኛም ይህንን ተዋሕዶውን እንደምናምን ለመግለጽ ተዋሕዶ እንባላለን። ክርስቲያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነን። እርሱ ክርስቶስ ምንም በደል ያልተገኘበት ንጹሐ ባሕርይ ነው። ነገር ግን አይሁድ በውሸት ከሰሱት። ናቁት፣ ሰደቡት፣ ተፉበት፣ በጥፊ እየመቱ ማን መታህ እያሉ ተሳለቁበት። እርሱ ጌታ ግን መከራ መስቀሉን እኛን ለማዳን ተጠቀመበት። ሰይጣን ጌታ ክርስቶስ በመስቀሉ እንደሚያድነን ቢያውቅ ኖሮስ ባላሰቀለውም ነበር። የጌታ ሥራ ድንቅ ነው። ጌታ ሰቃዮቹን ማጥፋት ይችል ነበር። ነገር ግን የመጣው ሊያድናቸው እንጂ ሊያጠፋቸው ስላልሆነ እየሰደቡት፣ እየተፉበት፣ እየተሣለቁበት፣ እየሰቀሉት ዝም አለ። እኛ ክርስቲያኖችም በእርሱ ስም ስለተጠራን ስለስሙ ሁልጊዜም መከራን እንቀበላለን። ቤተክርስቲያን ንጽሕት ሆና ሳለ በክፋዎች ዘንድ በክፋት ትነሣለች። በየቦታው ትነዳለች። አገልጋዮቿ በየቦታው መከራን ይቀበላሉ። ያለስሟ ስም ይሰጣታል። ለዓለም መዳን እና ሰላም የምትጸልይ ሆና ሳለ ነገር ግን እንደዐመፀኛ ተቆጠረች። የክርስቶስን ስም ስለያዘች በክፋዎች ዘንድ ተሰደበች፣ የሥልጣኔ ፀር ተባለች፣ የኢኮኖሚያዊና የማሕበራዊ ሕይወት እንቅፋት ተባለች። እውነታው ግን ይህ አይደለም። ቤተክርስቲያን ለሥልጣኔ ዋና በር ከፋች፣ የመልካም ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ሕይወት መሠረት ናት። እንደጌታዋ እንደክርስቶስ ንጽሕት ሆና ሳለ ክፋዎች በሐሰት ይከሷታል። ኢየሱስ ክርስቶስ በስሙ የተጠራን እኛን ክርስቲያኖችን ይጠብቀን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴፫

"ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" (ማቴ. ፲፥፴፯)። ከኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ የምንወደው ነገር የለም። ከዐሥሩ ሕግጋት አንዱ እናትህንና አባትህን አክብር የሚል ነው። እናትና አባትን ማክበር ማለት ደግሞ እናትንና አባትን መውደድ፣ መታዘዝ፣ ማክበር፣ መፍራት ናቸው። እናትና አባትን መውደድ ማለት ግን ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ነው። ከእግዚአብሔር ይልቅ እናትና አባቱን የወደደ ሰው ግን የኢየሱስ መሆን አይችልም። ሰው የኢየሱስ ክርስቶስ መሆን የሚችለው ከራሱም በላይ ኢየሱስ ክርስቶስን ሲወድ ነው። ራስን ሳይክዱ የኢየሱስ ነኝ ማለት አይቻልም። ኢየሱስ ፈጥሮ የሚገዛን አምላክ በመሆኑ ፍጥረታት ሁሉ የእርሱ ናቸው። የፍጥረታት ሁሉ ባለቤት እርሱ ነው። በተለየ በእርሱ አምነን፣ በእርሱ ስም ተጠምቀን የምንኖር እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ ልጆቹ ነን። ልጅ ደግሞ የአባቱን ንብረት የሚወርስ በአባቱ ንብረት የሚሾም ወራሽ ነው። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ "ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" ያለው ወራሽ አይሆንም ማለቱ ነው። እንጂ በተፈጥሮ የእኔ ገንዘቦች አይደሉም ማለቱ እንዳልሆነ ልብ ማድረግ ይገባል። በተፈጥሮ ፍጥረታት ሁሉ የእርሱ ገንዘቦች ናቸውና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴፮

ብዙዎች ስለቅዱሳን ስንናገር የኢየሱስን ክብር እንደመቀነስ ይቆጥሩታል። ነገር ግን ቅዱሳንን የምናከብረው ስለኢየሱስ ብለን እንደሆነ ቢያውቁ ሸጋ ነበረ። ራሱ ክርስቶስኮ "ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል። ጻድቅንም በጻድቅም ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ውሃ ብቻ የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም" ብሎ አስተምሮናል (ማቴ. ፲፥፵፩-፵፪)። ጻድቅን ጻድቅ ነው ብለን መቀበል የጻድቁን ዋጋ እንደሚያስገኝ እናምናለን። ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነግሮናል። ቅዱሳንን የምናከብራቸው አባታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳከበራቸው አይተን እርሱን አብነት አድርገን ነው። እርሱን ስናከብርና ቅዱሳንን ስናከብር ግን አከባበራችን የተለያየ ነው። ኢየሱስን ስናከብር እርሱ የባሕርይ አምላክ መሆኑን አምነን የባሕርይ የአምልኮት አክብሮት ነው። ቅዱሳንን የምናከብራቸው ግን በኢየሱስ አስተምህሮ ጸንተው ስላለፉና ኢየሱስም ስላከበራቸው ነው። የምናከብራቸውም በተሰጣቸው ጸጋ ስለሆነ የጸጋ ክብር ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴፯

በከተማዎቻቸው ሊያስተምርና ሊሰብክ ከዚያ አለፈ (ማቴ. ፲፩፥፩-፮)። የማስተማር ዋና ዓላማ ሰውን ከገቢረ ኃጢአት ወደገቢረ ጽድቅ መመለስ ነው። ያላመኑትን ማሳመን፣ ያመኑትን ማጽናት ነው። ጌታ ክርስቶስ ይህችን ዓለም ያለመምህር ትቷት አያውቅም። ቀድሞ ነቢያትን ልኮ ሕዝቡን ያስተምር ነበር። ሰው በነቢያት ትምህርት መጽናት ቢያቅተው ሰውን ወዳጅ እርሱ ራሱ ሥጋን ተዋሕዶ በመካከላችን እየተመላለሰ አስተማረን። ዋና መምህራችን እርሱ ኢየሱስ ነው። የጌታ ትምህርት ሁለት ዓይነት ነበር። አንደኛው በቃል ማስተማር ሲሆን፣ ሁለተኛው በተግባር ማስተማር ነበር። በቃሉ እኔና አብ አንድ ነን ብሎ አምላክነቱን የተናገረ ጌታ በተግባር ደግሞ ለምፃሞችን በማንጻት፣ ዕውራንን እንዲያዩ በማድረግ፣ ዲዳዎችን እንዲናገሩ በማድረግ፣ መስማት የማይችሉ ሰዎችን መስማት እንዲችሉ በማድረግ አምላክነቱን አሳወቀ። ዮሐንስ መጥምቅ ደቀመዛሙርቱን ልኮ የምትመጣው አንተ ነህን ብሎ ባስጠየቀው ጊዜ ጌታ የመለሰለት ምላሽ ተግባራዊ ምላሽ ነበር። አሁን መጥምቁ ዮሐንስ አስቀድሞ የኢየሱስን አምላክነት አላውቅ ብሎ አልነበረም። ደቀመዛሙርቱ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት እንዲረዱለት ነበር እንጂ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴፰

ጌታ ኢየሱስ "በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው" ብሏል (ማቴ. ፲፩፥፮)። በእርሱ የማይሰናከል ሰው ብፁዕ ነው። ብዙዎች ግን ስለጌታ ክርስቶስ የሆነውን ሳይሆን የመሰላቸውን በመናገር ተሰናክለው ወድቀዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውም አምላክም መሆኑን ዘንግተው እስላሞች ሰው ብቻ (ፍጡር) አድርገው ይቆጥሩታል። አንዳንዶች በመለኮት ከአብ ጋር አንድ የሆነውን እርሱን ጌታን ከአብ አሳንሰው ይናገሩለታል። ካቶሊኮች አምላክም ሰውም የሆነ አንድ ክርስቶስ ሆኖ ሳለ በአካል አንድ አድርገው በባሕርይ ሁለት ብለው በራሳቸው ግላዊ ፍልስፍና ተመርተው ተሰነካክለዋል። ቅባቶች ደግሞ ለክርስቶስ ሥጋ መንፈስ ቅዱስ ክብር ሆነው ብለው በምሥጢረ ሥጋዌ፣ በምሥጢረ ሥላሴ ላይ ደግሞ ቀባዒ፣ ተቀባዒ፣ ቅብዕ የሚል አካላዊ ግብር ጨምረው ተሰነካክለዋል። የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ግብር መውለድ

ማሥረጽ፣ መወለድ፣ መሥረጽ ብቻ መሆኑን ይዘነጉታል። በእርሱ በኢየሱስ ክርስቶስ የማትሰነካከለዋ ቅድስት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ግን ብፅዕት ናት። ቤተክርስቲያን ስለክርስቶስ ስትናገር

፩) ራሱ ስለራሱ የተናገረውን

፪) ነቢያት ስለእርሱ የተነበዩትን

፫) ሐዋርያት ስለእርሱ ያስተማሩትን

፬) ሊቃውንት ስለእርሱ ያመሰጠሩትን

መሠረት አድርጋ ነው። ከቀድሞ ጀምሮ ሲተረጎም የመጣውን ትርጓሜ ይዛ ትናገራለች። በራስ ስሜት ተነሳስቶ በክርስቶስ መሰነካከል አይገባም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴፱

"እውነት እላችኋለሁ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም። በመንግሥተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል" (ማቴ. ፲፩፣፲፩)። ስለቅዱሳን ታላቅነት የሚመሰክር ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጌታ ስለ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ታላቅነት ለሕዝቡ አስተምሯል። እኛም ጌታን አብነት አድርገን ስለቅዱሳን ታላቅነት እንናገራለን። ሉተራውያን የማይረዱትና ሊረዱትም የማይፈልጉት ጉዳይ ይህ ነው። በጩኸት ብዛት እውነትን ለመደበቅና ራሳቸውን በውሸት ለማጽናናት የሚያደርጉት ጥረት ይገርማል። ሴቶች ከወለዷቸው ሁሉ ከዮሐንስ መጥምቅ የሚበልጥ የለም። የዮሐንስ መጥምቅ ቅድስናው ክብሩ ገናና ነው። የቅዱስ ዮሐንስ ሕይወቱ በበረሃ ነበር። ልብሱም የተናቀ ነበር። ስለቅዱሳን ክብር መናገር የኢየሱስን ክብር አይሸፍነውም። ኢየሱስን የምናከብረው አምላክ ነው ብለን ነው። ቅዱሳንን የምናከብራቸው ደግሞ በኢየሱስ ትምህርት ጸንተው ስለኖሩና እንዴት በኢየሱስ ስም እንደፀኑ ከሕይወታቸው ትምህርትን ስለምናገኝ ነው። ይኸውም የጸጋ አክብሮት ነው። ኢየሱስን የምናከብረው ግን የአምልኮ አክብሮት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፵

ጌታ ክርስቶስ በባሕርይው ፍቅር ነው። ይህ ማለት ጥላቻ አይስማማውም ማለት ነው። አይሁድ እርሱን ጌታን ከኃጢአተኞችና ከቀራጮች ጋር ሲበላ አይተውት ነቅፈውት ነበር። "የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ" ብለውታል (ማቴ. ፲፩፣፲፱)። ኢየሱስ ኃጢኣታችን እንደ ምድር አሸዋ የበዛ ቢሆን እንኳ ንስሓ ብንገባ ይቅር የሚል አምላክ ስለሆነ ኃጥአንን ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ ምክንያት ለመሆን አብሯቸው ይበላ ይጠጣ ነበር። ጌታ ሰዎች ተአምራቱን አይተው፣ ትምህርቱን ሰምተው ከኃጢአታቸው ተመልሰው መልካም ሥራን ይሠሩ ዘንድ በከተማዎችና በመንደሮች እየተመላለሰ ያስተምር ነበር። ነገር ግን ይህ ሁሉ ተደርጎላቸው ከኃጢአታቸው ያልተመለሱ ሀገሮች ስለነበሩ ወዮልሽ ኮራዚ ወዮልሽ ቤተሳይዳ እያለ ወቅሷቸዋል። በፍርድ ቀን መከራ እንደሚበዛባቸውም ነግሯቸዋል (ማቴ. ፲፩፣፳-፳፫)።

ጌታ ኃጥአንን እንጂ ኃጢአታቸውን አይወድም። ኃጥአንን ከኃጢአታቸው ለመለየት ብዙ ተአምራትን አሳይቷል። ነገር ግን በባሕርይው ፍቅር የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርይው በትክክል የሚፈርድ (ፈታሒ በርትዕ) ስለሆነ ለሁሉም እንደየሥራው ይከፍለዋል። ፍቅሩና ፍርዱ የተስማማለት ጌታ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ የኃጢአተኞች ወዳጅ ነው እያልን ኃጥአን እንሁን ማለት ትልቅ በደል ነው። ጌታ ኃጥአንን በባሕርያቸው ይወዳቸዋል በግብራቸው ግን ይጠላቸዋል። ጻድቃንን ደግሞ በባሕርያቸውም በግብራቸውም ይወዳቸዋል። ስለዚህ እንደ ጻድቃን በግብርም ለመወደድ መልካም ሥራን መሥራት ይገባናል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፵፩

"ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል። ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም። ከወልድም በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም" (ማቴ. ፲፩፥፳፯)። አብ ወልድን፣ ወልድ አብን ያውቀዋል። ይህ ዕውቀት ባሕርያዊ ዕውቀት ነው። ወልድ አብን የሚያውቀው ከሆነና አብና ወልድ በክብር አንድ ከሆኑ ወልድ ከአባቱ ምንን ይቀበላል? በሥላሴ ዘንድስ አንዱ ሰጪ አንዱ ተቀባይ ይሆናል እንዴ? የዚህ ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው? ይህ ቃል የተነገረው ስለሥጋ እንግድነት ነው። ከተዋሕዶ በፊት አምላክ ያልነበረ ሥጋ ቃል በተዋሐደው ጊዜ ግን የአምላክነትን ክብር ሁሉ አግኝቷል። በተዋሕዶ ሥጋ ቃልን ቃል ሥጋን ገንዘቡ ሲያደርግ ለሥጋ በቃል አብ ልቡ፣ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋሱ ሆነዋል። በተዋሕዶ ሥጋ አምላክ እንዲሆን ማድረግ ደግሞ የሦስቱም የአንድነት ሥራ ነው። በማክበር አንድ ናቸውና። በአንድነት ሥራ ደግሞ በተለየ ከሦስቱ አካል አንዱ ቢጠራ እንኳ ሁለቱንም የሚመለከት ጉዳይ መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል። ተሰጠኝ ሲል ስለ ሰውነቱ እየተናገረ መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፵፪

"እናንተ ደካማዎች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደእኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ። እኔ የዋሕ በልቤም ትሑት ነኝና። ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ። ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና" (ማቴ. ፲፩፥፳፰-፴)። ክርስቶስ ከእኔ ተማሩ ብሏል። በእርግጥም የጽድቅን መንገድ ሊያሳየን የመጣ ቸሩ አምላክ እርሱ ስለሆነ ከእርሱ የበለጠ ሊያስተምረን የሚችል የለም። ከጌታ የምንማረው በቃሉ ከተናገረውም፣ በተግባር ካሳየውም ነው። እርሱ እንደጾመ እንጾማለን፣ እርሱ ለእኛ ጸሎትን ለማስተማር እንደጸለየ እንጸልያለን። እርሱ ትሑት ነኝ ብሎ እንደተናገረ እኛም ደጉን አባታችንን እርሱን በትሕትና ለመምሰል እንጥራለን። ጌታ በዚህ ምድር ካደረጋቸው ድርጊቶች አንዳንዶች ለእኛ ለአርአያነት ያደረጋቸው ናቸው። ይኸውም እኛ እርሱን አይተን እንድንተገብራቸው ነው። ለምሳሌ እርሱ ተጠምቋል። መጠመቁ ለእርሱ የሚጠቅመው ነገር የለም። ተጠምቆ ተጠመቁ ለማለት ለእኛ ለአርዓያነት ይሆን ዘንድ ግን ተጠምቋል። ጌታ ቀንበሬ ቀሊል ነው ብሎ ቀንበሬ ያላት ሕገ ወንጌልን ነው። ቀላል ናት ማለቱ ቅንነት ካለን እና መዳንን የምንሻ ከሆነ ለመተግበር የሚያስቸግር ሕግ እንደሌለ ለመግለጽ ነው። ከጌታ ተምረን እርሱ ባሳየን የጽድቅ መንገድ ብንጓዝ ለነፍሳችን ዕረፍትን እንደምናገኝ ነግሮናል። ኃጢአታችን በዝቶ ሸክማችን የከበደን እኛን

ወደ እኔ ኑ አሳርፋችኋለሁ ብሎናል። ስለዚህ ዕረፍትን እናገኝ ዘንድ በእርሱ አምነን፣ ተጠምቀን፣ መልካም ምግባርን ሠርተን፣ ሥጋውን ደሙን ተቀብለን ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት መጣር ይገባናል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺፫

"የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና" (ማቴ. ፲፪፥፰)። ጌታ ክርስቶስን ዕሩቅ ብእሲ ወይም ሥጋን ያልተዋሐደ አምላክ አድርጎ ማሰብ ክሕደት ነው። ሰውነቱን ዘንግተው "አምላክ ብቻ" ለሚሉ ከሓድያን በቂ ምላሽ የሚሰጥ "የሰው ልጅ" ብሎ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ማድረጉ ነው። ክርስቶስን ዕሩቅ ብእሲ (ሰው ብቻ) አድርገው በማሰብ ከነቢያት እንደ አንዱ አድርገው ለሚያስቡ ከሓድያን ደግሞ በቂ ምላሽ የሚሰጠው "የሰንበት ጌታ ነውና" የሚለው አገላለጽ ነው። የሰው ልጅም የሰንበት ጌታም የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ሰንበት ከሰባቱ ዕለታት አንዷ ናት። የሰንበት ጌታ ነኝ ሲል ከሰባቱ ዕለታት በተለየ የቅዳሜ ብቻ አምላክ ነኝ ለማለት አይደለም። ሰንበት ማለት ዕረፍት ማለት ነው። ስለዚህ ዕረፍትን የምሰጥ የዕረፍት አምላክ ነኝ ማለቱ ነው። የጊዜያትም የቅዱሳት መካናትም በጠቅላላው የፍጥረታት ሁሉ አምላክ እርሱ ነው። ብዙ ጊዜ አይሁድ ከእርሱ ይልቅ ለቤተመቅደስ ክብር ይሰጡ ነበር። ይኸውም የእርሱን የጌታን አምላክነት ባለማወቃቸው ነበር። እርሱ ጌታም "ከመቅደስ የሚበልጥ ከዚህ አለ" ብሎ አምላክነቱን እንዲረዱ ነግሯቸው ነበር (ማቴ. ፲፪፥፮)። ከመኖሪያው ኗሪው ይበልጣልና። ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔር ረድኤት የሚገለጥበት ቅዱስ ቦታ ነው እንጂ ራሱ እግዚአብሔር አይደለምና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺፬

ጌታ ክርስቶስ "በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዷል" ብሎ አስተምሮናል (ማቴ. ፲፪፥፲፪)። አይሁድ ከመሠረታዊው የሰንበት አከባበር ይልቅ የራሳቸውን ወግ በመጨመር ሕዝቡን ያታልሉ ነበር። ሰንበት እንድትከበር ለሙሴ ትእዛዝን የሰጠው ወልደ እግዚአብሔር ግን ትክክለኛውን የሰንበት አከባበር ነገረን። ጌታ ክርስቶስ በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት በተአምራት ድውያንን ይፈውስ ነበር። አይሁድ ግን በሰንበት ሰው እንዲፈወስ እንኳ አይፈልጉም ነበር። ይህ ብቻ አይደለም። ፍላጎታቸውን በዓል አድርገውት ነበር። ስለዚህ የሰንበት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትክክለኛውን የሰንበት አከባበር አስተማረን። ከዐሥሩ ትእዛዛት አንዱ ሰንበትን አክብር የሚለው ነው። በዚህ አገላለጽ ውስጥ "ሰንበት" የተባለች "ቅዳሜ ቀን" ናት። እሑድን ሰንበት ብለን ያከበርናት ከጌታ ትንሣኤ በኋላ ነው። ከመጀመሪያዋ ሰንበት ለመለየት ስንልም ሰንበተ ክርስቲያን ብለን እንጠራታለን። በሰንበት የማይሠራው ሥጋዊ ሥራ ነው እንጂ መንፈሳዊ ሥራን መሥራት ይቻላል። ይኸውም የታመሙትን መጠየቅ፣ የታሠሩትን እግዚአብሔር ያስፈታሕ ማለት፣ የተጣሉትን ማስታረቅ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ፣ መንፈሳዊ ትምህርቶችን መማር እና የመሳሰሉ መንፈሳዊ ሥራዎችን መሥራት ይገባል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺፭

ስለ ጌታ በነቢያት "የተቀጠቀጠን ሸንበቆ አይሰብርም" ተብሎ ተነግሮለታል (ማቴ. ፲፪፥፳)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርጋታው የተነሣ የተቀጠቀጠ ሸንበቆን እንኳ አይሰብርም ተብሏል። ትክክለኛው የሰውነት መለኪያ ክርስቶስን መምሰል ነው። ሰው ኃጢአትን የማይሠራ ከሆነ የተረጋጋ ሕይወትን ይኖራል። ጌታ በዚህ ምድር ሲመላለስ አንድም ቀን እንደሳቀ አልተጻፈም። ብዙ ጊዜ አለቀሰ እየተባለ ተጽፏል። በእርግጥ ተረጋግቶ ለሚያስብ፣ ተረጋግቶ ለሚናገር ሰው የሚያስቅ ነገር ያለ አይመስለኝም። ውካታ፣ ግርግር፣ ብስጭት፣ ለፍላፊነት፣ ክልብ ክልብ ማለት፣ ሳያዳምጡ መናገር እና የመሳሰሉት ነገሮች ሰው ያልተረጋጋ ሕይወትን ሲመራ የሚያጋጥሙት ነገሮች ናቸው። ሙሉ ሕይወታችን የተስተካከለ እና የተወደደ ይሆን ዘንድ ከፈለግን በፍኖተ ክርስቶስ መመራትና ክርስቶስን መምሰል ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፵፮

"በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሠረይለታል። በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለምም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሰረይለትም" (ማቴ. ፲፪፥፴፪)። ሰዎች እግዚአብሔርን እግዚአብሔር እንደሆነ አውቀው፣ ፈጣሪ እንደሆነ አውቀው ቢሰድቡትና ቢክዱት ኃጢአታቸው አይሰረይላቸውም። የሰው ልጅ የተባለ ጌታ ክርስቶስን ሰው ብቻ ነው ብለው ቢሳደቡ ይሰረይላቸዋል ብሏል። ምን ማለት ነው? ይህ ትርጓሜ ያሻዋል። ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአምላክነት አንድ ናቸው። ታዲያ ለምን ለአንዱ አይሰረይለትም ብሎ ለሌላው ይሰረይለታል አለ? ወልድ ሥጋን ስለተዋሐደ አምላክነቱን ባለማወቅ ሰውነቱን ብቻ አይተው ቢሰድቡትና ንሥሓ ቢገቡ ይቅር ይላቸዋል። ራሱ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ እየሰደቡት፣ እየተሳለቁበት እንኳ ይቅርታን ይለምንላቸው ነበርና። የኢየሱስ ክርስቶስነት አምላክነቱን አብ በደመና ሆኖ ልጄ ነው ብሎ መስክሮለት፣ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል አርፎበት አውቀው ሳለ ቢክዱት ግን ኃጢአታቸው አይሰረይላቸውም ማለት ነው። ይህም ቢሆን ግን ሰዎች ንሥሓ ገብተው ከክሕደት ተመልሰው ከመጡ በሁሉም ኃጢአታቸው ይሰረይላቸዋል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፵፯

"እናንተ የእፉኝት ልጆች" (ማቴ. ፲፪፥፴፬)። የጌታ ትምህርት ሦስት ዓይነት ነበር። አንደኛው ቃለ አራኅርኆ ነው። እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ ብሎ በርኅራኄ የሚናገርበት ወቅት ነበረ። ሁለተኛው ቃለ ተግሣጽ ነው። ይኸውም ሰዎች ከክፉ ሥራቸው ይመለሱ ዘንድ በግብራቸው ይጠራቸው ነበር። ይኸውም እውነትን ላለመቀበል ልባቸውን ያሳወሩትን ሰዎች "ዕውር ዕውርን አይመራውም" እያለ ይናገራቸው ነበር። ሦስተኛው ተግባራዊ ቅጣት ነበር። ይኸውም ቤቴ የጸሎት ቤት እንጂ የወንበዴዎች ዋሻ አይደለችም ብሎ ወገፍትዐ መዓዳቲሆሙ ለመወልጣን እንዲል በጅራፍ እየገረፈ ያስተማራቸው ትምህርት ነው። መምህራን ሕፃናት ደቀመዛሙርቶቻቸውን፣ እናት አባት ልጆቻቸውን ትምህርት አልከታተል ሲሏቸው እየተቆጡ መግረፋቸው ጌታን አብነት አድርገው ነው። ይህ የተፈቀደ ቅጣት ነው። ነገር ግን ቅጣታችን ፍትሐዊ እንዲሆንና እንቀጣለን ብለን ሕፃናትን ስንገርፍ ሞታቸው በእጃችን እንዳይሆን አማትበን፣ መግረፊያውን በጉልበታችን በራሳችን ፈትነን ሊሆን ይገባዋል። ሰው ከክፉ ሥራው ይመለስ ዘንድ በፍቅር ነግረነው ትምህርታችንን አልቀበል ካለ ሌባውን ሌባ፣ ውሸታሙን

ውሸታም፣ ገዳዩን ገዳይ እያልን በስሙ ብንጠራው በደል አይሆንብንም። ይህንንም የምናደርገው ግብሩ ጥሩ እንዳልሆነና እንደሚያስነቅፍ ተረድቶ ወደ መልካም እንዲሳብ ነው እንጂ ከጥላቻ ከመነጨስሜት መሆን የለበትም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፵፰

"እናቱና ወንድሞቹ ሊነጋገሩት ፈልገው በውጭ ቆመው ነበር" (ማቴ. ፲፪፥፵፯)። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም ናት። "ወንድሞቹ" ተብለው የተገለጹት አብረውት ያደጉት የዮሴፍ ልጆች ናቸው። ወንድማማችነት ከእናትና ከአባት በመወለድ ብቻ አይደለምና። ብዙ ዓይነት ወንድማማችነቶች አሉ። አንደኛው ከእናት ከአባት በመወለድ ነው። ይኸው እንደ አቤል እንደ ቃየል፣ እንደ ያዕቆብ እንደ ኤሳው ያለ ወንድማማችነት ነው (ዘፍ. ፳፯፥፲፩)። ጥብቅ ጓደኝነትን እንደ ወንድማማችነት የሚቆጥርበት ጊዜም አለ። ለምሳሌ ዳዊትና ዮናታን ጓደኝነታቸው ጥብቅ ስለነበረ ዳዊት ዮናታንን ወንድሜ ብሎታል (፪ኛ ሳሙ. ፩፥፳፯)። ከእናትና ከአባት ከመወለድ ውጭ ባለ ዝምድናም ወንድማማች መባል የተለመደ ነው ለምሳሌ ላባ ያዕቆብን ወንድሜ ይለው ነበር (ዘፍ. ፳፱፥፲፭)። በተፈጥሮ ሰው ሁሉ ወንድማማች ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው ያለ በዚህኛው አግባብ ነው (ማቴ. ፲፰፥፳፩)። በተጨማሪም ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ጌታ ሲናገር "ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው" ብሏል (ዕብ. ፪፥፲፯)። ይህ ማለት ሰው ሆነ ማለት መሆኑን ልብ ማድረግ ያስፈልጋል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉ ሰዎች የክርስቶስ ወንድሞች ተብለው ተጠርተዋል (ማር. ፫፥፴፭)። ጌታ ክርስቶስም "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ፣ እኅቴም እናቴም ነውና" ብሎ የተናገረው ለዚህ ነው። ከላይ የጌታ ወንድሞቹ የተባሉት ደግሞ አብሮ በማደግ፣ በሥጋዊ ዝምድና ምክንያት ነው እንጂ ከአንድ እናትና አባት በመወለዳቸው አይደለም። ለድንግል ማርያም ከክርስቶስ ውጭ ልጅ የላትምና። ክርስቶስንም የወለደችው ያለ ወንድ ዘር ነውና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፵፱

"በምሳሌም ብዙ ነገራቸው" (ማቴ. ፲፫፥ ፫)። ጌታ ቸር መምህር እንደመሆኑ ሲያስተምር ለሰማዕያኑ ትምህርቱ የተረዳ ይሆን ዘንድ ብዙ ጊዜ በምሳሌ ያስተምር ነበር። በእርሻ፣ በሰናፍጭ ቅንጣት፣ በዘሪ፣ በእርሾ፣ በመልካም እንቍ፣ በዓሣ መረብ እና በመሳሰሉት እየመሰለ ያስተምር ነበር። በምሳሌ የሚሰጥ ትምህርት ለብዙ ጊዜ በአእምሮ ስለሚቆይ አይረሴነት ይኖረዋል። ጌታም ለእያንዳንዱ ለኑሮው ቅርብ በሆነ ነገር እየመሰለ ምሥጢረ መንግሥተ ሰማያትን ለሰው ያስረዳ ነበር። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቃውንትም ረቂቁን ምሥጢረ ሥላሴን፣ ምሥጢረ ሥጋዌን ለማስረዳት ጌታቸው ኢየሱስ ክርስቶስን አብነት አድርገው በምሳሌ እየመሰሉ ያስተምራሉ። ይህ የዚህ ምሳሌ፣ ይህ የዚህ ምሳሌ እያልን ስንናገር አብነታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ልብ ማድረግ ያስፈልጋል። ምሳሌ ደግሞ ለሰው ግልጽ ይሆን ዘንድ ተተርጉሞ መቅረብ አለበት። ለምሳሌ ጌታ ስለ ዘሪው በምሳሌ ካስተማረ በኋላ መልካምን ዘር የዘራው የራሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ መሆኑንና እርሻ የተባለው ደግሞ ዓለም እንደሆነ ተርጉሞ አስተምሯል (ማቴ. ፲፫፥፴፯)። ጌታም ለመምህራን አብነት ለመሆን

"ኢየሱስም ይህን ሁሉ አስተዋላችሁን" ብሏቸዋል። አብነት ለመሆን ነው እንጂ ሳይጠይቃቸው ያስተዋሉትንና ያላስተዋሉትንን መለየት ይችላልና። እነርሱም "አዎን አሉት" ተብሏል (ማቴ. ፲፫፥፶፩)። የመምህራን መምህር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፶

"ብዙዎችና ነቢያትና ጻድቃን የምታዩትን ሊያዩ ተመኝተው አላዩም፣ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ተመኝተው አልሰሙም" (ማቴ. ፲፫፣ ፲፯)። ቅዱሳን ነቢያት የክርስቶስን መምጣት በታላቅ ጉጉት ይጠብቁት ነበር። ከዲያብሎስ እስራት ነጻ የሚያወጣቸው፣ ከዘለዓለም ሞት የሚያድናቸው፣ ሞትን አሸንፎ ዘለዓለማዊ ሕይወትን የሚያጎናጽፋቸው፣ ፍጹም ነጻነትን የሚያድላቸው ክርስቶስን በፍቅር በደስታ ይጠብቁት ነበር። እነ ዳዊት ኦ እግዚኦ አድኅንሶ (አቤቱ አሁን አድን) እያሉ ተናገሩ። እነ ኢሳይያስ "በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን" ብለው ትንቢትን ተናገሩ። እነ ሙሴ "ስቅልተ ትሬእያ እስራኤል ለሕይወትከ" ብለው ተናገሩ። በጠቅላላው የስብከታቸው ዋና ማዕከል የክርስቶስ መምጣት ነበር። ነቢያት ይመጣል፣ ያድነናል፣ ይወለዳል እያሉ ነገረ ክርስቶስን በትንቢት ተናገሩ። ሐዋርያት ደግሞ መጣ፣ ተወለደ፣ አዳነን እያሉ ተናገሩ። ሊቃውንተ ኢትዮጵያ ይህንን በሀገራችን ብሂል "ነቢያት በገደገዱ ሐዋርያት መደመዱ" ብለው ይገልጹታል። ነቢያት ሊያዩ የተመኙትን ሐዋርያት አዩት። ነቢያት ሊሰሙ የተመኙትን ሐዋርያት ከእግሩ ስር ቁጭ ብለው ተማሩ። ነቢያት በተስፋ ጠበቁት። ሐዋርያት ጌታ ተወልዶ የነቢያት ተስፋ ተፈጽሞ አዩ። በሐዲስ ኪዳን ያለን እኛ ምእመናንም ክርስቶስን ንስሓ እየገባን ሥጋውን ደሙን እየተቀበልን ሁልጊዜም በልባችን ነግሦልን ይኖራል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፶፩

"የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል" (ማቴ. ፲፫፣ ፵፩)። ኢየሱስ ክርስቶስ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪና ባለቤት ነው። የመላእክት ፈጣሪም እርሱ ነው። ለዚያም ነው በዚህ ኃይለ ቃል ባለቤትነቱን በሚያሳውቅ ዝርዝር "መላእክቱን" ተብሎ የተገለጸው። በግእዙ "ይፌንዎሙ ወልደ እጓለ እመ ሕያው ለመላእክቲሁ" ብሎ ገልጾታል "ሁ" የምትለው ዝርዝር ባለቤትነቷ ወልደ እጓለ እመሕያው ለተባለ ለክርስቶስ ነው። በዚህ ኃይለ ቃል የምናገኘው ትልቅ ቁም ነገር የሥጋና የቃል ተዋሕዶ ፍጹም እንደሆነ ነው። ሥጋ ቃልን ገንዘቡ በማድረጉ በቃል ርስት የመላእክት ፈጣሪ መሆኑን ያሳውቀናል። በሌላ መልኩ ቃልም ሥጋን ገንዘቡ በማድረጉ በሥጋ መጠሪያ መጠራቱን እንረዳለን። መላእክት ማለት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ማለት ነው። ጌታ ክርስቶስ መላእክቱን ይልካል መባሉም እግዚአብሔርነቱን ያስረዳናል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፶፪

"ይህን ጥበብና ተአምራት ይህ ከወዴት አገኘው፣ ይህ የጸራቢ ልጅ አይደለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን? እኅቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን? እንኪያስ ይህን ሁሉ ከወዴት አገኘው? ተሰናከሉበትም" (ማቴ. ፲፫፥፶፬-፶፯)። የአይሁድ ትልቁ ችግራቸው ክርስቶስን አለማወቃቸው ነበር። ከእነርሱ ጋር 33 ዓመት አብሯቸው ሲኖር

አላወቁትም፡፡ እና ብዙ ጊዜ የሆነውን ማንነቱን ሳይሆን የመሰላቸውን በመናገር ብዙ ጊዜ ተሰናክለዋል፡፡ ያዕቆብ፣ ዮሳ፣ ስምዖን፣ ይሁዳ አብረውት በማደጋቸው ወንድሞቹ የተባሉ እንጂ ከአንድ አባት ወይም ከአንድ እናት በመወለዳቸው ወንድሞቹ እንዳልተባሉ አይሁድ አልተረዱም ነበር፡፡ ይህ ብቻ አይደለም ጌታ መድኃኔዓለም በዚህ ምድር ያለ አባት ከእናት፣ ያለወንድ ዘር መወለዱን ባለማወቃቸው የጸራቢው የዮሴፍ ልጅ እያሉ ይናገሩ ነበር፡፡ "ተሰናከሉበትም" ተብሎ የተገለጸው ይህ ነው፡፡ ሌላኛው "ተሰናከሉበትም" ተብሎ የተገለጸው "ይህን ሁሉ ጥበብና ተአምራት ከወዴት አገኘው" በሚለው ጥያቄያቸው ነው፡፡ ምክንያቱም እስካሁን አምላክነቱን አልተረዱም፡፡ አምላክ መሆኑን ቢያውቁ ኖሮማ በዚህ ባልተደነቁ ነበር፡፡ ለአምላክ የሚሳነው ነገር የለምና፡፡ አምላክን ጥበብህን ከምን አገኘኸው ብለን አንጠይቀውም፡፡ ምክንያቱም ጥበቡና ተአምራቱ የባሕርይው ስለሆነ ነው፡፡ የባሕርይው ነው ማለትም ለጥበቡ ሌላ ምንጭ የሌለው እርሱ ራሱ የጥበባትና የተአምራት ምንጭ ነው ማለታችን ነው፡፡ ስለዚህ የክርስቶስን አምላክነቱን ባለመረዳታቸው "ተሰናከሉበትም" ተብሎ ተገልጿል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፶፫

ጌታ ሕዝቡን በባህርዳር ሲያስተምር ውሎ ርቧቸው ነበር፡፡ ሁለት ዓሣንና አምስት እንጀራን ባርኮም ሰጣቸው፡፡ ሴቶችና ሕፃናት ሳይቆጠሩ ከ5000 በላይ ሰዎች በልተው ጠግበው ዐሥራ ሁለት መሶብ ተረፈ፡፡ "ዐሥራ ሁለት መሶብ ሁሉ አነሡ" እንዲል (ማቴ. ፲፬፣ ፳)፡፡ ሁለት ዓሣና አምስት እንጀራ አንድ መሶብ እንኳ አይሞሉም፡፡ ታድያ ዐሥራ ሁለት መሶብ ከምን ተገኘ? ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ዓለም ከምንም (እምኀበ አልቦ) ፈጥሮታል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደመሆኑ የሌለን ነገር እንዲኖር ማድረግ፣ ያለን ነገር ደግሞ የሌለ ማድረግ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ይህች ዓለም አልነበረችም፡፡ ከዚህች ዓለም በፊት ይኖር የነበረ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ በኋላ ግን እግዚአብሔር ይህን ዓለም ከምንም ፈጥሮታል፡፡ በኋለኛው ዘመን (በዳግም ምጽአት) ደግሞ ይህን ዓለም ወደአለመኖር ይመልሰዋል፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ ስለሆነ ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ አምስት ሺ ሕዝብ አጥግቦ 12 መሶብ እንዲተርፍ አድርጓል፡፡ ጌታ ይህንን ሲባርክ ወደሰማይ አይቷል፡፡ ይኸውም ኅብስትን የመባረክና የማበርከት ሥልጣኑ ከአብ ጋር አንድ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፶፬

ኢየሱስ ክርስቶስ "ሕዝቡንም አሰናብቶ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ፡፡ በመሸም ጊዜ ብቻውን በዚያ ነበረ" ተብሏል (ማቴ. ፲፬፣፳፫)፡፡ ተራራ ሌላውን አጥርቶ ለማየት ይጠቅማል፡፡ ጌታም በሁሉም ቦታ ያለና የሚኖር ሆኖ ሳለ በተዋሐደው ሥጋ ወደተራራ ወጣ ተብሏል፡፡ ቅድስት ቤተክርስቲያን በተራራ ትመሰላለች፡፡ ሰው ቤተክርስቲያን ሲሄድ ሌላውንም ራሱንም አጥርቶ ያያል፡፡ ጌታ ለገዳማውያን አብነት ለመሆን ወደገዳም ወደተራራ ይሄድ ነበር፡፡ ገዳማውያንም እርሱን አብነት አድርገው በየተራራው ለጾም ለጸሎት ተግተው ይኖራሉ፡፡ "ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ" እንዲል (ዕብ. ፲፩፣፴፰)፡፡ አንዳንድ የፕሮቴስታንት አማኞች ምንኩስናን ሲነቅፉ ይስተዋላል፡፡ ነገር ግን የምንኩስና ሕይወት ክርስቶስ በተግባር ያሳየው ሕይወት ነው፡፡ መነኮሳትም ከሰው ተለይተው

ብቻቸውን ወደ ተራራ የሚሄዱት ይጸልዩ ዘንድ ነው:: ጌታ በተራራ የጸለየ በመጸለዩ ለእርሱ የሚጨመርለት ነገር እንደሌለ የታወቀ ነው:: ነገር ግን ለእኛ አብነት ለመሆን ጸልዩዋል:: መነኮሳት ግን የሚጸልዩት ለራሳቸውም ለሌላው ሰውም ነው:: ጸልየው ራሳቸውንም ሌሎችንም ይጠቅማሉ::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፶፭

"ደቀመዛሙርቱም በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ ምትሀት ነው ብለው ታወኩ:: በፍርሀትም ጮሁ" (ማቴ. ፲፬፥፳፮):: ወዲያውም ኢየሱስ ተናገራቸውና አይዟችሁ አትፍሩ እኔ ነኝ አላቸው:: ለአብዛኛው ሰው ክርስቶስ "ምትሀት" ይመስለው ነበር:: "ምትሀት" ማለት ያልሆነ ግን መስሎ የሚታይ ማለት ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔር በእውነት ሰው አልሆነም ከዚያ ይልቅ ሰው መስሎ ታየ ብለው የሚናገሩ ከሓድያን አሉ:: ጌታ ሰው የሆነው ግን ዘእንበለ ምትሀት (ያለ ምትሀት) በእውነት ነው:: ምትሀትን የሚያሳይ ሰይጣን ነው:: ምክንያቱም ሰይጣን እውነተኛ ማንነቱ ከታወቀ የሚከተለው አይኖርም:: ስለዚህ ርኩስ ሆኖ ሳለ የብርሃን መልአክ መስሎ ይታያል:: እና ሐዋርያትም ጌታ በባሕር ላይ እየተራመደ ሲመጣ ባዩት ጊዜ መጀመሪያ ምትሀት መስሏቸው ደንግጠውና ፈርተው ነበር:: ጌታ ግን አይዟችሁ አትፍሩ እኔ ነኝ ብሎ አረጋግቷቸዋል:: በእርግጥም ጌታ ከእኛ ጋር ካለ ምንም አያስፈራንም:: ሰው የሚፈራው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ ሳያውቅ ሲቀር ነው:: ወይም ደግሞ የበደለው በደል ካለ ፈሪ ይሆናል:: ነገር ግን ይህ እንዳይሆን የበደልነውን በደል በንስሓ ማራቅ እና ከጌታ ጋር መኖርን መምረጥ ይገባናል::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፶፮

"በታንኳይቱም የነበሩት በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት" (ማቴ. ፲፬፥፴፫):: ኢየሱስ ክርስቶስ ማዕበል፣ ሞገድ፣ ፍጥረታት ሁሉ የሚታዘዙለት አምላክ መሆኑን ተረድተው በታንኳይቱ የነበሩት ሰዎች ሰገዱለት:: የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት ተብሏል:: የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ነውና:: ይህ ልጅነት ባሕርያዊ ልጅነት ነው:: የሰው ልጅ ሰው ነው:: የአንበሳ ልጅ አንበሳ ነው:: የነብር ልጅ ነብር ነው:: ይህ ልጅነት ባሕርያዊ ልጅነት ይባላል:: የእግዚአብሔር ልጅም እግዚአብሔር ነው:: በጥምቀት በጸጋ ከእግዚአብሔር ተወልደን እኛ ክርስቲያኖችም የእግዚአብሔር ልጆች እንባላለን:: ልጅነታችን ግን የጸጋ ልጅነት ነው እንጂ የባሕርይ ልጅነት አይደለም:: ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ የተባለው ግን እንደእኛ በጸጋ ሳይሆን በባሕርይ ልጅነቱ ምክንያት ነው:: ከፈጣሪ ውጭ የባሕርይ ስግደት የሚገባው የለም:: ለፍጡራን የጸጋ ስግደትን እንጂ የባሕርይ ስግደትን መስገድ አልተፈቀደም (ዘዳ. ፲፯፥፫)::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፶፯

ጌታ ክርስቶስ አይሁድን "ስለወጋችሁም የእግዚአብሔርን ቃል ሻራችሁ እናንተ ግብዞች" ብሏቸዋል (ማቴ. ፲፭፥፯):: ከዚህ ቀደም እንደተማማርነው ከጌታ የትምህርት አሰጣጥ መንገዶች አንዱ ተግሣጽ ነው:: ይኸውም ወንበዴውን ወንበዴ፣ ግብዙን ግብዝ፣ ዕውረ ልብ የሆነውን

ዕውር ብሎ መናገር ነው። የአይሁድ አለቆች፣ ጸሐፍት ፈሪሳውያን እግዚአብሔር ከሰጣቸው ሕግ ውጭ ራሳቸው "ወግ" ሠርተው ሰውን በወጋቸው ይኮንኑ ነበር። ሐዋርያት ከጌታ ጋር ሳሉ እጃቸውን ሳይታጠቡ ቢበሉ ጸሕፍት ፈሪሳውያን ይህንን እንደኃጢአት ቆጥረው ደቀመዛሙርትህ ሳይታጠቡ እየበሉ ነው ብለው ነገሩት። ጌታ ግን ይህ እጅን ታጥቦ መብላት አይሁድ የፈጠሩት ወግ እንጂ ከትእዛዛት አንዱ እንዳልሆነ ነግሯቸዋል። አይሁድ ግን ይባስ ብለው ለወጋቸው ሲሉ የእግዚአብሔርን ቃል እስከ መሻር ይደርሱ ነበር። ወግ፣ ባህል፣ እሴት የሚባሉ ነገሮች ጥንታዊ ቢሆኑ እንኳ ከእግዚአብሔር ሕግ የሚያስወጡ ከሆኑ ሊናቁ፣ ሊተዉ፣ ሊተቹ ይገባል። ጌታ ኢየሱስ ሁልጊዜም የእግዚአብሔርን ቃል ማስቀደም እንዳለብን አስተምሮናል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፶፰

"የሰማዩ አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል" (ማቴ. ፲፭፥፲፫)። ኢየሱስ ክርስቶስ አብን "የሰማዩ አባቴ" እያለ ይጠራዋል። አብ ለወልድ አባቱ ነውና። ይህ አባትነት ግን በዚህ ምድር እንደምናየው ያለ አባትነት አይደለም። እንደሚታወቀው በዚህ ምድር አባት ልጅ ሳይኖር የነበረበት ጊዜ ነበር። ወደዚህ ዓለም በመምጣት ሂደት አባት ይቀድማል። ልጅ ደግሞ ይከተላል። ኢየሱስ ክርስቶስ አብን አባቴ እያለ ሲጠራው ግን በዘመን መቀዳደም የለባቸውም። አብ ኖሮ ወልድ ያልነበረበት ዘመን የለም። የአብ አባትነት፣ የወልድ ልጅነት ዘለዓለማዊ ነው። ይህንንም ለማስረዳት አባቶቻችን ሊቃውንት በፀሐይ ክበብና በፀሐይ ብርሃን ይመስሉታል። የፀሐይ ክበብ ከፀሐይ ብርሃን ተለይቶ አያውቅም። ብርሃን ከክበቡ ይወለዳል። ብርሃን ከክበቡ ተወለደ ወይም ተገኘ ስንል ግን የብርሃን መገኘት ከክበቡ በኋላ ነው አያሰኝም። ምክንያቱም ብርሃኑ ከክበቡ ጋር ያለው እድሜ አንድ ነው። የፀሐይ ክበቡ በአብ፣ የፀሐይ ብርሃን በወልድ ይመሰላል። "አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል" ሲል እየተናገረ ያለው ስለተክሎችና ፍራፍሬዎች እንዳልሆነ ግልጽ ነው። በተክል ስለተመሰለው የሰው ልጅ እየተናገረ ነው እንጂ። በዚህም ሰው ያለረድኤተ እግዚአብሔር ምንም ማድረግ እንደማይችል እንረዳበታለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፶፱

ጌታ ኢየሱስ ሐዋርያትን "ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል?" ብሎ ጠይቋቸው ነበር (ማቴ. ፲፮፥፲፫)። እነርሱም መጥምቁ ዮሐንስ፣ ነቢዩ ኤልያስ፣ ነቢዩ ኤርምያስ፣ ከነቢያት አንዱ እያሉ ይጠሩሀል ብለው መለሱለት። ጌታ ጥያቄውን ቀጥሎ እናንተስ እኔን ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ አላቸው። ከሐዋርያት መካከል አንዱ ቅዱስ ጴጥሮስም "አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" ብሎ መለሰለት። ጌታም ጴጥሮስን በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህንን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ አለው። አብዛኛው ሰው ስለኢየሱስ የተናገረው የመሰለውን ነው እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ የሆነውን ማንነቱን አልነበረም። የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት በትክክል የገለጸው ቅዱስ ጴጥሮስ ነው። ጌታን ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) አድርጎ አስቦ ነቢይ ነው ማለት ስሕተት ነው። አምላክም ሰውም ስለሆነ ስለክርስቶስ ትክክለኛው መልስ "የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" የሚለው ንግግር ነው። ስለእግዚአብሔር ራሱ የገለጠልንን፣ ሐዋርያት የሰበኩትን፣ ሊቃውንት ያመሰጠሩትን መሠረት አድርገን እንናገራለን እንጂ

በመሰለኝና በልብ ወለድ አንናገርም። ከዚህ ኃይለ ቃል የሚደንቅ ንግግር አለ። ጌታ የጠየቃቸው "የሰውን ልጅ ማን ይሉታል" ብሎ ሰውነቱን በሚያሳውቅ አነጋገር ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ "የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" ብሎ አምላክነቱን የሚያሳውቅ መልስ መለሰ። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅም የእግዚአብሔር ልጅም እየተባለ ይጠራል። አምላክም ሰውም ነውና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳

"ያን ጊዜም እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ለማንም እንዳይነግሩ ደቀመዛሙርቱን አዘዛቸው" (ማቴ. ፲፮፥፳)። ጌታ ለሐዋርያት ሰዎችን ከኃጢአታቸው የሚያድናቸው ክርስቶስ መሆኑን ከነገራቸው በኋላ ይህንን ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው። ለምንድን ነው እንዳይናገሩ ያዘዛቸው? ስንል አንደኛ ለእኛ አብነት ለመሆን ነው። መልካም ሥራ ሠርተን መልካምነታችንን ሌላ ሰው እንዲያውቅልን እንዳንፈልግ እና ከንቱ ውዳሴ እንዳይሆንብን ዝም ማለት እንዲገባን ሊያስተምረን ነው። ሁለተኛው ደግሞ ክብሩን ከተናገረ በኋላ ስቅለት (ስለ ሰው ሲል ውርደትን መቀበል) የሚጠብቀው ነውና። በአንድ ጊዜ ክብሩን ከትንሣኤ በኋላ እንዲናገሩ ለጊዜው ማለትም እስከ ዕለተ ትንሣኤ ክብሩን እንዳይናገሩ አዘዛቸው ተብሏል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፩

"የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋራ በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል" (ማቴ. ፲፮፥፳፯)። ለኢየሱስ ክርስቶስ የአባቱ ክብር የእርሱ ክብር ነው። ምክንያቱም አብና ወልድ በክብር አንድ ናቸው። በክብር መበላለጥ የለባቸውም። "በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለው" ተብሎ የተገለጸው ለዚያ ነው። በዚህ ኃይለ ቃል ውስጥ የምናገኘው ሌላው ቁም ነገር "ለሁሉ እንደሥራው ያስረክበዋል" የሚለው ነው። በዚህ ኃይለ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደመሆኑ ለሁሉ እንደሥራው የሚከፍል ፈራጅ መሆኑን እንረዳለን። በተጨማሪም በዚህ ኃይለ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን "የሰው ልጅ" ብሎ ሰውነቱን፣ ከመላእክቱ ጋራ ብሎ በባለቤትነት በመጥራት አምላክነቱን እንረዳበታለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፪

"በፊታቸውም ተለወጠ። ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ። ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ" (ማቴ. ፲፯፥፪)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐዋርያት ሦስቱን ማለትም ጴጥሮስን፣ ዮሐንስንና ያዕቆብን ይዞ ወደ ደብረ ታቦር ወጣ። ከዚያ በፊታቸው ተለወጠ፣ ፊቱ እንደ ፀሐይ አበራ፣ ልብሱም ነጭ ሆነ። ክርስቶስ በባሕርይው ብርሃን ነው። የሰው ልጅ እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ ማየት አይችልም። እግዚአብሔር ከመታየት በላይ ነውና። እንኳንስ ከመታየት ከመታሰብም በላይ ነው። ስለዚህ ሐዋርያቱ የጌታ ክርስቶስን አምላክነት ተረድተው ለሌላውም እንዲያስተምሩ አምላክነቱን በተራራ ገለጠላቸው። በዚያውም ለሞቱትም በሕይወት ላሉትም አምላካቸው እርሱ መሆኑን ለመግለጽ ሙሴንና ኤልያስን ተነሥተው እንዲነጋገሩት አደረገ። ለሐዋርያቱ ከአምላክነት ብርሃኑ ጥቂት ቢያሳያቸው በፊታቸው ወድቀዋል። ደንግጠውም ነበር። ብሩህ ደመና ጋረዳቸውና ከደመናው ላይ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው

እርሱን ስሙት" የሚል ቃልን ሰምተዋል:: ይህንን ቃል የተናገረው አብ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ እንደሆነ ሐዋርያቱ እንዲረዱት የተነገረ ቃል ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፷፫

በክርስቶስ ላይ የደረሰው መከራ ድንገታዊ አይደለም:: እኛን ለማዳን አስቀድሞ በነቢያት ያስነገረውን ፈጸመው እንጂ:: መከራ እንደሚቀበልም አስቀድሞ ያውቅ ስለነበር ለሐዋርያቱ "የሰው ልጅ ከእነርሱ መከራ ይቀበል ዘንድ አለው" ብሎ ነግሯቸዋል (ማቴ. ፲፯፥፲፪):: መከራ መቀበል የሚችል ሥጋን ስለተዋሐደ መከራን ተቀብሏል:: እርሱ ስለእኛ ቤዛ ሆኖ መከራን ተቀብሏል:: በመከራው መከራችንን አርቆልናል:: በሞቱ ሞትን አጠፋልን:: ክርስቶስ እንደሚሞት ብቻ ሳይሆን በሦስተኛው ቀን ከሙታን መካከል ተለይቶ እንደሚነሣ ለሐዋርያቱ "የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጥ ዘንድ አለው ይገድሉትማል:: በሦስተኛው ቀን ይነሣል" ብሎ ነግሯቸዋል (ማቴ. ፲፯፥፳፪-፳፫):: ሞት ቀድሞ አስፈሪ ነበር:: አሁን ግን ጌታ ክርስቶስ በሞቱ ሞትን ስለገደለልን:: ሞትን መውጊያህ ወዴት አለ እያልን እንደ ቅዱስ ጳውሎስ የምንሳለቅበት ሆኗል:: ጌታ ዓርብ በዘጠኝ ሰዓት ቅድስት ነፍሱን ከሥጋው ከለየ በኋላ እስከሦስተኛው ቀን ማለትም እስከ እሑድ በመቃብር ቆይቶ ተነሥቷል::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፷፬

የወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን ዋናና መሠረታዊ ምክንያት ሰውን ለማዳን ነው:: "የሰው ልጅ የጠፋውን ለማዳን መጥቷልና" እንዲል (ማቴ. ፲፰፥፲፩):: መዳንን መታመም ይቀድመዋል:: የሰው ልጅ በራሱ ፍትወት (ምኞት) ተታሎ ከነበረበት ልዕልና ወርዶ፣ ለኃጢአት ተገዢ ሆኖ፣ በእግረ አጋንንት እየተጠቀጠቀ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ ይኖር ነበር:: የዚህ ሁሉ ምክንያቱ ደግሞ እግዚአብሔር ያዘዘውን ትእዛዝ አለመጠበቁ ነበር:: "ዕፀ በለስን" እንዳይበላ ታዝዞ ነበር:: ነገር ግን በሰይጣን ተንኮልና በራሱ ፍትወት ተታሎ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው ሰው ወደቀ:: ክቡር ሆኖ ሳለ እንደ እንስሳ የሚኖር ሆነ:: በዚህ ሕመምና መከራ ክርስቶስ ተሰቅሎ እስኪያድነው ቆየ:: ጌታ ክርስቶስ በራሱ በደል የጠፋውን የሰው ልጅ ጠፍቶ እንዲቀር አላደረገውም:: ከዚያ ይልቅ የሰውን ማንነት ተዋሕዶ ሰውን ከነበረበት አዘቅት ሊያድነው መጣ:: ትእዛዛትን መጠበቅ አቅቶት የወደቀውን ሰው እንዴት ትእዛዛትን መጠበቅ እንዳለበት አርዓያ ሆኖ ሊያሳየው የጽድቅ መንገድን አሳየው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፷፭

"ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እገኛለሁ" (ማቴ. ፲፰፥፳):: የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ከሚገልጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ቃሎች አንዱ ይህ ነው:: "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እገኛለሁ" የሚለው ቃል:: ክርስቶስ አምላክ እንደመሆኑ የሌለበት ቦታ የለም:: በሁሉ ቦታ ያለ፣ ሁሉን የሚወስን እርሱን ግን ምንም ምን የሚወስነው የሌለ አምላክ ነው:: ታዲያ በሚሰበሰቡበት በዚያ እገኛለሁ የሚለው ቀድሞ ሳይገኝ ቀርቶ በኋላ ከዚያ ቦታ የሚገኝ ነው ማለት አይደለም:: ረድኤትን እሰጣችኋለሁ ሲል ነው እንጂ:: ይኸውም መልካም መዓዛ ያለው ሽቱ በቤት ውስጥ ቢርከፈከፍ

ጤነኞች ሲያሽቱት ጉንፋን ያመማቸው በሽተኞች ግን ሽታው ሳይደርሳቸው ይቀራል፡፡ ችግሩ የእነርሱ መታመም እንጂ የሽቱው አለመኖር አይደለም፡፡ ክርስቶስ በዓለም የመላ ቢሆንም በተለየ በእርሱ ስም ስንሰበሰብ የሚሰጠን ጸጋ አለ፡፡ በክርስቶስ ስም ስንሰባሰብ ክርስቶስ የሚሰጠን ረድኤተ ሥጋ ረድኤተ ነፍስ፣ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ፣ ፈውሰ ሥጋ ፈውሰ ነፍስ አለ ማለት ነው፡፡ ክርስቶስ በተዋሐደው ሥጋ ሦስት ክንድ ከስንዝር ቢባልም በቃልነቱ ግን በሁሉ ያለ፣ ወሰን የሌለበት ሁሉን ቻይ ፈጣሪ አምላክ ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፮

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለጋብቻ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለይ ብሎ አስተምሯል፡፡ አይሁድ ግን ጌታ ክርስቶስን የተቃወምን መስሏቸው ሙሴ እንድንፋታ ያስተማረበት ክፍል አለ ብለዋል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስም "ሙሴስ ስለልባችኹ ጥንካሬ ሚስቶቻችኹን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችኹ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም" አላቸው (ማቴ. ፲፱፥፰)፡፡ ለሙሴ ሕግን የሰጠው ራሱ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ የሙሴ ፈጣሪ እርሱ ነው፡፡ ስለዚህ ለሙሴ የሰጠውን ትእዛዝ ብቻ ሳይሆን ትእዛዙ የተነገረበትን ዋና ምክንያት ከሙሴ ይልቅ የሚያውቀው እርሱ ጌታ ክርስቶስ ነው፡፡ ስለዚህ ሙሴ ሚስቶቻቸውን እንዲፈቱ የፈቀደላቸው ስለልባቸው ክፋት እንደነበረ ነገራቸው፡፡ በትርጓሜ እንደተቀመጠው በኦሪት ባል ሚስቱ ካልሞተችበት በስተቀር ሌላ ማግባት አይገባውም ነበር፡፡ ሚስትም እንደዚያው ነገር ግን አንዳንዶች የሚጠሏትን ሚስት በትራስ አፍነው እየገደሉ ሌላ ያገቡ ነበር፡፡ ሴቶች ደግሞ በምግብ መርዝ እያደረጉ ባሎቻቸውን ይገድሉ ነበር፡፡ ይህ እንዳይሆን ሙሴ የሚፋቱበትን ምክንያት ተነጋግረው እንዲፋቱ ሥርዓት ሠርቷል፡፡ ጌታ ኢየሱስ የትእዛዛት ባለቤት ስለሆነ ትእዛዛቱ የተሰጡበትን ምክንያት ጠንቅቆ የሚያውቅ እርሱ ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፯

ጌታ ኢየሱስ "ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ" ብሎ አስተምሮናል (ማቴ. ፲፱፥፲፯)፡፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ ወደ ሕይወት አያስገባም፡፡ ማመን ብቻ ሳይሆን ትእዛዛትን መጠበቅም ይገባል፡፡ ትእዛዛት የሚባሉትም

፩) ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ

፪) የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ

፫) ሰንበትን አክብር

፬) እናትና አባትህን አክብር

፭) አትስረቅ

፮) አታመንዝር

፯) አትግደል

፰) የባልንጀራህን ንብረት አትመኝ

፱) በሐሰት አትመስክር

፲) ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ

ናቸው:: ስድስቱ ቃላተ ወንጌል የሚባሉትንም መጠበቅ ትእዛዛትን መጠበቅ ይመስላል:: ትእዛዛት እኛን ወደ መልካም ሕይወት የሚመሩን መሪ ሕጎች ናቸው:: እግዚአብሔር ትእዛዛትን የሚሰጠን እኛን ለመጨቆን ሳይሆን ፍጹም ነጻነትን ለማጎናጸፍ ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፰

"የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም" (ማቴ. ፳፥፳፰):: ጌታ ከሠራቸው ሥራዎች አንዱ #የቤዛነት #ሥራ ነው:: "ቤዛ" የሚለው ቃል በግእዝ ቋንቋ በአገባብ "ስለ" ተብሎ ይተረጎማል:: ቤዘወ አዳነ ከሚለው ግሥ ወጥቶ ጥሬ ዘር ሲሆን ደግሞ መድኃኒት፣ ማዳን፣ መዳኛ እና የመሳሰሉትን ከመዳን ጋር በተያያዙ የአማርኛ ስሞች ይተረጎማል:: "ቤዛ ኵሉ ዓለም ዮም ተወልደ" ሲል የዓለም መድኃኒት ዛሬ ተወለደ ማለት ነው:: ቤዛ "ስለ" ተብሎ ሲተረጎም ምሥጢሩ ምትክነት ነው:: አምላክ ሰው የሆነው ስለሰው ልጅ ብሎ ነው:: ይኸውም በሰው ልጆች ሁሉ ምትክ የሰውን ልጅ መከራ እርሱ ተቀብሎ ሰውን ሊያድን እንደመጣ የሚያሳውቀን ቃል ነው:: በጌታ ላይ የደረሰው የመስቀል መከራ ሁሉ ለእኛ ይገባ የነበረ ሲሆን፣ ነገር ግን ስለእኛ በእኛ ፈንታ በፈቃዱ ለእርሱ አደረገው:: በመከራውም መከራችንን አራቀልን:: ስለዚህ በእርሱ የደረሰው መከራ ለእኛ የክብር ምንጭ ስለሆነ እንደሊቁ "ይትባረክ እግዚአብሔር ዘሰመየ ሕማማተ ወልዱ ክብረ ወስብሐተ" ብለን እንናገራለን::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፱

"በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም አላቸው" (ማቴ. ፳፥፳፫):: ጌታ ኢየሱስ በግራ በቀኝ መቀመጥ፣ ቀኝ አዝማች ግራ አዝማች መሆን ሰማያዊ አባቴ ላዘጋጀላቸው ለነገሥታት ለመኳንንት ነው እንጂ ቀኝ አዝማችነትን ግራ አዝማችነትን እኔ የምሰጥ አይደለሁም ብሏል:: ምን ማለት ነው:: በሌላ ቦታ ላይ መኮንን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ እንደማይሾም ተገልጿል (ሮሜ ፲፫፥፩):: ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ እግዚአብሔር ነው (ዮሐ. ፩፥፩-፫):: ታዲያ በዚህ ጊዜ ለምን እኔ አልሰጥም አለ? ሲል ወደዚህ ምድር የመጣው ሥጋዊ ሹመትን ሽልማትን ሊሰጥ ሳይሆን ሰማያዊ ሹመትንና ሽልማትን ሊሰጥ ስለሆነ ሰው ከሆነበት ዓላማ ውጭ ጥያቄ ቢጠይቁት "እኔ የምሰጥ አይደለሁም" ብሏቸዋል:: ይኸውም ከመጣበት ዓላማ ውጭ ስለጠየቁት አልሰጣችሁም ማለቱ እንጂ እንደ አምላክነቱ ከአብ ጋር የሚሰጥ እርሱ መሆኑን መዘንጋት አይገባም:: በሌላ ቦታ "እኔና አብ አንድ ነን" ብሏልና:: አብ ያለው ሁሉ የወልድ ነው:: አብ የሚሰጠውን ሁሉ ወልድም ይሰጠዋል:: ለፍጡራን በሚያደርጉት ድርጊት ሦስቱ አካላት ማለትም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸውና::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፸

ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሠ ነገሥት ነው:: ምድራዊውንም ሰማያዊውንም ዓለም፣ በጠቅላላው ፍጥረታትን ሁሉ የሚገዛ ንጉሣችን ነው:: የሰላም ንጉሥ መሆኑን ለማሳወቅ በአህያ ተጭኖ መጥቷል:: በእስራኤል ባህል ነቢያት ዘመኑ ዘመነ ሰላም ነው ሲሉ በአህያ ተጭነው ይመጡ ነበር:: ጌታም በሆሣዕና "አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፥እጅግ ደስ ይበልሽ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፥እልል በዪ እንሆ፥ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው ትሑትም ሆኖ በአህያም፥ በአህያዪቱ ግልገል በውርንጫዪቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል" የሚለውን ትንቢት ፈጸመ (ትን. ዘካ. ፱፣፱፣ ማቴ. ፳፩፣፬):: ስለ ንጉሣችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢዩ ዘካርያስ ሲናገር ጻድቅና አዳኝ ትሑትም ነው ብሎታል:: በዚህ ምድር ያሉ ነገሥታት የጸጋ ገዢዎች ቢሆኑም ጌታ ክርስቶስን መምሰል ይገባቸዋል:: እርሱ ጻድቅ ነው ማለት መቼም መች ዋሽቶ አያውቅም ማለት ነው:: በባሕርይው ጻድቅ ነውና:: ጻድቅ ብቻ ሳይሆን ሕዝቡን የሚያድን ነው:: ጻድቅም ሆኖ፣ ሕዝቡንም አድኖ ግን ትሑትም ነው:: በሠራው ሥራ አይታበይም:: "ትዕቢትሰ ፀሩ ለክርስቶስ" እንዲል::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፸፩

"ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው" (ማቴ. ፳፩፣፱):: ሆሳዕና ማለት መድኃኒት ማለት ነው:: ለዳዊት ልጅ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡን ማዳን ይገባዋል:: ሕፃናቱ የሰላሙ ንጉሥ እርሱ ክርስቶስ ሲመጣ ቢያዩት ሆሳዕና እያሉ አመሰገኑት:: እንደሚያመሰግኑት ቀድሞም በትንቢት መልኩ ተነግሮ ነበር:: "ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ" እንዲል (መዝ. ፰፣፪):: ኢየሱስ ክርስቶስ በጌታ ስም የመጣ ነው:: ምክንያቱም ጌታ ነው:: ጌታ ማለት ምሥጢሩ ባለቤትነትን፣ ግዛትን፣ መንግሥትነትን አጠቃሎ የያዘ ቃል ነው:: እርሱ ክርስቶስ ደግሞ በባለቤትነት ከተረጎምነው የፍጥረታት ሁሉ ባለቤት እርሱ ነው:: በመንግሥትነት ከተረጎምነው ደግሞ የሁሉ ገዢና አስተዳዳሪ እርሱ ነው:: የተባረከ ነው መባሉ በባሕርይው ቡሩክ ስለሆነ ነው:: ጻድቃንን የተባረኩ ስንላቸው መባረካቸው የጸጋ ነው:: እርሱን የተባረከ ስንለው ግን ቡሩክነቱ የባሕርይ ነው:: ስለዚህ ለይተን እንናገራለን:: ጌታ ጻድቃንን "እናንተ የአባቴ ቡሩካን" ሲላቸው ቡሩካን ማለቱ የጸጋ ቡሩካን ማለቱ ነው:: እርሱ የተባረከ ሲባል ግን ቡሩክነቱን ከሌላ ያላገኘውና ማንም የማይወስድበት የራሱ ገንዘብ መሆኑን የሚያስረዳን ቃል ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፸፪

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢይ እየተባለም ይጠራል "ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ" እንዲል (ማቴ. ፳፩፣፲፩):: ደራሲም

ሰላም ለክሳድከ ግብረ መንፈስ ቅዱስ ኬንያ

አዳም ሥና ወመንክር ላሕያ::

ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢይ ወሐዋርያ::

አመ ወፅአ ስሙዓቲከ በአድያመ ኵሉ ሶርያ።

ብፁዓት አዕይንት ኪያከ ዘርእያ።

ብሎ ገልጾታል። ነቢይ ማለት አስተማሪ ማለት ነው። የወደፊቱን የሚናገር ማለት ነው። ቅዱሳን ነቢያት የወደፊቱን አውቀው የተናገሩት ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ጸጋ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የወደፊቱን አውቆ ሲናገር ግን ባባሕርይው ያለፈውንም ያለውንም የሚመጣውንም ስለሚያውቅ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክም ሰውም እንደ መሆኑ ነቢይ፣ ሐዋርያ፣ ሊቀ ካህናት፣ ወልደ እግዚአብሔር፣ ወልደ እጓለ እመሕያው ወዘተ እየተባለ ቢጠራ ይስማማዋል። ነገር ግን ክርስቶስን ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) አድርጎ አስቦ እንደ ሌሎች ነቢያት አድርጎ ማሰብ ትልቅ ክሕደት ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) አይደለም። አምላክም ሰውም የሆነ አንድ ነው እንጂ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፸፫

"በመንገድም አጠገብ በለስ አይቶ ወደ ርሷ መጣ ከቅጠልም ብቻ በቀር ምንም አላገኘባትምና፦ ለዘለዓለሙ ፍሬ አይገኝብሽ አላት። በለሲቱም ያን ጊዜውን ደረቀች" (ማቴ. ፳፩፥፲፱)። ይህ ቃል በጣም የሚደንቅ ቃል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው። አምላክ ከሆነ ደግሞ ወደ በለሲቱ ሳይሄድ እንኳ አስቀድሞ ከቅጠል ብቻ በቀር ፍሬ እንደማይገኝባት ያውቃል። ታዲያ ወደ እርሷ ለምን ሄደ? ለምንስ ረገማት?። መሄዱ ቅድመ ተዋሕዶ አላዋቂ የነበረ ሥጋን እንደተዋሐደ ለማስረዳት ነው። ነገሩ ግን ምሳሌያዊ ነው። በበለስ የተመሰለች ኃጢአት ናት። ወደ በለስ ሄደ መባሉ ጌታ ሰውን ለማዳን መከራን ሲቀበል ኃጢአተኛ ሳይሆን ኃጥእ ተባለ ማለት ነው። ሄዶ ፍሬ ቢያጣባት ረገማት ማለት ከኃጢአት ምንም ዓይነት የጽድቅ ፍሬ እንደማይገኝ አውቆ ኃጢአትን በአንቺ ምክንያት በፍዳ የሚያዝ አይኑር ብሎ ረገማት ማለት ነው። በለስቱ ፈጥና ደረቀች ተብላለች። ኃጢአት በፍዳ የምትይዝበት ዘመን ፈጥኖ ጠፋ ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ይህን የመሰለ ብዙ ምሳሌያዊ ትምህርት አለ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፸፬

"ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፏል። እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት" (ማቴ. ፳፩፥፲፫)። እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በሁሉ ቦታ ያለ አምላክ ቢሆንም በረድኤት የሚገለጥበት ልዩ ቤት ግን አለ። ይኸውም ቀድሞ በደብተራ ኦሪት ቀጥሎ በታላቁ ቤተ መቅደስ ነበር። ስለዚህ ሰሎሞን ለመጀመሪያ ጊዜ ያሠራው ቤተ መቅደስ "የእግዚአብሔር ቤት" ተብሏል (፩ኛ ነገ. ፰፥፵፯)። ይህ ቤት የተሠራው ሰዎች እንዲጸልዩበትና እግዚአብሔር ደግሞ ጸሎታቸውን ሰምቶ ረድኤትን፣ በረከትን የሚሰጥበት ቦታ ነው። አስተውሉ እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ረድኤትን መስጠት ይችላል። በሁሉም ቦታ ብንጸልይም ይሰማናል። በቤተ መቅደስ የተወሰነ አይደለም። ነገር ግን በተለየ በቤተ መቅደስ ብንጸልይ ደግሞ የተለየ ጸጋን እንደሚሰጠን ራሱ ተናግሯል። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ስለሆነ መቅደስን "ቤቴ" ብሎ ገልጿታል። በዚህች ቤት ወንበዴዎች በዝተው የንግድ ቦታ አድርገዋት ትኖር ነበር። በየዘመናቱ የእግዚአብሔር ቤት ትፈተናለች። በዘመናችንም ሙሰኞች ብዙ ብር ከፍለው የሚቀጠሩባት፣

ሌቦች አስተዳዳሪ ሆነው የሚዘርፉባት፣ ዘረኞች ገብተው ፖለቲካ የሚፈተፍቱባት የወንበዴዎች ዋሻ እየሆነች ነው። ጌታ ኢየሱስ ጅራፉን አንሥቶ ወንበዴዎችን እንዲያስወጣልን መልካም ፈቃዱ ይሁንልን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፸፩

የአይሁድ ትልቁ ችግር የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት አለማወቅ ብቻ ሳይሆን ለማወቅ አለመፈለግም ጭምር ነበር። "ወደ መቅደስም ገብቶ ሲያስተምር የካህናት አለቃዎችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ቀረቡና፦በምን ሥልጣን እነዚህን ታደርጋለኽ ይህንስ ሥልጣን ማን ሰጠኽ አሉት" ተብሏል (ማቴ. ፳፩፣፳፫)። ታላላቅ ተአምራትን ሲያደርግ አይተውታል። ስለዚህ ሥልጣን እንዳለው መደበቅ አልቻሉም። ሥልጣኑ ግን የባሕርይው መሆኑን ለማመን ተቸግረዋል። ስለዚህ ብዙ ጊዜ "ይህን ሥልጣን ማን ሰጠህ?" እያሉ ጠይቀውታል። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው ስንል አምላክነቱን ከማንም ያልተቀበለው፣ ማንም ያልሰጠው የራሱ የባሕርይው ነው ማለታችን ነው። የጠየቁት ስለሰውነቱ አስበው ከሆነ ደግሞ የሰው ልጅ የአምላክነትን ክብር ያገኘው ከቃል ጋር በተዋሐደ ጊዜ ነው። "ቃል ሥጋ ኮነ" በተባለበት ቅጽበት ቃል የሥጋ የሆነውን ገንዘብ ሁሉ ገንዘቡ ሲያደርግ ሥጋ ደግሞ የቃል የሆነውን ሁሉ ገንዘቡ አድርጓል። ከተዋሕዶ በኋላ ይህ የሰውነት ይህ የቃል እያልን የምንከፍለው ሥራ የለም። በአካልም በባሕርይ መዋሐድ የግብር ተዋሕዶን ያመጣልና። ኢየሱስ ክርስቶስ አብርሃም ሳይወለድ ነበርኩ፣ ዓለም ሳይፈጠር በነበረኝ ክብር አክብረኝ እያለ ተናግሯል። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ አብርሃም ሳይወለድ የነበረውና፣ ዓለም ሳይፈጠር በፊት የነበረው ክብርና ሥልጣን ነው አሁንም ያለው። ሥጋም ያን ሥልጣን ነው ገንዘቡ ያደረገው። አይሁድ ይህን ሥልጣን ከምን አገኘኸው ያሉት ይህንን ባለመረዳታቸው ነበር።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፸፪

አይሁድ የኢየሱስን አምላክነት ለመረዳት በመቸገራቸው ጠይቋቸዋል። "ፈሪሳውያንም ተሰብስበው ሳሉ፥ኢየሱስ፦ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል የማንስ ልጅ ነው ብሎ ጠየቃቸው፦ የዳዊት ልጅ ነው አሉት። ርሱም፦እንኪያስ ዳዊት፦ጌታ ጌታዬን፦ጠላቶችኽን የእግርኽ መረገጫ እስካደርግልኽ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው። ሲል እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል። ዳዊትስ ጌታ ብሎ ከጠራው፥እንዴት ልጁ ይሆናል አላቸው። አንድም ቃል ስንኳ ይመልስለት ዘንድ የተቻለው የለም፥ከዚያ ቀንም ጀምሮ ወደ ፊት ማንም ሊጠይቀው አልደፈረም" ተብሏል (ማቴ. ፳፪፣፵፩-፵፮)። ስለክርስቶስ በትንቢት ንጉሠ እስራኤል ዳዊት በመዝሙሩ ተናግሯል። አይሁድም የዳዊት ልጅ እንደሚሆን የነቢያትንና የሙሴን መጻሕፍት አንብበው ያውቁታል። እና ሰውነቱን ብቻ ተረድተው የዳዊት ልጅ ነው ብለው መልሰውለት ነበር። ጌታ ክርስቶስ ግን የዳዊት ልጅ ከሆነ ዳዊት ለምን በመንፈስ ጌታዬ አለው ሲላቸው አምላክነቱን የዳዊትን ቃል ጠቅሶ ቢነግራቸው ላለማመን ሳይመልሱለት ቀርተው ዝም ብለዋል። ይህ ቃል ግን የክርስቶስን አምላክነት የሚናገር ነው። ትንቢቱ "ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ" ይላል። ጌታዬ አብ ጌታዬ ወልድን በቀኜ ተቀመጥ አለው ማለት ነው። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመንግሥትነት አንድ ናቸው። ሁሉም ደግሞ በሁሉ ቦታ ያሉ ናቸው። አብ በወልድ አለ፣

ወልድም በአብ አለ። አብ በወልድ፣ ወልድ በአብ ካለ በቀኝ ተቀመጥ ያለው ትርጉሙ ምንድን ነው? ስንል ቀኝ የተባለ "ሥልጣን፣ ክብር፣ አምላክነት" ነው። ታዲያ በሥልጣን፣ በክብር፣ በአምላክነትስ አንድ አይደሉምን ከተባለ አንድ ናቸው። ታድያ "ንበር በየማንየ (በቀኜ ተቀመጥ)" ማለት ምን ማለት ነው? ከተባለ ሥጋ አምላክነትን ገንዘብ ማድረጉን የሚገልጽ ነው። ስለ ሥጋ እንግድነት የተነገረ ነው። አስቀድሞ አምላክ ያልነበረ ሥጋ ቃልን በመዋሐዱ አምላክ መሆኑን በንበር ገልጾታል። አስቀድሞ ንቡር ያልነበረ ሥጋ በተዋሕዶ ንቡረ አብ በየማን ሆኗልና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴፯

ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ መምህር ነው። ስለመምህራን ሊቃውንት በትርጓሜያቸው ሦስት ዓይነት አድርገው ይገልጿቸዋል። አንደኛው ሃይማኖቱ የቀና ምግባር የሌለው መምህር ነው። ሁለተኛው ምግባር ያለው ሃይማኖት የሌለው መምህር ነው። ሦስተኛው ሃይማኖትም ምግባርም ያለው መምህር ነው። ስለዚህ ምእመናን ካገኙ ሃይማኖቱም ኦርቶዶክሳዊ የሆነ፣ ሥነ ምግባሩም የተደነቀ ከሆነ መምህር ሊማሩ ይገባል። ይህ ዓይነት መምህር ክርስቶስን ይመስለዋል። በአንደበቱ ሐሰት ያልተገኘበት የደጋግ መምህራን ሁሉ መምህራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሁለተኛ ምእመናን ሃይማኖቱ ኦርቶዶክሳዊ፣ ሥነ ምግባሩ የተደነቀ መምህር ባያገኙ ሃይማኖቱ ከቀና ኃጥእ መምህር ቢማሩ እንደሚሻል ጌታ ተናግሯል። ጌታ ኢየሱስ "ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል። ስለዚህ፥ ያዘዟችኹን ሁሉ አድርጉ፥ ጠብቁትም ነገር ግን፥ እየተናገሩ አያደርጉትምና፥ እንደ ሥራቸው አታድርጉ" ብሎ እንደተናገረው (ማቴ. ፳፫፣፪-፫)። የክፉ መምህርን ክፉ ሥራውን አለመማርና እንደሥራው አለማድረግ ይገባል። አድርጉ ብሎ ያስተማረንን መልካም ሥራ ግን ማድረግ ይገባናል። ክርስቶስ ደግ መምህር ስለሆነ በተቻለን አቅም በቃሉ ያስተማረንንም፣ በሥራ ያሳየንንም በተግባር ለማዋል እንጥራለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴፰

ጌታ ሲያስተምር "እናንተ ግን፦ መምህር ተብላችኹ አትጠሩ መምህራችኹ አንድ ስለ ሆነ እናንተም ኹላችኹ ወንድማማች ናችኹ። አባታችኹ አንዱ ርሱም የሰማዩ ነውና፥ በምድር ላይ ማንንም፦ አባት ብላችኹ አትጥሩ። ሊቃችኹ አንድ ርሱም ክርስቶስ ነውና፦ ሊቃውንት ተብላችኹ አትጠሩ" ብሏል (ማቴ. ፳፫፣፰-፲)። የዚህ ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው? እንደምታውቁት በዘመናችን መምህር የሚባሉ ብዙ ናቸው። የአቋቋም መምህር፣ የቅኔ መምህር፣ የድጓ መምህር፣ የመጻሕፍት ትርጓሜ መምህር፣ የቅዳሴ መምህር፣ የዝማሬ መዋስእት መምህር፣ የፊዚክስ መምህር፣ የኬሚስትሪ መምህር___ ወዘተ እየተባለ የሚጠራ ብዙ ዓይነት መምህር አለ። አባት የሚባሉም ብዙ ናቸው። ወላጅ አባት አለ፣ የክርስትና አባት አለ፣ የነፍስ አባት አለ። ሊቃውንት የሚባሉም ብዙ ናቸው። በተማሩት ሙያ ብቁ ሆነው የተገኙ ሰዎች ሊቃውንት ይባላሉ። ጌታ ግን መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፣ አባት ተብላችሁ አትጠሩ፣ ሊቃውንት ተብላችሁ አትጠሩ ብሏል። ታዲያ የዚህ ትርጉሙ ምንድን ነው??? ሌላ ሳያስተምረው ዕውቀት የባሕርይው ሆኖ የሚያስተምር እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለዚህ በባሕርይው መምህር የሆነ እርሱ ብቻ ነው። ክርስቶስን መምህራችን እያልን ስንጠራው

በባሕርይው መምህር እርሱ ስለሆነ ነው፡፡ ሰዎችን መምህር የምንላቸው ግን በተሰጣቸው ጸጋ ስለሚያስተምሩን ነው፡፡ መምህር ባዕድ ቅጽል ነው ያስተማረ፣ የተማረ፣ የሚያስተምር፣ የሚማር እየተባለ ሊተረጎም ይችላል፡፡ የሰዎች መምህርነት ግን የጸጋ ነው፡፡ ሰዎችን መምህር ስንል መነሻችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ገማልያን መምህር ይለዋል (የሐዋ. ሥራ ፳፣፴፬)፡፡ ሊቃውንት የሚለውም በዚህ አግባብ የሚታይ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ቀጥሎ አባት ተብላችሁ አትጠሩ ብሏል፡፡ የፈጠረን አባታችን እግዚአብሔር ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ውጭ ፈጥሮ የሚንከባከበን አባት ብለን የምንጠራው የለም፡፡ ፈጥረውናል ብለን ሳይሆን ወልደውናል፣ አሳድገውናል፣ አስተምረውናል ብለን አባታችን የምንላቸው ግን አሉ፡፡ ለዚህም መነሻችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ አባታችን አብርሃም እንዲል (ያዕ. ፪፣፳፩)፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፱

"ስለስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ" (ማቴ.፳፬፣፲-፴፭)፡፡ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተባለ እኛ ክርስቲያን እንባላለን፡፡ እርሱ መሲሕ እንደተባለ እኛ መሲሓውያን እንባላለን፡፡ እርሱ ናዝራዊ እንደተባለ እኛ ናዝራውያን እንባላለን፡፡ በእርሱ ስም ተጠምቀን የእርሱ ልጆች ሆነናል፡፡ ነገር ግን እርሱ ጌታ ምንም በደል ሳይበድል በክፉዎች መከራን ተቀብሏል፡፡ ተሳልቀውበታል፣ ገርፈውታል፣ ሰቅለውታል፡፡ ይህ ሁሉ መከራ የደረሰበት ሊያድናቸው በመጡ ሰዎች ነው፡፡ ክርስቶስ ንጹሕ ሆኖ ሳለ የተለያዩ መከራዎችን ከሰዎች ተቀብሏል፡፡ ቅድስት ቤተክርስቲያን፣ ምእመናን በክርስቶስ ስም ተጠርተው፣ ንጹሓን ሆነው ቢኖሩ እንኳ በአሕዛብ ዘንድ (በሌላ እምነት ሰዎች) እየተጠሉ ይኖራሉ፡፡ ያለስማቸው ስም እየተሰጣቸው በውሸት ይከሰሳሉ፡፡ በየቦታው ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ ይገደላሉ፡፡ ይህ ሁሉ መከራ ግን ክብርን የሚያሰጥ መከራ በመሆኑ እሳት ወርቅን እንደሚያጠራው መከራም የቤተክርስቲያንን ቅድስናዋን የበለጠ እየገለጠ ይኖራል፡፡ ሰይፍን ለሚመረኮዝ ለእርሱ ወዮለት እንደተባለ ምእመናንን ለሚያሰቃይ ሰው ግን በምድርም በሰማይም ታላቅ መከራ ይገጥመዋል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፴

ኢየሱስ ክርስቶስ በጻድቃንና በኃጥኣን ላይ የሚፈርድ ፈራጅ አምላክ ነው፡፡ "በጎችን በቀኙ ፍየሎችን በግራ ያቆማቸዋል" እንዲል (ማቴ. ፳፭፣፴፫)፡፡ ሁሉን አውቆ፣ ልብና ኩላሊቱን መምርምሮ፣ ለሁሉ እንደየሥራው የሚከፍል በኃጥኣን የሚፈርድባቸው፣ ለጻድቃን የሚፈርድላቸው እውነተኛ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ስላለፈውም ዘመን፣ ስላለውም ዘመን፣ ስለሚመጣውም ዘመን ጠንቅቆ የሚያውቅ አምላክ እንደመሆኑ ፍርዱ ሁልጊዜም እውነተኛ ነው፡፡ ለትክክለኛ ፍርድ መሠረቱ ትክክለኛ ዕውቀት ነውና፡፡ ስለሆነም ጻድቃንን ተርቤ አብልታችሁኛል፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛል፣ ታስሬ ጎብኝታችሁኛል፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛል፣ ብታረዝ አልብሳችሁኛል፡፡ ስለዚህ እናንተ የአባቴ ቡሩካን ብሎ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያስገባቸዋል፡፡ የኃጥኣን የዘለዓለም መኖሪያ በማያቋርጥና ዘለዓለማዊ በሆነ ኀዘን በገሀነመ እሳት ነው፡፡ የጻድቃን ደግሞ የዘለዓለም መኖርያ በማያቋርጥ የደስታ ሕይወት (ተወስኮ ዘነሳእያን/ዘነሳሕያን)

በመንግሥተ ሰማያት መኖር ነው:: ጻድቃንን በገነት ኃጥኣንን በሲኦል የሚያኖር እርሱ ጌታ ክርስቶስ ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፳፩

"የሰው ልጅም ሊሰቀል አልፎ ይሰጣል" (ማቴ. ፳፮፥፪):: ጌታ ሰውን ተሰቅሎ ማዳን ይገባዋል:: በእርሱ መሰቀል የሰው ልጅ ድኅነት ይፈጸም ዘንድ በፈቃዱ ተሰቀለ:: በጌታ የስቅለት ሂደት:-

- √ አይሁድ ይሰቅሉት ዘንድ ተሰብስበው ተማከሩ
- √ አሳልፎ እንዲሰጣቸው ለይሁዳ 30 ብር ሰጡ
- √ ጴጥሮስ ፈርቶ ጌታን አላውቀውም አለ
- √ የሀገር ሽማግሌዎችና ሊቃነ ካህናት ሰይፍና ጎመድ የያዙ ጭፍሮችን አስከትለው መጡ
- √ ይሁዳ በሽንገላ ስሞ ጌታን አሳያቸው
- √ ሐዋርያት ጌታን ትተውት ሸሹ
- √ አይሁድ በጌታ ተፉበት፣ ተሳለቁበት፣ ኀሰሙት
- √ ጌታን የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ሲከሱት ምንም አልመለሰም (ማቴ. ፳፯፥፲፪)
- √ በርባንን ፈትተው ክርስቶስን አሰሩት
- √ የጌታን ራሱን መቱት፣ ገፈፉት፣ ራቁቱን ሰቀሉት
- √ ከስድስት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ምድር ጨለመች
- √ ሖምጣጤ አጠጡት
- √ ጌታ በራሱ ሥልጣን ነፍሱን ከሥጋው ለየ
- √ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከታች ተቀደደ
- √ ምድር ተናወጠች፣ ዓለቶች ተሰነጣጠቁ
- √ ሙታን ተነሡ
- √ ዮሴፍ ጌታን በንጹሕ በፍታ ከፈነው
- √ ከዐለት በወቀረው በአዲስ መቃብር ቀበረው
- √ አይሁድ ፈርተው መቃብሩን አስጠበቁ

ጌታ ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው ያውቅ ነበር። ይኸውም ይሁዳ ነጻ ፈቃዱን ተጠቅሞ እንደሚሸጠው አውቆ ነው እንጂ ይሁዳ እንዲሸጠው አላስገደደውም ነበር። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ሁሉ መከራ የተቀበለው በመከራው መከራችንን ሁሉ ያርቅልን ዘንድ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፹፪

"እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ በሚሰበክበት ርሷ ያደረገችው ደግሞ ለርሷ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል" (ማቴ. ፳፮፥፲፫)። አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ የበዛ የአልባስጥሮስ ሽቱ ይዛ ጌታ በማዕድ ተቀምጦ ሳለ በራሱ ላይ አፈሰሰችለት። በዚህም ጽንዐ ፍቅሯን ገለጸች። ይህ መልካምነቷ ጌታን ደስ ስላሰኘው ወንጌል በሚሰበክበት ቦታ ሁሉ ለእርሷ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ እንደሚነገርላት ተናግሯል። ቅዱሳን እግዚአብሔርን በመልካም ሥራቸው ደስ ያሰኙታል። እግዚአብሔርም ለእነርሱ መታሰቢያ እንዲሆን ስለእነርሱ ብዙ ተናግሯል። ለምሳሌ "በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ የማይጠፋም የዘለዓለም ስም እሰጣቸዋለሁ" ብሏል (ኢሳ. ፶፮፥፭)። እኛም የጌታን ቃል መሠረት አድርገን በቅዱሳን በስማቸው ታቦት እንቀርጽላቸዋለን፣ ስማቸውን በጸሎት እናነሳለን፣ ስለእነርሱ እናስተምራለን። ባለሽቱዋ ሴት በመልካም ሥራዋ መታሰቢያዋ እንደሚነገር ሁሉ ቅዱሳንም በመልካም ሥራቸው መታሰቢያቸው ይነገራል። ለዚህ ትምህርት ደግሞ መሠረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፹፫

"እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ለብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው። ከእርሱ ጠጡ" (ማቴ. ፳፮፥፳፮-፳፱)። የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ከዕለት መቅሠፍት፣ ከሥጋዊ መከራ ያርቅ ነበረ እንጂ የነፍስን መከራ ማራቅ አልቻለም ነበር። የሐዲስ ኪዳኑ መሥዋዕት ግን የነፍስንም የሥጋንም መከራ የሚያርቅ፣ ነፍስንም ሥጋንም የሚቀድስ፣ የዘለዓለም ሕይወትን የሚያስገኝ፣ ኃጢአትን የሚያስተሠርይ ቅዱስ መሥዋዕት ነው። መሥዋዕቱም የክርስቶስ ሥጋና የክርስቶስ ደም ነው። ጌታ ኅብስቱን አንስቶ ባርኮ እንኩ ይህ ሥጋዬ ነው ብሏል። ወይኑንም አንስቶ ይህ ደሜ ነው ብሏል። በዚህ አግባብ አሁንም ኅብስቱንና ወይኑን አቅርቦ ካህኑ በጸለየ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ኅብስቱን ወደ ክርስቶስ ሥጋነት፣ ወይኑን ወደ ክርስቶስ ደምነት ይለውጠዋል። ምእመናንም ንስሓ ገብተው፣ ተሩፋት ሠርተው ይቀበሉታል። እርሱም ፈውሰ ሥጋ ፈውሰ ነፍስን ይሰጣቸዋል። በማንኛውም የዕድሜ ክልል ያለ ምእመን ንስሓ ገብቶ ሥጋውን ደሙን መቀበል ይችላል። ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ ለሕፃናት ብቻ ወይም ለሽማግሌዎች ብቻ የተፈቀደ አይደለም። ለወጣቶችም፣ ለባለትዳሮችም፣ ላላገቡትም፣ ለማግባት ላሰቡትም፣ ለማንኛውም ምእመን ሁሉ የተፈቀደ ነው። ነገር ግን ወደ እርሱ ለመቅረብ ንስሓ መግባት ከሁላችንም ይጠበቃል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፹፬

"ነፍሴ እስከሞት ድረስ እጅግ አዘነች" (ማቴ. ፳፮፥፴፰)። ወልደ እግዚአብሔር ቃል ሥጋን ብቻ

እንጂ ነፍስን አልነሳም የሚሉ ሰዎች የሚረቱት (ረ ይጥበቅ) በዚህ ኃይለ ቃል ነው። ቃል ነፍስንም ሥጋንም ከድንግል ማርያም ነስቶ ሰው ሆኗል። ማዘን፣ መተከዝ የነፍስ ግብር ነው። ስለዚህ ጌታ የሚያዝን፣ የሚተክዝ ሰውነትን ገንዘብ በማድረጉ አዝኗል፣ ተክዟል። በኃዘኑ ኃዘናችንን፣ በትካዙ ትካዛችንን ያርቅልን ዘንድ መድኃኔዓለም ክርስቶስ አዘነ፣ ተከዘ። ይህ ሁሉ የቤዛነት ሥራ ነው። ማዘን፣ መተከዝ የሚገባን እኛ ሆነን ሳለ ኃዘናችንን አዝኖ፣ ትካዛችንን ተክዞ ከዘለዓለማዊ ሞት አዳነን። ወደ ሕይወት መንግሥተ ሰማያትም መለሰን። ለክርስቶስ በነፍሱ ምትክ መለኮቱ ሆነው የሚሉ ከሓድያን ተነስተው ነበር። ህየንተ ነፍሱ ኮኖ መለኮቱ ብለውታል። ነገር ግን ይህ ንግግራቸው ከንቱ መሆኑን የምናውቀው ነፍሱ ከሥጋው ተለየች በሚለው ቃልና ነፍሴ እስከሞት ድረስ እጅግ አዘነች በሚሉት ቃላት ነው። ነፍሱ ከሥጋው ተለይታለች። በነፍሱ ምትክ መለኮቱ ነው ካሉ መለኮት የሌለበትና የማይኖርበት ቦታ ስለማይኖር ከሥጋ ተለየ አያሰኝምና ክሕደታቸው መሠረት አልባ መሆኑን እንረዳለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፹፭

"ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም" (ማቴ. ፳፬፥፴፮)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመጣበትን ቀን ማንም አያውቅም። ዘመኑ ዘመነ ዮሐንስ፣ ዕለቱ ዕለተ እሑድ፣ ሰዓቱ መንፈቀ ሌሊት እንደሆነ ቢታወቅም ብዙ ዘመነ ዮሐንስ፣ ብዙ ዕለተ እሑድ፣ ብዙ መንፈቀ ሌሊት አለና አይታወቅም አለ። የሰማይ መላእክትም አያውቁትም። ልጅም አያውቀውም ተብሏል። "ልጅ" ያለው ማንን ነው ከተባለ ፍጥረታትን እንደ ሽማ ጠቅሎ ልጅ ብሏቸዋል። ኦሪት ዘልደት ሲል ኦሪት ዘፍጥረት እንዲል። "ኀደጎ ለእግዚአብሔር ዘወለደከ" ሲል "ዘፈጠረከ" ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው (ዘዳ. ፴፪፥፲፰)። ስለዚህ ልጅም ቢሆን አያውቅም የሚለው ቃል መላእክትም ሌሎች ፍጥረታትም አያውቁም ማለት እንደሆነ አስተውል። ከአብ በቀር የሚያውቃት የለም አለ። "በቀር" የሚለው ቃል "ከፍጡራን" ሲለየው ነው እንጂ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ሲለየው አይደለም። ይህን የመሰለ አገላለጽ ፩ኛ ጢሞ. ፩፥፲፯ "ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይሞተው ለማይታየውም ለዘለዓለም ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘለዓለም ድረስ ይሁን አሜን" ይላል። በዚህ አገላለጽ "ብቻውን" ስላለ አምላክ "አብ ብቻ" ሊመስለን ይችላል። ነገር ግን "ብቻውን" የሚለው ከፍጥረታት ሲለየው ነው እንጂ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ሲለየው እንዳልሆነ የሚያሳውቀን ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች "ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ ተወለደ እርሱም ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘለዓለም ቡሩክ አምላክ ነው" ብሎ የወልድን አምላክነት ነግሮናልና ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፹፮

"ሲጸልይ፦ አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ ነገር ግን፥ አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ" (ማቴ. ፳፮፥፴፱)። ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቱን "ጽዋ" ብሎ ገልጾታል። ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ ማለትም ወደ ምእመናን ትለፍ ማለት ነው። ይኸውም ምእመናን እኔን አብነት አድርገው ይሙቱ (ለእውነት ሰማዕት ይሁኑ) ማለቱ ነው። ነገር ግን የአንተ ፈቃድ ይደረግ እንጂ የእኔ ፈቃድ ይደረግ አልልም። አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ። ምን ማለት ነው? ራሱ ወልድ በሌላ ጊዜ "እኔና አብ አንድ ነን!

የአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው" እያለ ተናግሯል:: የአብ ያለው ሁሉ የእርሱ ከሆነ ለምን አንተ እንደምትወድ እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ? የተለያየ ፈቃድ፣ የተለያየ ሥምረት (መውደድ) አላቸውን? ከተባለ የላቸውም:: ትርጉሙ አብ: ፈቃድህ ፈቃዴ ስለሆነ አንተ እንደምትወድ ይሁን ማለት ነው:: አብ: የምትወደው የምወደው ስለሆነ የምትወደው ይሁን ማለት ነው:: ይህን የመሰለ አነጋገር ይሁዳ ጌታን እንደሚሸጠው በምልክት ራሱ ጌታ ለሐዋርያት ነግሯቸው ነበር:: ይሁዳ ጌታን "የማስይዝህ እኔ ነኝን" ባለው ጊዜ ግን "አንተ አልክ" ብሎ ነበር የመለሰለት:: በዚህ ጊዜ ይሁዳ እንደሚሸጠው ጌታም እንደተናገረ ሳለ እንደምትሸጠኝ እየተናገርክ ያለኸው አንተ ራስህ ነህ ማለቱ "እኔ ግን አልተናገርኩም" የሚል ትርጉምን አይሰጥም:: አንተም አልክ የሚል ትርጉምን ይይዛል እንጂ:: ከላይ ያለው ኃይለ ቃልም አብ አንተ እንደምትወድ ይሁን ሲል አንተ የምትወደው እኔ የማልወደው አይደለም የምወደው ነው እንጂ የሚል ትርጉምን እንደሚይዝ ማስተዋል ይገባል:: እኔ እንደምወድ አይሁን ማለት ደግሞ ሲጀምር ከአንተ ፈቃድ የተለየ እኔ የምወደው ነገር የለኝም ማለት ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፹፮

"በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፦ ኤሎሄ፥ ኤሎሄ፥ ላማ ሰበቅታኒ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ:: ይህም፦ አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ ማለት ነው" (ማቴ. ፳፯፡፵፮):: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አምላክ ሆኖ ሳለ ለምን አምላኬ አምላኬ እያለ ተናገረ? ለምን ተውከኝ ማለትስ ምን ማለት ነው? ለምን ተውከኝ ብሎ መናገሩ ኢየሱስ የአዳም ቤዛ በመሆኑ ነው:: ስለዚህ በሲኦል በተተወው የሰው ልጅ ተገብቶ ለምን ተውከኝ ብሏል:: "አምላኬ" ማለቱስ እንደምን ነው ቢሉ ለተዋሐደው ሥጋ አብ አምላኩ ፈጣሪው ነውና:: ፈጣሪ ቃል ፍጡር ሥጋን እንደተዋሐደ ግልጽ ነው:: ይህ ከሆነ የክርስቶስን ሥጋ ማን ፈጠረው? አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር አንድ ናቸው:: ስለዚህ ወልደ እግዚአብሔር የተዋሐደውን ሥጋ ማን ፈጠረው ካልን ሦስቱም በአንዲት ሥልጣን ፈጥረውታል:: አብ ፈጠረው፣ ወልድ ፈጠረው፣ መንፈስ ቅዱስ ፈጠረው ቢል አንድ ነው:: ስለዚህ አምላኬ አምላኬ ሲል ለተዋሐደው ሥጋ አብም፣ ራሱ ወልድም፣ መንፈስ ቅዱስም አምላኩ ስለሆኑ ነው:: አዳምን ለማዳን ወልድ በተለየ አካሉ ቢሰቀልም፣ ወልድ በተለየ አካሉ ቤዛ አዳም ቢሆንም አዳምን በማዳን ግን ሦስቱም አካላት ማለትም አብም፣ ወልድም፣ መንፈስ ቅዱስም አንድ ናቸው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፹፯

"ኢየሱስም፦ አንተ አልኸ፥ ነገር ግን፥ እላችኋለሁ፥ ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኀይል ቀኝ ሲቀመጥ፥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችኹ አለው" (ማቴ. ፳፮፡፷፬):: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ መካከል እየተመላለሰ የሕይወትን ትምህርት ቢያስተምራቸውም ትምህርቱን ግን ብዙዎች ሳይቀበሉት ቀርተዋል:: እርሱ ክርስቶስ በፍጹም ትሕትና ቢያስተምራቸውም ሳያምኑበት ቀርተዋል:: በታላቅ ግርማ መጥቶ ኃጥኣንን በግራ ጻድቃንን በቀኝ በሚያቆምበት ጊዜ ግን ሁሉም አምላክነቱን፣ መሢሕነቱን ይረዳሉ:: "በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ" የሚለው አነጋገር አምላክነቱን ያሳውቃል:: ያን ጊዜ አምላክነቱን ቢያውቁም ግን አይጠቀሙም:: ምክንያቱም ያን ጊዜ የሚመጣው ለፍርድ ነው:: በሰማይ ደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ የሚለው እርሱን ደመና

የሚሸከመው ሆኖ አይደለም:: እርሱ ደመናትን ይሸከማል እንጂ ደመናት እርሱን አይሸከሙትም:: በሰማይ ደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ መባሉ በግርማ መለኮት እንደሚመጣ ለመግለጥ ነው:: ወበእንተ ዕበይከ ትትሜሰል በደመና እንዲል::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፹፱

"በዚያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ የተባለው፦ ከእስራኤል ልጆችም አንዳንዶቹ የገመቱትን፥ የተገመተውን ዋጋ ሠላሳ ብር ያዙ፥ ጌታም እንዳዘዘኝ ስለሸክላ ሠሪ መሬት ሰጡት:: የሚል ተፈጸመ" (ማቴ. ፳፯፥፱-፲):: ነቢዩ ኤርምያስ ይህንን ቃል ከምን ላይ ተናግሮት ነበር? ይህ 66 ቁጥር ካለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ አይገኝም:: ይህ ቃል የሚገኘው ከሰማንያ አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው:: ተረፈ ባሮክ ላይ "እነሱስ ካባቶቻችሁ ይልቅ ፈጽማ የተናቀች ኃጢአትን ሠሩ:: እነሱ ዋጋ የሌለው ሰውን ይሸጡታል:: ከበሽታ የሚያድኝ ጌታን እንዲታመም ያደርጉታል:: ኃጢአት የሚያስተሠርይ ጌታንም ይፈርዱበታል:: እስራኤል ልጆች የተስማሙበት የሰው ልጅ ዋጋ ሠላሳውን ብር ይቀበሉታል ያንንም ብር ለሸክላ ሠሪ ቦታ ዋጋ አድርገው ይሰጡታል" ተብሎ ተገልጿል (ተረ. ባሮ. ፩፥፪-፫):: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መጻሕፍት አምላካውያት የሚባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች 81 ናቸው:: እነዚህም ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ሁለት ላይ ተገልጸዋል:: ተረፈ ባሮክ ቁጥሩ ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር ነው አንድ ተብሎ ይቆጠራል:: በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው ጌታን ሠላሳ ብር እንደሚሸጡት በትንቢት መልኩ ተነግሮ የነበረው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺

ኢየሱስ ክርስቶስ "ከሙታን ተነሣ::" (ማቴ. ፳፰፥፯):: የክርስትና ሃይማኖት ከሌሎች እምነቶች የሚለየው አስተምህሮው የተረጋገጠ መሆኑ ነው:: የሰው ልጅ ሁሉ ሞቶ እንደማይቀርና እንደሚነሣ በኵረ ትንሣኤ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ ተነሥቶ አሳየን:: አይሁድ ጌታ እንደሚነሣ ሲያስተምር ሰምተውት ስለነበር መቃብሩን በጭፍሮች እንዲጠበቅ አድርገውት ነበር:: ጌታ ግን ከሙታን መካከል ተነሣ:: በዚህ ጊዜ አይሁድ ከጭፍሮች ጋር ተመካክረው "እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ" አሏቸው:: ላለማመንና ራሳቸው ከድኅነት ለማራቅ ዋሹ:: ጌታ ግን ከሙታን መካከል ተነሥቶ ለሐዋርያቱ ተገልጾ ትምህርተ ኀቡዓትን፣ ኪዳንን አስተማራቸው:: እያዩትም ወደ ሰማይ ዐርጓል:: ከሞትን በኋላ ትንሣኤ እንዳለ ምስክራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ሌሎች ቤተ እምነቶች ግን ከሞት በኋላ ሕይወት ስለመኖሩ የሚያረጋግጥላቸው ነገር የለም:: ሞት የሕይወት መጨረሻ አይደለም:: ወደ ሌላ የሕይወት ክፍል መሸጋገሪያ ነው:: በዚህ ምድር የምንኖረው ለዘለዓለማዊው ሕይወት የሚያበቃንን ሥራ እንድንሠራ ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺፩

"ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ" (ማቴ. ፳፰፥፲፰):: "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ" ሲል ሰጪው ማነው? ተሰጪውስ ማን ነው? የሚለውን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል:: ይህ ቃል የተነገረው ክርስቶስ ስለተዋሐደው

ሰውነት እንደሆነ ግልጽ ነው። ምክንያቱም እንደ አምላክነቱ ሰጪ እንጂ ተሰጪ አይደለም። ሥጋ ግን ቃልን በተዋሐደ ጊዜ በማኅፀን የአምላክነትን ክብር አግኝቷል። ይኸውም አምላካዊ ሥልጣንን ገንዘቡ አድርጓል ማለታችን ነው። ስለዚህም "ሥልጣን ሁሉ ተሰጠኝ" ብሎ ይናገራል። ስለክርስቶስ መጻሕፍት ሲናገሩ አንዳንድ ጊዜ የሰውነቱን ነገር ያነሣሉ፣ አንዳንድ ጊዜ የአምላክነቱን ነገር ያነሣሉ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአንድነት የሰውነቱንም የአምላክነቱንም ነገር ያነሣሉ። ክርስቶስ ብዙ ጊዜ ራሱን የሰው ልጅ እያለ ጠርቷል። በዚህ ጊዜ አምላክነቱን ትቶ እንዳልሆነ ልብ ማድረግ ያስፈልጋል። ብዙ ጊዜ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ሲልም ይገኛል በዚህ ጊዜ ሰውነቱን ትቶ እንዳልሆነ ልብ ይሏል። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅ እየተባለ የሚጠራው ሰው በመሆኑ እንደሆነ ሁሉ ሥልጣን ተሰጠኝ ማለቱም ስለሰውነቱ መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺፪

"እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችኹንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (ማቴ. ፳፰፥፲፱)። ይህ ምሥጢረ ሥላሴ የተገለጠበት ኃይለ ቃል ነው። አሕዛብ ያላቸው ከልጅነት ውጭ ያሉ ሰዎችን ነው። ስለዚህ ሐዋርያት እነዚህን ሰዎች በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቁ ደቀመዛሙርት (ክርስቲያን) ያደርጓቸው ዘንድ ታዝዘዋል። ሰው ከመጠመቁ በፊት የማንም እምነት ተከታይ አይደለም። ክርስቲያንም አይደለም፣ እስላምም አይደለም፣ ፕሮቴስታንትም አይደለም። ሰው ብቻ ነው እንጂ። ሰው በሥላሴ ስም ሲጠመቅ ክርስቲያን ይሆናል። በሥላሴ ስም ማለት ሥላሴን አምኖ ማለት ነው። እግዚአብሔር ሦስት አካላት አሉት። እኒህም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። ሦስት አካላት ስላሉ ሦስት እግዚአብሔር፣ ሦስት አማልክት አሉ ግን አንልም። ምክንያቱም ሦስቱ አካላት ተገናዛቢ ናቸው። ይኸውም አብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ልብ፣ ወልድ የአብ የመንፈስ ቅዱስ ቃል፣ መንፈስ ቅዱስ የአብ የወልድ እስትንፋስ ነው። ሦስቱ አካላት በየአካላቸው ጸንተው በከዊን እየተገናዘቡ ይኖራሉ። የሦስቱ አካላት መገነዛዘብም አንድ አምላክ፣ አንድ እግዚአብሔር ያሰኛል እንጂ ሦስት አማልክት አያሰኝም። መገነዛዘብ ባይኖር ኖሮ ግን ሦስት ባሰኝ ነበር።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺፫

ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን "እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ዅልጊዜ ከእናንተ ጋራ ነኝ" ብሏቸዋል (ማቴ. ፳፰፥፲፱)። በሐዋርያት ካህናትን ሁሉ መናገሩ ነው። ይህም ማለት ክርስቶስ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ በካህናት አድሮ ጸጋውን እንደሚያድል የሚያስረዳ ቃል ነው። ከሁሉ ጋር ሁል ጊዜ መኖር የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። ፍጡር ውሱንነት ስላለበት በሁሉ ቦታ ከሁሉ ጋር በሁሉም ጊዜ መገኘት አይችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ፈጣሪ በመሆኑ ሐዋርያትን እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ ብሏቸዋል። ይህ "እስከ" ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው። ከዓለም ፍጻሜ በኋላም ለዘለዓለሙ ነግሦላቸው በእርሱ ዓለምነት ይኖራሉና። "ከእናንተ ጋራ ነኝ" የሚለው አባባል በረድኤት፣ ጸጋን በእነርሱ አድሮ በማደል እንደሆነ መረዳት ይገባል። በአካልማ በሁሉ ቦታ ያለ ስለሆነ ከሐዋርያትና በእነርሱ እግር ከተተኩት ከካህናት ጋር ብቻ

ሳይሆን ከፍጥረታቱ ሁሉ ጋር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሌለበት ቦታ ስለሌለ ከእርሱ ተሰውረን ምንም ነገር ማድረግ አንችልም። በየትኛውም ቦታ ብንኖር ያየናል ይሰማናል። ልባችንን ሳይቀር መርምሮ ያውቃል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺፬

"የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ" (ማር. ፩፡፩)። ወንጌላዊው ማርቆስ ወንጌሉን ሲጽፍ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ ይጀምርና ስለዮሐንስ መጥምቅ ይጽፋል። ነገረ ክርስቶስን ከነገረ ቅዱሳን ጋር አያይዞ ማስተማር የወንጌላዊ (ወንጌልን አስተምራለሁ የሚል ሰው) መገለጫ ነው። በጣም የሚገርመው ቅዱስ ማርቆስ ስለዮሐንስ መጥምቅ ስለልብሱ፣ ስለምግቡ ሳይቀር መጻፉ ነው። በተጨማሪም የንስሓን ጥምቀት ያጠምቅ እንደነበረ ጽፏል። ምክንያቱም ከቅዱሳን ሕይወትም እንድንማር ስለፈለገ ነው። ስለዚህ ስለቅዱሳን ሕይወት መናገር ነገረ ክርስቶስን አይጋርደውም። በዘመናችንም የቅዱሳን ሕይወትና ተጋድሎ በገድል መልኩ ተዘጋጅቶ የቀረበው ከሕይወታቸው ትምህርትን እንድናገኝበት ነው። ዮሐንስ መጥምቅ እርሱ በውሃ እንደሚያጠምቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል ብሏቸዋል። በእርሱ ጥምቀት ረቂቅ ልጅነትን ታገኛላችሁ ሲል ነው። ዮሐንስ መጥምቅ ከሞተ በኋላ ጌታ ተአምራትን እያደረገ፣ በሽተኞችን እየፈወሰ መጥቷል። አንዱን በሽተኛ ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ ብሎታል። ይኸውም ወደካህናት እየሄድን ንስሓ መግባት እንዳለብን ያመለክታል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺፭

ጌታ ኢየሱስ ሽባውን ፈውሶ "ኃጢአትህ ተሰረየችልህ" ብሎታል (ማር. ፪፡፭)። በዚህ ጊዜ አይሁድ "ከጻፊዎችም አንዳንዶቹ በዚያ ተቀምጠው ነበር በልባቸውም፦ ይህ ሰው ስለ ምን እንደዚህ ያለ ስድብ ይናገራል። ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኀጢአት ሊያስተሰርይ ማን ይችላል ብለው ዐሰቡ" ተብሏል። ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ቢሆን ኃጢአትን ይቅር ማለት አይችልም። አይሁድ ይህን ማወቃቸው ጥሩ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትን ይቅር ሲል ቢያዩት ይሳደባል ብለውታል። ይሳደባል ያሉት ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ "እግዚአብሔር" መሆኑን ባለመረዳታቸው ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስም አምላክ እንደሆነ እንዲረዱት "ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኀጢአትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ" ብሏቸዋል (ማር. ፪፡፲)። የሰው ልጅ ብሎ ስለሰውነቱ ነግሯቸዋል። በሥራው ደግሞ እግዚአብሔርነቱን ነገራቸው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺፮

"ኢየሱስም አላቸው፦ ሙሽራው ከነርሱ ጋራ ሳለ ሚዜዎች ሊጦሙ ይችላሉን ሙሽራው ከነርሱ ጋራ ሳለ ሊጦሙ አይችሉም። ነገር ግን፥ ሙሽራው ከነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፥ በዚያ ወራትም ይጦማሉ" (ማር. ፪፡፲፱-፳)። ሙሽራው የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሚዜዎች የተባሉት ሐዋርያት ናቸው። ጾምን ሕግ አድርጎ የሰጠ የጾም ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላቸው ሳለ ሐዋርያት እንደማይጾሙና ሙሽራ የተባለው እርሱ በሥጋ ከተለያቸው በኋላ ግን እንደሚጾሙ ተናግሯል። ጾም ምሥጢሩ መከልከል ነው። ይኸውም ለተወሰነ ሰዓት ከምግብ፣ ለተወሰኑ ዕለታት ከፍስክ ምግቦች፣ ለዘለዓለም ከክፉ ነገር መከልከል

ነው:: አይሁድ እየጾምን ነው ብለው አስበው እንኳ ከሐሜት ግን አልተለዩም:: እንዲህ ዓይነቱን ጾም ጌታ ኢየሱስ ከእኛ አይፈልገውም:: ጾም ፍቅርን ይዞ፣ ይቅርታን አንግቦ የሚፈጽሙት ነው:: ከላይ ባለው ቃል በባህላቸው በሙሽራው የሙሽርነት ጊዜ ሚዜዎች እንደማይጾሙ ያስረዳል:: በሀገራችንም ይህንን ይዘው ከሰባቱ የአዋጅ አጽዋማት መካከል በሙሽርነት ጊዜያቸው የማይጾሙ ሰዎች ይስተዋላሉ:: ነገር ግን ይህ ትልቅ ስሕተት ነው:: ጾም ሰባት ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ ምእመን ሁሉ የታዘዘ ስለሆነ ከባድ ሕመም ካልታመሙ በስተቀር ጾምን መሻር አይገባም:: ጌታም በባህላቸው ያለውን ተናገረ እንጂ በሙሽርነት ጊዜያችሁ አትጹሙ የሚል መልእክትን አላስተላለፈም::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፯

"የሰው ልጅ ለሰንበት እንኳ ጌታዋ ነው አላቸው" (ማር. ፪፥፳፰):: ሐዋርያት በሰንበት በእርሻ መካከል ሲሄዱ እሸት ቀጥፈው በልተው ነበር:: አይሁድ ግን በዕለተ ሰንበት ለምን እሸት ይቀጥፋሉ ብለው ጌታን ተቃውመውት ነበር:: ጌታ ግን ዳዊት ያደረገውን በታሪክ ነግሯቸዋል:: ዳዊት ያልተፈቀደለትን መሥዋዕት በተራበ ጊዜ እንደበላ ነግሯቸዋል:: ሰንበት የተፈጠረው ለሰው ነው እንጂ ሰው ለሰንበት እንዳልተፈጠረ ነግሯቸዋል:: የበዓል ክብሩ ከሰው ቀጥሎ ነው:: ከዕለት ሰው ይበልጣልና:: ሐዋርያት በተራቡ ጊዜ በሰንበት እሸት ቀጥፈዋል:: ይህ እንደበደል የሚታይ አይደለም:: ዳዊት በተራበ ጊዜ ለካህናት ብቻ የሚገባውን መሥዋዕት በልቷል:: ይህ ከበደል አልተቆጠረበትም:: በዕለተ ሰንበት የዕለት ምግብ ሠርተው ቢበሉ በደል አይሆንም:: የሚበላ ካልተገኘ በዕለተ ሰንበት እንጀራ ቢጋግሩ፣ ወጥ ቢሠሩ ሰንበትን ሻሩ አያሰኝም::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፰

"ልብሴን የዳሰሰ ማን ነው አለ" (ማር. ፭፥፴):: ለብዙ ዘመን ደም ይፈሳት የነበረች ሴት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ልብስ በዳሰሰች ጊዜ ተፈውሳለች:: ይህች ሴት ከበሽታዋ ለመዳን አስቀድማ ከብዙ ባለመድኃኒቶች ዘንድ ሄዳ ነበር:: ነገር ግን ገንዘቧን ከመጨረስ ውጭ ፈውስን ማግኘት አልቻለችም ነበር:: ኢየሱስ ግን በሽታዎችን ሁሉ እንደሚፈውስ ሰምታ ከኋላው ሄዳ ልብሱን ዳሰሰችና ፈጥና ተፈውሳለች:: ያን ጊዜ ጌታ ልብሴን የዳሰሰ ማን ነው ብሎ ጠየቀ:: እርሱ ጌታ ሁሉንም የሚያውቅ ነው:: ማን እንደዳሰሰውም ሳይጠይቅ በፊት ያውቃል:: ኃይል ከእርሱ እንደወጣም አውቋል:: ታዲያ እንዲህ ከሆነ ማን ዳሰሰኝ ብሎ መጠየቁ ለምንድን ነው? ተአምራቱን ሁሉ ሲያደርግ በዕውቀት እንደሚያደርግ ሐዋርያቱ ይረዱ ዘንድ ነው:: ደም ይፈሳት የነበረችዋ ሴትም ሳያውቅ ልብሱን ብነካ ተፈወስኩ እንዳትልና ሁሉንም በዕውቀት እንደሚሠራ ለማጠየቅ ማን ልብሴን ዳሰሰኝ ብሎ ጠይቋል::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፱

"ስለ ምን ቸር ትለኛለህ ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም" (ማር. ፲፥፲፰):: ኢየሱስ ክርስቶስ ቸር እንደሆነ ራሱ "ቸር እረኛ እኔ ነኝ:: ቸር እረኛ ራሱን ስለበጎቹ አሳልፎ ይሰጣል" ብሎ ተናግሯል (ዮሐ. ፲፥፲፩):: ስለዚህ አንድ ሰው "ቸር መምህር ሆይ የዘለዓለም ሕይወትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ" ብሎ በጠየቀው ጊዜ ከአንዱ ከእግዚአብሔር ውጭ ቸር

ማንም የለም ብሎ ጌታ ኢየሱስ መልሶለታል። ቸርነት የባሕርይው የሆነ ቸሩ እግዚአብሔር ብቻ ነው። የፍጡራን ቸርነት ግን የጸጋ ቸርነት ነው። የሰውየው አመጣጥ ውዳሴን ፈልጎ እንደሆነ የሚያሳውቀን አነጋገር ዝቅ ብሎ "ይህን ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄያለሁ" በማለቱ ነው። ስለዚህ ቸር ብለው ቸር ይለኛል ብሎ መጥቷል። ጌታ ግን ይህንን አስቀድሞ ስላወቀ ከእግዚአብሔር ውጭ ቸር የለም ብሎታል። ራሱ ጌታ ኢየሱስም እግዚአብሔር ስለሆነ ከእኔ ውጭ ቸር የለም እያለው እንደሆነ ግልጽ ነው። "ስለምን ቸር ትለኛለህ?" ማለቱም ቸር ያልክበት ምክንያት ምንድን ነው? ማለቱ ነው። ይህንንም መጠየቁ ያለበትን ምክንያት አላውቅ ብሎ አይደለም። ጌታ ለማናገር ሲሻ እያወቀ እንዳላወቀ መስሎ ይጠይቃልና። ይህን የመሰለ "አዳም ሆይ ወዴት አለህ" ብሎ ጠይቋልና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲

"በሰቀሉትም ጊዜ ሦስት ሰዓት ነበረ" (ማር. ፲፭፥፳፭)። ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ለሚሉ ፕሮቴስታንቶች ራስ ምታት የሚሆንባቸው እንዲህ ዓይነቱ ቃል ነው። በዮሐንስ ወንጌል፣ በሉቃስ ወንጌልና በማቴዎስ ወንጌል ጌታ የተሰቀለው በስድስት ሰዓት እንደሆነ ጽፈዋል። ማርቆስ ግን በተሰቀለ ጊዜ ሦስት ሰዓት ነበረ አለ። የትኛው ነው ትክክል? ነው ወይስ ብዙዎች ያሉት ስድስት ሰዓት ስለሆነ ያንን ይዘን የማርቆስን እንተወው? በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ አራቱም ወንጌላውያን የተናገሩት ሐሳብ ትክክል ነው። ሦስቱ ወንጌላውያን ስድስት ሰዓት ነበረ ያሉ በንዑስ አቆጣጠር ቆጥረው ነው። ንዑስ አቆጣጠር የሚባለው አንዱን ሰዓት ያው አንድ ሰዓት በማለት መቁጠር ነው። ማርቆስ በዐቢይ አቆጣጠር ቆጥሮ ሦስት ሰዓት አለ። ዐቢይ አቆጣጠር የሚባለው ሁለቱን ሰዓት አንድ እያሉ መቁጠር ነው። ይኸውም:- እያለ የሚቆጥር አቆጣጠር ነው። ይህ አቆጣጠር ሁለቱን ሰዓት በአንድ የሚቆጥር አቆጣጠር ነው። በዐቢይ አቆጣጠር አንድ ቀን 12 ሰዓት ነው ማለት ነው። ስለዚህ ማርቆስ በዚህ ዐቢይ አቆጣጠር ቆጥሮ ሦስት ሰዓት ተሰቀለ ሲል ሌሎቹ ደግሞ በንዑስ ቆጥረው ስድስት ሰዓት ተሰቀለ አሉ። ሁሉም ትክክል ናቸው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፩

ወንጌላዊው ሉቃስ ወንጌሉን በነገረ ቅዱሳን ጀምሮታል። ስለኤልሳቤጥና ስለዘካርያስ "በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ" ብሎ ጽፏል (ሉቃ. ፩፥፮)። ቅዱስ ገብርኤል ለዘካርያስ ዮሐንስ እንደሚወለድና መወለዱም ለብዙዎች ደስታ እንደሚሆን ተገልጿል። የቅዱሳን መወለድ ለብዙዎች ደስታ ነውና። ምክንያቱም በጸሎታቸው በምልጃቸው ብዙውን ስለሚያድኑ ነው። ወንጌላዊው ሉቃስ ስለቅዱሳን ከተናገረ በኋላ ወደ ነገረ ክርስቶስ አቅንቶ ድንግል ማርያምን ልጅ ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ ብሎ ቅዱስ ገብርኤል እንደነገራት ጻፈልን። ቀጥሎ ድንግል ማርያምን መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል አላት። ይህም ማለት ያለ ወንድ ዘር እንድትወልጂ ያደርግሻል ሲላት ነው። በዚህም መንፈስ ቅዱስ ይጠራ እንጂ ለሦስቱም አካላት የተነገረ መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል። ከድንግል ማርያም የሚወለደው የአብ የባሕርይ ልጅ ወልደ እግዚአብሔር እንደሆነ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ነግሯታል። ኤልሳቤጥ አርጅታ ሳለች መጽነስ እንደቻለች ለጌታ የሚሳነው ነገር እንደሌለና ድንግል ማርያምም ጌታን ያለ ወንድ ዘር፣

ያለሩከቤ እንደምትወልደው ነግሯታል። በኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ መላባትና ድንግል ማርያምን ቡርክት ነሽ ብላ አመሰገነቻት። መንፈስ ቅዱስ ያልተለየው ሰው ድንግል ማርያምን ያመሰግናልና። ድንግል ማርያምን ማመስገን፣ ስለቅዱሳን መመስከር ክርስቶስ ኢየሱስን አይሸፍነውም። ስለዚህ ስለቅዱሳንም እንናገራለን እናስተምራለን። ስለድንግል ማርያምም እንናገራለን እናስተምራለን። ስለኢየሱስ ክርስቶስም ሁልጊዜም እናስተምራለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፪

"ፀንሳ ከነበረች ከዕጮኛው ከማርያም ጋራ ይጻፍ ዘንድ ወጣ" (ሉቃ. ፪፥፭)። መጽሐፍ ቅዱስ ድንግል ማርያምን የዮሴፍ እጮኛ ይላታል። ይህኛው እጮኝነት እኛ ከምናውቀው እጮኝነት የተለየ ነው። ዮሴፍ የማርያም እጮኛ ነው ማለት ጠባቂ ነው ማለት ነው። ይጠብቃት ዘንድ በአደራነት ከአይሁድ የተሰጠችው ዘመዱ ናትና። ከእርሱ ጋር እንድትቆጠር ወደቤተልሔም ሄዳ ሳለ በዚያ የዓለም መድኃኒት ክርስቶስን ወለደችው። በእንግዶች ማረፊያ ቦታ ስላልነበረም የቦታዎች ሁሉ ባለቤት እርሱን በጨርቅ ጠቅልላ በግርግም አስተኛችው። የጌታን መወለድ መልአክ ለእረኞች (ኖሎት) የምሥራች ነገራቸው። መድኃኒት ተወልዶላችኋል የምሥራች አላቸው። መለእክትም "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ" ብለው አመሰገኑ። ድንግል ማርያም ጌታን ከመውለዷ ጀምሮ ብዙ ታላላቅ ምሥጢራትን አይታ የነበረ ቢሆንም ሁሉንም ግን በልቧ ትጠብቀው ነበር። በስምንተኛው ቀን ጌታን ሊገርዙት ወደቤተመቅደስ ወሰዱት ኢየሱስም ተባለ። ሊገርዙት ቢወስዱትም በተአምራት ምንም ደም ሳይፈሰው ተገርዟል። ይኸውም ያለ ገራዚ፣ እንበለ መላዒ ነው። በአርባኛው ቀን የመቅደሱን ባለቤት ወደ ቤተ መቅደስ ወሰዱት። በዚያም ስምዖን የጌታን መወለድ ሲጠባበቅ ይኖር ነበር። ጌታን አይቶም ደስ አለው። እንግዲህስ ባርያህን በሰላም አሰናብተው ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋልና አለው። ጌታ ክርስቶስም በጥበብ አደገ። በጥበብ አደገ ማለትም የጥበብ ባለቤት እርሱ በሥጋ ማደጉን ለማመልከት ነው። በአንድ ጊዜ ልደግ ሳይል እንደሰው ቀስ በቀስ በሥጋ አድጓልና። 12 ዓመት በሆነው ጊዜ ወደ ቤተመቅደስ ሄዶ ከሊቃውንት ጋር ይጠያየቅ ነበር። ቤተ መቅደስንም የአባቴ ቤት ይለው ነበር።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፫

"ኢየሱስም ሊያስተምር ሲዠምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያኽል ኾኖት ነበር" (ሉቃ. ፫፥፳፫)። ከሠላሳ ዓመቱ በፊት አላስተማረም ለማለት አይደለም። ጌታችን ከዚያም በፊት በተአምረ ኢየሱስ እንደተጻፈው ተግባራዊ ትምህርቶችን እያስተማረ ነበር። ጌታ ኢየሱስ በይፋ ወንበር ዘርግቶ፣ ሐዋርያትን መርጦ ማስተማር የጀመረው ግን በሠላሳ ዓመቱ ነው። ለሰው የሕይወትን መንገድ (የመልካም ኑሮን አኗኗር) በሕይወቱ እያሳየ ሲያስተምር ኖሯል። በ12 ዓመቱ በቤተ መቅደስ በሊቃውንቱ መካከል ተቀምጦ ሲጠያየቅ እንደነበረና በንግግሩ፣ በትምህርቱ ብዙዎች ይደነቁ እንደነበረ ተገልጿል። አዳም የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ የሚኖረውን አካላዊ ቁመና አህሎ ተፈጥሮ ሳለ በሰይጣን ትምህርት ተታሎ የሞት ሞትን ሞቶ ነበር። ስለዚህ አዳምን ክሦ ለማዳን ጌታም በሠላሳ ዓመቱ ማስተማር ጀመረ ተብሏል። ክፉ ቃልን

ከክፉ መንፈስ ሰምቶ የወደቀ የሰው ልጅ መልካም ቃልን ከአካላዊ ቃል ሰምቶ ወደ ገነት ተመለሰ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፬

"የመላልኤል ልጅ፥ የቃይናን ልጅ፥ የሄኖስ ልጅ፥ የሴት ልጅ፥ የአዳም ልጅ፥ የእግዚአብሔር ልጅ" (ሉቃ. ፫፥፴፰)። ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም እንደመወለዱ ከአዳም ጀምሮ የሚነገር ምድራዊ የዘር ሐረግ አለው። አባቶቹ፣ አያቶቹም በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ሦስት ላይ ተጠቅሰዋል። ስለዚህ የአዳም ልጅ፣ የሄኖስ ልጅ፣ የቃይናን ልጅ ወዘተ እየተባለ በቅድመ አያቶቹ ይጠራል። ይህንን ብቻ ይዘን ክርስቶስን ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ነው እንዳንል ግን ቀጥሎ የእግዚአብሔር ልጅ ብሎም ገልጾታል። ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ ነው። በቀዳማዊ ልደቱ ከአብ ያለ እናት የተወለደው እርሱ በደኃራዊ ልደቱ ከድንግል ማርያም ያለ አባት ተወለደ። በሰማያዊ ልደቱ አባት እንጂ እናት የለውም። በምድራዊ ልደቱ ደግሞ እናት እንጂ አባት የለውም። ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅ ስንለው የባሕርይ ልጁ ነው ማለታችን ነው። ይኸውም የአንበሳ ልጅ አንበሳ፣ የሰው ልጅ ሰው እንደሆነ ሁሉ የእግዚአብሔር አብ ልጁ እግዚአብሔር ወልድ ነው ማለታችን ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፭

"ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስ መልቶበት ከዮርዳኖስ ተመለሰ" (ሉቃ. ፬፥፩)። ለኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ እስትንፋሱ (ሕይወቱ) ነው። ለመንፈስ ቅዱስ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ አካላዊ ቃሉ ነው። ይህ ደግሞ ባሕርያዊ የኵነት ተገናዝቦ ነው። ባሕርያዊ የኵነት ተገናዝቦ ማለት ከጊዜ በኋላ የሆነ መገነዛዘብ ሳይሆን ዘለዓለማዊ የሆነና በዘመን ብዛት የማይለዋወጥ ተገናዝቦ ነው ማለታችን ነው። ይህ ከሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ መላበት ማለቱ ምን ማለቱ ነው? አስቀድሞ መንፈስ ቅዱስ የሌለው ሆኖ በኋላ መላበት ማለት አይደለም። በእርግጥ መንፈስ ቅዱስን እስትንፋሱ ሳያደርግ ለ5500 ዘመን የነበረ ሥጋ (ሰውነት) ቃልን በተዋሐደ ጊዜ አብ ልቡ፣ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋሱ ሆኗል። ከተጠመቀ በኋላ መንፈስ ቅዱስ መላበት ተብሎ መነገሩ ግን ትርጓሜው የባሕርይ ልጅነቱን ከመንፈስ ቅዱስ አስመሰከረ ማለት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፮

"ዲያብሎስም ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ እስከ ጊዜው ከርሱ ተለየ" (ሉቃ. ፬፥፩-፲፫)። ዲያብሎስ እስከ ስቅለት ድረስ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ፈጽሞ አላወቀም ነበር። እና ብዙ ጊዜ አምላክነቱን ለማወቅ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ይህን አድርግ እያለ ፈትኖታል። ጌታ ግን ዲያብሎስ አድርግ ያለውን አላደረገም። ያላደረገው ግን ማድረግ የማይችል ሆኖ አይደለም። ለሰይጣን መታዘዝ እንደማይገባ እኛን ሊያስተምረን ስለፈለገ ነው እንጂ። ሰይጣን ጌታን ሦስት ጥያቄዎችን ጠይቆታል። እነዚህም:-

√ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ይህን ድንጋይ እንጀራ ኹን ብለህ እዘዝ

√ አንተ በእኔ ፊት ብትሰግድ ሁሉ ለአንተ ይሆናል

√ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንክ ከዚህ ወደ ታች ራስኽን ወርውር

የሚሉት ናቸው። እነዚህን ማድረግ ጌታ ይችል ነበር። ነገር ግን ቢያደርግ የሰይጣን ታዛዥ ለማሰኘት ሰይጣን ፈትኖታል። ነገር ግን ጌታም ጥቅሱን በጥቅስ መልሶ ሰይጣንን አሳፍሮታል። ቀድሞ ዲያብሎስ በእባብ ተሰውሮ አዳምንና ሔዋንን አሳስቶ ነበር። ጌታ ደግሞ እርሱን የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ ድል ነሥቶታል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፯

"የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት፥ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ፦ የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆዎች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና። ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ተብሎ የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ። ርሱም፦ ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሯችሁ ተፈጸመ ይላቸው ጀመር" (ሉቃ. ፬፥፲፯-፳፩)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የነቢያትን ትንቢት የፈጸመ አምላክ ነው። ስለሆነም ነቢዩ ኢሳይያስ ስለእርሱ የተናገረው በእርሱ እንደተፈጸመ ነግሯቸዋል። የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው አለ። መንፈስ ቅዱስ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱ ነውና። አብ ልቡ ነው። ቀብቶኛል (ቀብዐኒ) ማለቱ በማክበር፣ በማዋሐድ ሦስቱ አካላት አንድ ስለሆኑ አብ ቢጠራም ለሁለቱም ይሆናል። ሥጋን የተዋሐደው ግን በተለየ አካሉ ቃል ስለሆነ ለሥጋ ቅብዕ የሆነው ቃል ነው። በዲያብሎስ ተንኮል ተታለው በሲኦል እስር ቤት ይማቅቁ ለነበሩ ነፍሳት ግእዛንን (ነጻነትን) ሰበከላቸው። እለ ውስተ ሲኦል ፃኡ ብሎም ነጻ አወጣቸው። ለታሰሩት መፈታትን እሰጣቸው ዘንድ፣ የታመሙትን እፈውስ ዘንድ መጣሁ ብሏል። ይህን ትንቢትም ጌታ ሕሙማንን በመፈወስ ፈጽሞታል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፰

"ኢየሱስም፦ ዝም በል ከርሱም ውጣ ብሎ ገሠጸው። ጋኔኑም በመካከላቸው ጥሎት ሳይጐዳው ከርሱ ወጣ" (ሉቃ. ፬፥፴፭-፴፮)። የሰይጣንን ንግግር መስማት እንደሌለብን ያስተማረን ራሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሰይጣን የውሸት አባት ስለሆነ አይታመንም። በአንድ በሽተኛ አድሮ በለፈለፈ ጊዜ ኢየሱስ "ዝም በል ከእርሱም ውጣ ብሎ" ገሥጾታል። አብነታችን መምህራችን እርሱ ኢየሱስ ነው። ብዙ አላዋቂ ሰዎች ሰይጣን በጸበልም በሌላ ቦታም የለፈለፈውን ንግግር ሰምተው ከጎረቤታቸው፣ ከባላቸው፣ ከዘመዶቻቸው የተጣሉ አሉ። እገሌ መተት አድርጎባችሁ ነው እያላቸው ይህን ሰምተው ምእመናንን ከቤተክርስቲያን መምህራን የሚያጣላ ሰይጣን አለ። ነገር ግን ሰይጣንን ምንም ቢናገር (የተናገረው ነገር እውነት ቢሆንኳ) ዝም በል አትናገር ብሎ መገሠጽ ይገባል። የሰይጣንን ንግግር ቁም ነገር አድርገው በሲዲ የሚቸበችቡ ሰዎችም አሉ። ነገር ግን ይህ ተገቢ አይደለም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፱

"እንዲህ ነፋሳትንና ውሃን እንኳ የሚያዝ ለርሱም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው አሉ"

(ሉቃ.፰፥፳፭):: ደቀመዛሙርቱ ከላይ ያለውን የመደነቅ ንግግር ተናግረዋል:: ይኸውም ጌታ ነፋሳቱን ሲያዝዝ፣ ማያትን ሲገሥጽ አይተውታልና ነው:: ኢየሱስ ፍጥረታትን ሁሉ በቃሉ የፈጠረ ፈጣሪ በመሆኑ ፍጥረታት ሁሉ ይታዘዙለታል:: ለእርሱ የማይታዘዝ ፍጥረት የለም:: "ትእዛዘ ወሀቦሙ ወኢኀለፉ" እንዲል መዝሙረ ዳዊት 148:6:: ሕገ ተፈጥሮን የሠራ አምላክ እርሱ ኢየሱስ ነው:: ፈጥሮ የሚገዛና የሚመለክ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ሌሎቹን ፍጡራን ሰዎች ቢያመልኳቸው እንኳ እንዳልፈጠሯቸው ግን የተረጋገጠ ነው:: ያልፈጠሯቸውን የሚያመልኩ ሰዎች ከንቱዎች ናቸው:: ፍጥረታት ለሰው ቢገዙ ከፈጣሪ በተሰጠው ጸጋ ይገዛሉ እንጂ ሰው በባሕርይው ገዥ ሆኖ አይደለም:: ፍጥረታት ለኢየሱስ ክርስቶስ ሲገዙ ግን ገዥነቱ የባሕርይ ነው:: ስለዚህ በባሕርይው ገዢ ለሆነ ጌታ ፍጥረታት ሁሉ ይገዙለታል ተብሏል::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፲

"የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም አለ" (ሉቃ. ፱፥፶፬-፶፮):: አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስን ብዙ ጊዜ ፈትነውታል:: ሐዋርያቱም በአንድ ወቅት የእግዚአብሔርን ቃል ያልሰሙ ሰዎችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያጠፋቸው ጠይቀውት ነበር:: የጌታ መልስ ግን የሰውን ልጅ ሳድን እንጂ ሳጠፋ አልመጣሁም የሚል ነበር:: አምላክ ሰው የሆነበት መሠረታዊ ዓላማ ሰውን ለማዳን ነው:: ይህን ያልተረዱ አይሁድ ግን በጊዜ ስቅለቱ እስኪ ራስህን አድን እያሉ ሲሳለቁበት፣ ምራቃቸውን ሲተፉበት፣ እስኪ ራስህን ከመስቀል አውርድ እያሉ ሲያፌዙበት ነበር:: ጌታ ይህ ሁሉ ሲደርስበት ዝም ብሎ በትዕግሥት መከራውን ተቀብሏል:: ምክንያቱም የመጣ ሰውን ሊያድን ነው እንጂ ሰውን ሊያጠፋ አልመጣምና ነው:: ሰነፎች ግን ጌታ ያን ሁሉ መከራ የተቀበለው ራሱን መከላከል ስላልቻለ ያለ ፈቃዱ ያ ሁሉ መከራ እንደደረሰበት አድርገው ይናገራሉ:: ነገር ግን እንዲያ አይደለም:: ጌታ ሰው የሆነም፣ ሰው ሆኖ መከራ የተቀበለም በፈቃዱ በውድ እንጂ በግድ አይደለም:: መከራውንም የተቀበለ በመከራው መከራችንን ያርቅልን ዘንድ ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፲፩

"ኢየሱስም፦ ለቀበሮዎች ጕድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አለው" (ሉቃ. ፱፥፶፰):: ኢየሱስ ክርስቶስ ለመናንያን አብነት ለመሆን ለሠላሳ ሦስት ዓመት በዚህች ምድር ሲኖር ቤት አልሠራም:: ሥጋዊ መኖሪያ ቤትን አልሠራም:: ለዚህም ነው ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም የተባለው:: መናንያንም ጌታን አብነት አድርገው በየዋሻው፣ በየተራራው፣ በየዱሩ ይኖራሉ:: ጌታ እንደ አምላክነቱ በሁሉ ቦታ ያለ ስለሆነ እርሱን የሚችል ቤት የለም፣ አይኖርም:: ምክንያቱም ፍጥረታትን ይቷርፋቸዋል እንጂ አይተርፋትምና ነው:: እንደ ሰውነቱ በቤት ማደር ቢችልም በዚህ ምድር ግን ቤትን አልሠራም:: ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው የጠፋነውን እኛን ለማዳን ነው እንጂ ሥጋዊ ቤት ሊሠራ አይደለምና ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፲፪

"የሚሰማችኹ እኔን ይሰማል፥ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል"

(ሉቃ. ፲፥፲፮)። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳን ሐዋርያትን እናንተን የሚሰማ እኔ ሰማ፣ እናንተን የጣለ እኔን ጣለ ብሏቸዋል። በእርግጥ ቅዱሳንን ጠልቶ ክርስቶስን እወደዋለሁ ማለት ድንቁርና ነው። ወንጌላውያንም፣ ነቢያትም ሲያስተምሩና ሲጽፉ ከነገረ እግዚአብሔር ቀጥለው ነገረ ቅዱሳንንም እያስተማሩ እየጻፉ ነበርና ነው። በብሉይ ኪዳንም በሐዲስ ኪዳንም ነገረ ቅዱሳን የሌለበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አናገኝም። ሐዋርያት ከእርሱ ከኢየሱስ የተላኩ፣ ኢየሱስ ያስተማራቸውን ትምህርት እንዲያስተምሩ የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ እነርሱን አልሰማም ማለት ኢየሱስን አልሰማም ማለት ነው። ቅዱሳን እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ ተጉዘው ይህችን ዓለም ድል አድርገው ወደዚያኛው ዓለም የሄዱ አሸናፊዎች (መዋዕያን) ናቸው። እግዚአብሔር ያከበራቸው ስለሆነ እኛም እናከብራቸዋለን። እግዚአብሔር ስለሚወዳቸው እኛም ልጆቹ እንወዳቸዋለን። መውደዳችንንም በጸጋ ምስጋናና በጸጋ አክብሮት እንገልጽላቸዋለን። ከላይ ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል "የላከኝ" ተብሎ የተገለጸው አብ ነው። በተለየ አካሉ ለአብ ይነገር እንጂ የጌታ ሰው መሆን የሦስቱም ፈቃድ ስለሆነ ለአብም፣ ለመንፈስ ቅዱስም ይነገራል። "የላከኝ" ሰው እንድሆን ያደረገኝ ተብሎ ይተረጎማል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፲፫

"ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል፥ ወልድንም ማን እንደ ሆነ ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም፥ አብንም ማን እንደ ሆነ ከወልድ በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር የሚያውቅ የለም አለ" (ሉቃ. ፲፥፳፪)። ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል ብሏል። ይህን ስለሰውነቱ ተናግሯል። ቅድመ ተዋሕዶ ምንም ያልነበረው ሥጋ ቃልን ሲዋሐድ በቃል ርስት ሁሉን ገንዘቡ አደረገ። ተሰጠኝ ማለቱ አምላክነትን ከቃል ጋር በመዋሐዱ ገንዘብ ማድረጉን ያመለክታል። ወልድን ከአብ በቀር በአምላክነቱ በባሕርይው የሚያውቀው የለም። አብንም በአምላክነቱ በባሕርይው ከወልድ በቀር የሚያውቀው የለም። እንዲህ ሲል መንፈስ ቅዱስን ዘንግቶ አይደለም። "በቀር" የሚለው አገላለጽ ፍጡራንን የሚያመለክት ቃል ነው። አብ ወልድን፣ መንፈስ ቅዱስን ያውቃቸዋል። ወልድም አብን መንፈስ ቅዱስን ያውቃቸዋል። መንፈስ ቅዱስም አብን ወልድን ያውቃቸዋል። የሥላሴ ዕውቀት ባሕርያዊ ዕውቀት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፲፬

"እኔ ግን በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ ከኾንኹ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች" (ሉቃ. ፲፩፥፳)። ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን አወጣለሁ ብሏል። ከዚህ ላይ "ጣት" ብሎ የገለጸው ሥልጣኑን ነው። በእግዚአብሔር ሥልጣን ለማለት በእግዚአብሔር ጣት ብሏል። ኢየሱስ ክርስቶስን አይሁድ በብዔል ዜቡል ያወጽኦሙ ለአጋንንት። በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ባሉት ጊዜ እርሱ ግን በአምላክነት ሥልጣኑ አጋንንትን እንደሚያወጣ ሲነግራቸው "በእግዚአብሔር ጣት" አጋንንትን አወጣለሁ ብሏል። የእግዚአብሔር ሥልጣን ገደብ የለውም። በፍጥረታት ላይ ሁሉ የሰለጠነ ስለሆነ በፍጥረታት ላይ የፈለገውን ያደርጋል። ለእርሱ የሚሳነው ነገር የለም። ማንኛውንም በሽታ ይፈውሳል። ማንኛውንም ችግር ይፈታል። የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ያልተረዱ አይሁድ ግን ጌታን በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ብለው ተሳደቡ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፲፭

"ከእኔ ጋራ ያልሆነ ይቃወመኛል" (ሉቃ. ፲፩፥፳፫)፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል ብሏል፡፡ ከእርሱ ከኢየሱስ ጋር አለመሆን ዐመፃ ነው፡፡ ከኢየሱስ ጋር መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

፩) ባስተማረው ትምህርት ማመን

፪) አድርጉ ያለንን ማድረግ

፫) እርሱን በግብር (በሥራ) መምሰል

ናቸው፡፡ እርሱን መምሰል ማለትም እርሱ በድንግልና ጸንቶ እንደኖረ ደናግላንም በድንግልናቸው ጸንተው በመኖር ይመስሉታል፡፡ እርሱ አርባ ቀን እንደጾመ እኛም እርሱ የጾመውን ጾም መጾም ነው፡፡ እርሱ እንደጸለየ መጸለይ ነው፡፡ እርሱ ጻድቀ ባሕርይ እንደሆነ እኛም እውነተኞች መሆን ነው፡፡ እርሱ በዚህ ምድር ሲኖር ቤትን እንዳልሠራ መነኮሳትም እርሱን አብነት አድርገው በገዳም ይኖራሉ፡፡ በጠቅላላው እርሱን መምሰል ማለት እርሱ ያደረገውን ነገር አብነት አድርገን ማድረግ ነው፡፡ ኢየሱስን አምነዋለሁ ማለት ብቻ ሳይሆን ማመንን በተግባር መግለጽ ነው፡፡ ይህንን ካላደረግን ግን እርሱን መቃወም እንደሆነ ልብ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡አለ፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፲፮

"ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ_____ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ" (ሉቃ.፲፩፥፴፩-፴፪)፡፡ አይሁድ የጌታን አምላክነት አልተረዱም ነበር፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ለመረዳትም ፍላጎት አልነበራቸውም፡፡ ነገር ግን ለንጉሥ ዳዊትና ለንጉሥ ሰሎሞን ልዩ ፍቅር ነበራቸው፡፡ እና በዚህ ክርስቶስ ወደእርሱ ይስባቸው ዘንድ የሰሎሞንንና የንግሥተ አዜብን ታሪክ ይነግራቸዋል፡፡ የዮናስንም ታሪክ ይነግራቸዋል፡፡ የእነ ሰሎሞንን ታሪክ ከነገራቸው በኋላ እርሱ ከእነ ሰሎሞን እንደሚበልጥ ይነግራቸዋል፡፡ የእነ ሰሎሞን ንግሥናቸው፣ ክብራቸው ከእርሱ ከወልደ እግዚአብሔር የተሰጠ ነው፡፡ የእርሱ ክብርና ንግሥና ግን የባሕርይው ስለሆነ ከሰሎሞን እንደሚበልጥ ተናገረ፡፡ የነቢዩ ዮናስ ዕውቀት ከእርሱ ከአምላክ የተሰጠ ዕውቀት ስለሆነ ወሰን አለበት፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ዕውቀት ግን ፍጹም ስለሆነ ዕውቀቱም ባሕርያዊ ስለሆነ ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ አለ፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፲፯

"ሲቀርብም ከተማዪቱን አይቶ አለቀሰላት" (ሉቃ.፲፱፥፵፩)፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ለከተማይቱ አለቀሰላት ተብሏል፡፡ በከተማይቱ ለሚኖሩ ሰዎች አለቀሰላቸው ማለት ነው እንጂ ለቦታው ማለት አይደለም፡፡ በስመ ኀዳሪ ይጼዋዕ ማኅደር፣ ወበስመ ማኅደር ይጼዋዕ ኀዳሪ እንዲል (በማደሪያው አዳሪውን፣ በአዳሪው ማደሪያውን መናገር ልማድ ነውና)፡፡ የሚያለቅስ፣ የሚያዝን፣ የሚደክም ሥጋን ስለተዋሐደ ስለ ጌታ ብዙ ቦታ ላይ አለቀሰ፣ አዘነ፣ ደከመ እየተባለ ተጽፏል፡፡ በማልቀሱ ልቅሷችንን ያርቅልን ዘንድ አለቀሰ፡፡ በኀዘኑ ኃዘናችንን ያርቅልን

ዘንድ አዘነ:: በድካሙ ድካማችንን ያርቅልን ዘንድ በተዋሐደው ሥጋ ደከመ:: አዳም እግዚአብሔርን በበደለ ጊዜና ከገነት በተባረረ ጊዜ መሪር ኀዘንን አዝኖ ነበር:: ጌታም ለካሣ (አዳምን ለመካሥ) ብዙ ቦታ ላይ አለቀሰ አዘነ እየተባለ ተገልጿል::

### ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺፲፰

"አባቴ እኔን እንደ ሾመኝ እኔ ደግሞ በመንግሥቴ__ (ሉቃ.፳፪፥፳፱):: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን አባቴ ሾመኝ ብሎ ተናገረ? መሾም ማለትስ ምን ማለት ነው?:: መድኃኔዓለም ይህን የተናገረው ስለሰውነቱ ነው:: የጸጋ ንጉሥ ብቻ የነበረ ሰውነት ቃልን በተዋሐደ ጊዜ የባሕርይ ንጉሥ ሆኗል:: ይህም የሆነ ጌታ በተጸነሰ ጊዜ መጋቢት ፳፱ ቀን በዕለተ እሑድ በዕለተ ትስብእት ነው:: ፍጡራን ንጉሥ ቢሆኑ፣ ንጉሥ ቢባሉ መንግሥትነታቸው ከፈጣሪ የተሰጠ ነው:: አንበሳን ንጉሠ ለአራዊት ይሉታል:: ንስርን ንጉሠ ለአዕዋፋት ይሉታል:: አጋዘንን ንጉሠ ለእንስሳት ይሉታል:: የኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥትነት ግን የባሕርይ መንግሥትነት ነው:: አባቴ ሾመኝ ማለቱ ስለ ሥጋ እንግድነት የተነገረ ነው:: ይኸውም ሥጋ አምላክ እንድሆን አደረገኝ ማለቱ ነው:: ይህም የአብ ብቻ ግብር አይደለም:: ሥልጣናዊ ግብር ስለሆነ አብ ቢጠቀስም የወልድም የመንፈስ ቅዱስም ሥራ ነው::

### ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺፲፱

"በዚያን ሰዓት ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐሤት አደረገ" (ሉቃ. ፲፥፳፩):: እግዚአብሔር የደስታ ምንጭ ነው:: ራሱም ደስታ ነው:: እግዚአብሔር ፍቅር ነው ባልነው አግባብ ደስታ ነው እንለዋለን:: አብ ወልድን ይወደዋል፣ ወልድም አብን ይወደዋል:: ስንል በፍቅር አንድ ስለሆኑ ነው:: ሦስቱ አካላት በአንዲት ፍቅር ይኖራሉ:: ስለዚህም እግዚአብሔር ፍቅር ነው ይባላል:: በዚህ አግባብ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐሴት አደረገ (ተደሰተ) ተብሎ ተገልጿል:: በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አብ በአንተ ደስ ይለኛል ብሎ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሮ ነበር (ሉቃ. ፫፥፳፪):: ይህ ደስታ ሦስቱም አካላት አንድ የሚሆኑበት ደስታ ነው እንጂ ለአንዱ ብቻ ወይም ለሁለቱ ብቻ የሆነ አይደለም:: ለእግዚአብሔር ባሕርይ የሚስማማ ደስታ ነው:: እግዚአብሔር በባሕርይው አያዝንም፣ አይጸጸትም:: ምናልባት አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ ተጸጸተ፣ አዘነ እየተባለ መገለጹ እንኳ ከሰው መታሰብ በላይ የሆነውን እግዚአብሔር በሰውኛ እንድንረዳው የተጻፈ እንጂ የሆነውን አይደለም:: ለምሳሌ ሳኦልን በማንገሤ ተጸጸትኩ ብሏል:: እግዚአብሔር አስቀድሞ ሁሉን የሚያውቅ ስለሆነ አይጸጸትም:: ታዲያ ለምን ተጸጸተ አለ ከተባለ ለመልካም አብነት አድርጌ ባነግሠው ለክፉ ሆነ ማለቱ ነው:: ይህንን ለእኛ ቅርብ በሆነ አማርኛ እንድንረዳው ተጸጸተ ተብሎ ተገልጿል::

### ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፺፳

"ይህንም ሲናገር፥ ከሕዝቡ አንዲት ሴት ድምጿን ከፍ አድርጋ፦ የተሸከመችኽ ማሕፀንና የጠባኻቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው:: ርሱ ግን፦ አዎን፥ ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው አለ" (ሉቃ. ፲፩፥፳፯-፳፰):: በዚህ በአንዱ ቃል ጌታ ሁለት መልእክት አስተላልፏል:: ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው ብሏል::

በዚህ አገላለጹ የተሸከመችህ ማሕፀንና የጠባኻቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው የሚለውን ቃልም እንዳጸናው እንረዳለን:: "ስ" በዚህ አገላለጽ አፍራሽ አይደለም:: ምክንያቱም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም የእግዚአብሔርን ቃል ሰምታ የምትጠብቅ በመሆኗ ከብፁዕነቷ አልወጣችምና ነው:: "እናቱ (ማርያም) ግን ይህን ሁሉ ነገር ትጠብቀው፣ በልቧም ታኖረው ነበር" ተብሎ ተገልጿልና (ሉቃ. ፪፣፶፩):: ይህ ከሆነ ከላይ ያለውን ቃል ጌታ የተናገረው ድንግል ማርያም ብፅዕት አይደለችም ለማለት የተናገረው እንዳልሆነ እንረዳለን:: በሌላ አገላለጽ ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው ብሎ "ስ" አፍራሽ ሆኖ ይገኛል:: ይኸውም በትርጓሜ ወንጌል እንደተገለጸው ይህች ሴት ብፁዕ ብለው ብፅዕት ይለኛል ብላ መጥታ ነበርና ጌታ የልቡናዋን አውቆ ብፁዓንስ ቃለ እግዚአብሔር ወንጌልን ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው ብሏታል::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፳፩

"ኢየሱስም፦ አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ" (ሉቃ. ፳፫፣፴፬):: ወልደ እግዚአብሔር ሰው የሆነበት ዋነኛ ምክንያት በበደሉ ምክንያት የጠፋውን ሰው ለማዳን ነው:: በዚህ ሰውን የማዳን ሂደት ውስጥ ጌታ በዚህ ምድር ያደረጋቸው ድርጊቶችን ጠቅለል አድርገን ብናያቸው ሦስት ናቸው::

፩) የቤዛነት ሥራ

፪) አጽድቆተ ትስብእቱ፣ አግሕዶ መለኮቱ

፫) መካሥ

ናቸው:: አንዳንድ ጊዜ ተራበ፣ ተጠማ ሲል ብናገኘው ሰው እንደሆነ እንድንረዳ ነው:: አንዳንድ ጊዜ የተራቡትን አጠገበ፣ የታመሙትን ፈወሰ፣ ኃጢአትን ይቅር አለ ሲል ብናገኘው ደግሞ አምላክ መሆኑን እንድንረዳ ነው:: የቤዛነት ሥራ የምንለው ደግሞ አዳም ሊያደርገው ይገባ የነበረውን ሥራ ስለ አዳም እርሱ ማድረጉን ነው:: "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ብሎ ጌታ ኢየሱስ ለሰው ልጅ ሁሉ ይቅርታን ለምኗል:: ይህ የቤዛነት ሥራ ነው:: ይቅርታውን መቀበል ግን የአባቱም፣ የእርሱም፣ የመንፈስ ቅዱስም የአንድነት ሥራ ነው:: ይቅርታን መለመን ግን በተለየ አካሉ የወልድ ነው:: ይኸውም በተለየ አካሉ ሥጋን የተዋሐደ ወልድ ስለሆነ እንደሰውነቱ ይቅርታን ለመነ እንላለን:: ካሣ የሚባለው አዳም ከገነት እንደተሰደደ እርሱም ለካሣነት ወደ ግብፅ መሰደዱ ነው:: አዳም እንደፈራ እርሱም ለካሣነት መፍራቱ ነው:: ይህንና ይህን የመሰሉ ድርጊቶች ካሣነት ይባላሉ::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፳፪

"እኔ ግን እምነትኽ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድኹ አንተም በተመለስኽ ጊዜ ወንድሞችኽን አጽና አለ" (ሉቃ. ፳፪፣፴፪):: ማማለድ ማለት መለመን ማለት ነው:: ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፳፩ ላይ እንደተገለጸው ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር ከሠራቸው ሥራዎች አንዱ የመለመን (የማማለድ) ሥራ ነው:: ይኸውም ከቤዛነት ሥራዎቹ አንዱ ነው:: አዳም በበደሉ ምክንያት

ከእግዚአብሔር ፊት መቆም የማይችል ቢሆንም ንጹሐ ባሕርይ ሊቀ ካህናታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ለአዳም ቤዛ ሆኖ ስለአዳም ለምኗል። ወሰአልኩ በእንቲኣክሙ ከመ ኢይድክም ሃይማኖትክሙ ብሎ በጴጥሮስ አንጻር ይናገር እንጂ ለሰው ሁሉ የተነገረ መሆኑን ልብ ማድረግ ያስፈልጋል። ቤዛነት በተለየ አካሉ ለወልድ ይነገራል። ይኸውም በተዋሐደው ሥጋ ነው። ስለዚህ እኛን ለማዳን እስከ ዕለተ ስቅለቱ ድረስ ስለእኛ ለምኗል (አማልዷል)። የቤዛነት ሥራውን ጨርሶ ከሙታን መካከል ከተነሣ በኋላ፣ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ግን የማማለድ ሥራ የለበትም። ስለዚህ ከትንሣኤ በኋላ ያማልዳል አንለውም። ሰው ከሆነበት ጀምሮ እስከ ዕለተ ሰቅለት ግን አማልዶናል። በዚህም ሂደት ምልጃን ማቅረብ ሰው ስለሆነ የእርሱ ሥራ ቢሆንም ምልጃውን መቀበል ግን የእርሱ የራሱ የኢየሱስ ክርስቶስም፣ የአብም፣ የመንፈስ ቅዱስም የአንድነት ሥራ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፳፫

"ኢየሱስም፦ እውነት እልኻለኹ፥ ዛሬ ከእኔ ጋራ በገነት ትኾናለኽ አለው" (ሉቃ. ፳፫፣፵፫)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደመሆኑ ፈያታዊ ዘየማንን (በቀኙ በኩል የተሰቀለውን ወንበዴ) ዛሬ ከእኔ ጋራ በገነት ትኖራለህ ብሎታል። ስለሰማዩ ሕይወት በእርግጠኝነት መናገር የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም አምላክ ስለሆነ በእርግጠኝነት ፈያታዊን ዛሬ ከእኔ ጋራ በገነት ትሆናለህ ብሎታል። በኃጥአን ፍዳን የሚያመጣ፣ ለጻድቃን ገነት መንግሥተ ሰማያትን የሚሰጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ፈያታዊ ዘየማን የተነሣሕያን አብነት ነው። ወንበዴው ኃጢአቱን ታምኖ የኢየሱስ ክርስቶስን ንጽሕና መናገሩ ገነትን እንዲያገኝ አድርጎታል። እኛም ምንም ያህል በደለኞች ብንሆን ንሥሓ ገብተን ስለኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ስንናገር ገነት መንግሥተ ሰማያትን እናገኛለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፳፬

"ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ፦ አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅኽ ዐደራ እሰጣለኹ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ" (ሉቃ. ፳፫፣፵፮)። ነፍሴን በእጅህ አደራ እስጣለሁ ማለት ምን ማለት ነው? እጅ ብዙ ጊዜ ሥልጣን ተብሎ ይተረጎማል። ስለዚህ ሰሚው አብ ሆኖ አብ ነፍሴን በሥልጣንህ ከሥጋዬ እለያለሁ ማለቱ ነው። ከዚህ ላይ በደንብ ማስተዋል የሚገባን ነፍስን ከሥጋ የመለየት ሥልጣን የአብ ብቻ እንዳይመስለን እንጠንቀቅ። የአንዱ ስም ቢጠቀስም ሁለቱም እንዳሉበት መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህንን የሚያስረዳን ኃይለ ቃል በዮሐ. ፲፣፲፰ ያለው ቃል ነው። ራሱ ወልድ "እኔ በፈቃዴ አኖራታለኹ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ" ብሏልና። ይህንን አይተን ደግሞ ነፍስን ከሥጋ መለየት የወልድ ሥራ ብቻ እንዳይመስለን። በአንድነት በሚሠሩት ሥራ አንዱ ቢጠቀስንኳ ሁለቱም እንዳሉበት መገንዘብ ያስፈልጋል

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፳፭

"ሲባርካቸውም ከነርሱ ተለየ ወደ ሰማይም ዐረገ" (ሉቃ. ፳፬፣፶፩)። ኢየሱስ ክርስቶስ በሁሉ ቦታ ያለ ነው። በሁሉ ቦታ ያለ አካል ደግሞ ወረደ፣ ዐረገ፣ ወጣ የሚሉት ቃላት አይስማሙትም።

ታዲያ ወልደ እግዚአብሔር ከሰማየ ሰማያት ወረደ ስንል ምን ማለታችን ነው? ዐረገ ማለታችንስ ምን ማለት ነው:: ወረደ ማለት ሰው ሆነ ማለት ነው:: እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ለቃል ርደት፣ ለሥጋ ዕርገት ምክንያት የሆነች እንላታለን:: ለቃል ርደት ማለት ለአምላክ ሰው መሆን ማለት ነው:: ለሥጋ ዕርገት ማለት ለሰው አምላክ መሆን ማለት ነው:: ዕርገት ሁለት ነው:: አንደኛው መጋቢት ፳፱ ጌታ የተጸነሰ ጊዜ ነው:: ያን ጊዜ ቃል በሥጋ በማኅፀን ሲወሰን፣ ሥጋ ደግሞ በቃል በኪሩቤል ጀርባ ተቀምጧል:: ግዙፉ ሥጋ በቃል ግዘፉን ሳይለቅ ረቂቅ ሆኗል:: ስለዚህም ይህ ዕርገት የርኀቀት ያይደለ የርቀት ዕርገት ነው:: ሁለተኛው ዕርገት ከትንሣኤ በአርባኛው ቀን ያረገው ዕርገት ነው:: ቃል ሥጋን ገንዘቡ አድርጎ በሥጋ የርቀት ያይደለ የርኀቀት ዕርገት ያረገው ዕርገት ነው:: ወእንዘ ይባርኮሙ ተረንቀሙ እንዲል::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፳፮

"በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ:: ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ" (ዮሐ. ፩፣፩-፪):: ምሥጢረ ሥላሴ ከተገለጠባቸው ጥቅሶች አንዱ ይህ ነው:: ቃል የወልደ እግዚአብሔር የከዊን ስሙ ነው:: ቃል የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ይህ ቃል እግዚአብሔር ነበር ብሎ የኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔርነት ይነግረናል:: በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ብሎ ደግሞ አብ በወልድ፣ ወልድ በአብ ህልው ሆነው እንደሚኖሩ ነገረን:: ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ብሎ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን ይገልጻል:: ለብዙ ከሓድያን የራስ ምታት የሚሆነው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው:: ቃል የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ የምናውቀው ያም ቃል ሥጋ ሆነ ተብሎ ሥጋን መዋሐዱን ዝቅ ብሎ በመናገሩ ነው (ዮሐ. ፩፣፲፬):: አብ በወልድም በመንፈስ ቅዱስም ህልው ነው:: ወልድ በአብም በመንፈስ ቅዱስም ህልው ነው:: መንፈስ ቅዱስ በአብም በወልድም ህልው ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፳፯

"ሁሉ በርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለርሱ አልሆነም" (ዮሐ. ፩፣፫):: የቃል ህልውና ከማርያም ወዲህ ነው ብሎ የተናገረ ፎጢኖስ የሚባል ከሓዲ በዚህ ቃል ይሸነፋል:: ህልውናው ከማርያም ወዲህ የሚጀምር ከሆነ ሁሉ በእርሱ የሆነ አምላክ መሆን አይችልምና:: አብ እርሱን ፈጥሮ ፈጠረበት ያለ አርዮስ ደግሞ "ያለ እርሱ ምንም ምን የሆነ የለም" በሚለው ኃይለ ቃል ይረታል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሰማይንና ምድርን እንዲሁም በውስጣቸው ያሉ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ አምላክ ነው:: የእርሱ ፈጣሪነት የባሕርይው ነው:: በሥላሴ ዘንድ አንዱ ፈጣሪ ሌላው ተፈጣሪ የሆነ የለም:: ሦስቱም አካላት በአንድነት ፈጣርያን ይባላሉ እንጂ:: በመፍጠርም አንዱ ከሌላው አይበልጥም:: በአንድ ህልውና፣ በአንድ ባሕርይ የሚኖሩ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር አንድ ናቸውና:: ከላይ ካለው ጥቅስ ሁሉ በእርሱ ሆነ ተብሎ የተገለጸው ወልድ ቢሆንም ይህ ባሕርያዊ ሥራ ስለሆነ ለሁለቱም ማለትም ለአብም ለመንፈስ ቅዱስም ቢነገር ይሆናል:: በባሕርያዊ ግብር አንዱ ቢጠቅስም ሁለቱም አሉበትና::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፳፰

"በዓለም ነበረ ዓለሙም በእርሱ ሆነ ዓለሙ ግን አላወቀውም" (ዮሐ. ፩፥፲)። እግዚአብሔር በዓለም መልቶ ይኖራል። በዓለም መልቶ ሲኖር ግን በባሕርይው የማይታይ፣ ረቂቅ አካል ያለው በመሆኑ ታይቶ አይታወቅም። በእምነት እናውቀዋለን እንጂ በስሜት ሕዋሳታችን ተመራምረን ደርሰንበት አናውቀውም። ዓለም በዓለምነቱ ጸንቶ የሚኖረው በእርሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ "ዓለሙም በእርሱ ሆነ" ተብሏል። በሌላ አገላለጽ "ዓለሙ ግን አላወቀውም" ማለት በአጭር ቁመት፣ በጠባብ ደረት ተወስኖ ወልደ እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ዓለሙ አምላክነቱን ሳይረዳ መቅረቱን ያመለክታል። ጌታ ኢየሱስ ለብዙዎች ዕሩቅ ብእሲ (ሰው ብቻ) እየመሰላቸው ሲሳሳቱ ይስተዋላል። አይሁድም ጌታን እስከመስቀል የደረሱት አምላክነቱን ቢነግራቸው ሰውነቱን እያዩ ለማመን በመቸገራቸው ነበረ። አምላክም ሰውም መሆኑን መረዳት አልቻሉም ነበር። አሁንም ቢሆን አምላክነቱን ዘንግተው ነቢይ ብቻ ነው ብለው የሚናገሩና ባለማወቅ ጸንተው ያሉ ብዙ ናቸው። እንግድህ ምን እንላለን። እግዚአብሔር ልቡና ይስጣቸው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፳፱

"ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ ዐደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን" (ዮሐ. ፩፥፲፬)። ከላይ ቃልም እግዚአብሔር ነበር ብሎ ነበር። አሁን ደግሞ ይህ ቃል ሥጋ እንደሆነ እየተናገረ ነው። እግዚአብሔር የማይለወጥ አምላክ እንደሆነ በትንቢተ ሚልክያስ "እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም" ብሎ ነግሮናል (ሚል. ፫፥፮)። ስለዚህ ቃል ሥጋ ሆነ ሲል እግዚአብሔርነቱን ሳይለቅ ነው ማለት ነው። ቃል ቃልነቱን ሳይለቅ ሥጋ ሆነ ማለት ሰው ሆነ። ሆነ፣ አደረ የሚሉት ቃላት ሰው ሆነ ተብለው ይተረጎማሉ። አምላክ ሰው ሲሆን ሰው አምላክ ሆነ። አብና ወልድ በክብር አንድ ናቸው። ስለዚህ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየንለት ተብሎ ተገልጿል። ቃል ሥጋ ሲሆን የቃል ገንዘብ ለሥጋ፣ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ሆኗል። ቅዱስ ቄርሎስ "እንቲኣሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ፣ ወእንቲኣሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል" ብሎ እንደተናገረው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፴

"ዮሐንስ ስለእርሱ መሰከረ እንዲህም ብሎ ጮኸ፦ ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ከእኔ በፊት ነበረና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኗል ስለእርሱ ያልኹት ይህ ነበረ" (ዮሐ. ፩፥፲፭)። መጥምቁ ዮሐንስ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰውነቱም ስለአምላክነቱም በአንድ ቃል ተናግሯል። ይኸውም "ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ" ብሎ ስለሰውነቱ ተናግሯል። ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ዮሐንስ መጥምቅ ከተወለደ በኋላ ተወልዷልና። ዮሐንስ ኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ ስድስት ወር ይቀድመዋልና። በመቀጠል "እርሱ ከእኔ በፊት ነበርና" ብሎ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ተናገረ። ጌታ በአምላክነቱ ከፍጠረታት ሁሉ ቀድሞ የነበረ ነውና። አንዳንዶች ጌታ ከድንግል ማርያም ከተወለደ እርሷ አስቀድማ ነበረች አይደል እንዴት ከፍጥረታት ሁሉ በፊት ነበረ እንላለን ብለው ይጠይቃሉ። ድንግል ማርያም ከጌታ በፊት የነበረችው በሥጋ ነው እንጂ በአምላክነቱማ እርሷን ጨምሮ የፈጠራትና እናቱ ያደረጋት እርሱ መሆኑን መገንዘብ

ያስፈልጋል:: "ድንግል ወለደቶ ለገባሪሃ ወውእቱኒ ፈጠረ ወላዲቶ" እንዲል ማር ኤፍሬም በሃይማኖተ አበው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፩

"የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" (ዮሐ. ፩፥፳፱):: ይህ ቃል ዘርፍና ባለቤት አንድ የሆኑበት አነጋገር ነው:: ከዚህ ቀደም ለምሳሌ ውዳሴ ማርያም ስንል ማርያም የውዳሴ ዘርፍ ነው እንል ነበር:: ውዳሴ ሌላ ነው ማርያም ሌላ ናት:: የማርያም ምስጋና ስንል ምስጋና ማርያም አይደለም:: ማርያምም ምስጋና አይደለችም:: ከላይ ባለው ኃይለ ቃል ግን በትርጉም ዘርፉ ባለቤት፣ ባለቤቱ ዘርፍ ሆኖ ይመጣል:: የእግዚአብሔር በግ ሲል ስለአዳም መሥዋዕት ሆኖ የመጣው በጉ ራሱ እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር የተባለውም በጉ ነው:: መሥዋዕቱ እርሱ ነው:: መሥዋዕቱን ተቀባይም ራሱ ነው:: መሥዋዕት አቅራቢውም ራሱ ነው:: የራሱን ሥጋና ደም በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ የሠዋ ሊቀ ካህናታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በመሥዋዕቱም ዓለምን ሁሉ አድኗል:: "የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ" የተባለው ለዚህ ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፪

"ኢየሱስም መልሶ፦ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለኹ አላቸው:: ስለዚህ፥ አይሁድ፦ ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፥ አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለኽን አሉት:: ርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር:: ስለዚህ፥ ከሙታን ከተነሣ በኋላ፥ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ ዐሰቡና፥ መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ" (ዮሐ. ፪፥፲፱-፳፪):: ጌታ ከሙታን መካከል የሚነሣው በራሱ ሥልጣን እንደሆነ የተናገረበት አንቀጽ ይህ ነው:: በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣም ያስተማረን እርሱ ነው:: ጌታ ስለሰውነቱ እየተናገረ አይሁድ ግን ባለመረዳት ስለቤተመቅደስ ነው ብለው በራሳቸው ትርጉም ተሸውደው ነበር:: ደቀመዛሙርቱ እንኳ ይህ ንግግር የገባቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን መካከል ከተነሣ በኋላ ነው:: በክርስትና አስተምህሮ ከሞት በኋላ ትንሣኤ እንዳለ ማስረጃችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ሌሎች ቤተ እምነቶች ግን ማስረጃ ሳይኖራቸው በግምት ትንሣኤ እንዳለ ይናገራሉ::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፫

"በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና" (ዮሐ. ፪፥፳፭):: የኢየሱስ ክርስቶስ ዕውቀት የባሕርይ ዕውቀት ነው:: ስለዚህ ከእርሱ የሚሰወር፣ እርሱ የማያውቀው ዕውቀት የለም:: የሰውን ልብ የፈጠረ እርሱ በሰው ልብ ያለውን ማወቁ ብዙም አያስገርምም:: ጌታ እስከ ዕለተ ምጽአት የሚነሣውን ሰው ልብ የሚያውቀው ገና ሳይፈጥረው ጀምሮ ነው:: እግዚአብሔር በየዘመኑ አዳዲስ ዕውቀትን ያውቃል አንልም:: ዕውቀቱ የባሕርይ ስለሆነ በዘመን ብዛት አይጨምርም:: በዘመን ብዛትም አይቀንስም:: ፍጡራን ሰው ያሰበውን ቢናገሩና ቢያውቁ እግዚአብሔር በገለጠላቸው መጠን ነው:: ስለዚህ ዕውቀታቸው የጸጋ ነው:: ኢየሱስ የሰውን ልብ ያውቅ የነበረው ግን ከሌላ ባገኘው ጸጋ አይደለም:: እርሱ ራሱ ወሀቤ ጸጋ (ጸጋን የሚያድል) ዕውቀት የባሕርይው የሆነ ነውና::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፴፬

"ከሰማይም ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፥ ርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው" (ዮሐ. ፫፥፲፫)። ወልደ እግዚአብሔር ሥጋን ከሰማይ ይዞ አልወረደም። ሥጋን ከድንግል ማርያም ነሥቶ ተዋሐደው እንጂ። ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ የለም። ይኸውም የሰው ልጅ ነው ብሏል። ይህንን ቃል በጥንቃቄ ማየት መልካም ነው። ከሰማይ ወረደ የተባለ ወልደ እግዚአብሔር ነው። ከዚህ ላይ ግን ወልደ እጓለ እመሕያው ነው እያለን ነው። ለዚህ ቃል አንክሮ ይገባል። ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋ በቃል ርስት ይጠራል። ቃልም በሥጋ ርስት ይጠራል። ተዋሕዶው ፍጹም ነውና። ስለዚህ ወልደ እጓለ እመሕያው ወልደ እግዚአብሔር ስለሆነ በቃል ርስት ከሰማይ ወረደ ተብሏል። በሌላ አገላለጽ ወልደ እግዚአብሔር በሥጋ ርስት ወደ ሰማይ ዐረገ ተባለ። ከሰማይ የወረደውም ወደ ሰማይ ያረገውም አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ልብ እናድርግ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፴፭

"በርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና" (ዮሐ. ፫፥፲፮)። ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ቦታ ላይ የእግዚአብሔር ልጅ (ወልደ እግዚአብሔር) እየተባለ ተጠርቷል። እና ብዙዎች ይህንንማ እኛስ ተጠምቀን የእግዚአብሔር ልጆች እንባል የለምን? የእግዚአብሔር ልጆች ብንባልም ግን እግዚአብሔር አይደለንም ብለው ይናገራሉ። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስንም የእግዚአብሔር ልጅ ያለው በዚህ አግባብ ነው ብለው ክሕደታቸውን ያስተላልፋሉ። ነገር ግን ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ የምንለው የአብ የባሕርይ ልጅ በመሆኑ ነው። ለዚህም ምስክሩ "አንድያ" ተብሎ መገለጹ ነው። ልጅነቱ እንደእኛ የጸጋ ቢሆን ኖሮስ አንድያ ልጁን ተብሎ ባልተገለጸ ነበር። ደግሞ እርሱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመሆኑ እንድናምንበት ተጽፏል። በእርሱ ስናምንም የዘለዓለም ሕይወትን እንደምናገኝ ተጽፏል። በፍጡር ማመን የዘለዓለም ሕይወትን አያስገኝም። በፈጣሪ ማመን ግን ዘለዓለማዊ ሕይወትን ያስገኛል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፴፮

"ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በርሱ አመኑ" (ዮሐ. ፪፥፲፩)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተአምረ ኢየሱስ እንደተገለጠው ከሕፃንነቱ ጀምሮ ታላላቅ ተአምራትን እየሠራ መጥቷል። ጭቃን ወፍ ሲያደርግ እንደነበረ ተጽፏል። ወደ ግብፅ በተሰደደ ጊዜም የፈያታዊውን የተሰባበረ ሰይፍ ወደቀድሞው መልሶለታል። ውሃን በልብሱ ቋጥሮ ለእናቱ ለቅድስት ድንግል ማርያም ይዞላት ይሄድ እንደነበረ ሁሉ ተጽፏል። ይህ ከሆነ የምልክቶችን መጀመሪያ በቃና ዘገሊላ አደረገ ለምን አለ? ወንበር ተክሎ ደቀመዛሙርትን ማስተማር ከጀመረ ወዲህ ያደረገው የመጀመሪያው ተአምር ስለሆነ ቀዳሜ ተአምር ብሎታል። "ክብሩንም ገለጠ" ማለቱም ለተከተሉት ደቀመዛሙርት አምላክነቱን አሳወቃቸው ማለት ነው። ለዚህም ምስክሩ ደቀመዛሙርቱም በእርሱ አመኑ ተብሎ መገለጹ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፯

"አባት ልጁን ይወዳል ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል። በልጁ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም" (ዮሐ. ፫፥፴፭-፴፮)። በተዋሕዶ ሥጋ በቃል ርስት የአብ ልጅ ተብሏል። ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል መባሉም ሥጋ በተዋሕዶ አምላክነትን ገንዘብ ማድረጉን ያመለክታል። አባት ልጁን ይወዳል። ልጅም አባቱን ይወዳል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው ማለት ይህ ነው። ሦስቱ አካላት በአንድ ህልውና፣ በአንድ ፍቅር፣ በአንድ መለኮት፣ በአንድ ባሕርይ ይኖራሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) አይደለም። አምላክም ሰውም የሆነ አንድ ልጅ (ወልድ ዋሕድ) ነው እንጂ። ስለዚህ አምላክ እንደመሆኑ እናምነዋለን። በፍጡር ማመን ኃጢአት ነው። ክርስቶስ ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ቢሆን ኖሮ አናምንበትም ነበር። ነገር ግን የአብ አንድያ ልጅ የሆነ አምላክ ወልደ አምላክ ስለሆነ እናምነዋለን። እርሱን በማመናችንም የዘለዓለም ሕይወትን እናገኛለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፰

"እግዚአብሔር መንፈስ ነው" (ዮሐ. ፬፥፳፬)። እግዚአብሔር መንፈስ ነው ማለት ረቂቅ ነው ማለታችን ነው። የርቀት ደረጃዎች አሉ። ከጠጣር ነገር ፈሳሽ ይረቃል፣ ከፈሳሽ ነገር አየር ይረቃል። ለምሳሌ ከድንጋይ ውሃ ይረቃል፣ ከውሃ ነፋስ ይረቃል። ከነፋስ ብርሃን ይረቃል (ይህ እንደ መለኪያችን ይለያያል። በመታየት ከሆነ ነፋስ ከብርሃን ይረቃል። በመያዝ ከሆነ ግን ብርሃን ከነፋስ ይረቃል። ምክንያቱም ብርሃን ብርጭቆን አልፎ ማብራት ይችላል። ውሃ ግን በብርጭቆ ይወሰናልና ነው)። ከብርሃን ነፍስ ትረቃለች። ብርሃንን የብረት ግድግዳ አያሳልፈውም። ነፍስን ግን ምንም ነገር አያግዳትምና ነው። ከነፍስ መላእክት ይረቃሉ። ከመላእክትም ከፍጥረታትም ሁሉ ደግሞ ከመታሰብ በላይ የሆነው እግዚአብሔር ይረቃል። እርሱ ፍጹም ረቂቅ ነው። ስለዚህ ይህንን ረቂቅነቱን ለመግለጽ መንፈስ ነው እንለዋለን። እግዚአብሔር ረቂቅ ቢሆንም በፍጡራኑ ይታወቅ ዘንድ በዘፈቀደ (እርሱ በወዱው) በዘይክሉ (ፍጡራን ሊያዩት በሚችሉት መጠን) ይገለጣል። ለአብርሃም በሦስት ሰዎች አምሳል። ለተለያዩ ነቢያት በተለያየ አምሳል ተገልጧልና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፱

"ኢየሱስ ይህን ሰው ተኝቶ ባየ ጊዜ፥ እስከ አሁን ብዙ ዘመን እንዲሁ እንደ ነበረ ዐውቆ፦ ልትድን ትወዳለህን አለው" (ዮሐ. ፭፥፮)። መጻጉዕ መዳን እንደሚፈልግ አስቀድሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ያውቃል። ነገር ግን ምን እንደሚመልስለት እያወቀ "ልትድን ትወዳለህን?" ብሎታል። ምክንያቱም ምንም የመጻጉዕን ፈቃድ ቢያውቅ ኢየሱስ የነጻነት አምላክ በመሆኑ አስገድዶ ያለ ሰውየው ፈቃድ አያድንምና ነው። የእያንዳንዳችንን ፈቃድ አስቀድሞ ያውቃል። ሰው እንደመሆናችን የሚያስፈልገንን ነገር ይሰጠናል። የምንፈልገው ልዩ ነገር ካለም ያንን ነገር እንደምንፈልግ አስቀድሞ ያውቃል። ነገር ግን እኛም የምንፈልገውን በጸሎት መጠየቅ ይገባናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ማንኛውንም ዓይነት በሽታ ማራቅ የሚችል አምላክ ነው። ስለዚህም ሠላሳ ስምንት አመት ታሞ አልጋ ላይ ተኝቶ ይኖር የነበረውን መጻጉዕን ፈውሶታል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፭

"እንግዲህ ሰንበትን ስለ ሻረ ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን፥ ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋራ አስተካክሎ፦ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስለ አለ፥ ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር" (ዮሐ. ፭፥፲፰)። አይሁድ ትልቁ ችግራቸው ይህ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑን ሲነግራቸውና አምላክነቱን በተለያዩ እግዚአብሔራዊ ሥራዎች እየገለጸላቸው እነርሱ ግን ላለመቀበል ኀሊናቸውን ይዘጉ ነበር። እርሱም አምላክ እንደመሆኑ "አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለኹ ብሎ መለሰላቸው" አለ (ዮሐ. ፭፥፲፯)። ይህን ሲሰሙ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካከለ ብለው ሊገድሉት ሳይቀር ይፈልጉ ነበር። ሰውነቱን አይተው እግዚአብሔርነቱን ቢነግራቸው አልቀበልም አሉ። ሰውም አምላክም እንደሆነ ማወቅ ቢሳናቸው ሊገድሉት ፈለጉ። አሁንም ብዙዎች እግዚአብሔርነቱን ባለማመን ዕሩቅ ብእሲ (ሰው ብቻ) መስሏቸው ከነቢያት አንዱ ነው ብለው ይናገራሉ። እርሱው ጌታ እውነታውን ይግለጥላቸው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፮

"ስለዚህ፥ ኢየሱስ መለሰ፥ እንዲህም አላቸው፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና። አብ ወልድን ይወዳልና፥ የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል። አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፥ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል" (ዮሐ. ፭፥፲፱-፳፩)። ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም ማለት ከራሱ ብቻ አንቅቶ ምንም ሥራ አይሠራም ማለት ነው። አብ ሲያደርግ ያየውን ያደርጋል እንጂ ማለትም አብ በህልውና የሠራውን ወልድም በህልውና ይሠራዋል ማለት ነው። ሙታንን የማስነሣት፣ ሕይወትን የመስጠት ሥልጣን የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ የአንድነት ሥራቸው ነው። በአንድነት ሥራቸው የአንዱ ስም ቢጠቀስም እንኳ አንዱ ብቻውን እንደሠራው ሊታሰብ አይገባም። የአንድነት ሥራቸው ስለሆነ የሦስቱም መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ወልድ ከራሱ ምንም ማድረግ አይችልም የተባለው ከራሱ ብቻ ምንም ማድረግ አይችልም ማለት ነው። ይኸውም ሥራውን ሁሉ የሚሠራው ሦስቱ አካላት በአንድ ባሕርይ ተገናዝበው እንደሆነ ለማስረዳት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፲፯

"ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ ባንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም" (ዮሐ. ፭፥፳፪)። አብ ምውታነ ሥጋን እንደሚያስነሳቸው ወልድም የወደደውን ያድነዋል። አብ በአንድ ሰውስ እንኳ አይፈርድም ሲል የመፍረድ ሥልጣን የለውም ማለት አይደለም። ፈታሒነት (በእውነት መፍረድ) የአብ የባሕርይ ገንዘቡ ነውና። ስለዚህ አብ በአንድ ሰውስ እንኳ አይፈርድም ማለቱ ተገልጾ ለሰው ታይቶ በማንም አይፈርድም ማለት ነው። ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ ማለትም በሥጋ ተገልጾ መፍረድን ለልጁ ገንዘብ አደረገለት ማለት ነው። በዚህ አግባብ ሰጪ ተደርጎ የቀረበውና ስሙ

የተጠቀሰው አብ ቢሆንም በባሕርያዊ ሥራ የአንዱ ስም ቢጠቀስም ሁለቱም ስላሉበት ሥጋ አምላካዊ ፍርድን፣ አምላክነትን ገንዘብ ያደረገው በሦስቱም የአንድነት ሥልጣን መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፴፫

"ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም" (ዮሐ. ፭፥፳፫)። ወልድን የአብ ልጅ ነው ብሎ የማያከብር፣ የላከው አብንም ወላዲ ነው ብሎ አያከብረውም። አባት የሌለው ልጅ፣ ልጅ የሌለው አባት የለምና። ወልድን ማክበር ማለትም ትእዛዛቱን መጠበቅ ነው። ለሦስቱ አካላት ማለትም ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ የሚቀርበው ምስጋና አንድ ነው። አንዱን ማክበር ሌላውንም ማክበር መሆኑን መዘንጋት አይገባም። አብን ማመስገን ወልድን መንፈስ ቅዱስን ማመስገን ነው። ወልድን ማመስገን አብን መንፈስ ቅዱስን ማመስገን ነው። መንፈስ ቅዱስን ማመስገን አብን ወልድን ማመስገን ነው። በአንጻሩ አብን አለማክበር ወልድን መንፈስ ቅዱስን አለማክበር ነው። ወልድን አለማክበር አብን መንፈስ ቅዱስን አለማክበር ነው። መንፈስ ቅዱስን አለማክበር አብን ወልድን አለማክበር ነው። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም የተባለው ለዚህ ነው። "የላከውን" የሚለው አገላለጽ ሰው እንዲሆን ያደረገውን ማለት ነው። ይኸውም ፈቃደ አብ ነው። እንዲህ ስላልን ግን የአብ ፈቃድ የወልድም የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ስለሆነ ሰው እንዲሆን ማድረግም የሦስቱም አንዲት ፈቃድ መሆኗን እንገነዘብ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፴፬

"እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም" (ዮሐ. ፭፥፳፬)። የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል (ትምህርት) መስማትና በአብ ማመን የዘለዓለም ሕይወትን ያስገኛል። በነገራችን ላይ ሰው ሁሉ ዘለዓለማዊ ነው። ዘለዓለማዊነቱ ግን ሁለት ዓይነት ነው። ለኃጥእ ሰው ዘለዓለማዊ የስቃይ ዘመን አለው። ለጻድቅ ሰው ደግሞ ዘለዓለማዊ የደስታ ዘመን አለው። ስለዚህ የዘለዓለም ሕይወት አለው ያለው የደስታውን ሕይወት ነው። በአብ ማመን ማለትም ወላዲ መሆኑን ማመን ማለት ነው። በተጨማሪም ወልድ ባሕርያዊ ልጁ መሆኑን ማመን ነው። ይህን ሳያምኑ ግን ዘለዓለማዊ ሕይወትን ማግኘት አይቻልም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፴፭

"አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥታልና። የሰው ልጅም ስለ ሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው" (ዮሐ. ፭፥፳፮-፳፯)። ለአብ ሕይወትነት እንዳለውና ሕይወት የባሕርዩ እንደሆነ ለወልድም ሕይወትን ሰጠው። በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ መበላለጥ የለም። በክብር በሕይወት አንድ ናቸው። ክርስቶስ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ ብሏል። በሃይማኖተ አበውም አብ ሕይወት፣ ወልድ ሕይወት፣ መንፈስ ቅዱስ ሕይወት፣ አንድ ሕይወት ተብሎ የተገለጸው ይህኛው ሕይወትነት ነው። ይህኛው ሕይወትነት ግብረ ባሕርይ ነው። በከዊን ግን ሕይወትነት የመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ለወልድ ሰጠው ማለቱም ለወልድ መቀበል የሚስማማው ሆኖ አይደለም። ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋ በቃል ርስት ወልድ ስለተባለ ስለ

ሰውነቱ የተነገረ መሆኑን ማስተዋል ይገባል። ለዚህም ምስክሩ ቀጥሎ "እስመ ወልደ እግዚአብሔር ወልደ ዕጓለ እመሕያው ውእቱ" ተብሎ ተገልጿል። ተሰጠው የተባለ የሰው ልጅ ስለሆነ እንደሆነ ተነግሯል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፯

"እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም እንደ ሰማኹ እፈርዳለኹ ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና" (ዮሐ. ፭፥፴)። ወልድ ከራሱ አንዳች ማድረግ አይችልም። ይህም ማለት አብ ልቡ ሆኖ፣ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋሱ ሆኖ በመገነዛዘብ ሥራውን ይሠራል እንጂ ብቻውን ምንም ማድረግ አይችልም ማለት ነው። ሦስቱ አካላት አንዱ ያለ አንዱ አይሠሩምና። የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻም ማለቱም ለእርሱ ከአብ የተለየ ፈቃድ እንደሌለው የሚያስረዳ ነው። የላከኝን ፈቃድ እሻለሁ ማለቱም የአብን ፈቃድ እሻለሁ ማለት ነው። ይህ ፈቃድ የእርሱም ፈቃድ ነውና። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደመሆኑ ፍርዱ ቅን ነው። ፍርዱን ዘመን አይሽረውም። ምክንያቱም እርሱ ሲፈርድ ሁሉንም በምልዐት አውቆ ነው። የፍጡራን ፍርድ ግን ጉድለት አያጣውም። ምክንያቱም በውስን ዕውቀት የሚደረግ ስለሆነ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፰

"እኔ በአባቴ ስም መጥቻለኹ አልተቀበላችኹኝምም ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ ርሱን ትቀበሉታላችኹ" (ዮሐ. ፭፥፵፫)። ኢየሱስ ክርስቶስ በአባቴ ስም መጥቻለሁ ብሏል። በአባቴ ስም ብመጣ አልተቀበላችሁኝም ማለትም የባሕርይ አምላክ ነኝ ብየ ብመጣ አላመናችሁኝም ማለቱ ነው። ይኸውም አባቴ አብ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ መስክሮልኝ ብመጣ አላመናችሁኝም ማለቱ ነው። ሌላው ግን በራሱ ስም ቢመጣ ትቀበሉታላችሁ ማለቱ ወደፊት ሐሳዊ መሲሕ ራሱ ባወጣው ስም አምላክ ነኝ ብሎ ራሱ በራሱ መስክሮ ቢመጣ ታምኑበታላችሁ ማለቱ ነው። ለሐሳዊ መሲሕ ሌላ ምስክር ሳይኖረው በራሱ ስም ብቻ መጥቶ ብዙውን በውሸት ያሳምናል። ለጌታ ግን አብ መስክሮለት፣ ዮሐንስ መጥምቅ መስክሮለት፣ ተአምራት መስክረውለት ቢመጣም ብዙዎች በእርሱ አለማመናቸውን ለመግለጽ እንዲህ አለ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፱

"ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችኹ ነበር እርሱ ስለ እኔ ጽፏልና" (ዮሐ. ፭፥፵፮)። አይሁድ የሙሴን ሕግ እንጠብቃለን ብለው ያስቡ ነበር። ነገር ግን የሙሴን ሕግ በትክክል ቢጠብቁ ኖሮ በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ነበረ። ምክንያቱም ለሙሴም ሕግን የሰጠው፣ ትንቢት ያናገረው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና። የሙሴ ትንቢት ስለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረ ነውና። ሙሴ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ጽፏል። "አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል ርሱንም ታደምጣለህ" ብሎ ለጊዜው ስለኢያሱ ፍጻሜው ግን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሯል (ዘዳ. ፲፰፥፲፭)። ሙሴ እስራኤላውያንን ከአለት ውሃ አልፍቶ እንዳጠጣቸው ተነግሯል። ያ ዐለት ፍጻሜው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ ጽፏል። "ወኰኵሕስ

ክርስቶስ ውእቱ" እንዲል። እና አይሁድ የሙሴን ሕግን ጠንቅቀው ቢያውቁ ኖሮ ክርስቶስን ባልተቃወሙት ነበር።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፵፱

"ኢየሱስም እንጀራውን ያዘ፥ አመስግኖም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም ለተቀመጡት ሰዎች ሰጧቸው እንዲሁም ከዓሣው በፈለጉት መጠን" (ዮሐ. ፮፥፲፩)። መድኃኔዓለም ክርስቶስ ለእኛ አርዓያ ለመሆን እንጀራን ይዞ አመስግኖ ለደቀመዛሙርቱ ሰጥቷል። ለእኛ አርዓያ ለመሆን አመሰገነ እንጂ እርሱ ራሱ የምስጋና ባለቤት ነው። የሚመሰገነው እርሱ እኛን ለማስተማር አመሰገነ። እኛም እርሱን አብነት አድርገን ምግብ ሲቀርብ አቡነ ዘበሰማያት ብለን እግዚአብሔርን አመስግነን ካህን ካለ ቆርሶ ይሰጠናል። አንድ ካህንና ብዙ ሰው ካለ ደግሞ ካህኑ ለዲያቆኑ ቆርሶ ይሰጠውና ዲያቆኑ ለሁሉ ያዳርሳል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፶

"ኢየሱስ መልሶ፦ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው" (ዮሐ. ፮፥፳፱)። እግዚአብሔር የላከው የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እግዚአብሔር ሲል አብን፣ ወልድን፣ መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል። "አንሰ ሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" እኔ እግዚአብሔር ባልኩ ጊዜ ስለ አብ፣ ስለ ወልድ፣ ስለመንፈስ ቅዱስ እላለሁ እንዲል (ሃይማኖተ አበው)። "የላከው" የሚለው ቃል "ሰው እንዲሆን ያደረገው" ተብሎ ይተረጎማል። ወልድን ሰው እንዲሆን ማድረግ ደግሞ የሦስቱም ሥራ ነው እንጂ ተለይቶ የአንዱ ብቻ አይደለም። በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን በአብም በመንፈስ ቅዱስም ማመን ነው። አብን፣ ወልድን፣ መንፈስ ቅዱስን የምናምነው እምነት አንድ እምነት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፶፩

"ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ኹልጊዜ ከቶ አይጠማም" (ዮሐ. ፮፥፴፭)። በዚህ ምድር የምንበላው እንጀራ ለጊዜው ቢያጠግብ ቆይቶ ያስርባል። ኢየሱስ ግን የሕይወት እንጀራ ስለሆነ ንሥሓ ገብተን፣ መልካም ሥራ ሠርተን፣ ሥጋውን ስንበላ ደሙን ስንጠጣ ዘለዓለማዊ የደስታ ሕይወትን እናገኛለን። ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም ማለቱ ሥጋዊ ረኀብን የሚያመለክት አይደለም። እንዳልሆነ የምናውቀውም ሐዋርያት ከእርሱ ጋር እያሉ እንኳ ርቧቸው በዕለተ ሰንበት እሸት ቀጥፈው በመብላታቸው ነው። ከቶ አይራብም ያለው ነፍሳዊ ረኀብን ነው። የነፍስ ረኀብ ቃለ እግዚአብሔርን ካለመስማት ይመጣል። ወደጌታ የሚሄድ ሰው ማለት ቃሉን ሰምቶ የሚተገብረው ሰው ከቶ አይራብም ከቶ አይጠማም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፶፪

"አባቱንና እናቱን የምናውቃቸው ይህ የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ አይደለምን እንግዲህ፦ ከሰማይ ወርጃለኹ እንዴት ይላል አሉ" (ዮሐ. ፮፥፵፪)። አይሁድ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸው አረዳድ ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) እንደሆነ ነው። ነገር ግን ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው የሆነ

ነው። ወልደ አብ ወልደ ማርያም ነው። አባቱን እና እናቱን የምናውቃቸው አይደለምን? ብለው ተደንቀው ተናግረዋል። ጌታን የዮሴፍ ልጅ ብለውታል። በእርግጥ ጌታ በሥጋ ያደገው ከዮሴፍ ቤት ነው። በእኛ አጠራር ደግሞ የአሳደገ ሰው አባት ይባላል። አይሁድ ግን ባለማወቃቸው ዮሴፍን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ሲሉ ወላጅ አባቱ መስሏቸው በውሸት ተናግረዋል። ጌታ በዚህ ምድር ከድንግል ማርያም ያለ አባት፣ ያለወንድ ዘር፣ ያለሩካቤ ተወልዷል። ስለዚህም በምድራዊ ልደቱ ወልደ ማርያም ይባላል። ቀድሞ ደግሞ በሰማይ ከእግዚአብሔር አብ ያለ እናት ተወልዷል። ስለሆነም በሰማያዊ ልደቱ ወልደ አብ ይባላል። ቀድሞ ከአብ የተወለደው ወልደ እግዚአብሔር በኋላ ከድንግል ማርያም በመወለዱ ከሰማይ ወርጃለሁ ብሏል። ሰው ሆኛለሁ ማለቱ ነው። አይሁድ ግን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ባለመረዳታቸው ለምን ከሰማይ ወረድኩ ይለናል ብለው አጉረምርመዋል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፶፫

"አብን ያየ ማንም የለም ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር፥ ርሱ አብን አይቷል" (ዮሐ. ፮፥፵፮)። እግዚአብሔር በባሕርይው የማይታይ አምላክ ነው። የፍጡር ዓይን እርሱን ማየት አይችልም። የፍጡር ኅሊና እርሱን ማሰብ ስለማይችልም ከመታሰብ በላይ ነው። ነገር ግን ቸር ስለሆነ እኛ ሳናውቀው እንድንቀር አላደረገንም። በተለያዩ ዘመናት በተለያየ አምሳል እየተገለጠ ህልዎቱን (መኖሩን) አሳውቆናል። አብርሃም በሰው አምሳል አይቶታል። ሌሎችም ነቢያት በተለያዩ አምሳላት አይተውታል። በባሕርይው ግን አይተውት አያውቁም። አንድ ሊቅ ይህንን ሲገልጽ በሃይማኖተ አበው "ለእመ ተጋብኡ ኅቡረ መላእክት ወሊቃነ መላእክት በበዘመዶሙ ዘምስለ ኵሎሙ ፍጡራን አሐተኔ ኢይክሉ ይርከቡ ኀዳጣ እምአእምሮተ ህላዌሁ ለእግዚአብሔር" ብሏል። ትርጉም መላእክትና ሊቃነ መላእክት በየነገዳቸው ከፍጡራን ጋር ሁሉ በአንድነት ቢሰበሰቡ የእግዚአብሔርን ባሕርይ በጥቂቱ እንኳ ማወቅ አይችሉም ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ አብን ያየ ማንም የለም ብሎ የተናገረው ለዚህ ነው። ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አብን አይቷል። "እርሱ አብን አይቷል" ብሎ በሩቅ አንቀጽ የተናገረው ስለራሱ ነው። መጻሕፍት ቅርቡን በሩቅ መግለጽ ልማዳቸው ነውና። ኢየሱስ ክርስቶስ አብን ያየው እርሱ ራሱም እግዚአብሔር ስለሆነ ነው። የአብ ቃሉ በመሆኑ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፶፬

"ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለኹ" (ዮሐ. ፮፥፶፬)። ሥጋውን ደሙን የተቀበለ ብቻ ሳይሆን በመጨረሻው ሰዓት (በምጽአት ጊዜ) ኃጥኣንም ይነሣሉ። የሞተ ሰው ሁሉ ትንሣኤ እንዳለው የታወቀ ነው። ትንሣኤ በሁለት ይከፈላል። አንደኛው ትንሣኤ ትንሣኤ ዘለኀሣር ይባላል። ይህ የኃጥኣን ትንሣኤ ነው። ኃጥኣን ለዘለዓለም ስቃይና መከራ ይነሣሉ። ጻድቃን ደግሞ ለዘለዓለም ደስታ ይነሣሉ። ይህኛው ሁለተኛው ትንሣኤ ትንሣኤ ዘለሕይወት ይባላል። ጌታ ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው። እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ ማለቱ ትንሣኤ ዘለሕይወትን የሚመለከት አነጋገር ነው። ታዲያ የክርስቶስን ሥጋና ደም ከየት እናገኘዋለን? ከተባለ ሁልጊዜም በቅዳሴ ጊዜ ካህናት ኅብስቱንና ወይኑን አዘጋጅተው ሥርዓተ

ቅዳሴን ሲያከናውኑ ኅብስቱ ወደ ክርስቶስ ሥጋነት፣ ደሙ ወደ ክርስቶስ ደምነት ይለወጣል። ምእመናንም ንሥሓ እየገቡ ይቀበሉታል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፶፭

"የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፥እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለኹ" (ዮሐ. ፮፥፵፬)። በሀብት ስቦ፣ በረድኤት አቅርቦ እግዚአብሔር አብ ካልሳበው በቀር ወደ ወልድ የሚመጣ የለም። አብ የሳበው እንጂ አብ ያልሳበው በወልድ ማመን አይችልም ማለት ነው። የላከኝ የሚለው አገላለጽ ከድንግል ማርያም ተወልጄ ተሰቅዬ አዳምን አድነው ዘንድ ሥጋን እንድዋሐድ ያደረገኝ ማለት ነው። ይህን ማድረግም የአብ ብቻ ሥራ አይደለም። አብ ይጠቀስ እንጂ የአንድነት ሥራ ስለሆነ የወልድም የመንፈስ ቅዱስም ሥራ ነው። "እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ" የሚለው አገላለጽ የሕይወት ትንሣኤን አስነሣዋለሁ ማለቱ ነው። በመነሣት ደረጃ ኃጥኣንም ጻድቃንም ይነሣሉና። "ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምኾን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል" (ዮሐ. ፮፥፶፯)። ወልድ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እሆናለሁ ማለቱ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ከአብ መወለዱን ያስረዳል። ከሕያው አብ የተወለድኩ ሕያው ወልድ ነኝ። ከሕያው አብ በመወለዴ እኔም ሕያው ነኝ ማለቱ ነው። የሕያው ልጅ ሕያው ነውና። ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣም ሕያው ይሆናል ማለትም ለዘለዓለም በደስታ ይኖራል ማለት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፶፮

"ነገር ግን፥ ከእናንተ የማያምኑ አሉ። ኢየሱስ የማያምኑት እነማን እንደ ሆኑ አሳልፎ የሚሰጠውም ማን እንደ ሆነ ከመጀመሪያ ያውቅ ነበርና" (ዮሐ. ፮፥፷፬)። ይህ ኃይለ ቃል የኢየሱስ ክርስቶስን ሁሉን አዋቂነት ያስረዳል። እርሱን ለአይሁድ አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳ እንደሆነ አስቀድሞ ያውቅ ነበር። እንደሚክደው እያወቀ አስከተለው። ይህም የእርሱን ቸርነት ያስረዳል። ለፍጡራን ዕውቀት ቢኖራቸው ዕውቀታቸው የጸጋ ዕውቀት ነው። ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለው ዕውቀት ግን ከሌላ ያልተገኘ የራሱ የባሕርይው የሆነ ዕውቀት ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሁዳ እንደሚክደው አስቀድሞ አወቀ እንጂ እንዲሸጠው አላስገደደውም። ይሁዳንም ጌታን እንዲሸጥ ትንቢቱ አላስገደደውም። ትንቢቱ የይሁዳን ፈቃድ አውቆ ተነገረ እንጂ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፶፯

"ኢየሱስም፦ እኔ እናንተን ዐሥራ ኹለታችኹን የመረጥኋችኹ አይደለምን ከእናንተም አንዱ ዲያብሎስ ነው ብሎ መለሰላቸው" (ዮሐ. ፮፥፸)። ሐዋርያትን የመረጣቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እግዚአብሔር ሁሉንም ለጽድቅ መርጦታል። መመረጥን ዐውቆ በመልካም ሥራ መጽናት የሰው ድርሻ ነው። ሐዋርያነትን ይሁዳም ተመርጦ ነበር። ነገር ግን አልጸናም። ገንዘብ አሸንፎት ለገንዘብ ሲል ጌታውን አሳልፎ ሰጠ። አሁንም ክርስቲያን ሆነው ሳለ፣ ለሐዋርያነት ተመርጠው ሳለ ነገር ግን ለግል ክብራቸውና ለገንዘብ ሲሉ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን የከዱ አሉ። አይሁድ ክርስቶስን ለመያዝ የተጠቀሙት ይሁዳን ነው። ምክንያቱም

ይሁዳ ጌታን ያውቀዋል። ስለዚህ የሚገኝበትን ሊጠቁም ከአይሁድ ጋር ተባበረ። ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ ሰውን በግብሩ ይጠራዋል። ይሁዳን በግብሩ ዲያብሎስ ብሎታል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፰

"አይሁድም፦ ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል ብለው ይደነቁ ነበር" (ዮሐ. ፯፣፲፭)። ዕውቀት መጻሕፍትን በማንበብ፣ ከመምህራን እግር ስር ቁጭ ብሎ በመማር፣ በመጠየቅ፣ በልምድ እና በመሳሰሉት ይገኛል። ሁለት ዓይነት ዕውቀት አለ። ይኸውም አእምሮ መንፈሳዊና አእምሮ ጠባይዓዊ ተብሎ ይከፈላል። አእምሮ ጠባይዓዊ የሚባለው ፍጥረታት በተፈጥሮ የሚያውቁት ዕውቀት ነው። ይህ ከላይ በጠቀስናቸው የማወቂያ መንገዶች ይሰፋል። አእምሮ መንፈሳዊ የሚባለው ደግሞ በሥላሴ ስም ተጠምቀን፣ ምግባር ትሩፋት ሠርተን የምናገኘው ነው። አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስን ሰው ብቻ አድርገው ያስቡት ስለነበር "ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል ብለው ይደነቁ ነበር" ተብሏል። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ስለሆነ በባሕርይው ከመምህር ሳይማር፣ መጻሕፍትን ሳያነብ ያውቃል። ይህንን ባለመረዳታቸው ነው እንደዚያ ያሉት።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፱

"ስለዚህ፥ ኢየሱስ መለሰ፥ እንዲህም አላቸው፦ ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም" (ዮሐ. ፯፣፲፮)። አይሁድ እግዚአብሔር አብን እንወዳለን የሚሉ ናቸው። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን ከወደዳችሁትማ ትምህርቴ ከእርሱ የተገኘች ናት ብሎ ለእነርሱ ኅሊና የሚስማማ መልስ ነገሯቸዋል። ከእኔ አይደለችም ማለቱ አይሁድ ጌታን ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) አድርገው ስለሚያስቡት ከሰው (ከዕሩቅ ብእሲ) የተገኘች አይደለችም ወልድ ዋሕድ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ከሆንኩ ከእኔም የተገኘች ናት እንጂ ለማለት ነው። በሌላ አገላለጽ ትምህርቴ ከእኔ ብቻ የተገኘች አይደለችም ከአብም የተገኘች ናት እንጂ ለማለት ነው። ምክንያቱም በፍጡራን ላይ ባላቸው ሥልጣናዊ ግብር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸውና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲

"እንግዲህ ኢየሱስ በመቅደስ ሲያስተምር፦ እኔንም ታውቁኛላችኹ ከወዴትም እንደ ኾንኹ ታውቃላችሁ እኔም በራሴ አልመጣኹም፥ ነገር ግን፥ እናንተ የማታውቁት የላከኝ እውነተኛ ነው። እኔ ግን ከርሱ ዘንድ ነኝ ርሱም ልኮኛልና፥ ዐውቀዋለኹ ብሎ ጮኸ።" (ዮሐ. ፯፣፳፰-፳፱)። ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ በራሴ አልመጣሁም ብሏል። በራሴ ፈቃድ ብቻ አልመጣሁም በአብም በመንፈስ ቅዱስም ፈቃድ መጥቻለሁ ማለቱ ነው። የላከኝ አብ እውነተኛ ነው ብሏል። የላከኝን እናንተ አታውቁቱም እኔ ግን አውቀዋለሁ ብሏል። እግዚአብሔርን በትክክል የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር አብን እግዚአብሔር ወልድ ያውቀዋል። እግዚአብሔር አብም እግዚአብሔር ወልድን ያውቀዋል። ጌታ ክርስቶስ ስለአብ ሲናገር እኔ ከእርሱ ዘንድ ነኝ ብሏል። ይኸውም ከአብ መወለዱን ያስረዳል። አብ የባሕርይ አባቱ ነውና። ይህ ልደትም እኛ በተፈጥሮ የምናውቀው ዓይነት ልደት አይደለም። በሰው ኅሊና ከመታሰብ በላይ የሆነ ልደት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፷፩

"ትፈልጉኛላችኹ አታገኙኝምም እኔም ወዳለኹበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም አለ" (ዮሐ. ፯፥፴፬)ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከእነርሱ እንደሚሄድ ለመግለጽ እንዲህ አለ። እኔ ወዳለሁበት ልትመጡ አትችሉም ማለቱ እኔ የሞትኩትን ሞት እኔ በተሰቀልኩበት መስቀል ተሰቅሎ እኔ ከገባሁበት ውስጤ መንጦላዕት ገብቶ መኖር አይቻላችሁም ማለት ነው። በተጨማሪም እኔ ወዳለሁበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም ማለት እኔ ከድንግል ማርያም የተወለድኩ የባሕርይ አምላክ ነኝ። እናንተ ግን የባሕርይ አምላክ አይደላችሁም ማለቱ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፷፪

"ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ፦ ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። ይህን ግን በርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ፥መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና" (ዮሐ. ፯፥፴፯)። ከጽድቅ የተጠማ ሁሉ ወደክርስቶስ ቀርቦ ይጠጣ። ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት መጠጥ ነውና። አካላዊ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስም የሕይወት መጠጥ ተብሏል። ይህን ስለመንፈስ ቅዱስ ተናገረ ያለው ለዚህ ነው። ምእመናን ይጠጡ የተባሉት ተጠምቀው ልጅነትን ያገኙ ለማለት ነው። መንፈስ ገና አልወረደም የሚለው አነጋገር ያመኑበት ሰዎች ስለሚቀበሉት ልጅነት የተነገረ ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ ካልተሰቀለ ካሣ አይፈጸምም፣ ካሣ ካልተፈጸመ ልጅነት አይሰጥምና ነው። ኢየሱስ ገና ስላልከበረ የሚለው አገላለጽ ገና ስላልተሰቀለ ለማለት ነው። ስቅለቱን ክብር ይለዋልና። "ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘሰመየ ሕማማተ ወልዱ ክብረ ወስብሐተ" እንዲል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፷፫

"ደግሞም ኢየሱስ፦ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይኾንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው" (ዮሐ. ፰፥፲፪)። ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርይው ብርሃን ነው። እርሱን የሚከተለው የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል። ጌታን መከተል ማለትም ሕጉን፣ ትእዛዙን መጠበቅ ማለት ነው። "ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው" እንዲል (መዝ. ፻፲፰፥፻፭)። በብርሃን የሚሄድ ሰው እሾህ እንቅፋት አያገኘውም። ከገደል ከጉድጓድ አይገባም። በምቹ መንገድ ይሄዳል። ክርስቶስን ያመነ ሰው በዚህ ምድርም ያለጭንቀት ይኖራል። ሕይወቱ የደስታ ይሆናል። የተረጋጋ ሕይወትን ይኖራል። በወዲያኛው ዓለምም መንግሥተ ሰማያትን ወርሶ እግዚአብሔር ነግሦለት ይኖራል። በክርስቶስ ብርሃንነት የሚመላለስ ሰው ራሱም ብርሃን ይሆናል። ጌታ ሐዋርያትን እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ብሏቸዋል። ብርሃንነታቸውምን ከክርስቶስ በጸጋ ያገኙት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፷፬

"የላከኝ አብ ከእኔ ጋራ ነው እንጂ ብቻዬን አይደለሁምና እኔ ብፈርድ ፍርዴ እውነት ነው" (ዮሐ. ፰፥፲፮)። ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ አብ ከእኔ ጋራ ነው ብሏል። ይህም

የህልውና አንድነት ነው:: አብ ካለበት ቦታ ሁሉ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አሉ:: ወልድ ካለበት ቦታ ሁሉ አብና መንፈስ ቅዱስ አሉ:: መንፈስ ቅዱስ ካለበት ቦታ ሁሉ አብና ወልድ አሉ:: አብ ህልው በወልድ ወበመንፈስ ቅዱስ፣ ወልድኒ ህልው በአብ ወበመንፈስ ቅዱስ፣ ወመንፈስ ቅዱስኒ ህልው በአብ ወወልድ:: በፍርድ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው:: መፍረድ የአንድነት ሥራቸው ነው:: የእግዚአብሔር ፍርድ ደግሞ እውነት ነው:: በዘመን ብዛት አይለወጥም:: ልብንና ኩላሊትን መምርምረው በሙሉ ዕውቀት የሚፈርዱ ስለሆነ ፍርዳቸው ሁልጊዜም እውነት ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፩

"እንግዲህ፦ አባትኽ ወዴት ነው አሉት:: ኢየሱስም መልሶ፦ እኔንም ወይም አባቴንም አታውቁም እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችኹ ነበር አላቸው" (ዮሐ. ፰፥፲፱):: እግዚአብሔርን እናውቀዋለን ብለው የሚያስቡ እግዚአብሔርን ግን የማያውቁ ሰዎች አይሁድ ናቸው:: እግዚአብሔር አብን ቢያውቁት ኖሮ እግዚአብሔር ወልድንም ያውቁት ነበረ:: ኢየሱስ ክርስቶስ እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር ያላቸው ለዚህ ነው:: አብን ወላዲ እንደሆነ ቢያውቁት ኖሮ ተወላዲው ወልድ መሆኑን ያውቁ ነበር:: አባትህ ወዴት ነው ብለውታል:: አባቱ የሌለበት ቦታ ግን የለም:: በሁሉ ምሉዕ የሆነ ነው:: በዓለሙ ሁሉ መልቶ የሚኖረውን ወዴት ነው ብለው ጠይቀዋል:: በስሜት ሕዋሳት የማንረዳው ከስሜት ሕዋሳት መረዳት በላይ ስለሆነ ነው እንጂ አብም ወልድም መንፈስ ቅዱስም በዓለሙ ሁሉ መልተው ይኖራሉ:: አይሁድ ወልድን ቢያውቁት ኖሮም አብን ያውቁት ነበር:: ወልድ ተወላዲ መሆኑን ሲያውቁ ወላዲው አብ መሆኑን ይረዱ ነበርና::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፪

"ኢየሱስም አላቸው፦ እግዚአብሔርስ አባታችኹ ከሆነ በወደዳችኹኝ ነበር እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለኹና እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣኹምና" (ዮሐ. ፰፥፵፪):: እግዚአብሔር አባታችን ነው የሚል ሰው እግዚአብሔርን መውደድ አለበት:: አይሁድ ግን እግዚአብሔር አባታችን ብለው እየተናገሩ እግዚአብሔር ወልድን ይጠሉት ነበረ:: እግዚአብሔር ወልድ ከእግዚአብሔር አብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወልዶ በኋለኛው ዘመን ደግሞ ሰውን ለማዳን ከድንግል ማርያም ተወልዶ መጥቷል:: ጌታ ኢየሱስ እኔ ከራሴ አልመጣሁም ብሏል:: በእኔ ፈቃድ ብቻ ሰው አልሆንኩም ማለቱ ነው:: ውረድ ተወለድ ሙት ተሰቀል ብሎ በአባቴም ፈቃድ መጥቻለሁ እንጂ ማለቱ ነው:: አይሁድ ከአብ መጥቻለሁ ሲላቸው እንኳ ማመን ነበረባቸው:: ከአብ ለመምጣቱ አብ የሚሠራውን እየሠራ ቢያሳያቸው እንኳ በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ብለው የራሳቸውን መላምት ከመናገር ውጭ ለማመን አልፈለጉም ነበር:: በዚህም ራሳቸውን ከመዳን አገለሉ::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፫

"ኢየሱስም፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለኹ አላቸው" (ዮሐ. ፰፥፶፰):: ፎጢኖስ የተባለ ሰው የወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ህልውና ከማርያም ወዲህ ነው

ብሎ ያስተምር ነበር። ወልድ ግን ፎጢኖስ እንዳለው ሳይሆን ድንግል ማርያምንም የፈጠረ፣ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ ቀዳማዊ አምላክ ነው። አይሁድም ጌታ ኢየሱስ ሰው ብቻ ይመስላቸው ስለነበር ህልውናው ከድንግል ማርያም ወዲህ ይመስላቸው ነበር። አብርሃም የምወለድበትን ቀን ሊያያት ወደደ ብሎ ሲያስተምራቸው 50 ዓመት ያልሆነህ አንተ አብርሃምን አየህን አሉት? እውነት ነው ጌታ በሰውነቱ እድሜው በዚያን ጊዜ ሠላሳ አካባቢ ነበር። በአምላክነቱ ግን እድሜ የማይቆጠርለት ብሉየ መዋዕል ነው። ስለዚህ ጌታ ሲመልስላቸው አብርሃም ሳይወለድ በፊትኮ ነበርኩ ብሎ ቀዳማዊነቱን ነገራቸው። ለጊዜው አብርሃምን መሠረት አድርገው ስለነበር ከአብርሃም በፊት ነበርኩ አለ እንጂ ፍጥረታት ሳይፈጠሩ በፊት ሁሉ ነበርኩ ማለቱ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፷፰

"መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል" (ዮሐ. ፲፣፲፩)። ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም እረኛ ተብሏል። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል። ታላቁ ሊቅ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ስለእረኝነት ሲናገሩ በሰው ዘንድ መልካም እረኛ የሚባለው በጎቹን በለመለመ መስክ የሚያሰማራ፣ ጥሩ ውሃ እያጠጣ እየተንከባከበ የሚያሳድግ ነው። ነገር ግን ይህን የመሰለውን ሰው ምንም እንኳ መልካም ብንለው መጨረሻ ላይ ወይ አርዶ ይበላቸዋል፣ ወይም ደግሞ አርዶ ለሚበላ ይሸጣቸዋል ይላሉ በቅኔያቸው። ኢየሱስ ክርስቶስን መልካም እረኛ ስንለው ግን በፈቃዳችን ምክንያት ወድቀን የነበርን እኛን ሰው ሆኖ ስላዳነን ነው። ከጽድቅ ተርበን የነበርን እኛን እንጠግብ ዘንድ ሥጋውን ቆርሶ እንኩ ብሎ አለን። ብንጠማ የሕይወት መጠጥ ደሙን አፍስሶ እንኩ ጠጡ አለን። ቢራቡበትና ቢጠሙበት ደሙን አፍስሶ፣ ሥጋውን ቆርሶ ለበጎቹ የሚሰጥ ቸር እረኛ ከእርሱ ከኢየሱስ በስተቀር ማን አለ!?። ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፷፱

"እኔ በፈቃዴ አኖራታለኹ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልኹ" (ዮሐ. ፲፣፲፰)። ኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሴን ከሥጋዬ በግድ የሚለያት የለም እኔ በፈቃዴ እለያታለሁ እንጂ ብሏል። በዚህም አምላክነቱን አስረዳ። ነፍስን ከሥጋ መለየት የአምላክነት ሥራ ነውና። የማኖርና የማስነሣት ሥልጣን ያለውም እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር እንደመሆኑ ላኖራትና ላስነሣት ሥልጣን አለኝ ብሏል። ይህንን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልኩ ያለው ስለሰውነቱ ነው። ቅድመ ተዋሕዶ ሙታንን ማስነሣት፣ ነፍስን ከሥጋ መለየት የማይችል ሥጋ ከተዋሕዶ በኋላ ግን ቃልን በመዋሐዱ አምላክነትን ገንዘብ አድርጓልና ተቀበልኩ ብሏል። ቃል ሥጋን እንዲዋሐድ ያደረገ ደግሞ አብ ነው። አብ ቢጠቀስም ግን በማዋሐድ ወልድም መንፈስ ቅዱስም አንድ ናቸው። በአንድነት ሥራቸው አንዱ ቢጠቀስም ለሁለቱም እንደሚሆን ከዚህ ቀደም በሰፊው ተመልክተናል። ስለዚህ ከዚህ ላይ ለይቶ ከአባቴ ተቀበልኩ ብሎ ይናገር እንጂ ከመንፈስ ቅዱስ ተቀበልኩ፣ ቃልን በመዋሐዴ ተቀበልኩ ቢል አንድ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፶፰

"የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን (ዮሐ. ፲፣፳፱-፴)። ስለሰውነቱ የሰጠኝ አለ እንጂ በአምላክነቱስ መስጠት እንጂ መሰጠት የለበትም። ስለሰውነቱ የሰጠኝ እያለ መናገሩም በጊዜ ተዋሕዶ አምላክነትን ገንዘብ ማድረጉን ያስረዳል። በተዋሕዶ ሥጋ አምላክነትን ገንዘብ አድርጓል። አምላክም ሥጋን ገንዘቡ አድርጓል። አብ አምላክ እንደመሆኑ ከሁሉ ይበልጣል። ኢየሱስ ክርስቶስ አብ ከሁሉ እንደሚበልጥ ከተናገረ በኋላ እኔና አብ አንድ ነን ብሏል። ከፍጡራን ሁሉ የሚበልጥ አብ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ግን አንድ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደአምላክነቱ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ነው። በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ መበላለጥ የለም። አንዱ ከአንዱ አያንስም። አንዱም ከአንዱ አይበልጥም። ለዚህም ነው ኢየሱስ ክርስቶስ እኔና አብ አንድ ነን ብሎ የተናገረው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፶፱

"አይሁድም፦ ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም ስለ ስድብ አንተም ሰው ስትኾን ራስኽን አምላክ ስለ ማድረግኽ ነው እንጂ ብለው መለሱለት" (ዮሐ. ፲፣፴፫)። እርሱ ጌታ ክርስቶስ አምላክነቱን ለአይሁድ በገለጠላቸው ጊዜ በድንጋይ ሊወግሩት ነበር። እውነቱን ቢነግራቸው ሰደቡከን አሉት። አንተ ሰው ስትሆን እንዴት ራስህን አምላክ ታደርጋለህ!? አሉት። አይሁድ ግማሽ እውነት ብቻ ይዘው በጌታ ሳያምኑበት ቀሩ። እውነት ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ነው። እርሱ ራሱም ብዙ ጊዜ ራሱን የሰው ልጅ እያለ ጠርቷል። እንደሌሎች ሰዎች ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ግን አይደለም። አምላክም ሰውም የሆነ አንድ ነው እንጂ። አይሁድ ሰውነቱን ብቻ አይተው አምላክነቱን ካዱት። እንደ አውጣኪ ያሉ ከሓድያን ደግሞ አምላክነቱን ብቻ አይተው ሰውነቱን አምላክነቱ ውጦታል ብለው ካዱ። እኛ ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው እንላለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፷

"ኢየሱስም፦ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል" (ዮሐ. ፲፩፣፳፭)። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ከሞት የሚያስነሣና በትንሣኤ ዘጉባዔ ለጻድቃን ዘለዓለማዊ የደስታና የዕረፍት ሕይወትን የሚሰጥ በመሆኑ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ ብሎ አስተምሯል። በእርሱ የሚያምን ሥጋዊ ሞትን ቢሞት እንኳ በዕለተ ምጽአት ጊዜ ነፍሱና ሥጋው ተዋሕደው ሕያው ሆኖ እንደሚነሣ ተናገረ። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ባላቸው ኩነት (መሆን) ግን ሕይወትነት ወይም እስትንፋስነት ለመንፈስ ቅዱስ ብቻ ይነገራል። አብ ልብ፣ ወልድ ቃል፣ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ (ሕይወት) ይባላሉና። በግብረ ልደትም አብ ወላዲ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ተብለው ይጠራሉ። ለፍጡራን ባላቸው ግብር ግን አብንም ወልድንም መንፈስ ቅዱስንም ወላዲ ወላዲ ወላዲ ሊላቸው ይችላል። ስለዚህ እነዚህን ቃላት ለግብረ ልደት ሲነገሩና ለግብረ ባሕርይ ሲነገሩ ያላቸውን ልዩነት ልብ ማድረግ ያስፈልጋል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፫

"ድንጋዩንም አነሡት፡፡ ኢየሱስም ዐይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ፦ አባት ሆይ፥ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንኻለኹ፡፡ ኹልጊዜም እንድትሰማኝ ዐወቅኹ ነገር ግን፥ አንተ እንደ ላክኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለቆሙት ሕዝብ ተናገርኹ አለ፡፡ ይህንም ብሎ በታላቅ ድምፅ፦ አልዓዛር ሆይ፥ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ" (ዮሐ. ፲፩፥፵፩-፵፫)፡፡ ጌታችን ዓይኖቹን ወደላይ አንሥቶ አባት ሆይ ስለሰማኸኝ አመሰግንሀለሁ አለ፡፡ ዓይኑን ወደ ሰማይ ማንሣቱ ምውት የማስነሣበት ሥልጣን ከሰማይ አባቴ ጋር አንድ ነው ሲል ነው፡፡ ስለሰማኽኝ አመሰግንሃለሁ ያለው በዙሪያው ስለቆሙት ሕዝብ ነው፡፡ ይኽውም እግዚአብሔር የሚሰማው ይህማ ከእግዚአብሔር የተላከ ቢሆን ነው እንጂ ብለው እንዲያምኑ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን ካመኑ በቃሉ ያምናሉና፡፡ በቃሉ ካመኑ እርሱም እግዚአብሔር መሆኑን ገልጾላቸዋልና አምላክነቱን ይረዳሉ፡፡ አምላክነቱን ከተረዱ ይድናሉና ስለዚህ በዙሪያ ስለቆሙት ሕዝብ ተናገርኩ አለ፡፡ እንደምትሰማኝ ዐውቅሁ ያለው ከዚያ በፊት አለማወቁን አይገልጽም፡፡ እንዲህ ማለቱ ለሕዝቡ አብ እንደሚሰማው እንዲረዱ ነው እንጂ፡፡ አመሰግንሃለሁ ማለቱ ለእኛ አብነት ለመሆን ነው፡፡ ይኽውም በጸሎት ጊዜ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ ሊያስተምረን ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፬

"አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለኹ አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ፡፡ ነገር ግን፥ ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣኹ" (ዮሐ. ፲፪፥፳፯)፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳምን ቤዛ ሆኖ ሊያድነው ከድንግል ማርያም ተወልዶ የመጣ እንደመሆኑ ለአዳም ስለአዳም ካሣ ለመክፈል አባት ሆይ ከዚህች ሰዓት አድነኝ አለ፡፡ አድነኝ ካለ በኋላ አድናትስ እንዳልል ስለዚህ ነገር ሰው ሆኛለሁ ብሏል፡፡ የመጣ ተሰቅሎ ሙቶ አዳምን ሊያድን ነውና፡፡ የአዳምን ጩኸት ጩኸቱ አድርጎ ከዚህ ሰዓት አድነኝ አለ፡፡ በእርሱ መታወክ ከእኛ መታወክን አራቀልን፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነፍስን አልነሣም፡፡ በነፍሱ ምትክ መለኮቱ ሆነው ብለው የተነሡ ከሓድያን ከላይ ባለው ኃይለ ቃል ይረታሉ፡፡ "ነፍሴ" ብሎ ነፍስ እንዳለው ተናግሯልና፡፡ ነፍሴ ያለው መለኮቱ ነው እንዳይሉ በመለኮት መታወክ የለበትምና ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፭

"እኔ ከራሴ አልተናገርኹምና ነገር ግን፥ የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ" (ዮሐ. ፲፪፥፵፱)፡፡ እኔ ከራሴ አልተናገርኩም ማለቱ ከራሴ ብቻ አንቅቼ የማስተምር አይደለም ማለቱ ነው፡፡ ምክንያቱም በሥላሴ የአንድነት ሥራ ውስጥ የራስ የሚባል ሥራ የለም፡፡ ሦስቱ አካላት ተገናዝበው በአንድነት ይሠራሉ እንጂ፡፡ ይኽውን አብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ልባቸው ነው፡፡ ወልድ የአብ የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የአብ የወልድ እስትንፋሳቸው ነው፡፡ በእነዚህ ኩነታቸው ተገነዛዝበው የሚሠሩት ሥራ የአንድነት ሥራ ነው፡፡ አብ ላከኝ፣ ትእዛዙን ሰጠኝ ብሎ ስለሰውነቱ ተናግሯል፡፡ ከዚህ ላይ ሰጪ ተደርጎ አብ ብቻ ቢጠቀስም ሥጋ አምላክነትን በተዋሕዶ ያገኘውና የትእዛዝ ባለቤት የሆነው ግን በአብም፣ በወልድም፣ በመንፈስ ቅዱስም የአንድነት ሥራ ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፴፮

"እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችኹ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ" (ዮሐ. ፲፫፥፲፫)። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መምህራችንም ጌታችንም ነው። የፈጠረን ጌታ እርሱ ነው። መልካምን መንገድ እያሳየ ያስተማረንና የሚያስተምረን መምህራችንም እርሱ ነው። ትሕትናን ሲያስተምረን የደቀመዛሙርቱን እግር እያጠበ አስተማረን። "መምህራችሁና ጌታችሁ ስሆን እግራችሁን ካጠብኳችሁ" እናንተም የወንድሞቻችሁን እግር ልታጥቡ ይገባችኋል አብነት ሆኛችኋለሁና" ብሏቸዋል። "እስመ አርአያየ ወሀብኩክሙ" እንዲል። የኢየሱስ ክርስቶስ መምህርነት የባሕርይ መምህርነት ነው። ከፍጡር ተምሮ ያገኘው አይደለም። ዕውቀቱን ከማንም ያላገኘው ማንም የማይወስድበት የባሕርይው ነው እንጂ። ሰዎችን መምህር ብንላቸው ትምህርታቸውን ከሌላ ተምረው በጊዜ ብዛት ያገኙት ነው። ይኸውም በመምህርነታቸው ላይ እንከን አለበት። ሁሉን የሚያውቅ ሰው የለምና። ኢየሱስ ክርስቶስን መምህር ስንለው ግን ሁሉን የሚያውቅ መምህር ነው ማለታችን ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፴፯

"ልባችኹ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ" (ዮሐ. ፲፬፥፩)። በእግዚአብሔር እመኑ ማለቱ ይህንን ዓለም ከምንም (እም ኀበ አልቦ) የፈጠረና ፈጥሮም የሚያስተዳድር እርሱ እግዚአብሔር በመሆኑ ነው። ሰውንም በአምሳሉ ፈጥሮ የጸጋ ገዢ ያደረገው እርሱ በመሆኑ ነው። ስለዚህ የሁሉ ፈጣሪ፣ ሁሉን ቻይ፣ ሁሉን ዐዋቂ፣ የነገሥታት ንጉሥ፣ ባዕለጸጋ እግዚአብሔር መሆኑን ዐውቆ የሚያኖረንና የሚመግበን እርሱ መሆኑን ከልብ ማመንና ትእዛዛቱን መፈጸም ተገቢ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥሎ በእኔም ደግሞ እመኑ አለ። እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እና እኛን ለማዳን ሰው የሆነ እንደሆነ አምነን ሕይወትን እንድናገኝ በእኔም እመኑ አለ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፴፰

"ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" (ዮሐ.፲፬፥፮)። ኢየሱስ ክርስቶስ የእውነት መንገድ ነው። እውነተኛ መንገድ ከእውነተኛ ቦታ ያደርሳል። እውነተኛ ልጅ ክርስቶስን ማወቅም እውነተኛ አብን ያሳውቃል። ወልድን ተወላዲ ነው ካልን ወላዲው አብን ያሳውቃል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም አለ። እኔን ተወላዲ ሳይል አብን ወላዲ ብሎ የሚያምን የለም ማለቱ ነው። ወልደ እግዚአብሔር የጽድቅን መንገድ፣ የትሩፋትን ሥራ ሰው ሆኖ አሳይቶናል። ስለዚህም ፍኖተ ጽድቅ (የእውነት መንገድ) ተባለ። ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ማለቱ እኔን አብነት አድርጎ መልካም ሥራን የማይሠራ ሰው ወደ አብ አይመጣም ማለት ገነት መንግሥተ ሰማያትን አይወርስም ማለቱ ነው። እኒህን የሚያደርግ ግን ወደ አብ ይመጣል አለ ረድኤትን፣ ገነት መንግሥተ ሰማያትን ያገኛል ማለት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፷፱

"ኢየሱስም አለው፦ አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያኽል ዘመን ከእናንተ ጋራ ስኖር አታውቀኝምን እኔን ያየ አብን አይቷል እንዴትስ አንተ፦ አብን አሳየን ትላለኽ" (ዮሐ. ፲፬፡፱)፡፡ እኔን ያየ አብን አየ ማለቱ አብና ወልድ በግብረ ባሕርይ አንድ መሆናቸውን ይገልጻል፡፡ ወልድ የሠራው እግዚአብሔራዊ ሥራ የአብም የመንፈስ ቅዱስም ሥራ ነው፡፡ በመለኮታዊ ሥራ አንዱ እንደሠራው በመጻሕፍት የተገለጸው ሁሉ ለሁለቱም ይነገራል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እኔን ያየ አብን አየ ማለቱ በግብር ማየት ነው እንጂ የወልድ አካል የአብ አካል ነው ማለት አይደለም፡፡ በሥላሴ ዘንድ በአካል አብ ወልድን ወልድም አብን አይሆንምና፡፡ በአካላቸው ቀውማን ጽኑዓን ናቸው፡፡ (አቃኒም) መባሉ ለዚህ ነው፡፡ ቀድሞም እግዚአብሔር አብን ያየው አንድም ሰው የለም፡፡ ነገር ግን ለፍጥረታቱ በሚያደርገው መግቦት ይታያል፡፡ ወልድ እኔ ያየ አብን አየ ማለቱም በግብሩ መታየቱን ያሳውቃል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፸

"እኔ በአብ እንዳለኹ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ ባይኾንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ" (ዮሐ. ፲፬፡፲፩)፡፡ በሥላሴ ዘንድ አንዱ አካል በአንዱ አካል ህልው ሆኖ ይኖራል፡፡ አብ በወልድ ይኖራል፡፡ ወልድም በአብ ይኖራል፡፡ እግዚአብሔር በፍጡራን ቢኖሩ የረድኤት ህልውና ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ስለሆነ በአብ ይኖራል፡፡ አብም እግዚአብሔር ስለሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ ይኖራል፡፡ "አብ ህልው በወልድ ወበመንፈስ ቅዱስ ወወልድ ህልው በአብ ወበመንፈስ ቅዱስ ወመንፈስ ቅዱስኒ ህልው በአብ ወወልድ" እንዲል፡፡ ሦስቱ አካላት በአንድ ህልውና ይኖራሉ፡፡ አብ በወልድ ህልው ነው፡፡ ህልውናው ግን መገነዛዘብም ያለበት ነው፡፡ አብ ልባቸው ሆኖ ወልድ ቃላቸው ሆኖ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋሳቸው ነው፡፡ ህልውናው አንዱ አንዱን ገንዘብ አድርጎ ነው፡፡ አብ በእኔ ህልው እንደሆነ ባታምኑ እንኳ አብ የሚሠራውን ሥራ እኔም ስሠራው አይታችሁ እመኑብኝ ብሏል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፸፩

"እኔ ወደ አብ እኼዳለኹና አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለኹ" (ዮሐ. ፲፬፡፲፫-፲፬)፡፡ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁ ማለቱ ተልዕኮዬን ፈጽሜ በአምላክነት ግብር ጸንቼ እኖራለሁ ማለቱ ነው፡፡ በሥጋው ወራት ሰውን ለማዳን ይራብ ይጠማ የነበረ እርሱ ከትንሣኤ በኋላ የማይራብ፣ የማይጠማ፣ የማይደክም ሆኖ ይኖራልና ወደ አብ እሄዳለሁ አለ፡፡ ወደ አብ ግብር እሄዳለሁ ማለቱ ነው፡፡ ይኸውም አብ እንዳልተራበና እንደማይራብ ሁሉ እኔም ከትንሣኤ በኋላ እንደማልራብና እንደማልጠማ ዕወቁ ሲል ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በስሜ አብን ብትለምኑት አደርግላችኋለሁ አለ፡፡ ይኸውም በስቁል ወልድከ በቅንው ወልድከ (በተሰቀለ ልጅህ) ብላችሁ አብን ብትለምኑት እኔ ልመናችሁን እፈጽምላችኋለሁ ሲል ነው፡፡ አብን ለምነነው ወልድ ይሰጠናል፡፡ ይህ አነጋገር በፈቃድ አንድ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ አብን መለመን ወልድን መለመን እንደሆነም ያስረዳል፡፡ ምክንያቱም አብን ብትለምኑት እኔ እሰጣችኋለሁ ተብሏልና፡፡ አብን በስሜ ለምኑት ይሰጣችኋል ቢልም ይሆናል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፹፪

"ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ" (ዮሐ. ፲፬፣፲፭)፡፡ ዐሥሩ የእግዚአብሔር ሕግጋት በዋናነት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነዚህም ፍቅረ ቢጽ (ባልንጀራን መውደድ) እና ፍቅረ እግዚአብሔር (እግዚአብሔርን መውደድ) ናቸው፡፡ ፍቅረ ቢጽ የሚባለው ለእኛ ሊደረግልን የምንፈልገውን ለሌላውም ማድረግ ነው፡፡ እንዲሁም በእኛ ሊደረግብን የማንፈልገውን በሌላውም እንዲደረግ አለመፈለግ ነው፡፡ ፍቅረ እግዚአብሔር የሚባለው ደግሞ እርሱ ያዘዘንን ትእዛዝ በተግባር ማዋል ነው፡፡ ብትወዱኝስ ትእዛዜን ጠብቁ ያለው ለዚህ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ስለሆነ በብሉይ ኪዳን ለሙሴ የሰጠውን ሕግጋት ትእዛዜ ብሏቸዋል፡፡ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሙሴ ዐሥሩ ትእዛዛትን እንደሰጠው ተጽፎ ነበር፡፡ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ የእነዚያ ትእዛዛት ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ "ትእዛዜ" ብሎ አሳውቋል፡፡ በዚህም የእርሱን እግዚአብሔርነት ተረዳን፡፡ ወበዝ አእመርነ እግዚአብሔርናሁ፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፹፫

"እኔም አብን እለምናለኹ ለዘለዓለምም ከእናንተ ጋራ እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል" (ዮሐ. ፲፬፣፲፮)፡፡ ጌታ እኔና አብ አንድ ነን ብሎ አስተምሯል፡፡ እነ ሰባልዮስ ይህንን ይዘው አብ የተባለ ወልድ ነው፡፡ አብም ወልድም መንፈስቅዱስም የተባለ ያው አንዱ አካል ነው ብለዋል፡፡ ነገር ግን በዚህ ኃይለ ቃል አብን እለምናለሁ ያለ ወልድ፣ ሌላ አጽናኝ የተባለ መንፈስ ቅዱስ መኖሩን እና በአካል ልዩ ልዩ መሆናቸውን ያሳውቃል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አብን እለምናለሁ ማለቱ ሰው የሆነው አዳምን ለመካስ ስለሆነ ቤዛ አዳም መሆኑን ያስረዳናል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰውነቱ መለመኑ በአምላክነቱ መዳንን ይሰጠን ዘንድ ነውና፡፡ ሰው እንደመሆኑ ምልጃን ቢያቀርብም አምላክ እንደመሆኑ ምልጃን የሚቀበልም እርሱዉ ነው፡፡ ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፡፡ የመንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል መገለጽ የሥስቱም ፈቃድ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ አካሉ ረቂቅ ነው፡፡ ነገር ግን በእሳት አምሳል ለሐዋርያት ተገልጿል፡፡ ተገልጾም ጸጋን ለሐዋርያት አድሏል፡፡ ለሐዋርያት ያደለው ጸጋ ግን የአብም የወልድም መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል፡፡ በእሳት አምሳል የወረደው ግን በተለየ አካሉ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ አጽናኝ የሚለው ቃልም በዚህ ዓረፍተ ነገር በተለየ ለመንፈስ ቅዱስ ይቀጸል እንጂ አብም አጽናኝ ነው፡፡ ወልድም አጽናኝ ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፹፬

"እኔ በአባቴ እንዳለኹ እናንተም በእኔ እንዳላችኹ እኔም በእናንተ እንዳለኹ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ" (ዮሐ. ፲፬፣፳)፡፡ አብ በወልድ ያለው ህልውና ተገናዝቦ ያለው ህልውና ነው፡፡ እርሱ ወልድ በሐዋርያት መኖሩ ግን በጸጋ አድሮባቸው ነው፡፡ የኅድረት ህልውና ነው እንጂ መገነዛዘብ ያለው ህልውና አይደለም፡፡ እርሱ በቅዱሳን አድሮ ታላላቅ ሥራዎችን ሲያሠራቸው ኖሯል ይኖራል፡፡ አብ በወልድ ቃልነት ይናገራል በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ሕያው ሆኖ ይኖራል፡፡ ወልድም በአብ ልብነት ያስባል በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ሕያው ሆኖ ይኖራል፡፡ መንፈስ ቅዱስም በአብ ልብነት ያስባል በወልድ ቃልነት ይናገራል፡፡ እግዚአብሔር በቅዱሳን አድሮ ታላላቅ ተአምራት ያሠራቸዋል፡፡ እንዲህ ስላልን ግን ቅዱሳንን በአብ ልብነት ያስባሉ፣

በወልድ ቃልነት ይናገራሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ሕያው ይሆናሉ አንላቸውም። በሦስቱም አካላት የአንድነት ሥራ ሕያዋን፣ ነባብያን፣ ለባውያን ሆነው ይኖራሉ እንጂ። ስለዚህ ክርስቶስ እኔ በአባቴ አለሁ ሲል መገንዛዘብ ያለው ህልውና መሆኑን መረዳት ይገባናል። እኔም በእናንተ እንዳለሁ ብሎ በሐዋርያቱ መኖሩን መናገሩ ግን በኀድረት የረድኤት ህልውና መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፹፭

"ኢየሱስም መለሰ፥ አለውም፦ የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል ወደ ርሱም እንመጣለን በርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን" (ዮሐ. ፲፬፣፳፫)። ኢየሱስ ክርስቶስን እወዳለሁ የሚል ሰው ቃሉን (ትምህርቱን) መጠበቅ አለበት። ይህን ያደረገ ጊዜ አብም ይወደዋል። ወልድን መውደድ አብን መውደድ ነውና። አብን መውደድም ወልድን መውደድ ነውና። ሰው ትእዛዛትን ሲጠብቅ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያድሩበታል። ሥላሴ የሌሉበት ቦታ የለም። በሁሉ ቦታ ይኖራሉ። ታዲያ ሰዎች ቃሌን ሲጠብቁ እናድርባቸዋለን ማለቱ ስለምን ነው? ቢሉ ረድኤትን፣ በረከትን፣ ፈውስን እንሰጠዋለን ማለቱ ነው። ጻድቃን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ቢሆን ወይም ቢያድርባቸው ታላላቅ ተአምራትን የሚያደርጉ ሆነዋል። የታመመን የሚፈውሱ ሆነዋል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፹፮

"የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም" (ዮሐ. ፲፬፣፳፬)። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃሌን የማይጠብቅ ሰው አይወደኝም ብሏል። ከዚህ ላይ ቃሌ ብሎ የገለጸው ትምህርቱን ነው። የጌታን ትምህርቱን ሳይቀበሉ ኢየሱስ ኢየሱስ፣ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ቢሉ ጥቅም አይገኝም። ትምህርቱን ሰምቶ በተግባር የሚያውል ሰው ግን ጌታን ይወደዋል። ይህ የምትሰሙት ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም ማለቱ ትምህርቱ የእኔ ብቻ አይደለም የአብም ነው እንጂ ለማለት ነው። የአብ ነው እንጂ ብሎ ለአይሁድ መንገሩ አብን እናከብረዋለን ይላሉና ነው። አብን ካከበራችሁትማ እኔ የምናገረውም ቃል የአብ ቃል ነው ብሎ ትምህርቱን ሰምተው እንዲድኑ ነው። ትምህርቱ ግን የራሱ የወልድም እንደሆነ ለማሳወቅ "ቃሌ" ብሎ ባለቤትነቱን ለራሱ አድርጎ በመናገሩ ይታወቃል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፹፯

"አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፥ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል" (ዮሐ. ፲፬፣፳፮)። ምሥጢረ ሥላሴን ከሚያስረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንዱ ይህ ነው። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በአንድ ህልውና በአንድ ባሕርይ ይኖራሉ። በሥላሴ አንዱ ከአንዱ አይበልጥም። አንዱ ከአንዱም አያንስም። መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ ተብሎም ይጠራል። ጰራቅሊጦስ ማለትም መጽንዒ፣ መንጽሒ፣ ናዛዚ፣ ከሣቲ፣ መስተፍሥሒ ማለት ነው። ይኸውም መጽንዒ በሃይማኖት በምግባር የሚያጸና፣ መንጽሒ ከኃጢአት የሚያነጻ፣ ናዛዚ ከመከራ ከኀዘን የሚያረጋጋ፣ ከሣቲ ምሥጢርን የሚገልጽ፣ መስተፍሥሒ ማለት ጸጋን ሰጥቶ የሚያስደስት ማለት ነው። አብም

ወልድም መጽንዒ፣ መንጽሒ፣ ናዛዚ፣ ከሣቲ፣ መስተፍሥሒ ይባላሉ:: በዚህ ጉዳይ ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፹፯ ላይም ስለተገለጸ ተጨማሪ ማብራሪያ ከዚያ ይመልከቱ::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፹፰

"ነገር ግን፥ አብን እንድወድ ዓለም ሊያውቅ፥ አብም እንዳዘዘኝ፥ እንዲሁ አደርጋለሁ:: ተነሡ ከዚህ እንሒድ" (ዮሐ. ፲፬፥፴፩):: ወልድ አብን ይወደዋል:: እንደሚወደውም በዚህ ኃይለ ቃል ተገልጿል:: አብም ወልድን ይወደዋል:: አብ ወልድን እንደሚወደው በዮርዳኖስ ወንዝ እና በደብረ ታቦር ታውቋል:: "ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ወሎቱ ስምዕዎ" የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት በማለቱ ታውቋል:: በዚህም አብ ወልድን እንደሚወደው ወልድም አብን እንደሚወደው ዓለም ዐወቀ:: ኢየሱስ ክርስቶስ አብ አዘዘኝ ማለቱ ሰው ሆኜ ዓለምን አድን ዘንድ ፈቃዴ እንደሆነ የእርሱም ፈቃዱ ነው ማለት ነው:: ሰው የሆነው ታዝዞ መታዘዝን ሊያስተምረን ነውና:: "ልህቀ በበሕቅ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ እንተ ይእቲ እሙ" እንዲል::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፹፱

"እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ ገበሬውም አባቴ ነው" (ዮሐ. ፲፭፥፩):: ኢየሱስ ክርስቶስ የወይን ግንድ እየተባለ ይጠራል:: በእርሱ አምነን በእርሱ የምንኖር እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ ቅርንጫፎች እንባላለን:: ቅርንጫፍ ያለ ግንድ ሕያው ሆኖ መኖር እንደማይችል ሁሉ ምእመናንም ሕይወታቸው ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ተለይተው አይኖሩም:: ገበሬውም አባቴ ነው ማለቱ ተክል በገበሬ እንደሚተከል የኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆንም በአብ ፈቃድ የሆነ ስለሆነ እንዲህ አለ:: ይኸውም በተለየ አካሉ አብ ይጠራ እንጂ የራሱ የወልድም የመንፈስ ቅዱስም ፈቃድ መሆኑን መረዳት ይገባል:: ወይን በዘሩት በሦስት ዓመት ይደርሳል:: ጌታም ማስተማር ከጀመረ ከሦስት ዓመት በኋላ ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቆርሶ እኛን አድኖናል:: በእርሱም ሕያዋን እንድንሆን አድርጎናል::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፺

"እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅኹ በፍቅሩም እንደምኖር፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችኹ" (ዮሐ. ፲፭፥፲):: እግዚአብሔር ፍቅር ነው:: ይህ ማለት ፍቅር የባሕርይው ነው ማለት ነው:: አብና ወልድ የሚኖሩት በአንድ ፍቅር ነው:: ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ የአባቴን ትእዛዝ ጠበቅኹ ማለቱ ሰው ሆኖ ሕገ ኦሪትን መፈጸሙን ለማጠየቅ ነው:: ይኸውም በስምንተኛ ቀን መገረዝን፣ በአርባኛ ቀን ቤተመቅደስ መግባቱን እና የመሳሰሉትን ነው:: ከዚህ ላይ የአባቴ ትእዛዝ ብሎ ይግለጻቸው እንጂ የእርሱም ትእዛዝ ናቸው:: ጌታ ሰው የሆነው የእውነትን መንገድ (ፍኖተ ጽድቅን) ሊያሳየን ነው:: ስለዚህ የትእዛዛት ባለቤት ሆኖ ሳለ ትእዛዛትን በመፈጸም አሳየን:: ይኸውም እኛ እርሱን አርዓያ አድርገን ትእዛዛትን እንጠብቅ ዘንድ ነው:: ትእዛዛትን ብንጠብቅ በእርሱ ፍቅር እንደምንኖርም ነግሮናል:: ከላይ የአባቴ ትእዛዝ ብሎት የነበረውን ከዚያው ቀጥሎ "ትእዛዜ" ብሎ ባለቤትነቱን ገለጸ:: በዚህም በአምላክነት አብም ወልድም አንድ መሆናቸውን እንረዳለን::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፺፩

"ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" (ዮሐ. ፲፭፥፲፫)። የፍቅር ፍጻሜ የሚባለው ይህ ነው። ወዳጆቹን ለማዳን ራሱን አሳልፎ መስጠት ነው። ከራስ በላይ ለሌላው ማሰብ የፍቅር ዋና መገለጫ ነው። ክርስቶስ ይህንን አሳይቶናል። የበደልነው እኛ የሰው ልጆች ሆነን ሳለ ስለእኛ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እኛን አዳነን። ቅዱሳን ለእርሱ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን ፍቅር በተለያየ መልኩ ገልጸዋል። ደናግል ፈተናውን ተቋቁመው በድንግልናቸው በመጽናት፣ ሰማዕታት መከራውን ታግሠው ስለእርሱ በመመስከር ገልጸዋል። ወተዐገሡ ሞተ መሪረ በእንተ መንግሥተ ሰማያት እንዲል። መነኮሳት ጾብዐ አጋንንትን ግርማ ሌሊትን ድምፀ አራዊትን ታግሠው ፍቅሩን ገለጹ። ሊቃውንት አንድነቱን ሦስትነቱን ተግተው በማስተማር ገልጸዋል። እግዚአብሔር እንዲሁ ስለወደደን እኛን ለማዳን ሰው ሆኖ በመስቀል ተሰቅሎ አዳነን። ክርስትና ከራስ በላይ ማሰብ ነው። ሌላውንም እንደ ራስ ወዶ ለሌላው መሥዋዕት መሆን ነው። የፍቅር ፍጻሜ የተባለው ይህ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፺፪

"እኔ መረጥኋችኹ እንጂ እናንተ አልመረጣችኹኝም አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችኹ፥ ልትሔዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬያችኹም ሊኖር ሾምኋችኹ" (ዮሐ. ፲፭፥፲፮)። ጌታ ሐዋርያትን መርጧቸዋል እንጂ ጭፍራ አለቃውን፣ ማኅበር አበ ማኅበሩን መርጦ እንዲሾም ሐዋርያት ጌታ ኢየሱስን አልሾሙትም አልመረጡትም። እርሱ መርጦ ሾሟቸዋል መርጧቸዋል እንጂ። አብን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በስቁል ወልድከ በቅንው ወልድከ (በተሰቀለ ልጅህ በችንካር በተቸነከረ ልጅህ) ብለን ብንለምነው ሁሉን ያደርግልናል። ዮሐ. ፲፬፥፲፫ ላይ በነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፹፩ ላይ እንደተማማርነው አብን በስሜ ለምኑት እኔ አደርገዋለሁ ብሎ አድራጊው እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ገልጾ ነበር። በዚህኛው በዛሬው ክፍል ደግሞ በስሜ ብትለምኑት ይሰጣችኋል ብሎ ሰጪው (አድራጊው) አብ እንደሆነ ገለጸ። ሁለቱ ቃላት እርስ በእርሳቸው አይቃረኑም። በሥላሴ የአንድነት ሥራ አንዱ ቢጠቀስ እንኳ ለሁለቱም የተነገረ እንደሆነ ማሰብ ያስፈልጋልና። ከሁለቱም መንፈስ ቅዱስም እንዳለበት ልብ ማድረግ ያስፈልጋል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፺፫

"ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችኹ አጽናኝ ርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፥ ርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል" (ዮሐ. ፲፭፥፳፮)። መንፈስ ቅዱስን ከአብ የሚወጣ ብሎ ገልጾታል። በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት አብ ወላዲ አሥራጺ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ይባላል። ወልድም ከአብ ወጣ ይባላል። "ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለኹ ደግሞ ዓለምን እተወዋለኹ ወደ አብም እኼዳለኹ" እንዲል (ዮሐ. ፲፮፥፳፰)። መንፈስ ቅዱስም ከአብ ወጣ ይባላል። ወልድ ከአብ የወጣውን አወጣጥ ሊቃውንት ልደት ብለው ሲገልጹት፣ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣውን አወጣጥ ደግሞ ሥርፀት ይሉታል። ስለዚህም ወልድን ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስን ሠራፂ እንለዋለን። አብን ደግሞ ወላዴ ወልድ አሥራጼ መንፈስ

ቅዱስ እንለዋለን፡፡ አብ ወልድን ስለወለደውና መንፈስ ቅዱስን ስላሠረጸው ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ በፊት ነበረ አንለውም፡፡ በቅድምና ሦስቱ አካላት አንድ ናቸውና፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፺፬

"አሁን ግን ወደላከኝ እኼዳለኹ" (ዮሐ. ፲፮፥፭)፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደላከኝ ወደ አብ እሄዳለሁ አለ፡፡ ይኸውም ውረድ ተወለድ ብሎ ወደላከኝ አብ እሄዳለሁ ማለቱ ነው፡፡ ከዚህም ሰው የሆነው በአብ ፈቃድ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በፈቃድ አንድ ናቸው፡፡ ስለዚህ የአብ ስም ተለይቶ ቢጠቀስም ሁለቱንም የሚመለከት ጉዳይ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ወደአብ እሄዳለሁ የሚለው ምሥጢራዊ ትርጓሜው ምንድን ነው? አብ በሁሉ ቦታ ያለ ነው፡፡ አብ የሌለበት ቦታ የለም፡፡ ወደ አብ እሄዳለሁ ያለው እስከ አሁን አብ ከሌለበት ቦታ ላይ ሆኖ አይደለም፡፡ መጀመሪያውንም አብ ልቡ ነውና፡፡ ወደ አብ እሄዳለሁ ያለው አብ እንደማይራብ፣ እንደማይጠማ፣ እንደማይደክም ከትንሣኤ በኋላም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማይራብ የማይጠማ የማይደክም ይሆናልና ከእንግዲህ ወዲህ በአብ ግብር ጸንቼ እኖራለሁ ሲል ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፺፭

"ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል፡፡ ርሱ ያከብረኛል፥ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና፡፡ ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው ስለዚህ፦ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል አልኹ " (ዮሐ. ፲፮፥፲፫-፲፭)፡፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ይመራል፡፡ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርም የሚለውና ከእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል የሚለው አገላለጽ ወልድ የአብም የመንፈስ ቅዱስም ቃላቸው ስለሆነ ቃልነትን ከእኔ ገንዘብ አድርጎ ይናገራል ማለቱ ነው፡፡ ወልድ ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው ብሏል፡፡ በአምላካዊ ሥራ አንድ ናቸውና፡፡ አብ የወልድም የመንፈስ ቅዱስም ልባቸው ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የአብም የወልድም እስትንፋሳቸው (ሕይወታቸው) ነው፡፡ እርሱ ያከብረኛል የሚለው ይገልጠኛል ማለቱ ነው፡፡ ከራሱ አይነግርም ማለቱ ከራሱ ብቻ አንቅቶ አይነግራችሁም ከእኔ ከወልድም ከአብም በህልውና የሰማውን ይነግራችኋል ማለቱ ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፺፮

"በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችኹ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችኹ አይደለሁም" (ዮሐ.፲፮፥፳፮)፡፡ ጌታ የማዳን ሥራውን ከፈጸመ በኋላ ማለትም ከዕለተ ስቅለት በኋላ መለመን (መማለድ) የለበትም፡፡ በዚህ ምድር ሳለ ግን ሰው የሆነው ለአዳም ቤዛ ለመሆን ስለሆነ ስለአዳም አዳም ሊያደርገው ይገባ የነበረውን እያደረገ አድኖናል፡፡ ምልጃን ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሆኖ የሚቀበል ራሱ ሆኖ ሳለ ምልጃን ስለአዳም ለአዳም ወደ አባቱና ወደመንፈስ ቅዱስ እንዲሁም ወደራሱ አቅርቧል፡፡ ከስቅለት በኋላ ግን እኛ በጌታ ስም እንለምናለን እንጂ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታዬ አብን አይለምንም፡፡ ምክንያቱም ከዚያ በኋላ ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ ተብሏልና፡፡ ጌታዬ አብ ጌታዬ ወልድን በቀኜ ተቀመጥ ብሎታል፡፡

ይኸውም በክብር አንድ መሆናቸውን ይነግረናል። ከትንሣኤ በኋላም እንደ አብ የማይራብ የማይጠማ የማይለምን ሆኖ ይኖራል። ከትንሣኤ በኋላ የማዳን ሥራውን ፈጽሞ ስለሄደ ምልጃን ያቀርባል አንለውም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፺፯

"ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለኹ ደግሞ ዓለምን እተወዋለኹ ወደ አብም እኼዳለኹ" (ዮሐ. ፲፮፥፳፰)። መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣ እንደሚባልና ወልድም ከአብ የወጣ እንደሚባል ከዚህ ቀደም አይተናል። ሊቃውንት ወልድ ከአብ የወጣውን ፀአት ልደት ብለው ሲጠሩት መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣውን ፀአት ደግሞ ሥርፀት ይሉታል። የሁለቱም ቃላት ምሥጢሩ ያው ፀአት ነው። ይህም በሰው ኅሊና ከመታሰብ በላይ ነው። "ልደተ ወልድ ወፀአተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ ይትነከር ወኢይትነገር" እንዲል። አብ ወልድን ያለ እናት ወልዶታል። ይህ ልደትም ከኅሊና በላይ ነው። ምክንያቱም አብ ወልድን ሲወልድ በቅድምና አብም ወልድም አንድ ናቸውና። ወልድ ወደ አብ እሄዳለሁ ማለቱ ሰው የሆነበትን ተልዕኮውን ፈጽሞ በአብ ዕሪና መኖሩን ያመለክታል። ይኸውም አለመራቡን፣ አለመጠማቱንና በጠቅላላው በአምላካዊ ሥራ ጸንቶ መኖሩን ያስረዳል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፺፰

"ሁሉን እንድታውቅ፥ ማንምም ሊጠይቅኽ እንዳትፈልግ አሁን እናውቃለን ስለዚህ፥ ከእግዚአብሔር እንደ ወጣኽ እናምናለን አሉት" (ዮሐ. ፲፮፥፴)። ከእግዚአብሔር ውጭ ሁሉን የሚያውቅ የለም። የፍጡራን ሁሉ ዕውቀት ውስንነት አለበት። ፍጡር በአንድ የትምህርት ዓይነት ምሁር ቢሆን በሌላ የትምህርት ዓይነት ደካማ ነው። በሁሉም የትምህርት ዘርፍ ሁሉን ዐዋቂ መሆን አይችልም። እድሜ ተጨምሮት 8000 ዓመት ቢኖር እንኳ እንኳንስ ስለፍጥረታት ሁሉ ሊያውቅ ራሱንም አጥንቶ መጨረስ አይችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ዕሩቅ ብእሲ (ሰው ብቻ) ስላልሆነ አምላክም ሰውም በመሆኑ ሁሉንም ያውቃል። በሰው ልብ የታሰበውን ከመነገሩ በፊት ያውቀዋል። ፍጡራንን ሳይፈጥራቸው በፊት ያውቃቸዋል። ለዕውቀቱ ወሰን የለበትም። ለዚህም ነው ሐዋርያት "ሁሉን እንድታውቅ፥ ማንምም ሊጠይቅኽ እንዳትፈልግ አሁን እናውቃለን" ብለው የመሰከሩለት።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፺፱

"ልጅህ ያከብርህ ዘንድ፥ በሥጋም ሁሉ ላይ ሥልጣን እንደ ሰጠኸው፥ ለሰጠኸው ሁሉ የዘለዓለምን ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ ልጅህን አክብረው" (ዮሐ. ፲፯፥፩)። አክብረኝ ማለት ግለጠኝ ማለት ነው። ወልድ አብን አከበረው ማለት የማይታይና ረቂቅ የሆነ አብን አንድ ልጁ ወልድ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ስለእርሱ በማስተማር ገለጠው ማለት ነው። አብ ከሁሉ በላይ እንደሆነ ገለጠ አስረዳ ማለት ነው። አብ ወልድን አከበረው ማለት ደግሞ አምላክ እንደሆነ በዮርዳኖስና በደብረ ታቦር የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ መሰከረለት ማለት ነው። ልጅነቱን መሰክሮ ገለጠው ማለት ነው። ሥጋ በተዋሕዶ የቃልን ገንዘብ ሁሉ ገንዘብ በማድረጉ ወልድ እየተባለም ይጠራል። ወልደ አብ ይባላል። ቃልም በተዋሕዶ የሥጋን ገንዘብ ሁሉ ገንዘቡ

በማድረጉ የሰው ልጅ ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ወልደ ማርያም ተብሏል፡፡ ወልደ አብ ወልደ ማርያም የሚባለው ያው አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በሥጋም ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠኸው የሚለው ቃል ስለሰውነት የተነገረ ነው፡፡ ቅድመ ተዋሕዶ ምንም ሥልጣን ያልነበረው ሥጋ በተዋሕዶ በፍጥረታት ሁሉ ላይ የተሾመ ባለሥልጣን አምላክ መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩፻

"እውነተኛ አምላክ ብቻ የኾንኽ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘለዓለም ሕይወት ናት" (ዮሐ. ፲፯፥፫)፡፡ አብ እውነተኛ አምላክ ነው፡፡ ወልድም እውነተኛ አምላክ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስም እውነተኛ አምላክ ነው፡፡ ሦስቱም አካላት አምላክ አምላክ አምላክ ተብለው ቢጠሩም ሦስት አማልክት ናቸው ግን አንልም፡፡ እርስ በእርስ በከዊን ይገናዘባሉና አንድ አምላክ ይባላሉ፡፡ ወልድ አምላክ እንደሆነ ሮሜ ፱፥፭ ላይ ተገልጿል፡፡ ይህ ከሆነ አብ "እውነተኛ አምላክ ብቻ" ተብሎ "ብቻ" የተባለ ለምንድን ነው? የሚለውን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ "ብቻ" ያለው ከፍጡራን ሲለየው ነው እንጂ ከአካላዊ ቃሉ ከወልድና ከአካላዊ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ሲለየው አይደለም፡፡ እንዳልለያቸው ምስክሩ ራሱ ዮሐንስ ሦስቱንም አካላት እግዚአብሔር ብሎ በመግለጹ ይታወቃል (ዮሐ. ፩፥፩-፫)፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፩

"እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርኹኽ" (ዮሐ. ፲፯፥፬)፡፡ እሠራው እፈጽመው ዘንድ የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በአግብዖተ ግብር (ዳግማይ ትንሣኤ) ገለጽኩህ ማለቱ ነው፡፡ የሰጠኸኝን ሥራ ሲል ሥራውን የሰጠው አብ ብቻ ይመስላል፡፡ ነገር ግን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በአምላካዊ ሥራ አንድ ስለሆኑ አብ ተለይቶ ቢጠቀስ እንኳ የወልድም የመንፈስ ቅዱስም እንደሆነ ልብ ማድረግ ይገባል፡፡ ለመሆኑ ወልድ ያደርገው ዘንድ የተሰጠው ሥራ ምንድን ነው? ብለን ብንጠይቅ አካላዊ ግብሩ መወለድ የሆነ ወልድ ጥንተ ግብሩን በሚገልጽ ሁኔታ ከድንግል ማርያም ተወለደ፡፡ ሰው ሆኖ የተወለደውም ለአዳም ቤዛ ሆኖ ተሰቅሎ ያድነው ዘንድ ነው፡፡ የተሰጠው ሥራ የተባለው ይህ ነው፡፡ ሥራውን ማን ሰጠው ከተባለ ግን ይህን ሥራ ለመፈጸም በአብ ፈቃድ በራሱም ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስም ፈቃድ መጥቷል፡፡ ይህ የሦስቱም የአንድነት ሥራ ነው፡፡ ለአዳም ቤዛ መሆንና በተዋሐደው ሥጋ መከራ መቀበል ግን በተለየ አካሉ የወልድ ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፪

"አሁንም፥ አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር ባንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስኽ ዘንድ አክብረኝ" (ዮሐ. ፲፯፥፭)፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ቀዳማዊነት ከሚያሳውቁን ኃይለ ቃሎች አንዱ ይህ ነው፡፡ ብዙዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ስለሚመስላቸው ህልውናው የሚጀምረው ድንግል ማርያም ከጸነሰችው በኋላ ይመስላቸዋል፡፡ ድንግል ማርያም ጸንሳ የወለደችው ቅድመ ዓለም የነበረ እርሷንም አባቶቿንም የፈጠረውን ወልደ እግዚአብሔርን ነው፡፡ ለዚያ ነው ሊቁ አፈ በረከት ማር ኤፍሬም ሶርያዊ "ድንግል ወለደቶ ለገባሪሃ ወውእቱኒ ፈጠረ ወላዲቶ" ያለው፡፡ ትርጉሙ ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው እርሱም እናቱን ፈጠረ ማለት

ነው። ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፻፺፱ ላይና ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻ ላይ እንደተገለጸው ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ አብን አከበረው ተብሎ ነበር። በዚህኛው ክፍል ደግሞ ወልድ አብን አክብረኝ እያለው ነው። ይኸውም ዓለም ያምንብኝ ዘንድ ግለጠኝ ማለቱ ነው። ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ምስጉን ሆኖ የነበረና የኖረ ፍጹም አምላክ ነው። ከድንግል ማርያም በመወለዱም ፍጹም ሰው እንለዋለን። ስለዚህም አንዱን ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ እንለዋለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፫

"ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምኽን ገለጥኹላቸው። የአንተ ነበሩ ለኔም ሰጠኻቸው" (ዮሐ. ፲፯፥፮)። ምሥጢረ ሥላሴ ወልደ እግዚአብሔር ሰው እስከሚሆን ድረስ ለብዙዎች አይታወቅም ነበረ። ወልደ እግዚአብሔር ሰው ከሆነ በኋላ ግን ለሁሉ ግልጥ ሆነ። ወልድ ስለአብ መሰከረ። ወልድ አብን በትምህርቱ ገለጠው። አብም ወልድን በተአምራት ገለጠው። ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ ሰው ሆኖ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን አንድነት አስተማረን። ኢየሱስ ክርስቶስ ከዓለም ለሰጠኸኝ ማለቱ ስለሰውነቱ እንግድነት ነው። ከተዋሕዶ በፊት ምንም ያልነበረው ሥጋ በተዋሕዶ ጊዜ የሁሉ ገዢ የሁሉ ፈጣሪ የሁሉ ንጉሥ ሆኗል። የአንተ ነበሩ ማለቱ አብ የፍጥረታት ሁሉ ባለቤት መሆኑን ያሳውቃል። ለእኔም ሰጠኻቸው ሲል ደግሞ ሥጋ በተዋሕዶ የሁሉ ባለቤት መሆኑን ያስረግጥልናል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፬

"የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው የአንተውም የእኔ ነው" (ዮሐ. ፲፯፥፲)። ኢየሱስ ክርስቶስ ለአብ የእኔ የሆነ ሁሉ የአንተ ነው ብሎታል። ይህ ብቻ ሳይሆን የአንተ የሆነውም የእኔ ነው ብሎታል። ይህም ማለት አብ አምላክ ነው። አብ አምላክ እንደሆነ ወልድም አምላክ ነው ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ አብም ጌታ ነው ማለት ነው። አብ ፈጣሪ እንደሆነ ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስም ፈጣሪ ነው። የአብ የሆነው የአምላክነት ሥራ ሁሉ የወልድም ነው። የወልድ የሆነው የአምላክነት ሥራ ሁሉ የአብም ነው። ይህንን ስንናገር መንፈስ ቅዱስ እንዳልዘነጋነው ማስታዎስ ይገባል። በአምላክነት ሥራዎች ለአብም ለወልድም የተነገሩት ነገሮች ሁሉ ለመንፈስ ቅዱስም ይነገራሉ። ለመንፈስ ቅዱስ የተነገሩት ሁሉም ለአብ ለወልድ ይነገራሉ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፭

"ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምኽ ጠብቃቸው" (ዮሐ. ፲፯፥፲፩)። ይህም ማለት እኛ በባሕርይ አንድ እንደሆንን እነርሱ ደግሞ በጸጋ አንድ ይሆኑ ዘንድ ማለት ነው። ሁላችንም ክርስቲያኖች በክርስቶስ አንድ ነን። በጥምቀት አማካኝነት ከልዑል እግዚአብሔር ተወልደናል። ስለዚህም ሁላችንም የቤተ ክርስቲያን ልጆች ነን። ወልድ የአብ የባሕርይ ልጅ ነው። አብ የወልድ የባሕርይ አባት ነው። እኛ ግን እግዚአብሔርን አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር እያልን ስንለምነው "አባታችን" ማለታችን በጥምቀት አማካኝነት

ከእርሱ በጸጋ ስለተወለድን ነው። አብ ቅዱስ አባት እንደሆነ ሁሉ ወልድም ቅዱስ ልጅ ነው። የእግዚአብሔር ስም ጠባቂ ስለሆነ በስምህ ጠብቃቸው አለ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፸፰

"እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ፥ ወደ ኋላ አፈግፍገው በምድር ወደቁ" (ዮሐ. ፲፰፣፮)። አይሁድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ይሰቅሉት ዘንድና መከራ ሊያጸኑበት ሊይዙት በሄዱ ጊዜ ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንን ትፈልጋላችሁ ቢላቸው ኢየሱስን እንፈልጋለን አሉት። ይህን ጊዜ እኔ ነኝ ሲላቸው ሁላቸውም አፈግፍገው ወደ ምድር ወድቀዋል። ይኸውም ጌታ መከራን የተቀበለው በፈቃዱ እንጂ በግድ እንዳልሆነ እንድንረዳ ነው። በፈቃዱ መከራን ተቀብሎ መከራ ነፍስን አራቀልን። ኢየሱስ ክርስቶስ በፈቃዱ ተራበ፣ በፈቃዱ ተጠማ፣ በፈቃዱ ደከመ፣ በፈቃዱ ተሰቀለ ወዘተ እንላለን እንጂ በግድ ተራበ፣ በግድ ተጠማ፣ በግድ ደከመ፣ በግድ ተሰቀለ አንለውም። ሁሉንም ያደረገው በፈቃዱ ነውና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፸፮

"እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለኹ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለኹ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው" (ዮሐ. ፲፰፣፴፯)። ወልደ እግዚአብሔር ሰው የሆነው ለእውነት ኖሮ፣ ለእውነት መሞትን ያሳየን ዘንድና በውሸት ተታሎ የወደቀውን ሰው ተሰቅሎ ሙቶ ያድነው ዘንድ ነው። ለእውነት ልመሰክር ተወልጃለሁ አለ። እውነት የተባለ አብ እውነት እንደሆነ ልመሰክር መጥቻለሁ ማለቱ ነው። ወደ ዓለም መጥቻለሁ ያለው ከዚህ ላይ ዓለም ያለው ሰውን ነው። ስለዚህ ወደዓለም መጥቻለሁ ማለቱ ሰው ሆኛለሁ ማለቱ ነው። ሰው የሆነውም አምላክነቱን ሳይለቅ ነው። የጌታን ድምፅ የሚሰማ ሰው ከእውነት የሆነ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፸፰

"ኢየሱስም የሾህ አክሊል ደፍቶ ቀይ ልብስም ለብሶ ወደ ውጭ ወጣ" (ዮሐ. ፲፱፣፭)። አይሁድ ለመሳለቅ ብለው ንጉሥ ሆይ እያሉ የሾህ አክሊል ሠርተው በጌታ ራስ ላይ አኖሩ። ቀይ ልብስም አልብሰው ወደ አደባባይ አወጡት። ፍጡር በፈጣሪው ላይ ዐመፀ። ጌታ ሊሰቅሉት የመጡትን ሰዎች በአንድ ጊዜ ማጥፋት ይችል ነበር። ነገር ግን የመጣው ሰውን ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ ስላልሆነ ይህንን ሁሉ መከራ በፈቃዱ ተቀበለ። የፍጥረታት ሁሉ ንጉሥ ለሆነው ለእርሱ የእሾህ አክሊል ደፉበት። እርሱም እንደሚታረድ በግ ምንም ሳይመልስ የደረሰበትን መከራ ሁሉ ተቀበለ። በመከራውም መከራችንን አራቀልን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፸፱

"ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን፦ አንቺ ሴት፥ እንሆ፥ ልጅሽ አላት። ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን፦ እናትኽ እነኋት አለው። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት" (ዮሐ. ፲፱፣፳፮-፳፯)። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ አማካኝነት ለሁላችን የተሰጠች እናት ናት። የዮሐንስ ወላጅ እናት ሌላ መሆኗ ይታወቃል። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ለሚወደው ደቀመዝሙር

የሚወዳትን እናቱን እናት ትሆነው ዘንድ ሰጠው። የሚወደውን ደቀመዝሙር ደግሞ ልጅ ይሆናት ዘንድ ለሚወዳት እናቱ ሰጣት። ደቀመዝሙሩ ዮሐንስም ወደ ቤቱ ወሰዳት ተብሏል። ብዙዎች የክርስቶስን እናት ድንግል ማርያምን ሲጠሏትና ሲሳደቡ ይስተዋላሉ። ጌታ ኢየሱስ ሕግን ሁሉ ፈጽሟል። ከሕግ አንዱ ደግሞ እናትና አባትህን አክብር የሚል ነው። ስለዚህ ጌታ እናቱን አክብሯል። ውሃ እየቀዳ ይታዘዛት እንደነበረም በተአምረ ኢየሱስ ተጽፏል። ስለዚህ ድንግል ማርያምን መጥላት ጌታ የወደደውን መጥላት ነው። እኛ ግን እርሱ ያከበራት እናቱን እንወዳታለን። የጸጋ ምስጋናንና የጸጋ ስግደትንም እናቀርብላታለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲

"የኢየሱስንም ሥጋ ወስደው፥ እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ፥ ከሽቱ ጋራ በተልባ እግር ልብስ ከፈኑት" (ዮሐ. ፲፱፥፵)። አይሁድ መድኃኒታቸውን ጠሉት። ከበሽታቸው የሚፈውሳቸውን መድኃኒት በጥፊ መቱት፣ ተሳለቁበት፣ ረገጡት፣ ማን መታህ እያሉ ተዘባበቱበት። እርሱ ግን ሁሉንም እኛን ለማዳን ተጠቀመበት። ኢየሱስ ክርስቶስ ውሱንም ምሉዕም ነው። እንደ አምላክነቱ በሁሉ ቦታ ያለ ሲሆን እንደ ሰውነቱ ደግሞ ሦስት ክንድ ከስንዝር ነው። እንዲህም ስለሆነ እነዮሴፍና ኒቆዲሞስ ገንዘው ቀብረውታል። እንደ ሰውነቱ በተልባ እግር ልብስ የተከፈነው እርሱ እንደ አምላክነቱ ግን በዓለሙ መልቶ፣ በኪሩቤል ጀርባ ተቀምጦ አለ ነበረ ይኖራል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲፩

"እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችኹ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችኹ ዐርጋለኹ ብለሽ ንገሪያቸው አላት" (ዮሐ. ፳፥፲፯)። አብ የወልድ የባሕርይ አባት እንደሆነ ደጋግመን ተመልክተናል። አብ ለእኛ ለክርስቲያኖች አባት መባሉ ግን የጸጋ አባትነት ነው። በዚህኛው አባትነት (ለእኛ ባላቸው የጸጋ አባትነት) ወልድም መንፈስ ቅዱስም አባት ሊባሉ ይችላሉ። አብ አምላካችን ነው። አምላካችሁ ተብሎ የተገለጸው ለዚህ ነው። ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ አብን አምላኬ ማለቱ ስለምንድን ነው? ቢሉ። ወልድ የተዋሐደውን ሥጋ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለው የአንድነት ግብር የፈጠረ እርሱ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰውነቱ አምላኬ ብሏል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲፪

"ቶማስም፦ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት" (ዮሐ.፳፥፳፰)። ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲፩ ላይ እንደተማማርነው አየሱስ ክርስቶስ ስለሰውነቱ አብን አምላኬ ብሎታል። በአምላክነቱ ግን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ እንደሆነ ማስተዋል ይገባል። ከሙታን ከተነሣ በኋላ የጌታን መነሣት ቶማስ ተጠራጥሮ ስለነበረ የጌታን ጎን ዳሰሰ። በዳሰሰ ጊዜም እጁን አቃጠለው። ይህን ጊዜ ቶማስ ጌታዬ አምላኬ ብሎ ተናገረ።  ስለሆነም ከጌታ እግር ስር ቁጭ ብለው የተማሩ ሐዋርያት የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ተረድተው ለዓለም ሁሉ አስተማሩ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲፫

"ደግሞም፦ የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደ ሰማይ እየተመለከታችኹ ስለ ምን ቆማችኋል ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሔድ እንዳያችኹት፥ እንዲሁ ይመጣል አሏቸው" (የሐዋ.ሥራ ፩፥፲፩)። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ አርባ ቀን ትምህርተ ኅቡዓትንና ኪዳንን እያስተማረ ቆየ። በዐርባኛው ቀን ሐዋርያቱ እያዩት ወደሰማይ ዐረገ። በሁሉ ቦታ ያለ እርሱ በተዋሐደው ሥጋ የርቀት ያይደለ የርኅቀት ዕርገትን ዐረገ። ወደሰማይ ያረገው ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ በሙታንና በሕያዋን ለመፍረድ ይመጣል። ያን ጊዜ የሚመጣው ለፍርድ ነው። ጻድቃንን በቀኙ ኃጥኣንን በግራው ሊያቆም። ለሁሉም እንደየሥራው ሊከፍለው ይመጣል። መቼ እንደሚመጣ ግን ከእርሱ ከእግዚአብሔር ውጭ የሚያውቅ ማንም የለም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲፬

"በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር" (የሐዋ.ሥራ ፪፥፬)። ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ ከሞላባቸው በኋላ በነበራቸው ቋንቋ ላይ ፸፩ ቋንቋ ተገልጾላቸው በዓለም ሁሉ ቋንቋ ወንጌልን አስተማሩ። መንፈስ ቅዱስ በዓለም ሁሉ በምልዓት የሚኖር ነው። መንፈስ ቅዱስ የሌለበት ቦታ የለም። ታዲያ በሁሉ ቦታ ካለ በሐዋርያት ብቻ ሞላባቸው መባሉ ለምንድን ነው ከተባለ ረድኤትን አሳደረባቸው። ጥቡዓን እንዲሆኑ አደረጋቸው። ምሥጢር ገለጠላቸው ማለት ነው። በእሳት አምሳል የታየው በተለየ አካሉ መንፈስ ቅዱስ ሲሆን ሞላባቸው ተብሎ የተነገረው ደግሞ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ነው። መጻሕፍት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን መንፈስ ቅዱስ ይሉታልና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲፭

"የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድናል" (የሐዋ. ሥራ ፪፥፳፩)። ከሌላ ቦታ ላይ ራሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት አይገባም አላውቀውም" ብሎ አስተምሯል። ከዚህ ላይ ደግሞ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል ብሏል። የዚህ ትርጉሙ ምንድን ነው? በማርቆስ ወንጌል ላይ ስለ አጋንንት "ርኩሳን መናፍስትም ባዩት ጊዜ በፊቱ ተደፍተው፦ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ እያሉ ጮኹ" ተብሏል (ማር. ፫፥፲፩)። ታዲያ አጋንንትም ይድናሉ ማለት ነውን? አይደለም። የጌታን ስም የሚጠራ ማለት በእርሱ አምኖና ተጠምቆ መልካም ሥራን የሚሠራ ሁሉ ይድናል ማለት ነው። ሳያምንና ሳይጠመቅ መዳን እንደማይቻል። "ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል" ተብሏልና (ማር. ፲፮፥፲፮)። አንድ ሰው አምኖ ተጠምቆ መልካም ሥራ ካልሠራ እንደማይድንም "ሃይማኖት ያለምግባር የሞተች ናት" ተብሎ ተገልጿል (ያዕ. ፪፥፲፯)።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲፮

"እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፥ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና_____ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው ለዚህም ነገር እኛ ኹላችን ምስክሮች ነን" (የሐዋ. ሥራ ፪፥፳፬-፴፪)። ኢየሱስን እግዚአብሔር ከሙታን መካከል ለይቶ አስነሣው ይላል። እግዚአብሔር

በሚለው ስም አብም፣ ራሱ ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስም፣ መንፈስ ቅዱስም ይጠሩበታል። "አንሰ ሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" እንዲል። ስለዚህ እግዚአብሔር አስነሳው ሲል በአምላክነቱ ሥልጣን እንደተነሣ ያሳውቃል። አብ አስነሣው፣ መንፈስ ቅዱስ አስነሣው ቢልም ይሆናል። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በማስነሣት አንድ ናቸውና። እኔ በፈቃዴ አኖራታለኹ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። "ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ" እንዲል (ዮሐ. ፲፣፲፰)። በዚህ ጊዜ አስነሽ ወልድ እንደሆነ ተናግሯል። ነገር ግን በተለየ ወልድ ቢጠቀስም በአምላካዊ ሥራ አንዱ ቢጠቀስ እንኳ ሁለቱንም የሚመለከት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲፯

"እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችኹትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በርግጥ ይወቅ" (የሐዋ. ሥራ ፪፣፴፮)። ሥጋን አምላክ ያደረገው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር በሚለው ስም ደግሞ አብም ወልድም መንፈስ ቅዱስም እንደሚጠሩ በነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲፮ ተማምረናል። ሦስቱ አካላት በማክበር፣ በክብር አንድ ናቸው። ስለዚህ ሥጋን አምላክ አድርጎ ማክበር የሦስቱም የአንድነት ሥራ ነው። ለሥጋ ክብር የሆነው ግን በተለየ አካሉ ወልድ ነው። ሰው የሆነው ወልድ ነውና። ሲጀምር ሥጋ ከበረ ማለት ቃልን ሆነ ማለት ነው። ቃል ነድየ ወረደ መባሉም ሰውን ሆነ ማለት ነው። ስለዚህ ለሥጋ ክብሩ (ቅብዑ) ቃል መሆኑን ልብ ይሏል። በማክበር ግን ሦስቱም አካላት አንድ ስለሆኑ አብም ቀባዒ ይባላል። መንፈስ ቅዱስም ቀባዒ ይባላል። መንፈስ ቅዱስን ቀባዒ ሲለው እስመ ውእቱ ቀብዖ ተብሎ ተገልጿል። አስተውል እስመ ውእቱ ቅብዐ ኮኖ አላለም። ቀባዒነቱን ለማስረገጥ ቀብዖ ብሎ በግልጽ ተናገረ እንጂ (ማቴዎስ ወንጌል አንድምታ ምዕራፍ ፩)። ሥጋ ቃልን በተዋሐደ ጊዜ አምላክ ሆነ። ቃልም ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ ሰው ሆነ። በተዋሕዶ የሥጋ ገንዘብ ለቃል፣ የቃል ገንዘብ ለሥጋ ሆነ። ይህ ሲሆን ቃልም ሥጋም ቅድመ ተዋሕዶ ያለውን ገንዘብነት ሳይለቁ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲፰

"ጴጥሮስም፦ ንስሓ ግቡ፥ ኀጢአታችኹም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችኹ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችኹ" (የሐዋ. ሥራ ፪፣፴፰)። በጣም ብዙ ጊዜ ደጋግመን እንደተመለከትነው በሦስቱ አካላት ማለት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ የአንድነት ሥራ አንዱ ተለይቶ ቢጠራ እንኳ ሁለቱንም የሚያካትት ነው። ቅዱስ ጴጥሮስም ሰዎች ድኅነትን ያገኙ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ብሎ አስተምሯል። በተለየ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ቢጠቀስም በአብ ስም ተጠመቁ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠመቁ ማለቱ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል። የምንጠመቀው በሦስቱም አካላት ስም ሲሆን ልጅነትንም የምናገኘው ከሦስቱም ነው። ስንጠመቅ የአብም የወልድም የመንፈስ ቅዱስም የጸጋ ልጅ እንሆናለን። "እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀመዛሙርቴ አድርጓቸው" እንዲል (ማቴ.፳፰፣፲፱)። የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ታገኛላችሁ ሲል

ተለይቶ መንፈስ ቅዱስ ይጠራ እንጂ የአብን ጸጋ የወልድን ጸጋ ታገኛላችሁ ሲል ነው። ጸጋ የተባለውም ልጅነት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፲፱

"እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር" (የሐዋ.ሥራ ፪፥፵፯)። ጌታ አንድ ጊዜ ተሰቅሎ ዓለምን አድኖታል። እግዚአብሔር አድኖኛል እያሉ ለክፉ ሥራቸው ማስተባበያ የሚሰጡ አንዳንድ አሳዛኝ ሰዎች አሉ። እግዚአብሔር የእርሱን የማዳን ድርሻ በመስቀል ላይ ፈጽሟል። የሰው ድርሻ ግን ይቀራል። ሰው እግዚአብሔር ያደረገለትን የማዳን ሥራ አምኖ መጠመቅና መልካም ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል። ይህን ሳያደርግ ድኛለሁ ማለት ግን ራስን ማታለል ነው። "ጌታም ዕለት ዕለት የሚድኑትን በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር" ተብሎ የተገለጸው ድኅነት የሰውን ልጅ ነጻ ፈቃድ መሠረት አድርጎ ለሰው የሚፈጸም እንደሆነ የሚያስረዳ ኃይለ ቃል ነው። ምእመናን እያመኑ እየተጠመቁ መልካም ሥራን እየሠሩ ከክርስቶስ የማዳን ሥራ ይሳተፋሉ እንጂ ሳያምኑ፣ ሳይጠመቁና መልካም ሥራን ሳይሠሩ ዝም ብሎ ድኛለሁ በማለት ከክርስቶስ የማዳን ሥራ መሳተፍ አይቻልም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፳

"ጴጥሮስ ግን፦ ብርና ወርቅ የለኝም ይህን ያለኝን ግን እሰጥኻለኹ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው" (የሐዋ. ሥራ ፫፥፮)። "ኵሉ ብነ እንዘ አልብነ ኵሉ" ሁሉ ሳይኖረን ሁሉ አለን እንዲሉ። ሐዋርያት የገንዘብ ድኻዎች የጸጋ እግዚአብሔር ሀብታሞች ነበሩ። በዘመናችን በሐዋርያት እግር የተተኩት አንዳንድ ጳጳሳትን ስንመለከት ደግሞ የገንዘብ ሀብታሞች የጸጋ እግዚአብሔር ድኻዎች ሆነው እናገኛቸዋለን። ሐዋርያት ሰውን የሚያድኑት ከፈጣሪያቸው ከኢየሱስ ክርስቶስ ባገኙት የመፈወስ ጸጋ ነው። እነ ቅዱስ ጴጥሮስ ድውያንን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይፈውሱ ነበር። የእርሱ ስም ከኃያላን ሁሉ የበለጠ ታላቅ ኃያል ነውና። ስለሆነም በከበረ ቦታ፣ በከበረ ጊዜ ይነገራል እንጂ በቀልዱም በዋዛ ፈዛዛውም ኢየሱስ ኢየሱስ እያሉ መጥራት ተገቢ አይደለም። ክቡር ስም መጠራት ያለበት በክቡር ቦታና በከበረ ነገር ነው። በጸሎት ጊዜ ኢየሱስ ኢየሱስ ኢየሱስ ዘሠረፀ እም ቤተ ሌዊ ኮሬባዊ መለኮታዊ እምድንግል ተወልደ እያልን እናመሰግነዋለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፳፩

"የአብርሃምና የይሥሐቅ የያዕቆብም አምላክ፥ የአባቶቻችን አምላክ፥ እናንተ አሳልፋችኹ የሰጣችኹትንና ሊፈታው ቈርጦ ሳለ በጲላጦስ ፊት የካዳችኹትን ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው" (የሐዋ. ሥራ. ፫፥፲፫)። ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው ማለት አምላክነቱን በደመና ሁኖ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ አብ ገለጠው ማለት ነው። የአብርሃምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ ተብሎ ስለአብ የተነገረ ቢሆንም "አምላክ" መባል ሦስቱ አካላት በአንድነት የሚጠሩበት ስለሆነ ወልድም አምላክ ነው። መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው። ጌታ የአብርሃም

የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ እየተባለ ተጠርቷል። በዚህም የደጋጎች አምላክ እንደሆነና በደጋጎች ቅዱሳን መጠራት እንደሚፈልግ እንረዳለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፳፪

"መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና" (የሐዋ. ሥራ ፬፥፲፪)። መዳን ያለው በእግዚአብሔር ነው። በትንቢተ ኢሳይያስ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም" ብሎ መዳን የሚገኝ ከእግዚአብሔር መሆኑን ገልጿል። ኢየሱስ ክርስቶስም እግዚአብሔር ስለሆነ መዳን በሌላ በማንም የለም በኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ተብሎ ተገልጿል። ይህ አነጋገር በባህርይው የሚያድን እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን የሚያመለክት አነጋገር ነው። ከእግዚአብሔር በተቀበሉት የማዳን ጸጋ የሚያድኑ ቅዱሳን ግን አሉ። እነርሱ በጸጋ ያድናሉ። "አገልጋይ የሆነ መልአክ ሩፋኤል ወደ ጦቢት ተላከ ጦብያንም በራጉኤል አገር ከሞት አዳነው" እንዲል (፩ኛ መቃ. ፫፥፲፱)። ሩፋኤል እንዳዳነ በዚህ ተገልጿል። ሩፋኤልም ሌሎች ቅዱሳንም ማዳናቸው የጸጋ ነው። የእግዚአብሔር ማዳን ግን የባሕርይው ስለሆነ ከሰማይ በታች ሌላ የሚያድን የለም አለ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፳፫

"በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናኽ በኢየሱስ ላይ____" (የሐዋ. ሥራ ፬፥፳፯)። ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀባ እየተባለ ይጠራል። ክርስቶስ ማለት ትርጉሙ ቅቡዕ (የተቀባ) ማለት ነው። የተቀባ ማለትም በአምላክነት የከበረ ማለት ነው። አፍቀርከ ጽድቀ ወዐመፃ ጸላዕከ በእንተዝ ቀብዐከ እግዚአብሔር ቅብዐ ትፍሥሕት እምእለ ከማከ እንዲል። እለከማከ ከተብሉት ከነቢያት የበለጠ የደስታ ዘይትን (አምላካዊ ክብርን) ቀባህ (አከበረህ) ተብሎ እንደተገለጸው ክርስቶስ ስለሰውነቱ ቅቡዕ ይባላል። ስለሰውነቱ ራሱን የሰው ልጅ እያለ ይገልጽ እንደነበረው ሁሉ በዚህ አግባብ ቅቡዕ እየተባለ ይጠራል። በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ የሚለውም ስለሰውነቱ የተነገረ መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል። በመቅባት (በማክበር) ሦስቱ አካላት አንድ ናቸው። ተለይቶ አንዱ ቢጠራ እንኳ ሁለቱንም የሚገልጽ አነጋገር መሆኑን ደጋግመን ተመልክተናል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፳፬

"ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ማስተማርንና መስበክን አይተዉም ነበር" (የሐዋ. ሥራ ፭፥፵፪)። የክርስትና አስተምህሮ ዋና ማዕከሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ የሐዋርያት ቀዳሚ ትምህርት ስለእርሱ ማስተማር ነበር። ስለእርሱ ማስተማርን አይተውም ነበር። አይሁድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላላመኑ ሌላ መሲሕን ይፈልጉ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ሐዋርያት አብራርተው ነግረዋቸዋል። ጌታ ራሱም ብዙ ጊዜ መሲሑ እርሱ መሆኑ በቃልም፣ በተአምራትም ነግሯቸው አሳይቷቸውም ነበር። ነገር ግን እነርሱ የጠበቁት ከሮም ቅኝ ግዛት ነጻ የሚያወጣ ሥጋዊ ንጉሥን (መሲሕን) ነበር። ቅዱሳት መጻሕፍት ስለመሲሑ የተናገሩትን ትተው የራሳቸው ኅሊና የፈጠረውን መሲሕ ስለጠበቁ በኢየሱስ ክርስቶስ አላመኑም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፹፫

"እነሆ፥ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለኹ አለ" (የሐዋ. ሥራ ፯፥፶፮)። ቅዱስ እስጢፋኖስ ስለኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎ መሰከረ። የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየ። እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ያለ ስለሆነ ይህ ቀኙ ነው ይህ ግራው ነው ተብሎ ተወስኖ የሚነገርለት አይደለም። ብዙ ጊዜ ሥልጣኑን ቀኝ ብሎ ይገልጸዋል። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስን በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየሁት ማለቱ በእግዚአብሔርነት ሥልጣኑ አየሁት ማለቱ ነው። ከትንሣኤ በኋላ መራብ መጠማት መታመም ሳይኖርበት በአምላካዊ ግብር ጸንቶ ይኖራልና። ሰማያት ተከፈቱ ማለቱ ሰማይ የሚከፈት የሚዘጋ ሆኖ አይደለም። የተዘጋ ቤት ሲከፈት የቤቱ ምሥጢር እንደሚታወቅ ሁሉ ሰማያዊ ምሥጢር ተገለጠልኝ ሲል ሰማይ ተከፈተ አለ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፹፬

"ጌታ ሆይ፥ ማን ነህ አለው። እርሱም፦ አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብኻል አለው" (የሐዋ. ሥራ ፱፥፭)። ከትንሣኤ በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ መሳደድ የለበትም። ነገር ግን የምእመናን ራስ፣ የቤተ ክርስቲያን አካል ስለሆነ ምእመናን መከራ ሲደርስባቸው የምእመናንን ስደትና መከራ የራሱ ስደትና መከራ እንደሆነ አስቦ ሳውልን ለምን ታሳድደኛለህ? ብሎታል። ሳውልም ተጸጽቶና እርሱን ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ ክርስቲያን ሆነ። ወንጌልን በየሀገሩ በማስተማሩም ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለመባል በቃ። ክርስቶስ የወይን ግንድ ነው። እኛ ምእመናን ደግሞ ቅርንጫፎቹ ነን። ቅርንጫፍ ከግንዱ ካልተለየ ለምልሞ፣ አብቦ ጥሩ ፍሬን ያፈራል። እኛም ከኢየሱስ ክርስቶስ ካልተለየን በመልካም ሥራ አሸብርቀን ገነት መንግሥተ ሰማያት እንገባለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፹፭

"እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኀይልም ቀባው፥ ርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከርሱ ጋራ ነበረና" (የሐዋ. ሥራ ፲፥፴፰)። በመንፈስ ቅዱስ ቀባው የሚለው ትርጉሙ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ቀባው ማለት ነው። ይኸውም ከመታሰብ በላይ የሆኑ አምላካዊ ሥራዎችን ቅዱሳት መጻሕፍት ለመንፈስ ቅዱስ አድለው ቢናገሩም መቀባት የሦስቱም የአንድነት ሥራ ነው። ሥጋ ከቃል ጋር ተዋሕዶ አምላክ እንዲሆን ማድረግም የሦስቱም የአንድነት ሥራ ነው። በሃይማኖተ አበውም ዘአንገሦ ለሥጋ አዳም በመንፈስ ቅዱስ ወረሰዮ ቅዱሰ ወማሕየዌ ሲል ይገኛል። በመንፈስ ቅዱስ አዋሐጅነት ሥጋን አምላክ አድርጎ ማሕየዊና ቅዱስ ያደረገው ተብሎ ተገልጿል። ከዚህም ላይ መንፈስ ቅዱስ ይጠቀስ እንጂ ማዋሐድ የሦስቱም አካላት የአንድነት ሥራ ስለሆነ አብም ወልድም ያሉበት ሥራ ነው። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋራ ነበረ ተብሎ መነገሩ በህልውና አብና መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ህልው ሆነው ስለሚኖሩ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፷፰

"ከሙታንም ከተነሣ በኋላ ከርሱ ጋራ የበላን የጠጣንም እኛ ነን" (የሐዋ. ሥራ ፲፣፵፩)፡፡ አንዳንዶች ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን መካከል አልተነሣም እያሉ ይክዳሉ፡፡ በቅርብ በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተመሠረተው የእስልምና እምነትም ይህን ያስተምራል፡፡ ነገር ግን ከሙታን እንደተነሣ በዘመኑ ከእርሱ የተማሩ ሐዋርያት ከሙታን መካከል እንደተነሣ አይተውታል፡፡ ወንጌላዊው ሉቃስ "ከሙታን ከተነሣ በኋላ ከእርሱ ጋር የበላን የጠጣንም እኛ ነን" ብሎ የጻፈውም ለዚህ ነው፡፡ የክርስትና ሃይማኖትን ከሌሎች ቤተ እምነቶች ልዩ የሚያደርገው ይህ የትንሣኤ ጉዳይ ነው፡፡ ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ትንሣኤ እንዳለ አረጋግጦልናል፡፡ ሌሎች ቤተ እምነቶች ትንሣኤ እንዳለ ቢያምኑ እንኳ ምስክር ግን የላቸውም፡፡ የእኛ ግን ራሱ ክርስቶስ ምስክር አለን፡፡ መነሣቱ እውነት እንደሆነም በዘመኑ የነበሩ ሰዎች ምስክር ናቸው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፷፱

"ጴጥሮስ ይህን ነገር ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ" (የሐዋ. ሥራ ፲፣፵፬)፡፡ "መንፈስ ቅዱስ ወረደ" ማለት ምን ማለት ነው? መንፈስ ቅዱስ የሌለበት ቦታ የለም፡፡ በሁሉ ቦታ ያለ ስለሆነ ወረደ ወጣ ሄደ የሚሉት ቃላት እንደ ቃላዊ ፍቻቸው አይተረጎሙም፡፡ አንድ ነገር ከሰማይ ወረደ ከተባለ ቀድሞ ከምድር አልነበረም ማለት ነው፡፡ ወደ ሰማይ ወጣ ከተባለ ደግሞ አስቀድሞ በምድር አልነበረም ማለት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ወረደ ማለት ግን ከሰማይ ታጣ ከምድር ተገኘ ማለት ሳይሆን ረድኤትን ሰጠ፣ ጸጋን አደለ ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ጸጋን ያሰጣል፡፡ ስለሆነም ጴጥሮስ ሲያስተምር በሰሙት ሰዎች ላይ ጸጋ እግዚአብሔር እንዳደረባቸው ለመግለጽ መንፈስ ቅዱስ ወረደ ተብሎ ተገልጿል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን መንፈስ ቅዱስ እያሉ እንደሚጠሩት ከዚህ ቀደም ተመልክተናል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፸

"በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው" (የሐዋ. ሥራ ፲፣፵፰)፡፡ በአብ ማመን በወልድ ማመን፣ በወልድ ማመን በአብ ማመን እንደሆነ ከዚህ ቀደም ተማምረናል፡፡ ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ብሎ ያዘዛቸው በእርሱ ስም መጠመቅ በአብ ስም መጠመቅ ስለሆነ ነው፡፡ በእርሱ ስም መጠመቅ በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቅ ስለሆነ ነው፡፡ በባሕርያዊ ግብር ሦስቱ አንድ ስለሆኑ የአንዱ ስም ቢጠቀስም ሁለቱንም የሚመለከት ጉዳይ እንደሆነ ደጋግመን ደጋግመን ተማምረናል፡፡ ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ማለት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠመቁ ማለት ነው፡፡ በጥምቀት የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች እንሆናለን፡፡ ስንጠመቅ ከጥምቀት በፊት የሠራነው ኃጢአታችን ይሠረይልናል፡፡ በጥምቀት ድኅነትን እናገኛለን፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፴፩

"ራሱን ያለምስክር አልተወም" (የሐዋ. ሥራ ፲፬፥፲፯):: የዚህች ዓለም ፈጣሪ፣ አስተዳዳሪ እንዳላትና ይኸውም እግዚአብሔር እንደሆነ በብዙ መንገድ ራሱ አሳውቆናል:: የፈጣሪን መኖር ከሚያረጋግጡልን ምስክሮች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::

፩) ሥነ ፍጥረት

፪) መጽሐፍ ቅዱስ

፫) ሥጋዌ

ቤት ያለባለቤት እንደማይገኝ ሁሉ ፍጡርም ያለ ፈጣሪ አልተገኘም:: ሁሉንም ፍጥረት ካለመኖር ወደመኖር ያመጣና የፈጠረ ለእርሱ ምንም ምክንያት የሌለው ልዑል እግዚአብሔር ነው:: ለእርሱ መኖር ሌላ ምክንያት እንደሌለውም "እስመ አልቦ ውስተ ህላዌሁ አመክንዮ" ተብሎ ተገልጿል:: በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉ የነቢያት ትንቢቶች ተፈጻሚ ሆነው በመታየታቸው ያጻፈው እግዚአብሔር እውነተኛ እንደሆነ ይመሰክራሉ:: ስለዓለም አፈጣጠር በእርግጠኝነት የሚናገር መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: የእግዚአብሔርን መኖር በጎላ በተረዳ ነገር የሚያሳውቀን ደግሞ ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ ከድንግል ማርያም ተወልዶ የአምላክነት ሥራን እየሠራ በማሣየቱ ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፴፪

"እምነታችኹ በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማች አስቀድሜ ስለ ኹላችኹ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለኹ" (ሮሜ ፩፥፰):: በምስጋና መጀመር ለሐዋርያት ልማዳቸው ነው:: እግዚአብሔር አብን አስቀድሜ አመሰግናለሁ አለ:: አምላኬ ያለው አብን ነው:: ወልድን ቀጥሎ የሚያመጣው ነውና:: በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ አለ:: ኢየሱስ ክርስቶስን ማመስገን አብን ማመስገን ነው:: አብን ማመስገን ኢየሱስ ክርስቶስን ማመስገን ነውና:: አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በምስጋና አንድ ናቸው:: እነርሱን የምናመሰግነው ምስጋና የባሕርይ ምስጋና ነው:: ይኸውም ይህን ዓለም ካለመኖር አምጥተው ስለፈጠሩ፣ ብንወድቅ ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ ሥጋችንን ተዋሕዶ በመስቀል ተሰቅሎ ስላዳነን፣ ብንራብና ብንጠማ ዘለዓለማዊነትን የሚያጎናጽፍ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ስለሰጠን እናመሰግነዋለን:: እግዚአብሔር ምስጋና የባሕርይው ነው ማለታችን ባሕርይው ምስጉን ነው ማለታችን ነው:: ይኸውም ቅዱሳን መላእክትና ሰዎች ቢያመሰግኑት የማይጨመርለት ባያመሰግኑት የሚቀነስበት አይደለም ማለታችን ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፴፫

"በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ" (ሮሜ ፫፥፳፬):: ቤዛነት ማለት ምትክነት ማለት ነው:: ይኸውም ለአዳም ስለአዳም እንደ አዳም ሆኖ የወደቀውን አዳምን ለማንሣት ያደረገው የቸርነት ሥራ ነው:: ባጠፋው ጥፋት ምክንያት መሰቀል ይገባው

የነበረ አዳም ነው። ነገር ግን በአዳም ምትክ (ህየንተ አዳም) ጌታ ተሰቅሎ አዳምን ነጻ አውጥቶታል። አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ ብሎ ማልቀስና ወደ እግዚአብሔር ማመልከት የሚገባው አዳም ነበር። ነገር ግን አዳም በበደል ስለተያዘ በፊቱ ቆሞ እንዲህ ብሎ ለመጮህ አልቻለም። ስለዚህ በአዳም ምትክ የአዳምን ጩኸት ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ጮኸለት። እንደ አምላክነቱም የአዳምን በደል በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ይቅር አለው። ምእመናን በክርስቶስ ቤዛነት እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ። ይህም ማለት ጌታ ያደረገውን የማዳን ሥራ አምነው፣ ተጠምቀው፣ ሥጋውን ደሙን ተቀብለው፣ መልካም ሥራን ሠርተው በእግዚአብሔር ቸርነት ይጸድቃሉ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ቸርነት ካልተጨመረበት ሰው ምንም ያህል በጎ ሥራ ቢሠራ መጽድቅ እንደማይችል ለመግለጽ እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ ብሎ ተናገረ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፴፬

"ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋራ በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን" (ሮሜ ፭፣፲)። ኢየሱስ ክርስቶስን ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ነው ብለው የሚናገሩ ሰዎች በዚህ ኃይለ ቃል ይሸነፋሉ። "ወልደ እግዚአብሔር አይሞትም፣ አይራብም፣ አይጠማም፣ አይደክምም ወልደ ማርያም ይሞታል፣ ይራባል፣ ይጠማል፣ ይደክማል" እያሉ አንዱን ኢየሱስ ክርስቶስን ሁለት አድርገው የሚናገሩ ሰዎች አሉ። እኛ ግን አንዱን ኢየሱስ ክርስቶስን ወልደ አብም ወልደ ማርያምም እንለዋለን። ከተዋሕዶ በኋላ የሠራውን ሥራ በተዋሕዶ ሠራው እንላለን እንጂ እየነጣጠልን ይህ የሥጋ ሥራ ነው፣ ይህ የመለኮት ሥራ ነው እያልን አንናገርም። ቅዱሳት መጻሕፍትም ኢየሱስ ክርስቶስን ወልድ ዋሕድ (አንድ ልጅ) ይሉታል እንጂ ሁለት አይሉትም። ይህንንም የሚያስረዳን ከላይ የጠቀስነው ኃይለ ቃል ነው። እግዚአብሔር በልጁ ሞት ታረቀን ብሎ ወልደ አብ በሥጋው እንደሞተ ነግሮናል። በምንታዌ (Dualism) የሚያምኑ ሰዎች የእግዚአብሔር ልጅ አይሞትም ካሉ እግዚአብሔር በልጁ ሞት ታረቀን ይልባቸዋልና ክሕደታቸው ከንቱ መሆኑን ይወቁ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፴፭

"ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋራ አንድ እንኾን ዘንድ የተጠመቅን ኹላችን ከሞቱ ጋራ አንድ እንኾን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን። ሞቱንም በሚመስል ሞት ከርሱ ጋራ ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከርሱ ጋራ እንተባበራለን" (ሮሜ ፮፣፫_፭)። በጥምቀት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ እንሆናለን። ስንጠመቅ ራሳችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይሆናል። እኛም ሕዋሳቶቹ እንሆናለን። ስንጠመቅ አካላችን የክርስቶስ ማደሪያ ይሆናል። ስለዚህ በእርሱ በክርስቶስ ክርስቲያን እንባላለን። ስንጠመቅ ሞቱን በሚመስል ሞት እንሞታለን። ሞቱን በሚመስል ሞት ስንሞት ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ እንተባበራለን። በጥምቀት ከእግዚአብሔር የጸጋ ልጅነትን እናገኛለን (ዮሐ. ፫፣፫)። በጥምቀት ሥርየተ ኃጢአትን እናገኛለን። ስንጠመቅ ከእርሱ ከጌታ ጋር አንድ እንሆናለን ማለት በጸጋ ተዋሕዶን ታላላቅ መንፈሳዊ ሥራዎችን እንድንሠራ ያደርገናል ማለታችን ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፴፮

"እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገ̈ባ̈ን አናውቅምና፥ ነገር ግን፥ መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል" (ሮሜ ፰፥፳፮)። መንፈስ ቅዱስን ይማልድልናል እያለ ነው። ዋጋ መስጠትን መማለድ ብሎ የሚገልጽበት ወቅት አለ። ይኸውም ውጤቱን በመቅድሙ መጥራት ነው። መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ መከራዎችን ስንቀበል ዋጋችንን ይሰጠናል። ከአብ ከወልድ ጋር አንድ ሆኖ ለምዕመናን ዋጋቸውን ይሰጣቸዋል። እግዚአብሔር ምእመናን እንዳይወድቁ ይማልድላቸዋል ማለት ጸጋውን ያድላቸዋል። ከእነርሱ ጋር በረድኤት ሆኖ የሚድኑበትን መንገድ ይገልጽላቸዋል ማለት ነው። ይማልድልናል የሚለው ቃል በግእዝ "ይትዋቀስ-ይከራከርልናል" ተብሏል። ይህ ከሆነ ደግሞ አብም እንደሚከራከርልን (እንደሚማልድልን) ተጽፏል። "ስለእርሳቸው ይከራከርላቸዋልና በጠላታቸምም እጅ አይጥላቸውምና ከሚጠሏቸው ከጠላቶቻቸው እጅ ያድናቸዋል" እንዲል (፩ኛ መቃ. ፳፥፫)። ትርጉሙ ዋጋን ይሰጠናል ማለት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፴፯

"የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚፈርደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው" (ሮሜ ፰፥፴፬)። ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፴፮ ላይ እንደተመለከትነው መንፈስ ቅዱስም ይማልድልናል (ይከራከርልናል) እንደተባለና አብም ይከራከርልናል (ይትዋቀስ በእንቲኣነ) እንደተባለ አይተናል። በዚህኛው ክፍል ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚፈርደው ተብሏል። ይህም በግእዙ "ወይትዋቀስ በእንቲኣነ" ይላል። ይኸውም ይከራከርልናል (ይማልድልናል) ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ሁሉንም ቢል ትርጉሙ ተመሳሳይ ነው። ዋጋችንን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሆኖ ይሰጠናል ማለት ነው። በሥጋው በደሙ አማካኝነት እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ጸጋውን እያደለ ሰይጣንን እንድንቃወም ይረዳናልና ይማልድልናል አለ እንጂ ከትንሣኤ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁልጊዜ እያማለደ ይኖራል ማለት አይደለም። ምድር ላይ በሠራልን የማዳን ሥራ አምነን ተጠምቀን ሥጋውን ደሙን ተቀብለን ብንኖር መንግሥተ ሰማያትን ሰጥቶ የሚፈርድልን እርሱ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፴፰

"ከእነርሱም (ከአባቶችም) ክርስቶስ በሥጋ መጣ፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ኾኖ ለዘለዓለም የተባረከ አምላክ ነው አሜን" (ሮሜ ፱፥፭)። ቅዱስ ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በግልጽ ከተናገረበት አንቀጽ አንዱ ይህ ነው። ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን የፈጠረ ወልደ እግዚአብሔር አዳምን ለማዳን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ። ከአባቶች ተወለደ ብሎ የተናገረው አያቶቹን ለመጥቀስ ነው። ይኸውም ከኢያቄም ጀምሮ እነ ዳዊትን እነአብርሃምን እና ሌሎችንም ታላላቅ ቅዱሳን ለመጥቀስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርይው አምላክ ነው። ቅዱሳን አምላክ ቢባሉ የጸጋ አምላክ ሆነው ነው። እርሱ ግን አምላክነቱ የባሕርይ አምላክ ነው። ለዘለዓለም የተባረከ አምላክ ተብሎ የተገለጸውም ለዚህ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፴፱

"ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍኽ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብኽ ብታምን ትድናለኽና" (ሮሜ ፲፥፱)። ጌትነት የባሕርይ ጌትነትና የጸጋ ጌትነት ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ጌትነት ምሥጢሩ ባለቤትነትን፣ ገዢነትን ያመለክታል። ለዓለም ጌታ አላት ማለት ባለቤት አላት ማለት ነው። ኢየሱስ ጌታ ነው ማለት የፍጥረታት ሁሉ ባለቤት እርሱ ነው ማለታችን ነው። ገዢነትን ሲያመለክት ደግሞ ኢየሱስ የፍጥረታት ሁሉ ገዢ ነው ማለታችን ነው። ፍጡራን ግን ጌታ ቢባሉ ከፈጣሪ ባገኙት ጸጋ ነው። ለሀብታቸው ባለቤት ቢሆኑ ሀብታቸውም ባለቤትነታቸውም ከፈጣሪ የተሰጠ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ ነው ስንለው ግን ለጌትነቱ፣ ለባለቤትነቱና ለገዢነቱ ሌላ ምክንያት የሌለው በባሕርይው ጌታ የሆነ ነው ማለታችን ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፵

"ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና፥ በአፉም መስክሮ ይድናልና" (ሮሜ ፲፥፲)። አንድ ሰው ለመዳን ቢያንስ አራት ነገሮች ያስፈልጉታል። እነዚህም መጀመሪያ ለዚህች ዓለም ሠራዒ፣ አስተዳዳሪ፣ መጋቢ እንዳላት ማመን። የፈጠራት እግዚአብሔር መሆኑን፣ ይህ እግዚአብሔር ደግሞ በአካል ሦስት በባሕርይ አንድ መሆኑን ማመን ይገባል። ከሦስቱ አካላት አንዱ መዋረዳችንን አይቶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ እንዳዳነን ማመን ነው። ሁለተኛው አምነን መጠመቅ ነው። ሦስተኛው መልካም ሥራዎችን መሥራት ነው። አራተኛው ሥጋውን ደሙን መቀበል ነው። ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃል ማለቱ እነዚህን ነገሮች ሁሉ አድርጎ ሲያምን ነው። በአፉም መስክሮ ይድናል ያለው እውነትን ይዞ ከላይ ያሉትን ነገሮች ሠርቶ ሲመሰክር ነው። እንጂ እነዚህን ሳያደርግ በማመን ብቻ ይጸድቃል ማለት አይደለም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፵፩

"የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና" (ሮሜ ፲፥፲፫)። የጌታን ስም ሰይጣናትም ይጠሩታል። ጠንቋዮችም ይጠሩታል። ሌቦች አመንዝራዎችም ይጠሩታል። በጠቅላላው ኢአማንያንም ይጠሩታል። ምግባረ ብልሹዎችም ይጠሩታል። ታዲያ የጠሩት ሁሉ ይድናሉ ያለው እነዚህን ሁሉ ይድናሉ ማለቱ ነውን? አይደለም። የጌታን ስም የሚጠራ ይድናል የተባለ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖና ተጠምቆ፣ ምግባር ትሩፋት ሠርቶ፣ ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ የሚኖር ሰውን ያመለክታል። መልካም ሥራን እየሠሩ የጌታን ስም መጥራት ያድናል። ንሥሓ ገብተው ሥጋውን ደሙን ተቀብለው የጌታን ስም መጥራት ያድናል። እነዚህንና የመሳሰሉ መልካም ሥራዎችን ሳይሠሩ ስሙን መጥራት ብቻውን ግን አያድንም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፵፪

"ሁሉ ከርሱና በርሱ ለርሱም ነውና ለርሱ ለዘለዓለም ክብር ይሁን አሜን" (ሮሜ ፲፩፥፴፮)። ራሱን በራሱ ያመጣ ፍጥረት የለም። ማንም ቢሆን ራሱን ካልካደ በቀር ራሴን በራሴ አመጣሁ አይልም። ፍጥረታትን ሁሉ በቸርነቱ ካለመኖር አምጥቶ የፈጠረ ልዑል እግዚአብሔር ነው።

ሲፈጥርም በፈቃዱ ፈጥሯቸዋል እንጂ እነርሱን እንዲፈጥር ያስገደደው ሌላ አካል የለም። ከፍጥረታት በፊት ከእግዚአብሔር ውጭ የሆነ ሌላ አካል አልነበረምና። "ሁሉ ከእርሱ ነው" ማለት ፍጥረታት ሁሉ ከእርሱ የተገኙ መሆናቸውን ይገልጻል። "ሁሉ በእርሱ ነው" ማለትም ፍጥረታት ሁሉ የተፈጠሩት በእርሱ መሆኑን ያመለክታል። "ሁሉ ለእርሱ ነው" ማለትም የፍጥረታት ሁሉ ባለቤት እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታል። ለእግዚአብሔር መኖር ግን ሌላ ምክንያት የለውም። "እስመ አልቦ ውስተ ህላዌሁ አመክንዮ" እንዲል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፵፫

"ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት" (ሮሜ ፲፫፥፲፬)። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት ማለት በእርሱ እምናችሁ፣ ተጠምቃችሁ፣ ሥጋውን ደሙን ተቀበሉ ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ ልበሱት ማለት በክርስቶስ ክርስቲያን ተባሉ ማለት ነው። እንዲሁም መልካም ሥራ ሠርታችሁ ክርስቶስ የጸጋ ተዋሕዶን ይዋሐዳችሁ ማለት ነው። ቅዱሳን ጻድቃን ክርስቶስን ስለለበሱት እውነትን በመመስከር ጸንተው ኖሩ፣ ታላላቅ ተአምራትን በእርሱ ስም አደረጉ። ቅዱስ አግናጤዎስ ለባሴ እግዚአብሔር ይባል ነበር። ይኸውም እግዚአብሔር በጸጋ የተዋሐደው የእግዚአብሔርን ሕግ በመዓልትም በሌሊትም የሚፈጽም ማለት ነው። ስለዚህ ክርስቶስን ልበሱት ማለትም በእርሱ እምናችሁ ተጠምቃችሁ ሕጉን ትእዛዙን ጠብቁ ማለት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፵፬

"በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና፥ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን። እንግዲህ በሕይወት ሆነን ብንኖር ወይም ብንሞት የጌታ ነን" (ሮሜ ፲፬፥፰)። ጻድቃን በዚህች ምድር ሲኖሩም ለእግዚአብሔር ኖሩ። ለእግዚአብሔር መኖር ማለትም ሕግጋቱን በመጠበቅ ኖሩ ማለት ነው። ሲሞቱም ለእግዚአብሔር ሞቱ። ለእግዚአብሔር መሞት ማለትም ሕጉን ትእዛዙን እየፈጸሙና ለዓለም ሁሉ እየተናገሩ ሰማዕት ሆኑ ማለት ነው። የቅዱሳን የኑሮ መመሪያቸው ሕገ እግዚአብሔር ነው። ለማንኛውም ሰው ባለቤት አለው። ሰው የራሱ አይደለም። ከአባት ዘር ከእናት ደም ከፍሎ ወደዚህ ምድር እንዲመጣ ያደረገው እግዚአብሔር ነው። ሁላችንም የፈጣሪ ገንዘቦች በመሆናችን ቅዱስ ጳውሎስ "የጌታ ነን" ብሎ ተናገረ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፵፭

"የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል" (ሮሜ ፲፮፥፲፮)። ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ሦስት ትርጉም አለው። አንደኛው አምልኮ የምንፈጽምበት፣ የምንጠመቅበት፣ የምንቆርብበት ቤት ሕንፃው ቤተ ክርስቲያን ይባላል። ሁለተኛው እያንዳንዱ ምእመን ቤተ ክርስቲያን ይባላል። ይኸውም ቤተ ክርስቶስ (የክርስቶስ ወገን) ማለት ነው። ሰው በክርስቶስ ሲጠመቅ የክርስቶስ ወገን ይሆናል። ሦስተኛው የምእመናን አንድነት ቤተ ክርስቲያን ይባላል። የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል የሚለው አገላለጽ በክርስቶስ አምነው፣ በክርስቶስ ስም ተጠምቀው የሚኖሩ ምእመናን ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል ማለቱ ነው እንጂ ሕንፃው ሰላምታ ያቀርብላችኋል ማለቱ አይደለም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፵፮

"ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘለዓለም ድረስ ክብር ይሁን አሜን" (ሮሜ ፲፮፥፳፯)። እግዚአብሔር ብቻውን ጥበብ ያለው ነው። ፍጡራን ጥበብ ቢኖራቸው ፈጣሪ በጸጋ የሰጣቸው ነው። አምላክ ግን ብቻውን ጥበበኛ ነው። "ብቻውን" የሚለው አገላለጽ ከፍጡራን ሲለየው ነው እንጂ አብን ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ፣ ወልድን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ፣ መንፈስቅዱስን ከአብና ከወልድ ሲለያቸው አይደለም። አብ ብቻውን ጥበብ ያለው ይባላል። ይህን ጊዜ "ብቻውን" የሚለው ቃል ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ ለማለት ሳይሆን ከፍጡራን ተለይቶ ለማለት ነው። ሦስቱ አካላት በጥበብ፣ በዕውቀት፣ በፈቃድ በጠቅላላው በአምላካዊ ሥራ አንድ ናቸውና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፵፯

"ወደልጁ ወደጌታችን ወደኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራችኹ እግዚአብሔር የታመነ ነው" (፩ኛ ቆሮ. ፩፥፱)። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ደጋግመን ተማምረናል። የእግዚአብሔር ልጅ ስንልም የአብ ልጅ ማለታችን ነው እንጂ የመንፈስ ቅዱስ ልጅ ማለታችን አይደለም። እግዚአብሔር በሚለው ቃል ሦስቱም አካላት የሚጠሩበት የአንድነት ስም ቢሆንም ከዚህ ላይ የተገለጸው ግን አብ እንደሆነ ልብ ማድረግ ይገባል። አብ ወልድን ስለወለደ የወልድ አባት ይባላል። መንፈስ ቅዱስን ስላሠረጸ ደግሞ አሥራጼ መንፈስ ቅዱስ ይባላል። ከዚህ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስን "ጌታችን" ብሎ ገልጾታል። ጌታ መባል የሦስቱም የአንድነት ግብር ስለሆነ አብም ጌታ ይባላል። መንፈስ ቅዱስም ጌታ ይባላል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፵፰

"እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን" (፩ኛ ቆሮ. ፩፥፳፫)። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ዋና ማዕከሏ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በቅዳሴዋ፣ በማኅሌቷ፣ በቅኔዋ፣ በዝማሬ መዋስእቷ፣ በትርጓሜዋ፣ በዜማዋ እና በጠቅላላው አገልግሎቷ የምትሰብከው ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። ሐዋርያት በስሙ ስለእርሱ ሰበኩ። ነቢያትም ቀድሞ እርሱ እንደሚወለድ ትንቢት ተናገሩ። ከሐዋርያት በኋላ የተነሡ ሊቃውንት ስለእርሱ ስለኢየሱስ ክርስቶስ አስተማሩ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሥላሴ አንዱ መሆኑን፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን፣ ዓለምን ለማዳን በመስቀል መሰቀሉን፣ በሦስተኛው ቀን ከሙታን መካከል ተለይቶ መነሣቱን፣ በአርባኛው ቀን ወደሰማይ ማረጉን እናስተምራለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፵፱

"እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኀይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይኾን" (፩ኛ ቆሮ. ፪፥፭)። ሃይማኖታችን በሰው ፍልስፍና የተመሠረተ አይደለም። ሰው ተጠብቦ ያገኘው ነገር አይደለም። ከዚያ ይልቅ እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ የገለጠልን እውነት ነው። ይህ እግዚአብሔር የገለጠልን እውነት ደግሞ አንድ ነው። ታዲያ በዓለም ላይ ይህ ሁሉ ቤተ እምነት ከምን ተገኘ ከተባለ በሁለት መንገድ ተገኝቷል። አንደኛ ሰው መሰለኹን እውነት አድርጎ በማመኑ

የተመሠረቱ ቤተ እምነቶች አሉ:: ሁለተኛ ሰይጣን በተለያዩ ምትሐታዊ ሥራዎቹ አታሏቸው እርሱን የሚያመልኩ ሰዎች አሉ:: ሰይጣን በሰው ልቡና ላይ ጥርጥርን በማምጣት ከትክክለኛዋና ከአንዷ ሃይማኖት ሰዎችን እየለየ ሌላ የተሳሳተ አመለካከትንና እምነትን እንዲከተሉ ያደርጋል:: የእኛ ግን ሃይማኖታችን በሰው ጥበብ ያይደለ በእግዚአብሔር ኃይል የተገለጠች በመሆኗ ሁልጊዜም ደስ ብሎን እንኖራለን::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፶

"ከዚችም ዓለም ገዢዎች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም ዐውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር" (፩ኛ ቆሮ. ፪፥፰):: ኢየሱስ ክርስቶስን ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) አድርገው የሚናገሩ ሰዎች በዚህ ኃይለ ቃል ይረታሉ:: ከዚህ የክብር ጌታ ብሎ ገልጾታልና:: የክብር ጌታ ደግሞ እግዚአብሔር ነው:: ስለዚህ ይህ ኃይለ ቃል የኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔርነት በግልጽ ይናገራል:: ክርስቶስን ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ የሚሉ ሰዎች ደግሞ ወልደ አብ አልታመመም ወልደ ማርያም ታመመ እያሉ አንዱን ለሁለት እየከፈሉ በራሳቸው ስሕተት ራሳቸውን ይጎዳሉ:: ይህ ኃይለ ቃል የተሰቀለው በሥጋው የክብር ጌታ (ወልደ እግዚአብሔር) መሆኑን በግልጽ ይናገርባቸዋልና ክሕደታቸው ከንቱ መሆኑን ይወቁ::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፶፩

"ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም" (፩ኛ ቆሮ. ፪፥፲፩):: "በቀር" የሚለው አገላለጽ ከፍጡራን ሲለየው ነው እንጂ ከወልድ ሲለየው አይደለም:: አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በዕውቀት አንድ ናቸው:: ወልድ አብንም መንፈስ ቅዱስንም ያውቃቸዋል:: መንፈስ ቅዱስ ወልድንም አብም ያውቃቸዋል:: አብ ወልድንም መንፈስ ቅዱስንም ያውቃል:: በሥላሴ ዘንድ የበላይና የበታች እያደረጉ የሚናገሩ ሰዎች በዚህ ኃይለ ቃል ይረታሉ:: በጕስዐተ ልብ ከመንፈስ ቅዱስ ወልድ ይበልጣል ከወልድ አብ ይበልጣል እያሉ ይናገራሉ:: ወልድን መንፈስ ቅዱስ አያውቀውም:: አብን ወልድ አያውቀውን እያሉ መዓርግ ያበላልጣሉ:: ከላይ ያለው ኃይለ ቃል እንደሚነግረን ግን መንፈስ ቅዱስ አብንም ወልድንም እንደሚያውቅና በባሕርይ አንድ መሆናቸውን የሚያመለክት ቃል ነው:: ለእግዚአብሔር ያለውን የሚያውቅ እግዚአብሔር ነው:: ከዚያ ውጭ ፍጡር እግዚአብሔርን በባሕርይው አይቶት አያውቅም::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፶፪

"ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ ርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" (፩ኛ ቆሮ. ፫፥፲፩):: የሃይማኖታችን መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ይህንንም ለማመልከት በእርሱ ስም እንጠራለን:: እርሱ ክርስቶስ እንደተባለ እኛም ክርስቲያን እንባላለን:: እርሱ ናዝራዊ እንደተባለ እኛም ናዝራውያን እንባላለን:: እርሱ መሲሕ እንደተባለ እኛም መሲሓውያን እንባላለን:: በጠቅላላው የሃይማኖታችን መሠረት እርሱ ነው:: ክርስቶስ ከመሠረተልን መሠረት ማለት ካስተማረን ትምህርት ውጭ ማንም ቢሆን ቢያስተምረን አንቀበለውም:: እርሱ ካስተማረው ትምህርት አፈንግጠው ብዙዎች ከእርሱ በኋላ ተነሥተው

እምነትን በራሳቸው የተሳሳተ አስተምህሮ መሥርተዋል፡፡ ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካስተማረው ትምህርት ውጭ ማንም ቢሆን ሌላ ትምህርት እንዳያስተምር ተነግሮ ነበር፡፡ ስለዚህ ይህንን ቃል ባለመስማታቸው ራሳቸውን በራሳቸው ይጎዳሉ፡፡ እኛ ግን እርሱ ባስተማረን ትምህርት ጸንተን እንኖራለን፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩፻፶፫

"ሁሉ የእናንተ ነው፥ እናንተም የክርስቶስ ናችኍ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው" (፩ኛ ቆሮ. ፫፥፳፫)፡፡ በክርስቶስ ስናምን ሁሉ የእኛ ይሆናል፡፡ ለዚያ ነው ሁሉ የእናንተ ነው የተባልነው፡፡ እናንተም የክርስቶስ ናችሁ ያለው በእርሱ ስም ተጠምቀን፣ በእርሱ ትምህርት ጸንተን፣ የእርሱን ሥጋ በልተን፣ የእርሱን ደም ጠጥተን ዘለዓለማዊ ሕይወትን ስለምናገኝ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ እናንተ የክርስቶስ ናቸው የሚለው የክርስቶስ የጸጋ ልጆች ናችሁ ማለት ነው፡፡ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው የሚለው ቃል ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይኸውም የአብ የባሕርይ ልጅ መሆኑን ያመለክታል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩፻፶፬

"ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና" (፩ኛ ቆሮ. ፭፥፯)፡፡ ፋሲካ ማለት ደስታ ማለት ነው፡፡ ደስታችን ክርስቶስ ታርዷል ማለት በመስቀል ላይ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ሰጠን ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ንስሓ ገብተን፣ ምግባር ትሩፋት ሠርተን መቀበል ይገባናል፡፡ ፋሲካ ማለት ሌላ ትርጉሙ መሻገሪያ ማለት ነው፡፡ "ፋሲካ ብሂል ማዕዶት ብሂል" እንዲል ቅዱስ ያሬድ (መጽሐፈ ድጓ)፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ከባርነት ወደ ነጻነት፣ ከሲኦል ወደ ገነት፣ ከምግባረ ኃጢአት ወደ ምግባረ ጽድቅ አሻጋግሮናልና ፋሲካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሏል፡፡ በኦሪት ዘመን እስራኤላውያን በጉን አርደው ከግብፅ ባርነት ተላቀው ባሕረ ኤርትራን ተሻግረው ወደ ከነአን ገብተዋል፡፡ ያ በግ የክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ይነገራል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩፻፶፭

"ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታውቁምን" (፩ኛ ቆሮ. ፮፥፪)፡፡ ሐዋርያት ስለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ አላስተማሩም፡፡ ስለጽድቅ ሥራዎች፣ ስለጾም፣ ስለጸሎት፣ በጠቅላላው ስለመልካም ሥራዎች አስተምረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ክርስቶስ ባስተማረው ትምህርት ጸንተው ስለኖሩ ቅዱሳን አስተምረዋል፡፡ ቅዱሳን በዓለም እንደሚፈርዱ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በግልጽ ነግሮናል፡፡ የቅዱሳን ፍርድ የጸጋ ፍርድ ነው፡፡ ይኸውም ከፈጣሪ ባገኙት ጸጋ ይፈርዳሉ፡፡ እግዚአብሔር ይፈርዳል ስንል ግን በባሕርይው ፈራጅ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩፻፶፮

"ለእኛስ ነገር ሁሉ ከርሱ የሆነ እኛም ለርሱ የኾን አንድ አምላክ አብ አለን፥ነገር ሁሉም በርሱ በኩል የሆነ እኛም በርሱ በኩል የኾን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን" (፩ኛ ቆሮ. ፰፥፮)፡፡ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን በአካል ልዩ ልዩ ቢሆኑም በባሕርይ ግን አንድ ስለሆኑ አንድ

አምላክ አለን እንላለን እንጂ ሦስት አማልክት አሉን አንልም። በዚያው በአንዱ ባሕርይ ሦስቱም አካላት ስለሚጠሩበት አብ አምላክ ይባላል። አብ አምላክ እንደሚባል በዚህ ጥቅስ ተጠቅሷል። ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስም አምላክ እንደሚባል ሮሜ. ፱፥፭ ላይ ተገልጿል። መንፈስ ቅዱስም አምላክ ይባላል። "አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን" የሚለው አገላለጽም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። አብም ጌታ ይባላል። መንፈስ ቅዱስም ጌታ ይባላል። አንድ ጌታ አለ መባሉ በባሕርይ አንድ ስለሆኑ ነው። በዚህ በአንዱ ባሕርይ አብም ጌታ ይባላል። ወልድም ጌታ ይባላል። መንፈስ ቅዱስም ጌታ ይባላል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፶፯

"ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ አለት ጠጥተዋልና፥ ያም አለት ክርስቶስ ነበረ" (፩ኛ ቆሮ. ፲፥፬)። ከትርጓሜ ስልቶች አንዱ ምሳሌ ነው። ምሳሌ ማለት በአንድ በተወሰነ ጉዳይ ተመሳሳይነትን መሠረት አድርጎ የሚቀርብ ማስረጃ መንገድ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ረቂቅ የሆነውን የሃይማኖት ትምህርት ለማስረዳት ምሳሌን ይጠቀማሉ። ይኸውም ምሥጢረ ሥላሴን በፀሐይ፣ ምሥጢረ ሥጋዌን በሰው ነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ እና በመሳሰሉት እየመሰሉ ያስተምራሉ። የቤተክርስቲያን የዚህ ሁሉ መሠረቷ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሙሴ ከአለት ላይ ውሃን አፍልቆ እስራኤላውያንን በምድረ በዳ አጠጥቷቸው ነበር። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያንን ድንጋይ ከክርስቶስ ጋር አመሳስሎታል። ይኸውም ያ ውኃ የተጠሙ እስራኤልን እንዳረካ፤ ክርስቶስ ደግሞ የሕይወት ውኃ በመሆኑ የተጠማውን ዓለም ልጅነትን በመስጠትና ሥጋውን ደሙን በመስጠት አርክቶታልና የዚያ ምሳሌ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፶፰

"እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ" (፩ኛ ቆሮ. ፲፩፥፩)። ቤተ ክርስቲያን ነገረ ክርስቶስን እንደምታስተምር ሁሉ ነገረ ቅዱሳንንም ታስተምራለች። ምክንያቱም ከቅዱሳን ሕይወት ብዙ ተግባራዊ ትምህርቶችን ስለምናገኝ ነው። ክርስቶስ ሲያስተምር "ተመሀሩ እምኔየ እስመ የዋህ አነ ወትሑት ልብየ" ብሏል። ይኸውም ከእኔ ተማሩ ማለት ነው። ቅዱሳን ከክርስቶስ ተምረው ክርስቶስን መስለው ኖረዋል። ቅዱስ ጳውሎስም ከእነዚህ ቅዱሳን አንዱ ነው። "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ" አለ። ስለዚህ የጳውሎስን ሙሉ ሕይወት ማወቅ ይጠቅመናል ማለት ነው። ምክንያቱም እርሱን ለመምሰል እርሱን ማወቅ ይገባልና ነው። ይህን መሠረት በማድረግ ለቅዱሳን ገድል ጽፈን፣ መታሰቢያ በዓል ወስነን ስለእነርሱ እናስተምራለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፶፱

"ነገር ግን፥ የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፥ የሴትም ራስ ወንድ፥ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ልታውቁ እወዳለሁ" (፩ኛ ቆሮ. ፲፩፥፫)። የሴት ራስ ወንድ ነው ማለት ከሴት ወንድ ይበልጣል ማለት አይደለም። ሴትና ወንድ ከተጋቡ በኋላ አንድ አካል ናቸው ተብሏልና። በክብርም ሴትና ወንድ እኩል ናቸው። ታዲያ ራስ መባሉ ስለ ምንድን ነው ከተባለ ሴት ከወንድ ስለተገኘች ነው። የክርስቶስ ራስ እግዚአብሔር ነው ማለቱስ ትርጉሙ ምንድን ነው?

ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ የተገኘ ስለሆነ ነው። ይህ ተረክቦም መቀዳደም የሌለበት ተረክቦ ነው። አብ ወልድን ስላስገኘ አብ ቀድሞ ነበረ ወልድ በኋላ ተገኘ አንልም። አብ ወልድን ወለደ ስንል ከኅሊና በላይ በሆነ ግብር ወልድን በዘመን ሳይቀድመው መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል። ስለዚህ እግዚአብሔር የክርስቶስ ራስ ነው የሚለው አገላለጽ ወልድ ከአብ መገኘቱንና በክብር አንድ መሆናቸውን ያመለክታል። ወንድን የሴት ራስ ነው ካለ በኋላ "ሴትና ወንድ በጋብቻ አንድ አካል ይሆናሉ" ብሎ በክብር አንድ እንደሚሆኑ ይገልጻልና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፰

"ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠኹትን እኔ ከጌታ ተቀብያለኹና" (፩ኛ ቆሮ. ፲፩፥፳፫)። የሃይማኖትን ትምህርት ከእግዚአብሔር ያገኘነው ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ነው። ስለዚህ በዚህ ላይ ግላዊ አስተያየት መጨመር አይገባም። ለዚያ ነው ቅዱስ ጳውሎስ ለእናንተ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና ብሎ የተናገረው። ሙሴ ሕገ ኦሪትን ከጌታ ተቀበለ። ሙሴ ደግሞ ለቀሪው ትውልድ አስተማረ። ሕዝቡ ተቀብሎ በሕጉ ተመራበት። ሐዲስ ኪዳንንም ራሱ ክርስቶስ መጥቶ አስተማረን። ክርስቶስ ለሐዋርያት አስተማረ። ሐዋርያት ለሕዝቡ አስተማሩ። እንዲህ እንዲህ እያለ በመቀባበል እስካሁኑ ጊዜ ደርሰናል። ወደፊትም በእርሱ ቸርነት ይቀጥላል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፰፩

"ቈርሶም፦እንካቹኹ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚኾን ሥጋዬ ነው ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ_____ይህን እንጀራ በበላቹኹ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣቹኹ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላቹኹና። ስለዚህ፥ ሳይገ̈ባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ፥ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት። ሳይገ̈ባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና" (፩ኛ ቆሮ. ፲፩፥፳፬-፳፱)። በቤተ ክርስቲያን የምናቀርበው የክርስቶስ ሥጋና ደም አማናዊ (የእውነት) ነው እንጂ ምሳሌ አይደለም። ጌታ ይህን ሥጋና ደም በምትቀበሉበት ጊዜ ለመታሰቢያዬ አድርጉት ብሏል። ይኸውም በቅዳሴ ጊዜ ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ እያልን ሞቱን ትንሣኤውን እያሰብን ስለምንቀበለው የተነገረ ነው እንጂ ሥጋውና ደሙ ምሳሌያዊ ነው ለማለት አይደለም። ሥጋውን ደሙን ስንቀበልም ንስሓ ገብተን፣ ምግባር ትሩፋት ሠርተን መሆን ይገባዋል። ንስሓ ሳንገባ በድፍረት ብንቀበለው ግን ሰማያዊ ፍርድ ይጠብቀናል

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፰፪

"ስለዚህ፥ ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር፦ ኢየሱስ የተረገመ ነው የሚል እንደሌለ፥ በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በቀር፦ ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ እንኳ እንዳይችል አስታውቃችኋለኹ" (፩ኛ ቆሮ. ፲፪፥፫)። ኢየሱስ ጌታ ነው ማለትማ ሰይጣናትም ይላሉ። ነገር ግን ሰይጣናት ከመንፈስ ቅዱስ ናቸው አንልም። ኢየሱስ የአብ የባሕርይ ልጅ መሆኑን አምኖ ኢየሱስ ጌታ ነው የሚል ሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነው ለማለት ነው። በአብ በወልድ በመንፈስ

ቅዱስ ስም አምነው ሳይጠመቁ፣ ተጠምቀው ሥጋውን ደሙን ሳይቀበሉ ኢየሱስ ጌታ ነው ቢሉ ከመንፈስ ቅዱስ ናቸው አይባሉም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፳፫

"ክርስቶስ ላንቀላፉት በኵራት ኾኖ ከሙታን ተነሥቷል" (፩ኛ ቆሮ. ፲፭፥፳)። ክርስቶስ የትንሣኤ በኩር ነው። ምእመናን እርሱን በኩር አድርገው በዕለተ ምጽአት ጊዜ ይነሣሉ። ከትንሣኤ በኋላ ሞት የለም። የእነ አልዓዛር ትንሣኤ ግን ሞት የሚከተለው ትንሣኤ ነበር። ስለዚህ ጌታ ካስነሣው በኋላ ትንሽ ቆይቶ ሞቷል። ቅዱሳን ያስነሷቸው ሙታንም ለጥቂት ጊዜ በዚህ ምድር ኖረው ሞተዋል። ሁለተኛ ሞት የሌለበት ትንሣኤን የተነሣው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናቸው። ሌላው ሰው ይህንን ትንሣኤ የሚነሣው በዕለተ ምጽአት ጊዜ ነው። ለዚህ ትንሣኤ በኩራችን ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፳፬

"በኋላም፥ መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኀይልንም በሻረ ጊዜ፥ ፍጻሜ ይሆናል። ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋልና" (፩ኛ ቆሮ. ፲፭፥፳፬-፳፭)። ይህ የተነገረው ስለ ዳግም ምጽአትና ትንሣኤ ዘጉባኤ ነው። አለቅነትን፣ ሥልጣንን፣ ኃይልን በሻረ ጊዜ ማለቱ የፍጡራን በፍጡራን ላይ ያላቸው አለቅነት፣ ሥልጣንና ኃይል ይሻራል ማለት ነው። ይኸውም ከምጽአት በኋላ ከእግዚአብሔር በስተቀር ገዢና አለቃ ስለማይኖር ነው። "ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋልና" ከሚለው ዓረፍተ ነገር "እስከ" ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው። ኢወለደት ሜልኮል እስከ አመ ሞተት እንደሚለው ያለ ነው። ይኸውም ጠላቶቹ ከተገዙለት በኋላ ንግሥናውን ይተዋል ማለት አይደለም። ለዘለዓለም ነግሦ ይኖራል ማለት ነው። ጠላቶቹ የተባሉ አይሁድ፣ አጋንንት ናቸው። "መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ" የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይኸውም የነበረውን ሥልጣን ትቶ ሥልጣኑን ሁሉ ለአብ በሰጠ ጊዜ ማለት አይደለም። ከአብ ጋር አንድ በሚሆንበት መንግሥትነት በኃጥኣን ላይ እንደሚፈርድ ለማመልከት የተነገረ ቃል ነው። ይህ አሳልፎ መስጠት የሚለው ቃል እርሱ መንግሥት እንደሆነ አብም መንግሥት እንደሆነ ለመግለጥ የተነገረ ቃል ነው። ይህንን የሚያስረዳን ሌላ ቃል "ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ ባንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም" የሚለው ነው (ዮሐ. ፭፥፳፪)። በዚህ ጊዜ ፈራጅነቱን ትቶ ፈራጅነትን ሁሉ ለወልድ ሰጠው ማለት አይደለም። የወልድን ፈራጅነት እየገለጠ ነው እንጂ። ከላይ ያለው ኃይለ ቃልም እንደዚህ ይተረጎማል። ወልድ መንግሥትነትን ለአብ አሳልፎ ሰጠ ሲል የአብን ንጉሥነት ለመግለጽ የተነገረ ነው። ምክንያቱም የወልድ ንጉሥነት ዘለዓለማዊ እንደሆነ በሌላ ቦታ ተገልጿልና ነው። "ርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል። በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለዓለም ይነግሣል ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም" ተብሏልና (ሉቃ. ፩፥፴፪-፴፫)።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፷፭

"ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቷልና። ነገር ግን፦ ሁሉ ተገዝቷል ሲል ሁሉን ካስገዛለት በቀር መሆኑ ግልጥ ነው። ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይኾን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል" (፩ኛ ቆሮ. ፲፭፥፳፯-፳፰)። እግዚአብሔር አብ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን አስገዛለት ተብሏል። ይህ ስለሰውነቱ የተነገረ ነው። ቅድመ ተዋሕዶ ንጉሥ ያልነበረ ሥጋ ቃልን ገንዘቡ ባደረገ ጊዜ የባሕርይ ንጉሥ ሆኗልና አስገዛለት ማለቱ ስለዚህ ነው። ሁሉን አስገዛለት ማለት ግን ሁሉን ካስገዛለት በቀር ነው ማለቱ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ ንጉሥ ሲሆን ንግሥናው ግን በአብና በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንዳልሆነ ለመግለጽ ነው። አብና መንፈስ ቅዱስ እንደ እርሱ የባሕርይ ንጉሥ ናቸውና። "በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል" የሚለው በምድር ያደረገውን ተልእኮውን ጨርሶ በአምላክነት ግብር ጸንቶ እንደሚኖር ይገልጻል። ለአብ ይገዛል ማለት ባለመታመም፣ ባለመራብ፣ ባለመጠማት ግብር ጸንቶ እንደ አብ ይሆናል ማለት ነው። "መገዛት" በዚህ ጊዜ ምሥጢሩ በንጉሡ ግብር መጽናት ማለት ነው። ይኸውም ነፍስ ሥጋን ገዛች ሲባል ሥጋ በነፍስ ግብር መጽናቱን መናገር ነውና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፷፮

"ነገር ግን፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን" (፩ኛ ቆሮ. ፲፭፥፶፯)። ያለ እግዚአብሔር ረድኤት ድል መንሣት (ማሸነፍ) አይቻልም። ስለዚህ ከጠላቶቻችን ጋር በሚኖረን ተጋድሎ ረድኤተ እግዚአብሔርን መጠየቅ ተገቢ ነው። ቅዱሳን በእርሱ ረድኤት ሰይጣናትን፣ እኩያት ፍትወታትን አሸንፈዋል። "ሞዕዎ ለእኩይ ኀሊና" እንዲል ቅዱስ ያሬድ። በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ሰጠን ማለቱ አዳም ከሳተ በኋላ "ምድር እሾህን ታብቅልብህ" ተብሎ ነበር። ይኸውም እኩያት ፍትወታት ይሰልጥኑብህ ማለት ነው። በዚህም ምክንያት ወልደ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ወደዚህ ምድር እስኪመጣ ድረስ ጠላት ዲያብሎስ በብዙ መንገድ ሰልጥኖብን ይኖር ነበር። እኩያት ፍትወታትንም እያሳሰበ የሰውን ልጅ ከእግዚአብሔር እንዲርቅ አድርጎት ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ ግን የዲያብሎስ ሥልጣን ተሻረ። እኩያት ፍትወታትንም ድል እንድናደርግ የሚያስችል ቃላዊና ተግባራዊ ትምህርትን ሰጥቶናልና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ሰጠን አለ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፷፯

"የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ" (፪ኛ ቆሮ. ፩፥፫)። አብ የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ተብሎ ተጠርቷል። የአምላክ ሌላ አምላክ የለውም። ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ነው ካልን የእርሱ ደግሞ ሌላ አምላክ አብ አለው አንልም። ይህ ከሆነ በዚህ ጥቅስ ያለው ኃይለ ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው? የሚለውን ማወቅ ያስፈልጋል። ይህ ቃል ስለሰውነቱ የተነገረ ነው። ክርስቶስ ለተዋሐደው ሥጋ አብ አምላኩ ነውና። ከዚህ ላይ አብ ይጠራ እንጂ በአምላክነት አብም ወልድም መንፈስ ቅዱስም አንድ ስለሆኑ ወልድንና መንፈስ ቅዱስንም ይመለከታል። ወልድ የተዋሐደውን ሥጋ ራሱ

እንደፈጠረ "ወኢተሳተፎ መኑሂ በፈጢረ ሥጋሁ" ተብሎ ተገልጿል፡፡ መንፈስ ቅዱስም ወልድ ለተዋሐደው ሥጋ አምላኩ መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል፡፡ ስለዚህ ስለሰውነቱ አብ አምላኩ ተባለ እንጂ በአምላክነትስ ከአብ ጋር አንድ ነው፡፡ አብ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት መባሉ ግን በባሕርይው አባቱ ስለሆነ ነው፡፡ ወልድ የአብ የባሕርይ ልጅ ነው፡፡ ይህን ለመግለጽ እንዲህ አለ፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፳፰

"አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ" (፪ኛ ቆሮ. ፭፥፲፬)፡፡ ክርስቶስ የሞተው እንደ ኃጥኣን ስቶ፣ እንደ ጻድቃን እሴት (ዋጋ) ሽቶ አይደለም፡፡ በክፉ ሥራችን ሞተን የነበርን እኛን ለማዳን ነው እንጂ፡፡ አንዱ እርሱ ስለሁሉ ቤዛ ሆኖ ሞተ፡፡ ሁሉንም በመስቀል ተሰቅሎ አዳነ፡፡ እንግዲህ ምን እንላለን፡፡ እኛን ለማዳን፣ ስለእኛ ተሰቅሎ መከራ የተቀበለልንን መድኃኔ ዓለምን ዛሬም ለዘለዓለምም እናመሰግነዋለን፡፡ በመከራው መከራችንን አራቀልን፡፡ በሞቱ ሞታችንን አጠፋልን፡፡ "ሞተ ክርስቶስ በሞተ ዚኣነ ከመ ይቅትሎ ለሞት በሞቱ" እንዲል፡፡ ሞትን በሞቱ ያጠፋልን ዘንድ ክርስቶስ የእኛን ሞት ሞተ፡፡ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወታችን ሁሉ በቸርነቱ ነግሦልን እንዲኖር የእርሱ መልካም ፈቃድ ይሁንልን፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፳፱

"ነገር ግን፥ የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋራ ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኾኖ ዓለሙን ከራሱ ጋራ ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቈጥርባቸውም ነበር በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ፡፡ (፪ኛ ቆሮ. ፭፥፲፰-፲፱)፡፡ አብና መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ታረቁን፡፡ ይህም ማለት ክርስቶስ ራሱ ሊቀ ካህናት ሆኖ በመስቀል ላይ ሆኖ የራሱን ሥጋና ደም መሥዋዕት አድርጎ ቢያቀርብ አብ፣ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስና መንፈስ ቅዱስ ታረቁን፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር የተባለው ይህ ነው፡፡ ለሊሁ ሠዋዒ፣ ለሊሁ መሥዋዕት፣ ለሊሁ ተዋካፌ መሥዋዕት ሆኖ ከታረቀን በኂላ ለሐዋርያትና በእነርሱ እግር ለሚተኩት ካህናት ሁሉ ደግሞ የማስታረቅን አገልግሎት ሰጠ፡፡ በብሉይ ኪዳን የነበሩ ካህናት ሰውን በነፍስ ከእግዚአብሔር ማስታረቅ አልቻሉም ነበር፡፡ ክርስቶስ መጥቶ ከታረቀን በኂላ ግን የሐዲስ ኪዳን ካህናት ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቁ ሆነዋልና "በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ" አለ፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፴

"እኛ በርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንኾን ዘንድ ኀጢአት ያላወቀውን ርሱን ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው" (፪ኛ ቆሮ. ፭፥፳፩)፡፡ ይህን ማለቱ ምንም ኃጢአትን ያልሠራ እርሱ ስለእኛ እኛን ለማዳን ራሱን ኃጥእ አሰኝቷልና ነው፡፡ ክርስቶስ የተሰቀለው በደል ተገኝቶበት አይደለም፡፡ እርሱ በኀልዮም፣ በነቢብም፣ በገቢርም ምንም ኃጢአትን ያልሠራ ንጹሐ ባሕርይ ነውና፡፡ አይሁድ በቅንዐት ሰቅለውታል፡፡ እርሱ ደግሞ መስቀሉን የእኛ መዳኛ አደረገው፡፡ በደልን ሳይሠሩ በደለኛ ተብለው በሰዎች ዘንድ ለሚፈረድባቸው ሰዎች አብነት ክርስቶስ ስላላቸው ደስ ይበላቸው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩፻፸፩

"በእግዚአብሔር ቅንአት እቀናላችኋለኹና፥ እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ላንድ ወንድ ዐጭቻችኋለኹና" (፪ኛ ቆሮ. ፲፩፥፪)። አንድ ወንድና አንዲት ሴት ከመጋባታቸው በፊት ፀባያቸውንና ግብራቸውን እየተጠናኑ እየተጠባበቁ ስለሚኖሩ እጮኛሞች ይባላሉ። መጠባበቅ ማለት ነው። እጮኝነት የሚለው ቃል ግን ከሴትና ወንድ ጋብቻ የዘለለ ትርጉም አለው። ለምሳሌ ንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያምን የዮሴፍ እጮኛ ይላት ነበር። ለዮሴፍ የሥጋ ዘመዱ ስለሆነች ይጠብቃትና ይንከባከባት ስለነበረ እጮኛ ተባለ እንጂ ባልና ሚስት በሚሆኑ ሰዎች መካከል እንዳለው እጮኝነት አይደለም። ድንግል ንጹሕ ለሆነ ለሰማያዊው ሙሽራ ለክርስቶስ አጭቻችኋለሁ የሚለው ቃልም በዚህኛው አግባብ ይተረጎማል። እጮኝነት ምሥጢራዊ ትርጉሙ ማስጠበቅ (መጠበቅ) ነውና። ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስ እንዲጠብቃችሁ መንፈሳዊ ቅንዐትን እቀናላችኋለሁ ማለቱ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩፻፸፪

"የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከኹላችኹ ጋራ ይሁን አሜን" (፪ኛ ቆሮ. ፲፫፥፲፬)። የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ሲል ጸጋ የእርሱ ብቻ፣ የእግዚአብሔርም ፍቅር ሲል ፍቅር የአብ ብቻ፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ሲል ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ ብቻ እንዳይመስለን መረዳት ይገባል። በሥላሴ የአንድነት ግብር አንዱ ቢጠራበትም ለሁለቱም ይሆናል። የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን ሲል የአብ ጸጋ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን ማለቱ ነው። ቀጥሎ ያለውም የአብ ፍቅር የወልድ ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ ፍቅር ከእናንተ ጋር ይሁን ማለት ነው። መጨረሻ ላይ ያለውም የአብ ኅብረት የወልድ ኅብረት የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ከእናንተ ጋር ይሁን ማለት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩፻፸፫

"በኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታንም ባነሣው በእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ የሆነ እንጂ ከሰዎች ወይም በሰው ያልሆነ ጳውሎስ ከእኔም ጋራ ያሉት ወንድሞች ሁሉ፥ ወደ ገላትያ አብያተ ክርስቲያናት" (ገላ. ፩፥፩-፪)። ቅዱስ ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን ያስነሣው አብ እንደሆነ ገልጿል። በማስነሣት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው። ስለዚህ የአንዱ ስም ይጠራ እንጂ ሁለቱንም የሚመለከት ጉዳይ መሆኑን ደጋግመን ተመልክተናል። ቅዱስ ጳውሎስ የተላኩት ከሰው ሳይሆን ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ ሐዋርያነቱን ያገኘው ከክርስቶስ መሆኑን ተናግሯል። በዚህ አገላለጹ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ገልጿል። የተላኩት ከሰው አይደለም ሲል የኢየሱስ ክርስቶስን ሰውነት ዘንግቶ አይደለም። ሐዋርያነቴን ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ከሆነ አካል አላገኘሁም። አምላክም ሰውም ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ አገኘሁ እንጂ ማለቱ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩፻፸፬

"ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጂ እኔ ከሰው አልተቀበልኹትም አልተማርኹትምም" (ገላ.፩፥፲፪)። በዚህ ኃይለ ቃል ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርቱን ከሰው አልተቀበልኩትም ከሰውም

አልተማርኩትም ካለ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ ገለጠልኝ እንጂ ብሏል፡፡ ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የመሰከረበት ቃል ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) አይደለምና፡፡ ክርስቶስ ሲያስተምር ብዙ ጊዜ ራሱን "የሰው ልጅ" እያለ አስተምሯል፡፡ ራሱን "የእግዚአብሔር ልጅ" እያለም አስተምሯል፡፡ አንዱ እርሱ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነውና፡፡ ክርስቶስ ሥግው ቃል ስለሆነ መለኮት ብቻ ወይም ሥጋ ብቻ አንለውም፡፡ በተዋሕዶ አምላክም ሰውም የሆነ አንድ ልጅ (ወልድ ዋሕድ) እንለዋለን እንጂ፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፸፭

"ነገር ግን፥ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይኾን ዐውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፥ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል፡፡ ነገር ግን፥ በክርስቶስ ልንጸድቅ የምንፈልግ ስንኾን ራሳችን ደግሞ ኀጢአተኞዎች ሆነን ከተገኘን፥ እንግዲያስ ክርስቶስ የኀጢአት አገልጋይ ነዋ አይደለም" (ገላ. ፪፥፲፮-፲፯)፡፡ በዚህ ዓረፍተ ነገር ሕግ ተብላ የተገለጸችው ኦሪት ናት፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ በሕግ ሥራ ሰው እንዳይጸድቅ እናውቃለን ማለቱ ሕገ ወንጌል ከመጣች በኋላ በኦሪት ሕግ ብቻ በማመንና የኦሪትን ሥራ ብቻ በመሥራት ሰው ክብርን እንደማያገኝ ለመግለጽ ነው፡፡ ይኸውም ክርስቶስን ሳያምኑ በኦሪት ሕግ ብቻ እንመራለን የሚሉ አይሁድ እንደማይጸድቁ ያሳውቀናል፡፡ ኦሪትስ መርሐ ኮነተነ እንዲል ኦሪት ሰውን ወደ ወንጌል ለማድረስ መሪ ሆነችን፡፡ ከዚህ በኋላ በሕገ ወንጌል እንመራለን እንጂ ጥምቀት እንበለ ግዝረት አይጠቅምም እያልን አናስተምርም፡፡ በክርስቶስ እናምናለን እያልን ኃጢአትን የምንሠራ ከሆነም ድኅነትን አናገኝም፡፡ በክርስቶስ አምነን መልካም ሥራንም በመሥራት እንጸድቃለን (እንድናለን) እንጂ፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፸፮

"አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም ኹላችኹ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችኹና" (ገላ. ፫፥፳፰)፡፡ በክርስቶስ ስም ከተጠመቅን በኋላ ሁላችንም በእርሱ አንድ ነን፡፡ መለያየት የለም፡፡ የግሪክም ሰው ቢሆን፣ ባሪያም ቢሆን፣ ሴትም ብትሆን፣ ወንድም ቢሆን፣ በጠቅላላው ምንም ቢሆን አንድ ነን፡፡ ቤተክርስቲያንን ኵላዊት ናት ስንል የሁላችንም ናት ማለታችን ሲሆን በዘር፣ በቋንቋ፣ በዘመን የማትለያይ ክርስቶስ ራሷ የሆነላት ናት ማለታችን ነው፡፡ በጥምቀት አንድ ከሆንን በኋላ ባላባት፣ ባሪያ፣ ሽማኔ፣ ቀጥቃጭ እያሉ መለያየት ተገቢነት የለውም፡፡ በስሙ አምነን ከተጠመቅን በኋላ ለምሥጢረ ክህነትም፣ ለምሥጢረ ተክሊልም ለሌሎችም ምሥጢራት በሥርዓታቸው መሠረት የተገባን ሆነን ከተገኘን ክህነትም፣ ተክሊልም ለሁላችንም የተፈቀደ ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፸፯

"ነገር ግን፥ የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ" (ገላ. ፬፥፬)፡፡ ወልደ እግዚአብሔር ሰው እንደሚሆን አስቀድሞ በቅዱሳን ነቢያት ትንቢትን አስነግሯል፡፡ ምሳሌ አስመስሏል፡፡ ሱባዔ አስቆጥሯል፡፡ ለአዳም

የገባለት የቃል ኪዳን ዘመን በደረሰ ጊዜ ጌታ ሳይዘገይ በጊዜው ከድንግል ማርያም ያለወንድ ዘር ተፀነሰ:: ለአዳም ከ5500 ዘመን በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ያለው ዘመን ደርሶ መጋቢት 29 ቀን በዕለተ እሑድ ድንግል ማርያም ይኩነኒ ስትል ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ተፀነሰ:: ታኅሣሥ 29 ቀን በዕለተ ማክሰኞም ተወለደ:: የዘመኑ ፍጻሜ ያለው ይህንን ነው:: ልጁን ሳከ የተባለ አብ ነው:: ወልድ የአብ የባሕርይ ልጅ ነውና:: ከሕግ በታች ማለት በኦሪት ፀንቶ የኦሪትን ሕግ እየሠራ ወደ ሕገ ወንጌል መምራቱን የሚያመለክት ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩፻፸፰

"ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልኹበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ከእኔ ይራቅ" (ገላ. ፮፥፲፬):: የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል መመኪያችን ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ እንኳ "ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ከእኔ ይራቅ" ብሏል:: መስቀል ያለው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የደረሰውን መከራ ነው:: የክርስቶስ መስቀል በሲኦል ተግዘን እንኖር ለነበርነው እኛ ነጻነትን ያገኘንበት፣ በዲያብሎስ ጽኑ አገዛዝ ተሰቃይተን የነበርን እኛ ዕረፍትን ያገኘንበት፣ በኀዘን የነበርን እኛ ደስታን ያገኘንበት ስለሆነ በመስቀሉ እንመካበታለን:: ጌታም እኛ ድኅነትን ስላገኘንበት መስቀሉን ክብር ብሎ ጠርቶታል:: "ይትባረክ እግዚአብሔር ዘሰመየ ሕማማተ ወልዱ ክብረ ወስብሐተ" እንዲል::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩፻፸፱

"በክርስቶስ ኢየሱስ ዐዲስ ፍጥረት መኾን ይጠቅማል እንጂ መገረዝ ቢኾን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና" (ገላ. ፮፥፲፭):: በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን ለማመንና ለማምለክ ምልክቱ ግዝረት ነበር:: ይኸውም በስምንተኛው ቀን ይከናወን ነበር:: ግዝረት የእምነት ምልክት ሆኖ የተሰጠው መጀመሪያ ለአብርሃም ነው:: ከዚያ በኋላ ከአብርሃም የተወለዱት ሁሉ እየተገረዙ አምልኮታቸውን ይፈጽሙ ነበር:: በሐዲስ ኪዳን ግን መገረዝም አለመገረዝም ነውርነት የለውም:: ከአምልኮት ጋር የሚያያዝ ነገር የለውም:: ተጠምቆ ያልተገረዘ ሰው ክህነት ልቀበል ቢል መቀበል ይችላል:: ያልተጠመቀ ሰውም ሳይገረዝ ልጠመቅ ቢል መጠመቅ ይችላል:: ግዝረት በሐዲስ ኪዳን ከአምልኮተ እግዚአብሔር ጋር የሚገናኝ ነገር የለውም:: በብሉይ ኪዳኑ ግዝረት አሁን ጥምቀት ተተክቶበታልና::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፩፻፹

"ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በኾን ጊዜ ከክርስቶስ ጋራ ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና" (ኤፌ. ፪፥፭):: ሞት ምሥጢሩ መለየት ማለት ሲሆን ሁለት ዓይነት ነው:: አንደኛው የነፍስ ከሥጋ መለየት ሞት ይባላል:: ሁለተኛው ሰው ኃጢአት ሠርቶ ከእግዚአብሔር ሲለይ ሞተ ይባላል:: ቅዱስ ጳውሎስ በበደላችን ሙታን ነበርን ያለው ይህኛውን ሁለተኛውን ሞት ነው:: ሞተን የነበርን እኛን ከድንግል ማርያም ተወልዶ ያዳነን እና የእኛን ሞት ሞቶ ሕይወትን የሰጠን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: "እንቲኣነ ሞተ ነሥአ ወእንቲኣሁ ሕይወተ ወሀበነ ዘሎቱ ክብር ወስብሐት" እንዲል:: ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን ያለው ይህ

ነው:: ሥጋ ቃልን በተዋሐደ ጊዜ ባሕርያዊ ሕይወትን ገንዘቡ አድርጓል:: ክርስቶስ ደግሞ ስለእኛ ተሰቅሎ ባዳነን ጊዜ የጸጋ ሕይወትን አገኘን:: በጸጋ ድናችኋል ማለቱ ለዚህ ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፹፩

"ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በርሱ ኹለታቸውን ባንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋራ ያስታርቅ ዘንድ ነው" (ኤፌ. ፪፥፲፮):: ሁለታቸውን አካል ያስታርቅ ዘንድ ያለው ሕዝብን አሕዛብን ማስታረቁን ለመግለጽ ነው:: በአንድ አካል አስታረቃቸው ማለት ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆኖ በዋሕድ አካሉ ማስታረቁን ለማስረዳት ነው:: እርሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ በመስቀሉ አፈረሰው:: በመስቀሉ ሰላምን አደረገ:: ጥልን አጠፋ:: "ወገብረ ሰላመ በመስቀሉ" እንዲል:: አንድም በመስቀል ዲያብሎስ ድል ነሣው:: ዲያብሎስን በግብሩ ጥል አለው:: ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀን የሚለው ከራሱ ጋር፣ ከአብ ጋር፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አስታረቀን ማለት ነው:: እግዚአብሔር በሚለው ስም ሦስቱም አካላት ይጠሩበታልና::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፹፪

"በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማእዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው" (ኤፌ. ፪፥፳):: የሐዋርያትና የነቢያት መሠረት የተባለው እምነታቸው ትምህርታቸው ነው:: ቤተ ክርስቲያን በነቢያት ትንቢት፣ በሐዋርያት ስብከት ጸንታ የምትኖር መሆኗን ለመግለጽ እንዲህ አለ:: የማዕዘኑም ራስ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ማለት ለነቢያት የትንቢታቸው ምንጭ፣ ለሐዋርያትም የትምህርታቸውና የእምነታቸው መሠረት መምህረ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት ነው:: "አንተ ዐለት ነህ በአንተ ዐለትነት ቤተ ክርስቲያኔን እመሠርታታለሁ" ብሎ ለቅዱስ ጴጥሮስ ራሱ ጌታ እንደነገረው (ማቴ. ፲፮፥፲፰):: ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ነው:: ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት "ግንበኞዎች የናቁት ድንጋይ፥ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ" ብሎ ትንቢት የተናገረለት እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (መዝ. ፻፲፯፥፳፪):: ግንበኞች የተባሉ አይሁድ ባለማወቅ የናቁትና የሰቀሉት ከሁሉ በላይ የሆነ አምላክ እርሱ ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፹፫

"በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው" (ፊልጵ. ፪፥፱):: እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ይኸውም በሰውነቱ እንደሆነ ልብ ማድረግ ይገባል:: ሥጋ በተዋሕዶ ቃልን ገንዘቡ ባደረገ ጊዜ ሥጋነቱን ሳይለቅ አምላክ ሆኗል:: አምላክ መሆን ደግሞ ከምንም በላይ ስለሆነ ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው ተብሏል:: ከስምም በላይ ያለውን ስም ሰጠው ማለቱ ወልደ እጓለ እመሕያው ብቻ ይባል የነበረ ሰውነት በተዋሕዶ አምላክ ወልደ አምላክ ለመባል በቅቷልና ነው:: ሥጋ ቃልን ገንዘቡ ቢያደርግ ወልደ አብ ተባለ:: ቃልም ሥጋን ገንዘቡ ቢያደርግ ወልደ ማርያም ተባለ:: ያው አንዱ አካል ክርስቶስ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ተባለ::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፹፬

"ኹልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችኹ ደግሜ እላለኹ፥ ደስ ይበላችኹ" (ፊልጵ. ፬፥፬)። ደስታ አራት ዓይነት ነው። ይኸውም የቀበሮ ደስታ፣ የኖሎት ደስታ፣ የሰይጣን ደስታና፣ የመላእክት ደስታ ናቸው። ቀበሮ በበረሃ የጣዝማ ማር ያገኘች እንደሆነ ከደስታዋ ብዛት የተነሣ ማሩ እስኪጠፋት ትዘላለች ይባላል። ይህ ሁሉ ደስታዋ ሥጋዊ ምግብን አገኘሁ ብላ ስለሆነ ደስታዋ ሥጋዊና ኃላፊ ነው። ሁለተኛው ደስታ ጌታ የተወለደ ጊዜ እረኞች ከሰይጣን ባርነት ነጻ የሚያወጣቸው ኢየሱስ ክርስቶስ በመወለዱ የተደሰቱት ደስታ ነው። ነፍሳዊ ዋጋን የሚያገኙበትን ነገር በማግኘታቸው የተደሰቱት ደስታ ነው። የሰይጣን ደስታ የሚባለው ደግሞ ሰው ኃጢአት ሠርቶ ከእግዚአብሔር ሲጣላ የሚደሰተው ደስታ ነው። ሰይጣን ምቀኛና ቅንዐተኛ ስለሆነ በሌሎች ኀዘን እርሱ ላይጠቀም ይደሰታል። የመላእክት ደስታ ደግሞ ሌሎች ሰዎች በመጠቀማቸው የሚደሰቱት ደስታ ነው። ሐዋርያው በጌታ ደስ ይበላችሁ አለን። በገንዘብ፣ በውበት፣ በጉልበትና በመሳሰሉት መደሰት ቆይቶ ኀዘንን ያመጣል። ሁሉም እንዳልነበሩ ይሆናሉና። ጌታ እግዚአብሔር ግን ዘለዓለማዊ ስለሆነ በእርሱ መደሰት ኀዘን የለበትም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፹፭

"ኀይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለኹ" (ፊልጵ. ፬፥፲፫)። አካላችንን፣ ተፈጥሮን፣ ዕውቀትን፣ ኃይልን፣ ጉልበትን፣ ገንዘብን እና የመሳሰሉትን ነገሮች ያገኘነው ከፈጣሪያችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከፈጣሪ ያላገኘነው ነገር የለም። "ምንት ብከ ዘኢነሣእከ እምኀበእከ ወምንት ብል ዘኢኮነ ውሁበ ለከ" እንዲል። በባሕርይው ኃያል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለፍጡራን ኃይልን የሚሰጥም እርሱ ስለሆነ "ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ" ብሎ ሐዋርያው ተናገረ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፹፮

"የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችኹ ጋራ ይሁን አሜን" (ፊልጵ. ፬፥፳፫)። ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን የሚለው ከእናንተ ጋር ይሁን ለማለት ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሚባለው ልጅነት፣ ረድኤት ነው። የተጠመቁ ሰዎች እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር አለ። ረድኤተ ሥጋ ረድኤተ ነፍስን፣ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን፣ ፈውሰ ሥጋ ፈውሰ ነፍስን ይሰጣቸዋል። አሜን የሚለው ቃል ለታሪክ ሲሆን እውነት ነው ማለት ነው። ለበረከት ሲሆን ይደረግልኝ ይፈጸምልኝ ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ መጨረሻ ላይ አሜን ማለቱ መልካሙ ሁሉ ይሁንላችሁ ይደረግላችሁ ሲል ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፹፯

"የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ኹልጊዜ እናመሰግናለን" (ቈላ. ፩፥፫)። ምስጋና ሁለት ዓይነት ነው። እነዚህም የባሕርይ ምስጋና እና የጸጋ ምስጋና ተብለው ይከፈላሉ። የባሕርይ ምስጋና የሚገባው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። የጸጋ ምስጋና የሚገባቸው ደግሞ ቅዱሳን መላእክት፣ ቅዱሳን ነገሥታት፣ ቅዱሳን መነኮሳት፣ ቅዱሳት አንስት፣ ቅዱሳን

ሰማዕታት እና በጠቅላላው ቅዱሳን ናቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን ብሏል። ይህ ምስጋና የባሕርይ ምስጋና ነው። አብን ማመስገን ወልድን ማመስገን ነው። ወልድን ማመስገን አብን ማመስገን ነውና። ሦስቱ አካላት በምስጋና አንድ ናቸውና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፹፰

"ርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው" (ቈላ. ፩፥፲፭)። በዚህ አግባብ ምሳሌ የሚለው ቃል ትርጉሙ የማይታይና የማይመረመር እግዚአብሔር አብን በመልክ የሚመስለው በባሕርይ የሚተካከለው ማለት ነው። የሚተካከለው የሚለው ቃል በባሕርይ አንድ መሆናቸውን የሚገልጽ ነው እንጂ ለየብቻ ባሕርይ ኖሯቸው ያ ባሕርያቸው የሚመሳሰል ነው ለማለት አይደለም። የሦስቱም ባሕርይ አንድ ነውና። አብን ያየው አንድም የለም። ወልድንም በሰውነቱ እንጂ በመለኮቱ ያየው አንድም የለም። መንፈስ ቅዱስንም ያየው የለም። ሦስቱ አካላት በጣም ረቂቃን በመሆናቸው ከፍጡራን ኅሊና በላይ ናቸውና። ሦስቱም ተመሳሳይ መልክ፣ ተመሳሳይ አካል፣ ተመሳሳይ ገጽ አላቸው። በገጽ፣ በአካል፣ በመልክ ሦስት ናቸው። በባሕርይ ግን አንድ ናቸው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፹፱

"በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በርሱ ተፈጥረዋልና፥ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው። ሁሉ በርሱና ለርሱ ተፈጥሯል" (ቈላ. ፩፥፲፮)። ይህ የምናየው ፍጥረት ሁሉ በራሱ የተገኘ አይደለም። ፈጣሪ አለው። ፍጥረታት ፍጡራን በመሆናቸው መነሻ ዘመን አላቸው። መነሻ ዘመን የሌለው ዘለዓለማዊ እግዚአብሔር ብቻ ነው። በሰማይም በምድርም ያሉ ፍጥረታት የተፈጠሩት በልዑል እግዚአብሔር ነው። ከፍጥረት ሁሉ በኩር ነው ማለት ፍጥረታትን ሁሉ ቀድሞ የሚኖር አምላክ ነው ማለት ነው። ሁሉ በእርሱ ተፈጥሯል የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በዚህ አገላለጽ ሁሉን መፍጠርን ለኢየሱስ ክርስቶስ አድርጎ ቢናገርም በባሕርያዊ ግብር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ስለሆኑ ሁሉ በአብ ተፈጥሯል፣ ሁሉ በወልድ ተፈጥሯል፣ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተፈጥሯል ቢል ሁሉም ምስጢሩ አንድ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፺

"ርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው። ርሱም በሁሉ ፊተኛ ይኾን ዘንድ፥ መጀመሪያ ከሙታንም በኵር ነው" (ቈላ. ፩፥፲፰)። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካሉ ተብላ ተገልጻለች። ይኸውም በእርሱ አምናና ተጠምቃ የእርሱን ትምህርት በማስተማር ጸንታ ስለምትኖር ነው። እርሱም የቤተክርስቲያን ራስ ተብሏል። ራስ ከሁሉ በላይ እንዲገኝ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ስለሆነ የሁሉ በላይ ነውና። መጀመሪያ ከሙታን በኩር ነው የሚለው አነጋገር ሞቶ አማናዊውን ትንሣኤ በመነሳት የመጀመሪያ ነው ለማለት ነው። ሞት በአቤል ተጀምሯል። ሞት በአቤል ቢጀመርም አቤል አማናዊውን ትንሣኤ ገና ስላልተነሣ በኵረ ሙታን አልተባለም። ሞትን ሞቶ አማናዊውን ትንሣኤ የተነሣ የመጀመሪያው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለሆነም በኵረ ሙታን በኵረ ትንሣኤ ይባላል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፺፩

"በርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷልና" (ቈላ. ፩፥፳)። አዳም ከፈጣሪው ጋር በኃጢአት ምክንያት በተጣላ ጊዜ መላእክትም አዳምን ተጣልተውት ነበር። በኋላ ግን መድኃኔዓለም ክርስቶስ በደላችንን ይቅር ብሎ በመስቀል ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ ካዳነን በኋላ ቅዱሳን መላእክትም ታረቁን። በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷል ያለው ለዚህ ነው። መላእክትን በመኖሪያቸው ሰማያት ብሏቸዋል። እርሱ ራሱ ከራሱ ጋር ካስታረቀን በኋላ የማስታረቅን ሥልጣን ለቅዱሳን ሐዋርያት ሰጥቷል። ይህ የማስታረቅ ሥልጣን እስከ ዕለተ ምጽአት ለሚነሡ ካህናት ሁሉ የተሰጠ ነው። በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል እንዲል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፺፪

"በፊት የተለያችኹትን ክፉ ሥራችኹንም በማድረግ በዐሳባችኹ ጠላቶች የነበራችኹትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችኹ" (ቈላ. ፩፥፳፪)። በፊት የተለያችሁትን ያለው አዳም አትብላ የተባለውን ትእዛዝ ተላልፎ ከእግዚአብሔር ተለይቶ እንደነበረ የሚያመለክት ቃል ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ከተለየ በኋላ እኩያት ፍትወታት (ክፉ ምኞቶችና ሐሳቦች) ሠልጥነውበት ይኖር ነበር። "አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ" ያለው በኋላ ግን ወልደ እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ በሥጋው ሞቶ አስታረቀን ማለት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፺፫

"እናንተም በበደላችኹና ሥጋችኹን ባለመገረዝ ሙታን በሁናችሁ ጊዜ፥ ከርሱ ጋራ ሕይወትን ሰጣችኹ። በደላችኹን ሁሉ ይቅር አላችሁ" (ቈላ. ፪፥፲፫)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቈላስይስ ሰዎች አብዝቶ ስለ ይቅርታ አስተምሯል። ይቅርታ ሌሎች ሰዎች የበደሉንን በደል ከልብ ይቅር ማለት ነው። እኛም የበደልናቸውን ሰዎች በበደላችን ተጸጽተን ራሳችንን ዝቅ አድርገን ይቅር ማለት ነው። ይቅርታ የሻከረ ግንኙነትን ይጠግናል። ወንድማማችነትን፣ ሕብረትን፣ ፍቅርን ያጎለብታል። በባሕርይው መሓሪ (ይቅር ባይ) እግዚአብሔር ነው። ብዙ በደል በድለን ይሆናል። እግዚአብሔር ግን ይቅር ባይ ስለሆነ ኃጢአታችንን ይቅር ይለን ዘንድ ንስሓ እንግባ። ኃጢኣታችን እንደ አለላ ብትቀላ እርሷን አስወግዶ እንደ ባዘቶ ነጭ ያደርገናል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፺፬

"ክርስቶስ ይቅር እንዳላችኹ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ" (ቈላ. ፫፥፲፫)። ክርስቶስ ይቅር ያለን እንዲሁ ነው። እኛ ያደረግንለት ነገር ሳይኖር በፍቅሩ ይቅር አለን። ይቅርታ የፍቅር መቅድም ነው። ይቅርታ የፍቅር ፍጻሜም ነው። ሰው ሰውን ሲወድ በደሉን ሳያስብ እንዲሁ ይወደዋል። ይቅርታ ሰዎች ካደረሱብን መከራና በደል ይልቅ ፍቅራቸው ይበልጥብኛል ብሎ የደረሰብንን መከራና በደል መተው ነው። በእኛ ዘንድ የበደለ ክሦ የተበደለ ተክሦ ይቅርታን ይጠይቃል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅር ያለን ግን በዚህ መንገድ አይደለም። የበደልነው እኛ

ሆነን ሳለ የካሠንም እርሱ ራሱ ነው። የተካሥን ደግሞ እኛ የበደልነው ሰዎች ነን። እኛም መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስን አብነት አድርገን የበደሉንን ይቅር ማለት ይገባናል።

### ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፺፩

"ወንጌላችን በኀይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና" (፩ኛ ተሰሎ. ፩፥፭)። ሃይማኖታችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ የተሠጠች ናት። በቃል ብቻ የተሰጠች አይደለችም። አንድ ነገር በቃል ብቻ ሲነገር ታማኝነቱ ዝቅ ያለ ነው። የብዙዎች እምነት በቃል ብቻ የተመሠረተ ነው። እምነቱ ትክክል መሆን አለመሆኑ በተአምራትና በመንፈሳዊ ኃይል አልተገለጠም። በሰይፍና በጉልበት በሥጋዊ ኃይል መጥቶ በዚሁ መንገድ ተስፋፋ እንጂ። የክርስትና እምነት ግን ቀድሞ በነቢያት በቃልም በኃይልና በመንፈስም የተገለጠ በኋላም ራሱ ወልደ እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ተወልዶ በዚህች ምድር ተመላልሶ በማስተማርና አምላካዊ ሥራዎችን እየሠራ በማሳየት የተገለጠ ነው።

### ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፺፪

"ጌታም ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ወደ ክርስቶስም ትዕግሥት ልባችንን ያቅናው" (፪ኛ ተሰሎ. ፫፥፭)። በዚህ ዓረፍተ ነገር ምሥጢረ ሥላሴ ተገልጿል። ጌታም ብሎ አብን፣ እግዚአብሔር ብሎ መንፈስ ቅዱስን፣ ክርስቶስን ብሎ ወልደ እግዚአብሔርን ገልጿል። በዚህ አገላለጽ አብ ወደ ወልድና ወደ መንፈስ ቅዱስ ልባችንን ያቅናልን እያለ ነው። በዚህ ጊዜ ልብን ማቅናት የአብ ሥራ መስሎ ቀርቧል። የፍጡራንን ልብ በማቅናት አብም ወልድም መንፈስ ቅዱስም አንድ ናቸው። በፍጡራን ላይ ባላቸው ግብር ሦስቱ አካላት አንድ ናቸውና። ለፍጡራን ባላቸው ግብር አንዱ አካል ብቻ ተጠቅሶ አንድ ኃይለ ቃል ቢነገርም ያ ኃይለ ቃል ግን በጊዜው ላልተጠቀሱት ሁለቱ አካላትም እንደሚሆን ደጋግመን ተማምረናል።

### ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፺፫

"ጌታ ከኹላችኹ ጋራ ይሁን" (፪ኛ ተሰሎ. ፫፥፲፮)። ጌታ ከሁላችሁ ጋራ ይሁን የሚለው አገላለጽ በረድኤት ከእናንተ ጋር ይሁን ማለት ነው። በአካል ግን ጌታ የሌለበት ቦታ ስለሌለ ማንኛውም ፍጡር ካለበት ቦታ ሁሉ አለ። ፍጡራንን ይቶርፋቸዋል እንጂ አይተርፉትም። ፍጡራን በቦታ በጊዜ የተወሰኑ ናቸው። ፍጡራን ምንም ያህል ትልቅ ቢሆኑ መነሻና መድረሻ አላቸው። ለፈጣሪ ግን ወሰን የለበትም። ከሁላችሁ ጋር ይሁን ማለት ለሁላችሁም ረድኤተ ሥጋ ረድኤተ ነፍስን ይስጣችሁ ማለት ነው።

### ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፺፬

"ብቻውን አምላክ ለሚኾን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘለዓለም ድረስ ይሁን አሜን" (፩ኛ ጢሞ. ፩፥፲፯)። ብቻውን አምላክ የሆነ እግዚአብሔር ነው። አብ ብቻውን አምላክ ነው። ወልድ ብቻውን አምላክ ነው። መንፈስ ቅዱስም ብቻውን አምላክ ነው። ሦስቱ አካላት በከዊን ስለሚገነዛዘቡ አንድ አምላክ ይባላሉ እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም። "ብቻውን" የሚለው ቃል ከፍጡራን ለመለየት ነው። "ለማይጠፋውና ለማይታየው"

የሚለው ቃል አምላክ የማይታይ ረቂቅ፣ ሙስና የሌለበት ዘለዓለማዊ ሕያው ነው ለማለት ነው። "የዘመናት ንጉሥ" የሚለው ፍጡራን ንጉሥ ቢባሉ ሠላሳና አርባ ዓመት ገዝተው ሞት አለባቸው። በሞት ንግሥናቸውም ይፈጸማል። እግዚአብሔር ግን ሞት የሌለበት ለዘለዓለም ንጉሥ የሆነ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፪፻፺፱

"ከመድኀኒታችንም ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ምሕረት ሰላምም ይሁን" (ቲቶ ፩፥፬)። ኢየሱስ ማለት ትርጉሙ መድኃኒት ማለት ነው። ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ጌታ" እና "መድኃኒት" ብሎ ገልጾታል። በዓለም ላይ ያሉ መድኃኒቶች እያንዳንዳቸው የሚያድኑት ጥቂት በሽታዎች ይኖራሉ። አንዱ መድኃኒት ግን ሁሉንም በሽታዎች አያድንም። አንድ መድኃኒት ጥቂት በሽታዎችን ብቻ ሊያድን ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስን መድኃኒት ስንለው ግን ዓለምን ሁሉ ያዳነ ነው ማለታችን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ነው። አንዱ እርሱ ማንኛውንም በሽታ ይፈውሳል። ኢየሱስ የማያድነው በሽታ የለም። ስለዚህ የምንመካበት ዋናው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻

"ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዐይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን። ርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ኾኖ፥ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ፥ ኀጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ፥ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ። ከመላእክት ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ስምን በወረሰ መጠን፥ እንዲሁ ከነርሱ አብዝቶ ይበልጣል" (ዕብ. ፩፥፩-፬)። ሃይማኖት እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠው አንዱ ስጦታ ነው። እግዚአብሔር ህልውናውን ከአዳም ጀምሮ ለተነሡ አባቶቻችን ገልጿል። ይኸውም በራእይ፣ በሕልም፣ በቃል፣ በዘፈቀደ ተገልጾላቸዋል። በብዙ ዓይነትና ጎዳና ተናገረ ማለቱ በትንቢት፣ በምሳሌ፣ በራእይ መገለጹንና ማስተማሩን ያስረዳል። በኋላ ግን ነቢያት ይወለዳል ያሉት ጌታ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሥግው ሆኖ አስተማረን። ወልደ እግዚአብሔር ዓለማትን የፈጠረ መሆኑን ገልጾልናል። አብ በወልድ ፍጥረታትን ፈጠረ ማለት አብ የወልድ ቃልነት ሳይለየው ፍጥረታትን ፈጠረ ማለት ነው። ለጊዜው ወልድ ይጠቀስ እንጂ የመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነትም ሳይለየው ለማለት ነው። ብዙዎች ከሓድያን ወልድ ከአብ ያንሣል፣ አብ ወልድን ፈጥሮ ፈጠረበት ይሉ ነበርና "የክብሩ ነጸብራቅ" አለባቸው። ነጸብራቅ የተለየው ብርሃን የለም። አብን ብርሃን ካሉ ወልድን ነጸብራቁ ይልባቸዋል። ይህም የወልድ ህልውና እንደ አብ ቅድመ ዓለም መሆኑን እንረዳለን። አሐቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ ወዕሩያን እሙንቱ በቅድምና እንዲል። ኃጢአታችንን በራሱ አነጻን አለ። ይኸውም ራሱ መሥዋዕት ሆኖ ራሱ ተወካፌ መሥዋዕት ሆኖ አነጻን ማለት ነው። በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ ማለቱ ባለመራብ፣ ባለመጠማት፣ ባለመታመም ግብሩ ጸንቶ ኖረ ማለት ነው። ሥጋ ቃልን ቢዋሐድ ከመላእክት ይልቅ የሚበልጥ ስምን ወረሰ አለ አምላክ መባልን ገንዘብ አደረገ። ከተዋሕዶ በኋላ ከመላእክት የሚበልጥ ሆነ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፩

"ከመላእክትስ፦ አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወልጄኻለኹ፥ ደግሞም፦ እኔ አባት እሆነዋለኹ ርሱም ልጅ ይሆነኛል። ያለው ከቶ ለማን ነው ደግሞም በኵርን ወደ ዓለም ሲያገባ፦ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለርሱ ይስገዱ ይላል" (ዕብ. ፩፣፭-፯)። አንተ ልጄ ነህ የሚለው ቃል ወልድ የአብ ልጅ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ወልድ ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወልዷልና። "እኔ አባት እሆነዋለሁ" የሚለው አገላለጽ ስለሰውነቱ የተነገረ ቃል ነው። ቃል ሥጋን ሲዋሐድ የሥጋ ገንዘብ ለቃል የቃል ገንዘብ ለሥጋ ሆኗል። ይህም ማለት ለሥጋ አብ አባቱ፣ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕይወቱ ሆኑት ማለት ነው። በተዋሕዶ ቃል ሰው እንደሆነ መጠን ሥጋ የባሕርይ አምላክ ሆነ። ይኸውም ሥጋም ቃልም የቀደመ ማንነታቸውን ሳይለቁ በተዐቅቦ ነው። "ዛሬ ወለድኩህ" የተባለው ስለሰውነቱ ነው። ወልድ በአምላክነቱ ዛሬ ከተባለችዋ ጊዜ ቀድሞ ይኖር ነበርና። መለኮት በሰውነቱ ዛሬ ወለድኩህ መባልን ገንዘብ አደረገ። "ወለድኩህ" የሚለው ቃል "ልጄ አደረጉህ" ማለት ነው። ሰው አምላክ ስለሆነ ቅዱሳን መላእክት የሚሰግዱለትና የሚገዙለት መሆኑን ለመግለጽ "የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይስገዱ" ተባለ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፪

"ጽድቅን ወደድኽ፥ ዐመፅንም ጠላኽ ስለዚህ፥ እግዚአብሔር አምላክኽ ከጓደኞችኽ ይልቅ በደስታ ዘይት ቀባኽ ይላል" (ዕብ. ፩፣፱)። ከዚህ የነገሩ ባለቤት ወልደ እግዚአብሔር ነው። ጽድቅን ወደድክ ማለት ሰው መሆንን ወደድክ ማለት ነው። ዐመፅን ጠላህ ማለት ሰው አለመሆንን ጠላህ ማለት ነው። እግዚአብሔር ጓደኞችህ ከተባሉ ነቢያት የበለጠ የደስታ ዘይትን ቀባህ አለ። የደስታ ዘይት የተባለ ክብር ነው። ነቢያት ክብር ቢኖራቸው የጸጋ ክብር ነው። ክርስቶስ የተዋሐደው ሥጋ ያገኘው ክብር ግን የባሕርይ ክብር ነው። ጓደኞቹ ከተባሉት ይልቅ የደስታ ዘይትን ቀባህ ማለቱ ለዚህ ነው። ቀባህ ማለቱ አከበረህ ማለት ነው። በማክበር ደግሞ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፫

"ጠላቶችኽን የእግርኽ መረገጫ እስካደርግልኽ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ" (ዕብ. ፩፣፲፫)። ጠላቶችህ የተባሉት አጋንንት፣ ከሓድያን፣ አይሁድ ናቸው። የእግርህ መረገጫ የተባሉት ሐዋርያት፣ ሥልጣነ መለኮት፣ ረድኤት መስቀል ናቸው። ስለዚህ በሐዋርያትህ፣ በሥልጣነ መለኮትህ፣ በረድኤትህ፣ በመስቀልህ ጠላቶችህን እስካጠፋልህ በቀኜ ተቀመጥ አለው። ይኸውም ጠላቶቻችን ከተባሉት ከእነዚህ ጋር እስከ ዕለተ ምጽአት በሚነሱ ካህናት እያደረ ያጠፋልናል ማለቱ ነው። ጠላቶችህን በእግርህ እርግጥ አድርጌ እስካስገዛልህ በዕሪናየ ኑር። ይህ "እስከ" ፍጻሜ የሌለው "እስከ" ነው። በዕለተ ምጽአት በአጋንንት፣ በከሓድያን፣ በአይሁድ ከተፈረደባቸው በኋላ በቀኙ አይቆምም ማለት አይደለም። ከዚያ በኋላም በአምላክነቱ ጸንቶ ይኖራል ማለት ነው እንጂ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፬

"እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ በምልክትና በድንቅ ነገር በልዩ ልዩ ተኣምራትም፥ መንፈስ ቅዱስንም በማደል ዐብሮ መሰከረለት" (ዕብ. ፪፡፬)። እግዚአብሔር አብ ለኢየሱስ ክርስቶስ በብዙ መንገድ መስክሮለታል። በደመና ሆኖ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ መስክሮለታል። መንፈስ ቅዱስንም በማደል አብሮ መሰከረለት ማለት መንፈስ ቅዱስ የሥጋ የባሕርይ ሕይወቱ ሆነው ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑን በብዙ መንገድ ለሰው ልጆች አሳይቷል። የታመሙትን ሁሉ በመፈወስ፣ በፍጥረታት ላይ ሁሉ ችሎታ እንዳለው ባሕርን በመገሠጽ፣ አጋንንትን በማውጣትና በጠቅላላው በታላላቅ ተአምራትና በድንቅ ነገር ራሱን ገልጦልናል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፭

"ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አሳነስኸው የክብርና የምስጋና ዘውድ ጫንኸለት፥ በእጆችኽም ሥራ ላይ ሾምኸው" (ዕብ. ፪፡፯)። የክብርና የምስጋና ዘውድ ጫንኸለት ማለት በተዋሕዶ ሥጋ የባሕርይ ክብር እንዳለውና የባሕርይ ምስጋናን እንደሚመሰገን ያስረዳል። በእጆችህ ሥራ ላይ ሾምከው ማለትም ሥጋ ቃልን በመዋሐዱ የፍጥረታት ሁሉ ገዢ መሆኑን ያመለክታል። "ከመላእክት ጥቂት አሳነስከው" የተባለው ስለሕማሙ የተነገረ ነው። በዚህ ጊዜ መለኪያ መስፈርቱ አለመታመም ነው። መላእክት ረቂቅ ስለሆነ ሥጋዊ ሕማምን አይታመሙም። ወልደ እግዚአብሔር ግን ሥጋን በመዋሐዱ በሥጋው ታሟል። መከራን ተቀብሏል። በአለመታመም መስፈርት አብም ከወልድ ይበልጣል። አብ የሚታመም ሥጋን አልተዋሐደምና። ወልድ ግን የሚታመም ሥጋን በመዋሐዱ መከራን ተቀብሏል። "ከእኔ አብ ይበልጣል" እንዲል (ዮሐ. ፲፬፡፳፰)።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፮

"ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛኸለት ብሎ መሰከረ። ሁሉን ከርሱ በታች ባስገዛ ጊዜ ያልተገዛለት ምንም አልተወምና። አሁን ግን ሁሉ እንደ ተገዛለት ገና አናይም" (ዕብ. ፪፡፰)። ሥጋ ቃልን ቢዋሐድ ሁሉን የሚገዛ (የሁሉ ገዢ) ሆነ። አምላክ ሰው ሲሆን ሰው አምላክ ሆነ። በዚህ ጊዜ ሥጋ ፍጥረታትን ሁሉ የሚገዛ ሆነ። የሁሉ ንጉሥ ሆነ። "አሁን ግን ሁሉ እንደተገዛለት ገና አናይም" ማለቱ ምንም እንኳ ገዢያቸውና አምላካቸው መሆኑን ቢያውቁ አጋንንት በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው አለመዳናቸው ነው። ከሓድያን አይሁድም በጌታ ሳይምኑበት ስለቀሩ "አሁን ግን ሁሉ እንደተገዛለት ገና አናይም" አለ። በምጽአት ጊዜ ግን ሁሉም በጌታ ያምናሉ። ነገር ግን ድኅነትን አያገኙም። ያን ጊዜ የሚመጣው ለፍርድ ነውና።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፯

"ስለዚህ፥ የሕዝብን ኀጢአት ለማስተስረይ፥ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን፥ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው" (ዕብ. ፪፡፲፯)። ወልደ እግዚአብሔር ሰው የሆነው ለአዳም ቤዛ ሆኖ ያድነው ዘንድ ነው። የሕዝቡን ኃጢአት

ለማስተስረይ ነው። ስለዚህም ሊቀ ካህን ሆኖ በመስቀል ላይ የራሱን ሥጋና ደም መሥዋዕት አድርጎ፣ ራሱም መሥዋዕት ተቀባይ ሆኖ ይቅር አለን። ለሊሁ ሠዋዒ፣ ለሊሁ መሥዋዕት፣ ለሊሁ ተወካፌ መሥዋዕት። በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው ማለቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት በስተቀር ሰው የሚያደርገውን ነገር ሁሉ በማድረግ ወንድሞቹ የተባልን እኛን የሰው ልጆችን መሰለ ማለት ነው። "ወኮነ ሰብአ ከማነ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ" እንዲል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፰

"የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ" (ዕብ. ፫፥፩)። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ተብሏል። ሐዋርያት ዓለምን ዞረው የሚያስተምሩ ሂያጆች ማለት ነው። ለእነርሱ ደግሞ አብነታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሕዝቡን ለማስተማር በእስራኤል አውራጃዎች ሁሉ እየሄደ (እየተመላለሰ) አስተምሯልና። ሊቀ ካህናት የተባለበትን ምክንያት ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፯ ላይ ተማምረናል። "ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ" ያለው ሰው ፓትርያርክም ቢሆን፣ ጳጳስም ቢሆን፣ መምህርም ቢሆን፣ ዲያቆንም ቢሆን፣ ቄስም ቢሆን፣ ምሁርም ቢሆን ኃጢአት ሊሠራ ይችላል። ስለዚህ ሰውን ካልሞተ በስተቀር ፍጹም አርዓያ ልናደርገው አንችልም። ይሁዳ ከሐዋርያነት ወርዷልና። አሳዳጅ የነበረው ጳውሎስም ዋና ሐዋርያ ሆኗልና። ሁልጊዜም የማይሳሳት ንጹሐ ባሕርይ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ ሁልጊዜም እርሱን እንድንመለከት ቅዱስ ጳውሎስ ነግሮናል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፱

"ቤትን የሚያዘጋጀው ከቤቱ ይልቅ የሚበልጥ ክብር እንዳለው መጠን፥ እንዲሁ እርሱ ከሙሴ ይልቅ የሚበልጥ ክብር የተገባው ኾኖ ተቈጥሯልና" (ዕብ. ፫፥፫)። ከቤት ባለቤት ይበልጣል። ቤት ሕይወት የሌለው ሲሆን ሰዎች ራሳቸው ለራሳቸው ጥቅም የሚያዘጋጁት ነው። ከቤት ይልቅ ባለቤት ክቡር ነው። እንዲሁም ሙሴን የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። ሙሴን ፈጥሮ ሀብተ ትንቢትን የሰጠውም ራሱ እግዚአብሔር ነው። እስራኤላውያን ለሙሴ ትልቅ ክብር አላቸው። ሙሴን እያከበሩ የሙሴን ፈጣሪ ኢየሱስ ክርስቶስን ግን አምላክ ነው ብለው አያከብሩትም ነበር። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ግን ከሙሴ ጌታ እንደሚበልጥ "ከሙሴ ይልቅ የሚበልጥ" ብሎ ነገራቸው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፲

"ሙሴስ በኋላ ስለሚነገረው ነገር ምስክር ሊሆን በቤቱ ሁሉ እንደ ሎሌ የታመነ ነበረ፥ ክርስቶስ ግን እንደ ልጅ በቤቱ ላይ የታመነ ነው" (ዕብ. ፫፥፭)። ሎሌ ማለት አገልጋይ ማለት ነው። ይኸውም በዐስብ (በደመዎዝ) ለጌታው የሚሠራ ማለት ነው። ልጅ የሚባለው ደግሞ አባቱን የሚወርስ፣ የአባቱ ገንዘብ ሁሉ የእርሱ የሚሆን ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ሙሴን እንደሎሌ የታመነ ነበረ ይለዋል። ይኸውም ሎሌ እንደመሆኑ በሎሌነቱ የታመነ አገልጋይ ነበረ ብሎታል። ክርስቶስን ግን እንደ ልጅ በቤቱ ላይ የታመነ ነው ማለቱ የባሕርይ ልጅ እንደመሆኑ በቤቱ ላይ የታመነ ነው ማለት በሁሉ የተሾመ ነው ማለት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፲፩

"ከኀጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው" (ዕብ. ፬፥፲፭)። ኃጢአት በሦስት መንገድ ይሠራል። ይኸውም በነቢብ (በመናገር)፣ በኀልዮ (በማሰብ)፣ በገቢር (በተግባር) ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም ኃጢአትን አልሠራም ማለታችን ንጹሐ ባሕርይ ስለሆነ በኀልዮም፣ በነቢብም፣ በገቢርም ጻድቅ ንጹሕ ነው ማለታችን ነው። ከኃጢአት በቀር ግን እንደ እኛ የተፈተነ ነው ማለቱ መራቡን፣ መጠማቱን፣ በሥጋ መድከሙን (ወደክመ በሐዊረ ፍኖት እንዲል)፣ በጠቅላላው መከራ መቀበሉን ያስረዳል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፲፪

"አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘለዓለም ካህን ነህ ይላል" (ዕብ. ፭፥፮)። እንደ መልከ ጼዴቅ ባለ ሹመት ተሹመህ የምእመናን አገልጋይ ነህ አለው። መልከ ጼዴቅ መሥዋዕት ሲያቀርብ በስንዴና በወይን ነበር። አብርሃም ነገሥተ ኮሎዶጎሞርን አሸንፎ ሲመለስ ከዐሥር አንድ ዐሥራት አውጥቶለታል። መልከ ጼዴቅ በብሉይ ኪዳን በዚህ ጊዜ ሞተ ተብሎ አልተጻፈም። ጌታ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣ ዘለዓለማዊ አምላክ ነው። ለጌታ ክህነት የመልከጼዴቅ ክህነት ምሳሌው ነው። መልከ ጼዴቅ ከካም ተወልዶ ካህን ሆኗል። የሐዲስ ኪዳን ካህናትም ያለ ዘር ምርጫ ብቁ ሆነው ሲገኙ ይሾማሉ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፲፫

"ርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋራ ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት" (ዕብ. ፭፥፯)። ሰው በሆነበት ወራት ጸሎቱን እንደ ላም፣ ስኢልን እንደ በግ አድርጎ ምእመናንን ከሞት ወደሚያድንለት ወደ አባቱ አቀረበ። እግዚአብሔርም እውነተኛ ልመናውን ሰማው። ኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛ አዳም ሆኖ በሥጋው ወራት ከእንባ ጋራ ጸሎትንና ምልጃን አቅርቧል። ምልጃውም እንደተሰማለት ተገልጿል። ቀድሞ ነቢያት ምልጃን ቢያቀርቡም እነርሱም በጥንተ አብሶ ተይዘው ይኖሩ ስለነበረ ምልጃቸው ነፍሳዊ ድኅነትን ማሰጠት አልቻለም ነበር። ክርስቶስ ግን ንጹሐ ባሕርይ ስለሆነና ጥንተ አብሶ ስለሌበት ምልጃው ተሰማለት ተብሏል። ምልጃውን የሰማለት ሰሚው ማን ነው? ከተባለ ግን ራሱ ወልድ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል። ጌታን የማዳን ሥራውን በመልእልተ መስቀል ከፈጸመ በኋላ የምልጃ ሥራ አለበት አንለውም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፲፬

"ምንም ልጅ ቢኾን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ" (ዕብ. ፭፥፰)። ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ ልጅ ሲሆን ታዝዞ መከራ ስለተቀበለ አባቱ ምእመናንን ከሞት እንደሚያድንለት ዐወቀ። በዚህ ጊዜ ምእመናንን ማዳን የአብ ብቻ ግብር እንዳልሆነ ዕወቅ። አብ በተለየ ይጠቀስ እንጂ ምእመናንን ማዳን የወልድም የመንፈስ ቅዱስም ሥራ ነው። ወልድ ታዝዞ መከራን ተቀበለ መባሉ መከራ የሚቀበል ሥጋን በተዋሕዶ ገንዘቡ ስላደረገ ነው። በሌላ አገላለጽ በኵር ሆኖ መከራ ስለተቀበለ መታዘዝን ለምእመናን አመለከተ መከራ ተቀብሎ መከራ ተቀበሉ አለ

ማለት ነው፡፡ መታዘዝን ተማረ ማለት መማር ለማወቅ ነውና መታዘዝን አወቀ ማለት ነው፡፡ ይህም አዲስ ዕውቀትን አገኘ ማለት ሳይሆን መከራን መቀበልን በተግባር አሳየ ማለት ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፲፭

"በዚያም ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘለዓለም ሊቀ ካህናት የሆነው፥ ስለ እኛ ቀዳሚ ኾኖ ገባ" (ዕብ. ፮፥፳)፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መልከጼዴቅ ያለ ሹመት እንደ ተሾመ ብዙ ጊዜ ተገልጿል፡፡ ቢሆንም ግን ምሳሌ ከሚመስልለት ያነሰ ስለሆነ የኢየሱስ ክርስቶስ ክህነትም ከመልከ ጼዴቅ ክህነት ይበልጣል፡፡ የመልከ ጼዴቅ ክህነት አዳምን ወደ ቀደመ ቦታው ሊመልሰው አልቻለም ነበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሊቀ ካህናት ሆኖ በመስቀል ላይ በሠዋው መሥዋዕት የሰውን ልጅ ሁሉ አድኖ ወደ ቀደመ መልካም ቦታው መልሶታል፡፡ ይህ አንድ ጊዜ በመስቀል የሠዋው መሥዋዕት ሁልጊዜም የሚያድን ስለሆነ እርሱም የዘለዓለም ሊቀ ካህናት ይባላል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእኛ ቀዳሚ ሆኖ ገባ ማለት ለመልካም ሥራ፣ ለትንሣኤና በጠቅላላው በሰውነታችን ለምናገኛቸው መልካም ነገሮች በኵራችን ሆነ ማለት ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፲፮

"እርሱ ግን ለዘለዓለም የሚኖር ስለ ሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፡፡ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና፥ ስለዚህ ደግሞ በርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል_____ርሱም እንደነዚያ ሊቃነ ካህናት አስቀድሞ ስለራሱ ኀጢአት በኋላም ስለሕዝቡ ኀጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጓልና" (ዕብ. ፯፥፳፬-፳፯)፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘለዓለማዊ አምላክ ነው፡፡ ስለዚህ ክህነቱም ዘለዓለማዊ ነው፡፡ እርሱ አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ በፈጸመው አስታራቂነት ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል፡፡ በዚህ ኃይለ ቃል ስለኢየሱስ ክርስቶስ አስታራቂነትና አዳኝነት በአንድ ጊዜ ተገልጿል፡፡ አስታራቂውም ታራቂውም ያው አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ካህናት ራሳቸውም ከኃጢአት ንጹሕ ስለማይሆኑ አስቀድመው ስለራሳቸው መሥዋዕት ይሠዉ ነበር፡፡ መሥዋዕት ሲያቀርቡም በየጊዜው ያቀርቡ ነበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን መሥዋዕት ያቀረበው አንድ ጊዜ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ተሰቅሎ ነው፡፡ ያ አንድ ጊዜ ያደረገው የማስታረቅ (የመማለድ) ተግባር አምነው ተጠምቀው ሥጋውን ደሙን ለሚቀበሉ እስከ ዕለተ ምጽአት ለሚነሡ ምእመናን ዋጋቸውን ሲሰጣቸው ይኖራል ማለት ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፲፯

"እርሱ የዐዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው" (ዕብ. ፱፥፲፭)፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የሐዲስ ኪዳን መካከለኛ ይባላል፡፡ መካከለኛ መባሉም በታራቂና በአስታራቂ መካከል ያለ ታራቂም አስታራቂም በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም በሰውም በእግዚአብሔርም መካከል ያለው ሰውም እግዚአብሔርም በመሆኑ ነው፡፡ አብና መንፈስ ቅዱስ የሰውን ሥጋን ስላልተዋሐዱ አምላክ እንጂ አምላክም ሰውም አንላቸውም፡፡ ወልድ ግን በተለየ አካሉ ሥጋን በተዋሕዶ ገንዘቡ በማድረጉ

አምላክም ሰውም ይባላል። መካከለኛ የተባለው እንደ ሰው ሰው፣ እንደ አምላክ አምላክ ሆኖ ሰውን ከፈጣሪው ያስታረቀ ፈጣሪ በመሆኑ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፲፰

"ሊቀ ካህናትም በየዓመቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ፥ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም። እንዲህ ቢኾንስ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኀጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጧል" (ዕብ. ፱፥፳፭-፳፮)። የብሉይ ኪዳኑ ሊቀ ካህናት ደመ ላህም (የላም ደም)፣ ደመ ጠሊ (የፍየል ደም) ይዞ በዓመት በዓመት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባ ነበር። እንዲህ አድርጎም ግን መሥዋዕቱ ሥጋዊ መከራን እንጂ ነፍሳዊ መከራን ማራቅ አልቻለም ነበር። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እንደ ብሉዩ ሊቀ ካህናት በየዓመቱ መሥዋዕትን መሠዋት አላስፈለገውም። መሥዋዕቱ የራሱ ሥጋና ደም በመሆኑ በየዓመቱ መሥዋዕትን የሚያቀርብ ቢሆን ኖሮማ ብዙ ጊዜ መከራን መቀበል ባስፈለገው ነበር ተብሏል። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ ባቀረበው መሥዋዕት እስከ ዕለተ ምጽአት የሚነሡ ምእመናንን እያስታረቀ ያድንበታል። መሥዋዕቱም ኃጢአትን የሚያስተሠርይ ዘለዓለማዊ ሕይወትን የሚያድል ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፲፱

"እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው________ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፥ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን" (ዕብ. ፲፩፥፩-፫)። ሃይማኖተ ርእይን ሃይማኖተ ሰሚእ ይቀድመዋል። በመስማት በተቀበልነው የሃይማኖት ትምህርት ጸንተን ስንገኝ በማየት እናረጋግጠዋለን። ስለመንግሥተ ሰማያት፣ ስለገነት፣ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን። እስካሁን ግን ገነትንም፣ መንግሥተ ሰማያትንም፣ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወትም ሞተን አላየነውም። ነገር ግን እነዚህ ነገሮች እንዳሉ አምነን ለእነዚህ የተገባን እንሆን ዘንድ መልካም ሥራን ሠርተን ጸንተን ስንኖር እነዚህን በማየት የምታስረግጥልን እምነት ናት። አሁን ያላየነውን እንደምናይ አስረግጦ የሚነግረን እምነት ነው። ዓለም ሲፈጠር አላየንም አልነበርንም። ዓለምን የፈጠረ እግዚአብሔር እንደሆነ አስረግጦ የሚነግረን እምነት ነው። ዓለምን የፈጠረ እግዚአብሔር እንደሆነ አስረግጦ የሚናገር ከእምነት ውጭ ሌላ የለም።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፳

"በሰውም ወደተጣለ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ወደተመረጠና ክቡር ወደሆነው ወደ ሕያው ድንጋይ ወደ እርሱ እየቀረባችኹ" (፩ኛ ጴጥ. ፪፥፬-፯)። ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው ድንጋይ ይባላል። ቅዱስ ጳውሎስ "ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ አለት ጠጥተዋልና፥ ያም አለት ክርስቶስ ነበረ" ብሎ ክርስቶስ አለት እንደሚባል ገልጾ ነበር (፩ኛ ቆሮ. ፲፥፬)። ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ ጌታን ሕያው ድንጋይ አለው። ድንጋይ ጽኑዕ እንደሆነ ኢየሱስ ክርስቶስም ጽኑዕ አምላክ ነውና። ምሳሌ ከሚመሰልለት ያንሣል ብለን ከዚህ ቀደም እንደተናገርን ክርስቶስን በአለት ቢመስለውም አለት ግን ሕይወት የሌለው ስለሆነ ምሳሌው ሕፀፅ አለበት። ስለዚህም ብዙ ጊዜ

ምሳሌ ምሳሌ ዘየሐፅፅ ተብሎ ይገለጻል። ቤቱን በአለት ላይ የሠራ ሰው ቤቱ አይናወጽበትም። ዝናብ፣ ወጀብ፣ ነፋስ፣ ጎርፍ ቢመጣ አያስፈራውም። ሕይወቱን በክርስቶስ ትምህርት የመሠረተ ሰውም ክሕደት ቢበዛ፣ ዓለም ብትታወክ፣ መከራ ቢበዛ አይናወጽም ማለት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፳፩

"ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ኾኖ ስለ ዐመፀኞዎች አንድ ጊዜ በኀጢአት ምክንያት ሞቷልና በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" (፩ኛ ጴጥ. ፫፣፲፰)። ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቀ ባሕርይ መሆኑን እናውቃለን። ጻድቅ ሆኖ ሳለ እኛን ዐመፀኞዎችን ለማዳን በእኛ ኃጢአት ምክንያት በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ። ሞተ ስንል ግን በሥጋው ሞተ እንላለን እንጂ እንደ አምላክነቱ ሞት የሌለበት ነው። እመሰ ትቤ መለኮት ሞተ አንተ ትከውን ቀታሊሆሙ ለሥሉስ ቅዱስ እንዲል። ክርስቶስ ሞተ ስንል ነፍሱ ከሥጋው ተለየች ማለታችን ነው እንጂ መለኮት ከሥጋው ተለየ ማለት አይደለም። መለኮት በመቃብር ከሥጋ ጋር፣ ነፍሱ ነፍሳትን ከሲኦል ለማውጣት ስትሄድም ከነፍስ ጋር ነበረ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው እንደመሆኑ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ አምላክ እንደ መሆኑም በኪሩቤል ጀርባ ተቀምጦ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአንዲት ምስጋና ሲመሰገን ነበረ። በሥጋው ሲሞት በመንፈስ ሕያው ነው ያለው በመለኮት ሕያው ነው ሲል ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፳፪

"ክርስቶስም በሥጋ ስለ እኛ መከራን ስለተቀበለ____" (፩ኛ ጴጥ. ፬፣፩)። መለኮት በባሕርይው መከራን የማይቀበልና መከራ የማይስማማው ነው። ሥጋን በተዋሕዶ ገንዘቡ ባደረገው ጊዜ ግን በሥጋ ታመመ፣ በሥጋ ሞተ፣ በሥጋ መከራን ተቀበለ ይባላል። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ "በሥጋ ስለእኛ መከራን ተቀበለ" ያለው ለዚህ ነው። መከራ የተቀበለም እኛን ለማዳን ስለእኛ ነው እንጂ እርሱ ራሱ ዋጋን የሚያገኝበትና በባሕርይው የሚጨመርለት ነገር ኖሮ አይደለም። ይህን ለመግለጽ ሐዋርያው "ስለእኛ" ብሎ ተናገረ። ሊቃውንትም ይህንን በሐተታ እንደ ሰማዕታት ዕሴት ሽቶ፣ እንደ ኃጥአን ስቶ የተሰቀለ አይደለምና "በእንቲኣነ (ስለእኛ)" አለ ብለው ያትታሉ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፳፫

"ስለክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና፥ ብፁዓን ናችኹ" (፩ኛ ጴጥ. ፬፣፲፬)። ቅዱስ ጴጥሮስ በክርስቶስ ስም ስለአመናችሁ፣ በክርስቶስ ስም ክርስቲያን ተብላችሁ ስለተጠራችሁ፣ ክርስቶስን ስላስተማራችሁ ሰነፎች በደለኞች ቢሏችሁ ብፁዓን ናችሁ ማለት ንዑዳን ክቡራን ናችሁ ይለናል። ስለ ስሙ ብንነቀፍ ኃይል ተአምራት ይደረግልናል። የመንፈስ ቅዱስም ጸጋና ረድኤት ይሰጠናል። የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋል ያለው ጸጋውን ነው። ይኸውም ከዚህ በተለየ መንፈስ ቅዱስ ይጠራ እንጂ አብ በእናንተ ላይ አርፏል፣ ወልድ በእናንተ ላይ አርፏል ቢልም አንድ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፷፬

"ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችኹ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፥ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን" (፪ኛ ጴጥ. ፩፥፬)። ከመለኮት ባሕርይ ተካፋይ እንድትሆኑ ማለት በባሕርይው ክቡር እግዚአብሔር እንደሆነ እናንተም በጸጋ ክቡራን ትሆኑ ዘንድ ማለት ነው እንጂ የባሕርይ አምላክ እንድትሆኑ ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ቸር ስለሆነ እርሱ በባሕርይው ክቡር፣ ይቅር ባይ፣ ቅዱስ፣ ፈታሒ በጽድቅ፣ ሁሉን ቻይ እና የመሳሰሉትን እንደሆነ ሁሉ የሰው ልጆች ደግሞ በጸጋ ቅዱሳን፣ ክቡራን፣ ፈታሕያን በጽድቅ፣ መሓርያን እንዲሆኑ ፈቅዷል። የመለኮቱ ባሕርይ ተካፋዮች እንድንሆን ፈቅዶልናል ማለት ይህ ነው። ይህን ላደረገልን ለእርሱ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይገባል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፷፭

"ከገናናው ክብር፦ በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሏልና" (፪ኛ ጴጥ. ፩፥፲፯)። በደብረ ታቦር አብ ወልድን ሲያከብረው እነ ቅዱስ ጴጥሮስ ሰምተዋል። ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሏል ያለው ይህንን ነው። አከበረው ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ ልጅ መሆኑን ገለጠው ማለት ነው። የገለጠውም ሐዋርያት እንዲያውቁ ነው። "ምስጋናን ተቀብሏል" ሲል በዚህ ጊዜ አብ ወልድን እንዳመሰገነ ተነግሯል። ከዚህ ቀደም እንደተማማርነው ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስም አብን አመስግኗል። ይህ መመሰጋገን በምስጋና አንድ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው። እኔ የምመሰገንበት ምስጋና የአንተ ነው። አንተ የምትመሰገንበት ምስጋና የእኔ ነው ሲል ነው። ይህንንም ሐዋርያት ዐውቀው እንዲያስተምሩት ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፷፮

"ኅብረታችንም ከአባት ጋራ ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ ነው" (፩ኛ ዮሐ. ፩፥፫)። ከእኛ ከምእመናን ጋራ በሃይማኖት አንድ መሆን ከእግዚአብሔር አብ፣ ከባሕርይ ልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አንድ መሆን ነው። በሦስቱ አካላት ማለትም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው አንድነት ባሕርያዊ አንድነት ነው። እኛ ከሥላሴ ጋር ያለን አንድነት ደግሞ የጸጋ ተዋሕዶ (አንድነት) ነው። የእኛ የምእመናን የኅብረታችን መሪና ራስ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፷፯

"የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል" (፩ኛ ዮሐ. ፩፥፯)። የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደሙ ከኃጢአታችን ያነጻናል። ከጥምቀት በፊት የሚሠራ ኃጢአት በጥምቀት ይሠረያል። ከጥምቀት በኋላ የሚሠራ ኃጢአት ግን ንስሓ ገብተን ሥጋውን ደሙን በመቀበል ይሠረያል። "ኃጢአት ዘእምቅድመ ጥምቀት ይሠረይ በጥምቀት ወኃጢአት ዘእምድኅረ ጥምቀት ይሠረይ በሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ" እንዲል። የክርስቶስ ሥጋና ደም

ከኃጢአታችን አንጽቶ ዘለዓለማዊ የደስታ ሕይወትን ያጎናጽፈናል። ስለዚህ ማንኛውም ምእመን ንስሓ እየገባ ቅዱስ ቊርባንን ሊቀበል ይገባዋል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፷፰

"ልጆቼ ሆይ፥ ኀጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኀጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጰራቅሊጦስ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" (፩ኛ ዮሐ. ፪፥፩)። በድለን ንስሓ የገባን ሰዎች ብንኖር ኃጢአታችንን የሚያስተሠርይልን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ዘንድ የሚሰድልን ጰራቅሊጦስ አለን። ጰራቅሊጦስን ወደሰው አብ ላከው፣ ወልድ ላከው ቢል የምሥጢር ለውጥ አያመጣም። ለፍጡራን ባላቸው ግብረ ባሕርይ (የባሕርይ ሥራ) ሦስቱ አንድ ናቸውና። አንዱ ቢጠቀስም ለሁለቱም ይሆናል። "አነ ወአብ ወመንፈስ ቅዱስ ንመጽእ ኀቤሁ ወንገብር ምዕራፈ ውስቴቱ" ካለው ጋር በምሥጢር አንድ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፷፱

"ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛው ማን ነው አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው" (፩ኛ ዮሐ. ፪፥፳፪)። አይሁድ ሌላ መሲሕን እየጠበቁ ነው። መሲሑ ግን ኢየሱስ ነው። ስለዚህ ሌላ ክርስቶስ በመፈለጋቸው ውሸታሞች ይባላሉ። አብን ወላዲ አሥራጺ፣ ወልድን ተወላዲ ነው ብሎ የማያምን ሰው የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው። በዚህ ዓረፍተ ነገር ወልድ የተባለው ራሱ ክርስቶስ መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል። "ወዘሰ የአምን በወልድ ወበአብኒ ሀለወ" ወልድን ተወላዲ ብሎ በማመን ጸንቶ የኖረ ሰው አብንም ወላዲ ነው ብሎ ያምናል። በአብ አምነው በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ካላመኑ ድኅነት የለም። በወልድ አምነውም በአብና በመንፈስ ቅዱስ ካላመኑ ድኅነት የለም። በመንፈስ ቅዱስ አምነውም በአብና በወልድ ካላመኑ ድኅነት አይገኝም። ሦስቱን አካላት የምናምነው እምነት አንድ ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፸

"የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው" (፩ኛ ዮሐ. ፬፥፪)። ከዚህ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ብሎ የገለጸው ትምህርትን ነው። የእውነተኛ ትምህርት መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ሰው ሆኖ እንደመጣ ማመን ነው። ይህንን የማያምንና የማያስተምር መምህር ግን ሐሰተኛ መምህር ይባላል። "ወዘንቱ ውእቱ ሐሳዌ መሢሕ ዘሰማዕክሙ ከመ ይመጽእ" እንዲል። ክርስቶስ መጣ የተባለ በሥጋ ነው። በመለኮቱ መጣ እንዳይባልማ መለኮት የሌለበት ቦታ ስለሌለ መጣ ሄደ የሚሉት ቋንቋዎች አይስማሙትም። ሐዋርያውም ይህንን ጠንቅቆ ሊያስረዳን "በሥጋ እንደመጣ" ብሎ ነገረን። መጣ ለመለኮት የሚቀጸል ከሆነ ረድኤት ሠጠ፣ ሰው ሆነ እየተባለ እንደየአመጣጡ ይተረጎማል።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፸፩

"የሚመሰክሩት መንፈሱና ውሃው ደሙም ሦስት ናቸውና ሦስቱም ባንድ ይስማማሉ" (፩ኛ ዮሐ. ፭፥፰)። ሦስቱ ምስክሮች የተባሉ እነዚህ ናቸው። መንፈሱ ያለው መንፈሰ ልደትን

(ልጅነትን) ነው:: ከተጠመቅን በኋላ የእርሱ ልጆች መሆናችንን እናረጋግጣለንና:: በብሉይ ኪዳን የነበሩ ሰዎች መንፈሰ ረድኤት እንጂ መንፈሰ ልደት አልነበራቸውም:: በሐዲስ ኪዳን ላለን ምእመናን ግን ራሱ ክርስቶስ መንፈሰ ልደትን ሰጠን:: ውሃ የተባለው ከጎኑ የፈሰሰው ውሃ (ማየ ገቦ) ነው:: በዚህም በአርባ ቀን በሰማንያ ቀን ተጠምቀን ልጅነትን እናገኝበታለን:: ደም የተባለው የምንቀበለው ሥጋው ደሙ ነው:: ይኸውም አስቀድመን ከኃጢአት ያነጻናል ብለን የተናገርነው ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፺፪

"የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ÷ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን እውነተኛም በሆነው በርሱ አለን÷ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው" (፩ኛ ዮሐ. ፭፥፳):: ወልደ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ እንዳስተማረን እናውቃለን:: የባሕርይ አምላክ እግዚአብሔር አብን እንድናውቅም አስተምሮናል:: እኛም የባሕርይ አምላክ በሚሆን በወልደ እግዚአብሔር፣ የባሕርይ አምላክ በሚሆን በአብ፣ የባሕርይ አምላክ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ በማመን ጸንተን እንኖራለን:: እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው:: እርሱ የተባለው እግዚአብሔር ነው:: ይኸውም የሦስቱ አካላት የአንድነት ስም ነው:: አብ እውነተኛ አምላክ ነው፣ ወልድ እውነተኛ አምላክ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ አምላክ ነው:: ነገር ግን ሦስቱ አካላት ስለሚገነዛዘቡ አንድ አምላክ እንላለን እንጂ ሦስት አማልክት አንልም::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፺፫

"እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለኽ መልካም ታደርጋለኽ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል______ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችኹ_____ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው" (ያዕ. ፪፥፲፬-፳፮):: እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አጋንንትም ያምናሉ:: የሚያድነን ግን እምነት ብቻ ሳይሆን መልካም ሥራንም መሥራት ጭምር ነው:: ሐዋርያው ያዕቆብ በግልጽ "ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንደሚመጸድቅ ታያላችሁ" አለን:: አንዳንድ ከሓድያን ግን "እምነት ብቻ" እያሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር ሲጋጩ እንመለከታለን:: ሥጋን ነፍስ ከተለየችው መንቀሳቀስ፣ ማውራት፣ መተንፈስ የማይችል ሬሳ ይሆናል:: ሰው እምነት ብቻ አለኝ እያለ መልካም ምግባርን የማይሠራ ከሆነም ተንቀሳቃሽ ሬሳ ነው::

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፺፬

"ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችኹ እጽፍላችኹ ዘንድ ግድ ሆነብኝ" (ይሁዳ. ፩፥፫):: ሃይማኖት በየዘመናቱ ሰዎች የሚመሠርቱት ነገር አይደለም:: አንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ለቅዱሳን የተሰጠ ነው:: የእኛ ድርሻ እግዚአብሔር የሰጠንን ሳንቀንስ ሳንጨምር ተቀብለን ለልጅ ልጆቻችን ማስተላለፍ ነው:: ቅዱሳን ሰማዕታት ይህችን ሃይማኖት አስተምህሮዋን በማስተማር፣ የክሕደት ትምህርት እንዳይቀላቀልባት ክሕደቱን በመቃወም እስከ ዕለተ ሞታቸው ታምነዋል:: ቅዱሳን መነኮሳት የሃይማኖትን

ተግባራዊ አስተምህሮ ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ጤዛ ልሰው፣ ዳዋ ጥሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ ድምፀ አራዊትን ታግሠው በገዳም ኖሩ፡፡ ቅዱሳን ሊቃውንት በአደባባይ ስለዚች ሃይማኖት በማስተማር ዐረፍተ ዘመን እስኪገታቸው ኖሩ፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፴፭

"ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፦ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል" (ራእ. ፩፥፰)፡፡ ከእግዚአብሔር ግብረ ባሕርያት አንዱ ይህ ነው፡፡ የመጀመሪያ መጀመሪያ እርሱ ስለሆነ አልፋ ይባላል፡፡ የመጨረሻ መጨረሻ እርሱ ስለሆነም ዖሜጋ ይባላል፡፡ ዓለም ሳይፈጠር እግዚአብሔር ነበረ፡፡ አሁንም አለ፡፡ ወደፊትም ዓለምን አሳልፎ ይኖራል፡፡ እግዚአብሔር ሁሉንም የሚገዛ አምላክ ነው፡፡ ፍጡራን ገዢ ቢባሉ በጸጋ ያገኙት ነው፡፡ ያውም ጥቂቶችን ብቻ ለትንሽ ዘመን ይገዛሉ እንጂ ፍጥረታትን ሁሉ ለብዙ ዘመን አይገዙም፡፡ እግዚአብሔር ግን ፍጥረታትን ሁሉ ፈጥሮ የሚገዛ እንዲሁም ለጥቂት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ለዘለዓለም ንጉሥ የሆነ አምላክ ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፴፮

"ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል" (ራእ. ፪፥፰)፡፡ ሦስቱ አካላት ማለትም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ፊተኛና ኋለኛ ይባላሉ፡፡ ከሦስቱ አካላት አንዱ ከድንግል ማርያም ሥጋንና ነፍስን ነሥቶ ሰው ከሆነ በኋላ የሰውን ልጅ ሁሉ ለማዳን በመስቀል ተሰቅሎ ሞቶ ነበር፡፡ በሦስተኛው ቀን ከሙታን መካከል ተለይቶ ተነሥቷል፡፡ ከተዋሕዶ በኋላ በተዐቅቦ የቃል ገንዘብ ለሥጋ፣ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ሆኗልና "ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው" ተብሎ ተነገረለት፡፡ ቃል በሥጋ ገንዘብ ሞተ ተብሎ ይነገራል፡፡ ሥጋም በቃል ገንዘብ ዘለዓለማዊ ሆነ ይባላል፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፴፯

"የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘለዓለምም እስከ ዘለዓለም ይነግሣል________ያለኸና የነበርኸ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ትልቁን ኀይልኸን ስለ ያዝኸ ስለ ነገሥኸም እናመሰግንኻለን" (ራእ. ፲፩፥፲፭-፲፯)፡፡ ፍጡራን ነገሥታት ቢባሉ የጸጋ ንጉሥ ናቸው፡፡ የሚነግሡትም ለጥቂት ዘመን ያውም ግፋ ቢል ለተወሰኑ ሀገራት ብቻ ይሆናል፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥነት ግን የባሕርይ ንጉሥነት ነው፡፡ ስለዚህ መንግሥትነቱም ዘለዓለማዊ ነው፡፡ የነገሠውም በፍጥረታት ሁሉ ላይ ነው፡፡ ፍጥረታት ሳይኖሩም ንጉሥ ነበር፡፡ "ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም" እንዲል፡፡ ጻድቃን በመንግሥተ ሰማያት ክርስቶስ ነግሦላቸው በደስታ ላይ ደስታ እየተጨመረላቸው እያመሰገኑት ይኖራሉ፡፡ "ስለነገሥክም እናመሰግንሀለን" ይሉታል፡፡ ያን ጊዜ እንደ አዲስ የሚነግሥ ሆኖ አይደለም፡፡ ንጉሣችን በመሆንህ እናመሰግንሃለን ሲሉት ነው፡፡

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፴፰

"የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ሙሽራይቱም ራሷን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ

ክብርንም ለርሱ እናቅርብ" (ራእ. ፲፱፥፯)። በግዕ ተብሎ የተገለጸው ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ሙሽራ የተባለች ደግሞ ምእመን (ቤተክርስቲያን) ናት። በግዑ ክርስቶስ ምእመናንን የጸጋ ተዋሕዶ የሚዋሐድበት ጊዜ ደረሰ። ምእመንም ለተዋሕዶ በቅታ ተገኘች። ይህም ማለት ምእመናን በሠሩት መልካም ሥራ በዳግም ምጽአት ጊዜ ሰማያዊ ክብርን ያገኛሉ ማለት ነው። በዚህ ፍጹም ደስታን እንደሠት ደስ ይበለን።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፴፱

"በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው ኹለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ፥ ከርሱም ጋራ ይህን ሺሕ ዓመት ይነግሣሉ" (ራእ. ፳፥፮)። ፊተኛው ትንሣኤ ያለው ትንሣኤ ልቡና ነው። ይኸውም ምእመናን በክርስቶስ አምነው፣ ተጠምቀው፣ ሥጋውን ደሙን ተቀብለው፣ ምግባር ትሩፋት ሠርተው የሚያገኙት አዲስ ሕይወት ነው። እኒህን በሚያደርግ ምእመን ሁለተኛው ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን አይኖረውም። ሁለተኛው ሞት የተባለው የሰው ከእግዚአብሔር መለየት ነው። ከላይ ያሉትን መልካም ምግባራት የሚሠራ ሰው ግን ከእግዚአብሔር የተለየ ስለማይሆን ሁለተኛው ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውም ብሏል። ከእርሱም ጋራ ሺ ዓመት ይኖራሉ ያለው ብዙ ዘመን ይኖራሉ ሲል ነው እንጂ በቁጥር እኛ በምናውቀው ሺ ዓመት ይኖራሉ ማለት አይደለም። ከዋናው ትንሣኤ በኋላም ለዘለዓለም ይኖራሉ።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፵

"እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችኹ መልአኬን ላክኹ። እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፥ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ" (ራእ. ፳፪፥፲፮)። መላእክት እግዚአብሔር የሚልካቸው የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስም አምላክ ስለሆነ "መልአኬን ላክሁ" ብሏል። አያይዞም የዳዊት ሥር ነኝ ብሏል። "ትወፅእ በትር እም ሥርወ ዕሴይ" ያለውን ትንቢት ከዚህ ተረጎመው። ክርስቶስ በሥጋ የተወለደው ከዳዊት ዘር ስለሆነ የዳዊት ሥር ነኝ ብሏል። አያይዞም የሚያበራ የንጋት ኮከብ ነኝ ማለቱ የንጋት ኮከብ ሌሊት አልፎ መዓልት መምጣቱን የሚያበስር ደስ የሚያሰኝ እንደሆነ ሁሉ ክርስቶስም ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ ሞትን በሞቱ አጥፍቶ በኵረ ትንሣኤ ስለሆነን በዚህ ደስ ያሰኘናልና ነው።

## ነገረ ክርስቶስ ክፍል ፫፻፵፩

ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክም ሰውም እንዳልነው ሁሉ ፈጣሪም ፍጡርም እንለዋለን። ይህንንም ግልጽ በሆነ አነጋገር ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ጽፎልናል። "ፍጡር ወኢፍጡር" እንዲል (ሃይ. አበ. ፴፰)። ፍጡር ሥጋ ፍጡርነቱን ሳይለቅ ፈጣሪ ሆነ። ፈጣሪ መለኮትም ፈጣሪነቱን ሳይለቅ ፍጡር ሆነ። በሃይማኖተ አበው ምዕራፍ ፴፯ እንደተገለጸው ኢያፍለሰ ትስብእቶ ፍጡረ ለከዊነ ፈጣሪ ወኢያፍለሰ ፈጣሪ መለኮቶ ለከዊነ ፍጡር ተብሏል። ፍጡር ሥጋ ፍጡርነትን ሳይለቅ ፈጣሪነትን ገንዘብ አድርጓል። መለኮትም ፈጣሪነትን ሳይለቅ ፍጡር ሥጋን ገንዘብ አድርጓል። ይህ የየቀድሞ ማንነትን ሳይለውጡ ሌላውን ገንዘብ ማድረግ ተዋሕዶ በተዐቅቦ ይባላል። ክርስቶስ በሥጋው ፍጡር ይባላል። ይህም ማለት ሥጋው ቅድመ ዓለም የነበረ

ሳይሆን የተፈጠረ ነው ማለት ነው። አርዮስ ክርስቶስ በመለኮቱ ፍጡር በማለቱ ታላቅ ክሕደትን ካደ። ለዚህም ሠለስቱ ምእት በመለኮቱ ፈጣሪ መሆኑን ለመግለጽ ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ ብለው መልሰውለታል። በሥጋው ፍጡር እንደሆነ ግን እነ ቅዱስ ቄርሎስ፣ እነ ቅዱስ ጎርጎርዮስና ሌሎችም ቅዱሳን ሊቃውንት የጻፉት ነው። አንዳንዱ ክርስቶስን አምላክም ሰውም፣ ፈጣሪም ፍጡርም ስንለው እንደ ካቶሊክ የምንታዌ ትምህርት አድርገው ያስቡታል። ግን ስሕተት ነው። አንድን ሰው በነፍሱ ረቂቅ በሥጋው ግዙፍ ስንለው ሁለት እያደረግነው አይደለም። ያው አንዱ አካል ረቂቅም ግዙፍም መሆኑን መግለጽ ነው እንጂ። አንዳንዶች ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋ ፍጡርነቱን ለቋል የሚሉ አሉ። ነገር ግን ሃይ. አበ. ፴፮ ላይ በግልጽ ተጽፏል። ሲዋሐድ ቅድመ ተዋሕዶ የነበረውን እንቲኣሁነት (የራሱን ገንዘብነት) ሳይለቅ ነው። በተዋሕዶ ጊዜ ፈጣሪ ቃል ወደፍጡር ሰውነት አልተለወጠም። ፍጡር ሥጋም ወደ ፈጣሪ መለኮት አልተለወጠም። አይ ከተዋሕዶ በኋላ ፈጣሪ ብቻ እንለዋለን ከተባለ ግን ይህ የአውጣኪ ክሕደት ነው። መለኮት ሥጋን ውጦታል ያሰኛል። ክርስቶስን ከተዋሕዶ በኋላ ሰው ካልነው ፍጡርም እንለዋለን ማለት ነው። ሰው ስንለው ግን እንደሌላው ዕሩቅ ብእሲ (ሰው ብቻ) አንለውም። አምላክም ሰውም ፈጣሪም ፍጡርም እንለዋለን እንጂ።

ስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር አሜን